የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

የ1996 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት

የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ

አዲስ አበባ
ሚያዝያ 1996

ማ ው ጫ

አርእስት ገጽ

1	አጠቃላይ መመሪያ	1
2	የጥናቱ ዓላማዎች	3
3	ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ርዕሶች..	3
4	ጽንስ ሀሳቦችና ፍቸዎቻቸው.	4
5	የአመዘጋገብ፣ የመመዝገቢያ ቅጾች አሞላልና የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ	6
	5.1. የከተማ ቤቶችና ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ 96/ከ/0 አሞላል መመሪያ	6
	5.2. በገጠር የቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ 96/ገ/0 አሞላል መመሪያ. . . .	13
	5.3. በከተማ የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ ዘዴ	18
	5.4. በገጠር ለግብርና እና ለቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ እንዲሁም ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ ዘዴ	19
	5.5. ቅጽ 96/1 የአሞላል መመሪያ	22
6	ቅጽ 1 የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ ፣ የሥነ ባህሪያትና የሥራ ሁኔታ.	28
7	ቅጽ 2 የትምህርት ሁኔታ	47
8	ቅጽ 3 የጤና ሁኔታ	58
9	6. ቅጽ 4 ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ የህጻናት ክብደት፣ ቁመት ልኪቶሽና ጤና ሁኔታ	66
10	ቅጽ 5 ቤተሰቡ በቤት ውስጥ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች/Amenities/. . .	75
11	ቅጽ 6 የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የርቀትና የአጠቃቀም ሁኔታ.	87
12	ቅጽ 7 የቤተሰቡ የቤትና የመሬት ይዞታ ሁኔታ እና ሌሎች ቋሚ ንብረቶች. .	91
13	ቅጽ 8 ጠቋሚ የኑሮ ደረጃ መለኪያዎች	101
14	ቅጽ 9 የHIV (AIDS) ሁኔታ.	109
15	የቆጠራ ቦታ ካርታ አጠቃቀም	113

ዕዝል

1. የኢንዱስትሪ ኮድ ዝርዝር
2. የክብደትና ቁመት አለካክ መመሪያ

አጠቃላይ መመሪያ

1.1. የመረጃ ሰብሳቢው ተግባርና ኃላፊነት

በተመረጡ ወረዳዎች ተመድቦ በመሠረታዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጠቋሚ ጥናት የሚሰማራ መረጃ ሰብሳቢ ለጥናቱ ሥራ መሳካት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ስለሆነም መረጃ ሰብሳቢው የመረጃ አሰባሰቡን ተግባር በቅንነት፣ በታማኝነትና በታታሪነት ማከናወን ይገባዋል። መረጃ ሰብሳቢው ከተመደበበት ቦታ ነዋሪ ከሆነ ሕዝብ ጋር ተግባብቶ ባህሉን አክብሮ የመረጃ አሰባሰቡን ተግባር ከማከናወኑም በላይ የሕዝቡን ድጋፍና ትብብር ለማግኘት ከአስነዋሪ ድርጊቶች ሁሉ መራቅ ይኖርበታል። በተጨማሪም ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢ <u>በሥራው ወቅት</u> ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌላቸው ተግባራት (መነገድ፣ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት ቅስቀሳዎችና የመሳሰሉት) ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መሰማራት አጥብቆ የተከለከለ ስለሆነ ይህንን አውቆ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል።

መረጃ ሰብሳቢው ተግባሩን ለማከሄድ ወደየቤተሰቡ በሚደርስበት ወቅት ሰላምታ በመስጠት እራሱን ማስተዋወቅ፣ ስለ መጣበት ዓላማ መግለጽና ለጥናቱ ቀና ትብብር የሚያገኝበት መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል። ለጥናቱ መረጃ ሰብሰባ ሥራ የሚጠየቁ ጥያቄዎች በመመሪያው መሠረት መሆን ያለበት መሆኑን በመገንዘብ አግባብ የሌለውን ጥያቄ መጠየቅ አይኖርበትም። ሥራውንም ካጠናቀቀ በኋላ ቤተሰቡን አመስግኖ መሰናበት ይኖርበታል። በአጠቃላይ ሥራው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ ታታሪ፣ ትሁት፣ ቀልጣፋና ተግባቢ መሆን ያስፈልጋል።

መረጃ ሰብሳቢው ተግባሩን ለማከናወን የተለያዩ ቅጾችንና ጥያቄዎችን በእርጋታ በማጤን መሙላት ይኖርበታል። እንደዚሁም የሞላቸው ሁሉ በመመርመር አስፈላጊውን ዕርማት ማድረግ ያለበት ከመሆኑም በላይ ካስፈለገ ወደ ቤተሰቡም በመመለስ በስህተት የተሞሉ፣ የማይመስሉ፣ እርስ በእርስ የማይጣጣሙ፣ ... ወዘተ ምላሾችን ማስተካከል አለበት። ለጥናቱ የሚሰጡትን ደክመንቶችና ሌሎች ሰቀዎች በጥንቃቄ መያዝና በመረጃ ሰብሰባው ወቅት የሚሰበስቡትን <u>መረጃዎች በሚስጥር መጠበቅና ከቅርብ ተቆጣጣሪውና ከሌሎች የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን ሠራተኞች በስተቀር ለማንም ግለሰብ ማሳየት አይገባውም።</u> ከዚህም ሌላ በሥራ ወቅት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ እንደ የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ የሕዝናት ሚዛን፣ ሜትር እና ሌሎች ቁሳቁሶች ከመረጃ ሰብሳቢው ሊለዩ አይገባቸውም።

መረጃ ሰብሳቢው ከቤተሰቡ ዘንድ በመሄድ የቤተሰቡን ኃላፊና ቢቻል የቤተሰቡን አባላት በማነጋገር በቅጾቹ የተመለከቱትን ጥያቄዎች እየተረዳው እንዲመልሱ ማድረግ ይገባዋል።

1.2. የአፈፃፀም ቅደም ተከተል፣ አስፈላጊ ዶኩመንቶችና ቁሳቁሶች

1.2.1. የአፈፃፀም ቅደም ተከተል፦

የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት መጠይቅ ለመሙላት (መረጃ ለመሰብሰብ) የሚሰማሩ መረጃ ሰብሳቢዎች ስራቸውን በሚከተለው ቅደም ተከተል ያከናውናሉ።

ሀ. ስልጠናው እንደተጠናቀቀ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶችና እቃዎች (መጠይቆች፣ መመሪያዎች፣ የሕፃናት ክብደት መለኪያ ሚዛን፣ ቁመት መለኪያ ሜትርና የመሳሰሉት) ቆጥሮ በጥንቃቄ መረከብ፤

ለ. በየጊዜው የተሞላውን መጠይቅ በመመርመር ያልተሟሉ ዓምዶችን ወይም ጥያቄዎችን በተቻለ መጠን የጉብኝቱ ጊዜ ሳያልፍ ወደ ቤተሰቡ በመመለስ ማሟላትና አስቸጋሪ ጉዳይ ካጋጠመ ተቆጣጣሪውን በማማከር መፍትሄ መሻት፤

ሐ. በሥራው ወቅት ችግር ሲያጋጥም ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ መፍትሄ ማግኘትና የተሰጠውን የመፍትሄ ሐሳብ መመዝገብ፤

መ. ሥራው በትክክል ተሰርቶ መጠናቀቁን ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ካረጋገጡ በኋላ ለተቆጣጣሪው ማስረከብ።

1.2.2. ለሥራው የሚያስፈልጉ ዶክመንቶችና ዕቃዎች

ለሥራው የሚያስፈልጉ ዶክመንቶችና ዕቃዎች፦

ሀ. የመረጃ ሰብሳቢው መመሪያ፤
ለ. የተጠረዘ ቅፅ መጠይቅ ፤
ሐ. የጽህፈት መሳሪያዎች
መ. ቤተሰቦች ለመምረጥ የሚያገለግል የራንደም ቴብል፤
ሠ. የሕፃናት ክብደትና ቁመት መለኪያ ሚዛንና የጣውላ ላይ ሜትር፤
ረ. የመታወቂያ ወረቀት፤
ሰ. ለቀበሌ/ገበሬ ማኅበራት የሚፃፍ የትብብር ደብዳቤ (ካለ) ናቸው።

2. የጥናቱ ዓላማዎች፦

የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ደህንነት ጥናት የሀገሪቱን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ አፈፃፀም ክትትልና ግመገማ ለማካሄድ የሚያስችል መረጃዎችን ማሰባሰብ ሆኖ ቤተሰቦችን ከዝቢ ውጭ ያሉትን የድህነት ገጽታዎችን ለማወቅ የሚያስችል የሚከተሉት የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

1. በአገሪቱ ውስጥ ለሚታየው የድህነት ሁኔታ መሠረታዊና ጠቋሚ መረጃዎችን በማሰባሰብ ወደፊት የሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጦችን ለመከታተልና ለማጥናት፤

2. ለአሮሮና ለመካከለኛ ጊዜ የታቀዱ አዳዲስ ፖሊሲዎች በቤተሰብ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ደህንነት ላይ የሚያስከትሉትን ውጤት ለመገምገም፤

3. ደህንትን ለመቀነስና ለማጥፋት እንዲቻል በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮረ ዘላቂ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ ስልት በመቀየስ አስተማማኝ መረጃ ለማቅረብ፤

ዝርዝር ዓላማዎቹም

1. የሀገሪቱን የትምህርት አገልግሎት ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎችን ማሰባሰብየሀገሪቱን
2. የጤና አገልግሎትን በተመለከተ ስርጭቱ፤ ጥራቱና አጠቃቀሙን በማወቅ የሚረዱ ጠቋሚ መረጃዎችን ማቅረብ፤
3. የሕፃናት የጤና፤ የአመጋገብና ዕድገት የሚያመለክቱ ጠቋሚ መረጃዎችን ማሰባሰብ፤
4. በሃገሪቱ ያለውን የሥራና የሥራ አጥ ሁኔታ አመላካች መረጃዎችን ማቅረብ፤
5. የቤተሰቦች መሠረታዊ ግልጋሎቶች (የንፁህ ውሃ አቅርቦት፤ የመፀዳጃ ሁኔታዎች፤ የመብራትና ማገዶ አቅርቦት ወዘተ) አቅርቦትና የአገልግሎት ጥራትን የሚያመለክቱ መረጃዎችን ማሰባሰብ፤
6. የቤተሰቦች ቋሚ ንብረቶች ይዞታ አመልካች ስታቲስቲክስ ማሰባሰብ
7. የቤተሰቦችን አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ በምግብ፤ በመጠለያ ወዘተ ጠቋሚ መረጃዎችን ማሰባሰብ ናቸው።

3. ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ርዕሶች

ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ርዕሶች በዘጠኝ ዋና ዋና ክፍሎች (ቅጽ 1-9) በተከፋፈሉ ቅጾች (መጠይቆች) ሥር የተጠቃለሉ ሲሆን እያንዳንዱ ክፍል የሚያመለክተው ርዕስ የሚከተለው ነው።

ቅፅ 1- የቤተሰብ አባላት ዝርዝር የሥነ ሕዝብ ባህርያት እና የሥራ ሁኔታ

ቅፅ 2- የትምህርት ሁኔታ

ቅፅ 3- የጤና ሁኔታ

ቅፅ 4- ከ5 ዓመት በታች ዕድሜ ስላሉ ህፃናት የክብደት፡ የቁመትና የጤና ሁኔታ

ቅፅ 5- ቤተሰቡ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች

ቅፅ 6- የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የርቀትና አጠቃቀም ሁኔታ

ቅፅ 7- የቤተሰብ የቤት፡ የመሬት ይዞታ ሁኔታናና ሌሎች ቋሚ ንብረቶች ሁኔታ

ቅፅ 8- የኑሮ ደረጃ ጠቋሚ መለኪያዎች

ቅፅ 9- የኤች አይ ቪ ሁኔታ

4. <u>ዕንስ ሀሳቦችና ፍቺዎቻቸው፡-</u>

ሀ. <u>ቤተሰብ፡-</u> ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ማዕድቤት አብስለው በአንድነት የሚመገቡ ሰዎችን ያጠቃልላል። የቤተሰብ አባላት በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱትንና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላል። በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፡ ሚስት፡ ልጅ፡ የባል/የሚስት ወላጆች፡ እህት፡ ወንድም፡ አጎት፡ አክስት ... ወዘተ ናቸው። በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ለምሳሌ በቤት ሠራተኝነት፡ በዘበኝነት የሚያገለግሉ ግለሰቦች ከቤተሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩና የሚመገቡ ከሆነ እንደ ቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ።

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል። ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል፡ ወይም ሌሎች ሰዎች እንደ ዘመኞች፡ ጥገኞች ... ወዘተ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ነገር ግን ጥናቱ ከሚከናወንበት ዕለት በፊት ቤተሰቡን ትቶ በእንግድነት ወደ ሌላ ቤተሰብ በመሔድ እዚያ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ ለቤተሰቡ አባል ይሆናል ማለት ነው።

ጋብቻው በአንድ ሚስት ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ቤተሰብ ባልኝ፡ ሚስትኝ፡ ልጆችኝ፡ የጉዲፈቻ ልጆችኝ፡ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን (የቤት ሠራተኞች ... ወዘተ) ሊያጠቃልል ይችላል። ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ (አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ካሉት) የሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ... ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይኖሩና ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የማይበሉ ከሆነ፡ ባልየው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት (አንጋፋ) ሚስቱ ጋር እንደ አንድ የቤተሰብ አባል ተቆጥሮ ሌሎቹ የሰውየው ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ እንዳላቸው ሆኖ መቆጠር አለባቸው። ይህም የሚሆነው ሰውየው የቤተሰብ አባልነት መመዘኛ የሚያሟላ ሲሆን ነው።

ለ. <u>መደበኛ የቤተሰብ አባል፦</u> አንድ ሰው መደበኛ የቤተሰብ አባል ነው የሚባለው ቢያንስ ስድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰብ ጋር የኖረ እንደሆነ ነው። ከቤተሰቡ ጋር ለዘለቄታው ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል ይቆጠራሉ። ከስድስት ወር በታች ከቤተሰቡ ለጊዜው ተለይተው የቆዩ የቤተሰብ አባላት እንደመደበኛ የቤተሰቡ አባል መቆጠር አለባቸው፣ ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው፣ ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደው የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም።

<u>የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት እንደ መደበኛ የቤተሰብ አባል መቆጠር ይኖርባቸዋል።</u>

1. በጥናቱ ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ቢያንስ ለስድስት ወር የቆዩ።

2. ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም ከቤተሰቡ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ለመቆየት ዕቅድ ያላቸው ሁሉ፦ ለምሳሌ ባል አግብታ ከወላጆችዋ ቤት ወደ ባልዋ የሄደች ሴት ስድስት ወር ባይሞላትም የባሏ ቤተሰብ መደበኛ አባል ትሆናለች ማለት ነው። እንዲሁም ሥራ አግኝቶ/ታ ለዘለቄታው ለመኖር ወደ ሌላ ቤተሰብ የሄደ/ች ስድስት ወር ባይሞላውም/ትም በጥናቱ ወቅት የተገኘበት/ችበት ቤተሰብ አባል ይሆናል/ትሆናለች።

3. የቤት ሠራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚያድሩና ሌላ መኖሪያ የሌላቸው ሁሉ።

4. በጥናቱ ጊዜ ከስድስት ወር ላነሰ ከቤተሰቡ ለጊዜው የተለዩ፤ ለምሳሌ በዕረፍት ላይ ያሉ፤ በዓመት በዓል ወደ ሌላ ቦታ የሄዱ፤ ሆስፒታል የገቡ፤ ዘመድ ለመጠየቅ የሄዱና ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ጉዳይ ላይ ያሉትን አባላት ሁሉ ያጠቃልላል።

5. ሌላ መኖሪያ ሥፍራ የሌላቸውና በጥናቱ ወቅት ከቤተሰቡ ጋር የሚኖሩ አባላት ሁሉ፤ ለምሳሌ በተለያዩ ቤቶች እያቀያየሩ ለሚኖሩና መደበኛ መኖሪያ የሌላቸው ግለሰቦች በጥናቱ ወቅት በሚገኙበት ቤተሰብ እንደ መደበኛ አባል ተቆጥረው ይመዘገባሉ።

6. <u>ተማሪዎች፦</u> ከቤተሰቦቻቸው፤ ከወላጆቻቸው፤ ከመደበኛ የመኖሪያ ሥፍራቸው ተለይተው በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፤ በኮሌጆች፤ በዩኒቨርስቲዎች ... ወዘተ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት አካባቢ መደበኛነዋሪዎች ሆነው መመዝገብ አለባቸው። በአጭር

ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም ከወላጆቻቸው ተለይተው ቤት ተከራይተው ወይም ከዘመድ ተጠግተው እየኖሩ የሚማሩ ተማሪዎች ምንም እንኳን በየሳምንቱ ወይም በየአሥራ አምስት ቀን ሰንቅ ለማምጣት ወይም ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ቤተሰቦቻቸው ቢሄዱም እንደ መደበኛ የቤተሰብ አባል የሚታሰቡት በሚኖሩበት አካባቢ እንጂ በወላጆቻቸው ቤት አይደለም:: ነገር ግን ከመደበኛ መኖሪያቸው (ከቤታቸው) በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤቶች እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ የሚኖሩበት ቤተሰብ መደበኛ አባል ሆነው መመዝገብ አለባቸው::

ሐ. <u>የቤተሰብ ኃላፊ:-</u> «የቤተሰብ ኃላፊ» ማለት የአንድ ቤተሰብ መደበኛ አባል የሆነ ወንድ/ሴት በቤተሰቡ አባላት እንደ ኃላፊ የሚቆጠር/የሚታይ ነው:: ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሰው ሚስቶቹ በተለያዩ ቤተሰብ የሚኖሩ ከሆነ እሱ የቤተሰቡ ኃላፊ ሆኖ የሚመዘገበው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት/አንጋፋ ሚስቱ ጋር ይሆናል:: ሌሎች ሚስቶች ግን የየራሳቸውን ቤተሰብ ኃላፊ(አባል) ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህም የሚሆነው ባልየው በሚያሻማ መልኩ ከሁሉም ሚስቶቹ ጋር የማይኖር ከሆነ ነው::

7. <u>ጥናቱ የሚያቅፋቸው ቤተሰቦች አመራረጥ:-</u>

በጥናቱ የሚታቀፉ ቤተሰቦች በቤተሰብ ዝር፡ ፍጆታ ወጪ ጥናት የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ ውስጥ ተካቷል::

8. <u>በጥናቱ የሚሸፈኑ የቆጠራ ቦታዎችና ቤተሰቦች</u>

በዚህ ጥናት በገጠር 2072 የቆጠራ ቦታዎች እንደሁም በከተማ 790 የቆጠራ ቦታዎች ይሸፍናሉ:: በገጠር ከሚመረጠው አጋንዳንዱ የቆጠራ ቦታ 12 ቤተሰቦች (በጠቅላላው 24,864 ቤተሰቦች) እንዲሁም ከእያንዳንዱ የከተማ የቆጠራ ቦታ 16 ቤተሰቦች በጠቅላላው 14,660 ቤተሰቦች) በጥናቱ የሚሸፈኑ ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ በጥናቱ የሚሸፈኑ ቤተሰቦች ጠቅላላው ብዛት 39524 ይሆናል::

5. <u>የአመዘጋገቢ፡ የመመዝገቢያ ቅጾች አሞላል እና የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ ዘዴ</u>

ይህ ጥናት የቤተሰብ ዝር፡ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነትን ብቻ የሚመለከት መሆኑ ይታወቃል:: ይሁንና የ1997 ዓ.ም. የምርት ዘመን የግብርና ናሙና ጥናትን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ቤተሰቦች ምዝገባ እና የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ምርጫም ከዚህ ጥናት ጋር በተጓዳኝ የሚከናወን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም የቤተሰብ ዝር፡ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት በገጠርም በከተማም የሚካሄድ ሲሆን በገጠር የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት

ለግብርና ናሙና ጥናት በተመረጡት የቆጠራ ቦታዎች በሙሉ ይከናወናል። የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጭ ጥናት ግን ለግብርና ናሙና ጥናት ከተመረጡት ውስጥ በተወሰኑት የቆጠራ ቦታዎች ብቻ የሚካሄድ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው። ዝርዝር የመመዝገቢያ ቅጾች አሞላልና ለጥናቱ የሚፈለጉ ቤተሰቦች አመራረጥ ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

5.1 የከተማ ቤቶችና ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅፅ 96/ከ/0 አሞላል መመሪያ

በከተማ ለሚካሄደው ጥናት የናሙና ቆጠራ ቦታዎች የተመረጡት በያዝነው ዓመት በተካሄደው አገር አቀፍ የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ወቅት ወቅታዊ በሆኑት (Updated) የቆጠራ ቦታዎች አማካኝነት ነው። በመሆኑም በኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ወቅትም የቆጠራ ቦታዎች ወቅታዊ ሲደረጉ የተወሰኑት የካርታቸው ድንበር ከነመግለጫው ወቅታዊ የተደረገ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ ወቅታዊ የተደረጉት በቆጠራ ቦታ መግለጫ (U-5) ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ለቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት ምዝገባ በአንዳንድ የቆጠራ ቦታዎች ካርታ ከነመግለጫው በአንዳንዶቹ ደግሞ መግለጫ (U-5) ብቻ ልንጠቀም እንደምንችል ማወቁ ተገቢ ነው። በዚህም ምክንያት የከተማ ቤቶችና ቤተሰቦችን ምዝገባ የሚያከናውኑት በአብዛኛው አዲስ የተቀጠሩ እና ስለካርታ መሠረታዊ ዕውቀት የሌላቸው መረጃ ሰብሳቢዎች ስለሆኑና የቆጠራ ቦታውን በመግለጫ ብቻም ይሁን ካርታና መግለጫ በመጠቀም ያለተቆጣጣሪ እገዛ ማከናወን ስለማይችሉ፡ የከተማ ቆጠራ ቦታዎችን ድንበር የማካለሉ ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ በተቆጣጣሪዎች ላይ የተጣለ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ በከተማ የተመደበ መረጃ ሰብሳቢ የቤቶችና ቤተሰቦች ምዝገባን ከመጀመሩ በፊት በተቆጣጣሪው አማካኝነት የቆጠራ ቦታውን ዞሮ ማካለልና የምዝገባውን ትክክለኛ ድንበር ለይቶ ማወቅ ይኖርበታል። ተቆጣጣሪዎችም የከተማ ቆጠራ ቦታዎችን ድንበር ማካለልና ለመረጃ ሰብሳቢዎች የማስገንዘብ ኃላፊነት የተጣለባቸው መሆኑን ተገንዝበው ተቆጣጣሪው በሊለበት መረጃ ሰብሳቢው ድንበር በማካለል ምዝገባ እንዳይጀምር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

ክፍል 1የአካባቢ መለያ

የቤተሰቦች አመዘገብ ሁኔታ

በተመረጠው ቆጠራ ቦታ የሚገኙ ቤተሰቦች በሚከተለው ሁኔታ መመዝገብ አለባቸው።

ሀ. በመጀመሪያ ለጥናቱ የተመረጠውን የቆጠራ ቦታ በተሰጠው የቆጠራ ቦታ ካርታና መግለጫ ወይም መግለጫ ብቻ መሠረት አካባቢውን ከሚያውቅ ሰው ጋር በመሆን ድንበሩን/ክልሉን ዞሮ ማየትና ማጥናት፤

ለ. የቤቶችን፣ የመንገዶችንና የመንደሮችን አቀማመጠ ማየት፤

ሐ. ምዝገባውን ከቆጠራ ቦታው ሰሜን ምዕራብ ከሚገኘው መንደር/አካባቢ በመነሳት ወደ ምስራቅ ከዚያ ወደ ምዕራብ/ጥምዝምዝሽ/ሥርዓት ባለው መንገድ በመንዝ እያንዳንዱን ቤተሰብ መመዝገብ። እያንዳንዱን ቤተሰብ

ከመዝገቡ በኋላ በቤቱ በር ወይም ሊጠፋ ከማይችል ቦታ ላይ በቾክ/ጠመኔ በእያንዳንዱ ቤት ላይ እንደአመዘጋገባቸው ቅደም ተከተል WM001, WM 002, WM010, HB123 ... ወዘተ በማለት መጻፍ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ከተመረጠው ቆጠራ ቦታ በመውጣት ምዝገባ እንዳይካሄድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም በአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰቦች/ደባሎች/ ከኖሩ እንዳይዘነጉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ደባል የሆኑ ቤተሰቦች ከተገኙም ለእያንዳንዱ ደባል ቤተሰብ የራሱ የሆነ የቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር መሰጠት እንዳለበት መገንዘብ ያሻል።

ዓምድ 1-3: ክልል፤ ዞን፤ ወረዳ

በነዚህ ዓምዶች በአሁኑ ወቅት የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክልል፤ ዞን እና ወረዳ ስም እና ካርድ ኮለሙ ከቅ/ጽ/ቤት በሚሰጠው መሠረት ይሞላሉ።

ዓምድ 4 ከተማ

የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ከተማ ስም እና ካርድ ኮለሙ ከቅ/ጽ/ቤት በሚሰጠው መሠረት በዓምዱ ይሞላሉ።

ዓምድ 5 ክፍለ ከተማ/ከፍተኛ/ወረዳ

የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክፍለ ከተማ/ከፍተኛ/ወረዳ ስም እና ካርድ ኮለሙ ከቅ/ጽ/ቤት በሚሰጠው መሠረት በዚህ ዓምድ ይሞላሉ።

ዓምድ 6 ቀበሌ

የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ቀበሌ ስም/ቁጥር እና ካርድ ኮለሙ ከቅ/ጽ/ቤት ተወስዶ በዚህ ዓምድ ይሞላሉ።

ዓምድ 7 የቆጠራ ቦታ

የቆጠራ ቦታው ቁጥር ከቅ/ጽ/ቤት ተወስዶ ለዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ዓምድና ካርድ ኮለም ክፍት ቦታ ላይ ይሞላል።

ክፍል 2 የቤተሰቦች ዝርዝርና የአመራረጥ ቅደም ተከተል

ዓምድ 8 የቤት ተከታታይ ተራ ቁጥር

በቆጠራው ቦታ ለሚገኙ ቤቶች እንደ አመዘጋገባቸው ቅደም ተከተል ተከታታይ ተራ ቁጥር 001፤ 002 ... ወዘተ በማለት ቤቶቹ ተመዝግበው እስከአለቁ ድረስ በዚህ ዓምድ ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላሉ። በተጨማሪም በቤቱ በር ከፍ ብሎ በስተግራ ባለው ጥግ ወይም በር ከሌለው አመቺ በሆነና ዝናብና ልጆች ሊያጠፉት በማይችሉበት ቦታ በጠመኔ WM001, WM002 ... ወዘተ በማለት መጻፍ አለበት። በአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ

ቤተሰቦች/ደባሎች ቢኖሩበት የእያንዳንዳቸው ኃላፊዎች በዓምድ 12 በየተራ በሚመዘገቡበት ጊዜ ተከታታይ ተራ ቁጥር አንድ ስለሆነ በዓምድ 8 አንዱ ቁጥር ተደጋግሞ መጻፍ ይኖርበታል። በሌላ በኩል ደግሞ ፎቅ በሆነበት ውስጥ አራት መኖሪያ ቤቶች ካሉ የተለያዩ ቤቶች ስለሆኑ ለአራቱም ተከታታይ የሆነ የተለያየ ተራ ቁጥር በዓምድ 8 መስጠት ያስፈልጋል። በሌላ አንጻር በአንድ አጥር ግቢ አንድ ቤተሰብ የሚኖርባቸው የተለያዩ ቤቶች ቢኖሩ እንደ አንድ ቤት ስለሚቆጠሩ አንድ የቤት ተራ ቁጥር ይሰጣቸዋል። ነገር ግን በአንድ አጥር ግቢ ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰብ የሚኖርባቸው ቤቶች ካሉ ለእያንዳንዱ ቤት የተለያየ የቤት ተራ ቁጥር በተከታታይ መስጠት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በአንድ ግቢ ውስጥ ሆነው ለተመሳሳይ ዓላማ የሚያገለግሉ ህንጻዎች ካሉ እንደ አንድ ቤት ይቆጠራሉ።

ዓምድ 9 የቤት ቁጥር/ንዑስ ቁጥር

በዚህ ዓምድ በቆጠራ ቦታው ለሚገኙ ቤቶች ሁሉ የቤት ቁጥር ያላቸው ከሆኑ የቤት ቁጥሩ ይመዘገባል። በቆጠራው ቦታ ለሚገኙ ለአብዛኛው ቤቶች በቀበሌው ጽ/ቤት የመለያ ቁጥር ተሰጥቷቸዋል። ይኸው ቁጥር በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። አንዳንድ ጊዜ አንድ ቤተሰብ ከአንድ በላይ የሆኑ የተለያዩ ቁጥሮች ያሉዋቸው መኖሪያ ቤቶች ሊይዝ ይችላል። እንዲሁም ደግሞ በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ቤተሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ የቤት ቁጥር በዚህ ዓምድ ከመሞላቱ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች በተጨማሪ ማስተዋል ያስፈልጋል።

1. በአንድ መኖሪያ ቤት ከአንድ በላይ ቤተሰቦች የሚኖሩ ከሆነ ይኸው ቁጥር ለእያንዳንዱ ቤተሰብ እየተደጋገመ በዓምድ 9 ይሞላል።

2. አንድ ቤተሰብ ከአንድ በላይ የሆኑና የተለያዩ ቁጥሮች የተሰጣቸው ቤቶች ከያዘ ቤተሰቡ የሚኖርበት የዋናው ቤት ቁጥር በዓምድ 9 ይሞላል።

3. ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሱት ትናንሽ ቤቶች ("ሰርቪስ") በተለያዩ ቤተሰቦች የተያዙ እንደሆነና የትልቅ ቤት ተቀጽላ ቁጥር የተሰጣቸው ካልሆነ በዓምድ በተሰጠው ቦታ የትልቁን ቤት ቁጥር በመሙላት ቤቶቹ የትልቅ ቤት ተቀጥላዎች መሆናቸውን በአስተያየት ዓምድ መግለጽ ያስፈልጋል። ነገር ግን ትናንሾቹን (ሰርቪሶች) የተለያዩ የራሳቸው ቁጥር በቀበሌው ጽህፈት ቤት ከተሰጣቸው ይህንኑ ቁጥር በዓምድ 9 መሙላት ያስፈልጋል።

4. በአንድ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ መኖሪያ ቤቶች በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ቤተሰቦች ተይዘው ካሉ የተሰጠው የመኖሪያ ቤት ቁጥር ግን ለግቢው የሚያገለግል አንድ ቁጥር ብቻ ከሆነ ይኸው ቁጥር ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በዓምድ 9 በእያንዳንዱ ቤት አቅጣጫ መመዝገብ

አለበት:: እነዚህ ተደጋጋሚ የቤት ቁጥሮች ለግቢው የተሰጡ መሆናቸው በአስተያየት ዓምድ መግለጽ ያስፈልጋል::

5. ቤቱ በጥናቱ ጊዜ (በምዝገባው ቀን) ቁጥር የሌለው ከሆነ ዓምዱ ባዶ በታ ይተዋል:: አንዳንድ ጊዜ ቀበሌዎች በዞን የተከፈሉ ሲሆን የቤት ቁጥር አሰጣጡም በዞኖች የተመሠረተ በመሆኑ የቤቶቹ ቁጥር ሊደጋገም ይችላል:: ይኸም ማለት ለምሣሌ በዞን 1 የቤት ቁጥር 001 ቢኖር በዞን 2፤ 3፤ ... ወዘተ ቁጥራቸው 001 የሆኑ ሌሎች ቤቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ስለዚህ ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም የዞን ቁጥርና የቤቶች ቁጥር ይጻፋል/ለምሣሌ 1/001፤ 1/002 ... ወዘተ:: ቤቱ በተለያዩ ንዑስ ቤቶች ወይም መኖሪያ ቤቶች ተከፋፍሎ የተለያዩ ቤተሰቦች የሚኖሩበት ሊሆን ይችላል:: ለእነዚህ ንዑስ ቤቶች ወይም መኖሪያ ቤቶች ከዋናው ቤት ቁጥር ቀጥሎ ለእያንዳንዳቸው ንዑስ ቁጥር በቀበሌው ተሰጥቶ እንደሆነ እነዚህ ንዑስ ቁጥሮች ከቤት ቁጥር ቀጥሎ ይመዘገባሉ:: ለምሣሌ የፎቁ ቤት ዋና ቁጥር 50 ሆኖ በውስጡ አራት ቤቶች ካሉት ለእያንዳንዱ ቤት 1፤ 2፤ 3 እና 4 የሚል ንዑስ ቁጥሮች ካላቸው እነዚህ ንዑስ ቁጥሮች ከቤቱ ቁጥር ጋር በሚያያዝ በተከታታይ 50/1፤ 50/2፤ ... ወዘተ ተብለው ይመዘገባሉ:: እንዲሁም በአንድ ግቢ ውስጥ ባሉ ቤቶች የተለያዩ ቤተሰቦች የሚኖሩ ከሆነ ለግቢው ራሱን ይቻለ ቁጥር ተሰጥቶ በግቢው ውስጥ ላሉት ቤቶች ለእያንዳንዳቸው የተለያዩ ቁጥሮች ወይም ፊደሎች ተሰጥቷቸው ከሆነ እነዚህ ቁጥሮች እንደ ንዑስ ተወስደው በዚህ ዓምድ ይመዘገባሉ::

ዓምድ 10 የቤቱ አገልግሎት

በዚህ ዓምድ የቤቱ አገልግሎት ተጠይቆ ይመዘገባል:: ዓምዱ ከመሞላቱ በፊት የሚከተሉትን ፅንሰ ሀሳቦች መገንዘብ ያስፈልጋል::

1. ለመኖሪያ ብቻ

የተመዘገበው ቤት በጥናቱ ወቅት ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያ ብቻ የሚያገለግል ከሆነ "ለመኖሪያ ብቻ" የሚል መልስ ተመዝግቦ ኮድ "1" ለኮድ መፃፊያ በተሰጠው ክፍት በታ ይሞላል::

2. ለመኖሪያና ለድርጅት

የተመዘገበው ቤት በጥናቱ ወቅት የሚሰጠው አገልግሎት በከፊል ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያና በከፊል ደግሞ ለድርጅት አገልግሎት የዋለ እንደሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመኖሪያና ለድርጅት" ተብሎ ይመዘገብና ኮድ "2" ለኮድ መፃፊያ በተሰጠው ክፍት በታ ይሞላል:: ለምሣሌ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ጠላ የሚሸጡ ቤቱ ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚል ስም ይሰጠዋል::

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

በአገር አቀፍ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የ1996 የቤተሰብ ዝርያ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት

የከተማ ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ

ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ

1	2	3	4	5	6	7
ክልል	ዞን	ወረዳ	ከተማ	ክ.ክ/ክፍተኛ/ወረዳ	ቀበሌ	የቆጠራ ቦታ

ክፍል 2 - የቤተሰቦች ዝርዝርና የአመራረጥ ቅደም ተከተል

8	9	10		11	12	13	14
				ቤቱ ለመኖሪያ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ከሆነ			
የቤት ተራ ቁጥር	የቤት ቁጥር /ንዑስ ቁጥር/ በቀበሌ የሚሰጥ	የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ = 1 ለመኖሪያና ለድርጅት = 2 ለሌላ = 3	ኮድ	የቤተሰብ ተራ ቁጥር	የቤተሰብ ኃላፊው ስም ከነአያት	የአመራረጥ ቅደም ተከተል	አስተያየት

ራንደም ስታርት ኮለም_____ ራንደም ስታርት_____ ራንደም ኢንተርቫል_____

ጠቅላላ ቤተሰቦች ብዛት _____(ከዓምድ 11)

	ስም	ፊርማ	ቀን
መረጃ ሰብሳቢ			/ /
መስክ ተቆጣጣሪ			/ /
የት/ጽ/ቤት ኃላፊ			/ /

ገጽ___ ከ___ ገጾች

ክፍል 2 - የቤተሰቦች ዝርዝርና የአመራረጥ ቅደም ተከተል

8	9	10		11	12	13	14
				ቤቱ ለመኖሪያ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ከሆነ			
የቤት ተራ ቁጥር	የቤት ቁጥር /ንዑስ ቁጥር/ በቀበሌ የሚሰጥ	የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ =1 ለመኖሪያና ለድርጅት = 2 ለሌላ =3	ኮድ	የቤተሰብ ተራ ቁጥር	የቤተሰብ ኃላፊው ስም ከነአያት	የአመራረጥ ቅደም ተከተል	አስተያየት

5.2 በገጠር የቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ 96/ገ/0 አሞላል መመሪያ

ይህ ቅጽ በተመረጠው የቆጠራ ቦታ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች በሙሉ ለመመዝገብ ያገለግላል። ምዝገባው የሚካሄደው በቆጠራ ቦታው ክልል ውስጥ ከቤት ወደ ቤት በመሄድ ስለሆነ በምዝገባው ጊዜ ቤቶች እንዳይረሱና ወይም በድጋሚ እንዳይመዘገቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች በተሟላ አኳኋን መመዝገብ ይኖርባቸዋል። የአመዘጋገቡ ተግባር እንደ ቤቶቹ አቀማመጥ ሳይዘበራረቅ መሆን አለበት።

የቤተሰቦች አመዘጋገብ ሁኔታ

በተመረጠው ቆጠራ ቦታ የሚገኙ ቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች በሚከተለው ሁኔታ መመዝገብ አለባቸው።

ሀ. በመጀመሪያ ለጥናቱ የተመረጠውን ቆጠራ ቦታ ከሚያውቅ ሰው ጋር በመሆን ድንበሩን/ክልሉን ዞሮ ማየትና ማጥናት፤

ለ. የቤቶቹን፤ የመንገዶችንና የመንደሮችን አቀማመጥ ማየት፤

ሐ. ምዝገባውን ከቆጠራ ቦታው ሰሜን ምዕራብ ከሚገኘው መንደር/አካባቢ/በመነሳት ወደ ምሥራቅ ከዚያም ወደ ምዕራብ/ጥምዝምዞሽ/ ሥርዓት ባለው መንገድ በመጓዝ እያንዳንዱን ቤተሰብና በሥራቸው የሚገኙትን የግብርና የግል ባለይዞታዎች በቅደም ተከተል መመዝገብ። እያንዳንዱን ቤተሰብ ከመዘገቡ በኋላ በቤቱ በር ወይም ሊጠፋ ከማይችል ቦታ ላይ በቾክ/ጠመኔ/ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል። ነገር ግን ምልክቶቹ ከሌሎች ጥናቶች ምልክቶች ጋር መመሳሰል የለባቸውም። ስለሆነም በተመዘገበው ቤተሰብ ቤት በር ላይ WM001, WM002 ...ምልክት መፃፍ ይኖርበታል። በተጨማሪም ከተመረጠው ቆጠራ ቦታ በመውጣት ምዝገባ እንዳይካሄድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ክፍል 1 የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ክልል ስም እና ኮድ ከቅ/ጽ/ቤት በሚሠጠው መሠረት በዓምዱና ካርድ ኮለሙ ይሞላል።

ዓምድ 2 ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ዞን ስም/ቁጥር እና ኮድ ከቅ/ጽ/ቤት በሚሠጠው መሠረት በዓምዱና ካርድ ኮለሙ ይሞላል።

ዓምድ 3 ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ወረዳ ስም እና ኮድ ከቅ/ጽ/ቤት በሚሠጠው መሠረት በዓምዱና ካርድ ኮለሙ ይሞላል::

ዓምድ 4 ገበሬ ማኅበር

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ገበሬ ማኅበር ወይም ሠፈራ ጣቢያ ወይም ጣቢያ ... ወዘተ ስም እና ኮድ ከቅ/ጽ/ቤት በሚሠጠው መሠረት በዓምዱና ካርድ ኮለሙ ይሞላል::

ዓምድ 5 የቆጠራ ቦታ ኮድ

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ ኮድ ከቅ/ጽ/ቤት በሚሠጠው መሠረት በዓምዱና ካርድ ኮለሙ ይሞላል::

ክፍል 2 የቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝር

ዓምድ 1 የቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር

በተመረጠው የቆጠራ ቦታ ለሚገኙ ቤተሰቦች በዚህ ዓምድ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ከ001 በመጀመር 002፤ 003፤ ... ወዘተ በማለት የቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ይሞላል::

ዓምድ 2 የቤተሰብ ኃላፊ ስም ከነአያት

በዓምድ 1 በተሰጠው ተራ ቁጥር አንፃር ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ከነአያት በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 3 በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ/አለ፤ የለም/

በዓምድ 2 በተመዘገቡት ቤተሰቦች ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ መኖር አለመኖሩ ተጠይቆ ካለ «አለ» ተብሎ ኮድ «1» ከሌለ ደግሞ «የለም» ተብሎ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 4 የግብርና የግል ባለይዞታ የሌላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር

በዚህ ዓምድ በዓምድ 3 ኮድ 2 የተሞላላቸውን ቤተሰቦች በመለየት/በመምረጥ/እንደቅደም ተከተላቸው ከ001 በመጀመር 002፤ 003፤ ... ወዘተ የቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ይሞላል::

ዓምድ 5 በዓምድ 3 መልሱ አለ ከሆነ የግል ባለይዞታዎች ተራ ቁጥር

በዓምድ 3 ኮድ «2» ከተሞላ በቤተሰቡ ውስጥ የግል ይዞታ ያላቸው ባለይዞታዎች ተከታታይ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 6 የግል ባለይዞታ ስም

በዚህ ዓምድ በዓምድ 5 በተሰጡት ተራ ቁጥሮች አንፃር የግል ባለይዞታው ስም ይሞላል::

ዓምድ 7 በቤተሰቡ ውስጥ የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር

በዚህ ዓምድ በዓምድ 3 ኮድ «1» የተሞላላቸውን ቤተሰቦች በመለየት/በመምረጥ/እንደቅደም ተከተላቸው ከ001 በመጀመር 002፤ 003፤ ... ወዘተ የቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ይሞላል::

ዓምድ 8-9 የአመራረጥ ቅደም ተከተል

ዓምድ 8 ለግብርና ናሙና ጥናት

ይህ ዓምድ ለግብርና ናሙና ጥናት የሚመረጡት 25 የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች እንደአመራረጥ ቅደም ተከተላቸው ከ01 በመጀመር እስከ 25 ድረስ የሚመዘገብበት ነው::

ዓምድ 9 ለቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት

(ለቤተሰብ በጀት)

ይህ ዓምድ ለቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት (የቤተሰብ በጀት ጥናት) የሚመረጡ 12 ቤተሰቦች እንደአመራረጥ ቅደም ተከተላቸው መሠረት ከ01 በመጀመር እስከ 12 ድረስ የሚመዘገብበት ነው::

ማስታወሻ:-

- በቆጠራ ቦታው ውስጥ የግል ይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት ከመጨረሻው ገጽ በዓምድ 7 በመውሰድ በተሰጠው ቦታ ላይ ይመዘገባል::

- በቆጠራ ቦታ ውስጥ የግል ይዞታ የሌላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት ደግሞ ከክፍል-2 ዓምድ 4 የመጨረሻው ተከታታይ ቁጥርን በመውሰድ በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል::

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የ1996 የቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት
የገጠር ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ

ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ

1	2	3	4	5
ክልል	ዞን	ወረዳ	ገበሬ ማኅበር	ቆጠራ ቦታ

ክፍል 2 - የቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝርና የምርጫ ቅደም ተከተል

1	2	3		4	5	6	7	8	9
በአከባቢ መለያ ቁጥር	የቤተሰብ ኃላፊ ስም ከአያት	በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ አለ 1 የለም 2	ኮድ	የዝርያ ግል ባለይዞታ የሌላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር (ዓምድ 3 ኮድ 2 ለተሞላላቸው)	በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ይዞታ ያላቸው ባለይዞታዎች ተከታታይ ቁጥር (ዓምድ 3 ኮድ 1 ለተሞላላቸው)	የባለይዞታው ሙሉ ስም	የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር	የአመራረጥ ቅደም ተከተል ለግብርና ጥናት	ለቤተሰብ በጀት ጥናት

ራንደም ስታርት ኮለም_____ ራንደም ስታርት_____ ራንደም ኢንተርቫል_____

1. የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት_____

2. የግል ባለይዞታ የሌላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት_____

ገጽ__ ከ__ ገጾች

	ስም	ፊርማ	ቀን
መረጃ ሰብሳቢ			/ /
መስክ ተቆጣጣሪ			/ /
የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ			/ /

ክፍል 2 - የቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝርና የምርጫ ቅደም ተከተል

1	2	3		4	5	6	7	8	9
ዘይሰክ መሰያ ቁጥር	የቤተሰብ ኃላፊ ስም ከነአያት	በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ አለ 1 የለም 2	ኮድ	የግብርና ግል ባለይዞታ የሌላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር (ዓምድ 3 ኮድ 2 ለተሞላላቸው)	በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ይዞታ ያላቸው ባለይዞታዎች ተከታታይ ቁጥር (ዓምድ 3 ኮድ 1 ለተሞላላቸው)	የባለይዞታው ሙሉ ስም	የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር	የአመራረጥ ቅደም ተከተል	
								ለግብርና ጥናት	ለቤተሰብ በጀት ጥናት

5.3 በክተማ የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ ዘዴ

በቅጽ 96/ከ/0 በዓምድ 10 የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ (ኮድ 1) ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት በጋራ አገልግሎት የሚሰጥ ቤት (ኮድ 2) ተብሎ በተለየው መሠረት በዓምድ 11 የቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር ተሰጥቶባቸው የሚመዘገቡት ቤተሰቦች በተሟላ ሁኔታ መጠናቀቁን፤ ቤተሰቦች ሳይዘለሉ ወይም ሳይረሱ መመዝገባቸው ከተረጋገጠ በኋላ በቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት የናሙና ጥናት የሚታቀፍ 16 ቤተሰቦች የሚከተለውን የአመራረጥ ዘዴ በመከተል ይመረጣሉ።

በቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 11 በቆጠራ ቦታው ለሚገኙ ቤተሰቦች የተሰጠውን የመጨረሻ ተራ ቁጥር በመውሰድ በጥናቱ ለሚታቀፉት 16 ቤተሰቦች ማካፈል። በዚህ ስሌት የተገኘው ቁጥር/ኢንቲጀር/ ካልሆነ ክፍልፋዩን ትቶ ሙሉው ቁጥር ይወሰዳል። ይህ ቁጥር «መ» ነው እንበል። ከዚህ በኋላ «መ»ን በመያዝ የራንደም ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ«1» እስከ «መ» ካሉት ቁጥሮች መካከል (1ና መን ጨምሮ)በመጀመሪያ የተገኘው ቁጥር ይመረጣል። ይህም የተመረጠው ቁጥር በመጀመሪያ የተመረጠውን ቤተሰብ ያመለክታል። በዚህ መሠረት ቤተሰቡ መጀመሪያ መመረጡን ለማመለከት በቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 11 ላይ የቤተሰቡ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይከበብና በዚሁ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 13 በተመረጠው ቤተሰብ አንዣር «01» ተብሎ ይፃፋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠውን ቤተሰብ ለማግኘት በመጀመሪያ ለተመረጠው ቤተሰብ በዓምድ 11 የተከበበው ተራ ቁጥር ላይ «መ» ይደመርና የሚገኘውን ቁጥር በዓምድ 11 ከተዘረዘሩት ተራ ቁጥሮች የያዘው ቤተሰብ ተራ ቁጥር ይከበብና በዓምድ 13 «02» ይፃፋል። ይህ አሠራር በጥናቱ የሚሸፈኑ 16 ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል ማለት ነው።

ምሳሌ:- በአንድ ለዚህ ጥናት በተመረጠ የቆጠራ ቦታ የተመዘገቡት ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት በዓምድ 11 ተከታታይ ተራ ቁጥር የተሰጣቸው 219 ቢሆኑና ለጥናቱ የሚመረጡት ቤተሰቦች ብዛት ደግሞ 16 ስለሆኑ:-

$$መ = \frac{219}{16} = 13.69$$

ከነጥብ በኋላ ያለው ቁጥር ይተውና መ = 13 ተብሎ ይወሰዳል። የራንደም ቁጥር ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-13 ካሉት ቁጥሮች ውስጥ (1ንና 13ን ጨምሮ) በቅድሚያ የተገኘው ቁጥር ይመረጣል። በመጀመሪያ የተገኘው ቁጥር 08 ቢሆን በመጀመሪያ የተመረጠውን ይህን ቁጥር የያዘው በዓምድ 11 «008» የቤተሰብ ተራ ቁጥር የተሰጠው ቤተሰብ ይሆናል ማለት ነው። 008 የቤተሰብ ተራ ቁጥር በዓምድ 11 ይከበብና በአንዣሩ በዓምድ 13 «01 ይፃፋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠው ቤተሰብ ደግሞ 08+13 =21 ስለሆነ በስሌቱ መሠረት በዓምድ 11 21ኛውን ተከታታይ ተራ ቁጥር የያዘው ቤተሰብ ይሆናል ማለት ነው። ይህ ቁጥር በዓምድ 11 ይከበብና በአንባሩ በዓምድ 13 «02» ይባላል። ይህ አሠራር 16 ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል። በዚህም መሠረት የመጨረሻው 16ኛው ቤተሰብ ሲመረጥ በዓምድ 11 ላይ ሊኖረው የሚችል ተከታታይ ተራ ቁጥር 203 ይሆናል ማለት ነው።

ምርጫው እንደተጠናቀቀም ምዝገባውን ያካሂደው መረጃ ሰብሳቢ የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪና የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ስለ ሥራው ትክክለኛነት ስማቸውን ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበት/የተረጋገጠበት ቀን በተሰጠው ቦታ ማስፈር አለባቸው።

ማስታወሻ፡-

1. በዓምድ 11 የሚገኘው የመጨረሻው የቤተሰብ ተከታታየ ተራ ቁጥር በ16 ተካፍሎ የሚገኘው ቁጥር («መ») 10 እና ከዚያ በላይ ከሆነ የራንደም ቁጥር ሠንጠረዥ መጠቀም ያለበት ባለ ሁለት ቤት ቁጥር (2 Digits) ሲሆን፤ ተካፍሎ የተገኘው ቁጥር («መ») ግን ከ1-9 ከሆነ መጠቀም ያለብን የራንደም ቁጥር ባለ አንድ ቤት ቁጥር (One Digit) ይሆናል።

2. በቅጽ 96/ከ/0 ግርጌ ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ በራንደም ቁጥር ሠንጠረዥ ላይ የተጀመረበት ዓምድ (Random Start Column)፤ በ«1» እና «መ» መካከል (1 እና «መ»ን ጨምሮ) የተገኘው የመጀመሪያ ቁጥርና (Random Start) በዓምድ 11 ያለውን የመጨረሻው የቤተሰብ ቁጥር በ16 ተካፍሎ የተገኘው ቁጥር ማለት «መ» (Random Interval) ይመዘገባሉ።

5.4 በገጠር ለግብርና እና ለቤተሰብ፤ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ ዘዴ

በገጠር የሚካሄደው የቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት በግብርና ሥራ የተሰማሩና ያልተሰማሩ ቤተሰቦችን ማቀፍ ስለሚኖርበት እና እንዲሁም ለተጣዩ የግብርና ናሙና ጥናት እንዲያገለግል የታሰበ በመሆኑ የናሙናው ምርጫ ከከተማው በተለየ መልኩ ይከናወናል።

በተጨማሪም በመጀመሪያ ለግብርና ናሙና ጥናት የሚያስፈልጉት 25 የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ምርጫ የሚከናወን ሲሆን፣ ቀጥሎም ለቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት የሚያስፈልጉት 12 ቤተሰቦች ለግብርናው ጥናት ከተመረጡት ውስጥ እና እንዲሁም የግብርና የግል ባለይዞታ ከሌላቸው ቤተሰቦች ውስጥ ይመረጣሉ። ዝርዝር የአመራረጥ ሁኔታውም እንደሚከተለው ነው።

5.4.1 <u>ለግብርና ናሙና ጥናት</u>

1. በቅጽ 96/ገ/0 የሚመዘገቡት ቤተሰቦች ምዝገባ በተሟላ ሁኔታ መጠናቀቁን ቤተሰቦች ሳይዘለሉ ወይም ሳይረሱና የግብርና የግል ይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ሳይምታታና በትክክል መከናወኑን ደጋግሞ በማረጋገጥ የግብርና የግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው 25 ቤተሰቦች የሚከተለውን የአመራረጥ ዘዴ በመከተል ይመረጣሉ::

2. በቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 7 የግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ላላቸው ቤተሰቦች የተሰጠውን የመጨረሻ ተራ ቁጥር በመውሰድ ለሚመረጡት ቤተሰቦች ብዛት (25) ይካፈላል:: በዚህ ስሌት የተገኘው ቁጥር/ኢንቲጀር/ ካልሆነ ክፍልፋዩን ትቶ ሙሉው ቁጥር ይወሰዳል:: ይህ ቁጥር «መ» ነው እንበል:: ከዚህ በኋላ «መ»ን በመያዝ የራንደም ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-«መ» ካሉት ቁጥሮች መካከል በመጀመሪያ የተገኘው ቁጥር /«1» እና «መ»ን ጨምሮ/ ይመረጣል:: ይህም የተመረጠው ቁጥር በመጀመሪያ የተመረጠውን የግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያለውን ቤተሰብ ያመለክታል:: በዚህም መሠረት ቤተሰቡ መጀመሪያ መመረጡን ለማመልከት በቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 7 ላይ የቤተሰቡ ተከታታይ ተራ ቁጥር የከበብና በዚሁ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 8 በተመረጠው ቤተሰብ አንዣር «01» ተብሎ ይፃፋል::

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠውን የግብርና የግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያለውን ቤተሰብ ለማግኘት በመጀመሪያ ለተመረጠው ቤተሰብ በዓምድ 7 የተከበበው ተራ ቁጥር ላይ «መ» ይደመርና የሚገኘውን ቁጥር በዓምድ 7 ከተዘረዘሩት ተራ ቁጥሮች የያዘው ቤተሰብ ተራ ቁጥር ተከቦ በዓምድ 8 «02» ይፃፋል:: ይህ አሠራር በጥናቱ የሚሸፈኑ የግብርና ግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል ማለት ነው::

<u>ምሣሌ</u>:- በአንድ ለዚህ ጥናት በተመረጠ የቆጠራ ቦታ የተመዘገቡ በቤተሰባቸው ውስጥ የግብርና ግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት በዓምድ 8 ተከታታይ ተራ ቁጥር የተሰጣቸው 191 ቢሆኑና ለጥናቱ የሚመረጡት ቤተሰቦች ብዛት ደግሞ 25 ስለሆነ:-

$$መ = 191/25 = 7.64$$

ከነጥብ በኋላ ያለው ቁጥር ይተውና መ = 7 ተብሎ ይወሰዳል:: የራንደም ቁጥር ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-7 ካሉት ቁጥሮች ውስጥ በቅድሚያ የተገኘው ቁጥር ይመረጣል:: ይህን በማድረግ የተገኘው ቁጥር 02 ቢሆን በመጀመሪያ የተመረጠው ይህን ቁጥር የያዘው በዓምድ 7 «02» የቤተሰብ ተራ ቁጥር የተሠጠው ቤተሰብ ይሆናል ማለት ነው:: 002 የቤተሰብ ተራ ቁጥር በዓምድ 7 ይከበብና በአንዣሩ በዓምድ 8 «01» ይፃፋል

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠው ግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያለው ቤተሰብ ደግሞ 02 + 7 = 09 በስሌቱ መሠረት በዓምድ 7 9ኛውን ተከታታይ ተራ ቁጥር የያዘው ቤተሰብ ይሆናል ማለት ነው። ይህ ቁጥር በዓምድ 7 ይከበብና በአንዣሩ በዓምድ 8 «02» ይዣፋል። ይህ አሠራር 25 የግብርና ግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል።

2.4.2 <u>ለቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት</u>

ለቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት የሚመረጡት ቤተሰቦች ብዛት በአጠቃላይ 12 ሲሆኑ የአመራረጡም ሁኔታም እንደሚከተለው ይሆናል። የቤተሰቦች ምዝገባ ተጠናቅቆ በቆጠራ ቦታው የተገኙት ቤተሰቦች በሙሉ በግብርና የተሰማራ የግል ባለይዞታ ያላቸው ከሆኑ (በዓምድ 4 ተከታታይ ተራ ቁጥር ካልተሰጠ) ለቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት የሚፈለጉት 12 ቤተሰቦች በሙሉ ለግብርና ናሙና ጥናት ከተመረጡት 25 ቤተሰቦች መካከል ይመረጣሉ።

ነገር ግን በቆጠራ ቦታው ከተመዘገቡት ቤተሰቦች መካከል የግብርና የግል ባለይዞታ <u>የሌለው</u> ቤተሰብ የተገኘ ከሆነ (በዓምድ 4 ተከታታይ ተራ ቁጥር ተሠጥቶት ከሆነ) ለዚህ ጥናት 11 ቤተሰቦች የግብርና የግል ባለይዞታ ካላቸው እና ለግብርና ናሙና ጥናት ከተመረጡት 25 ቤተሰቦች መካከል ሲመረጡ ቀሪው 1 ቤተሰብ ደግሞ የግብርና የግል ባለይዞታ <u>ከሌላቸው</u> ቤተሰቦች ውስጥ ይመረጣል። አመራረጡም እንደሚከተለው ይሆናል።

በቆጠራ ቦታው የተገኙት ቤተሰቦች በሙሉ በግብርና የተሠማራ የቤተሰብ አባል ያላቸው ከሆኑ (በዓምድ 4 ተከታታይ ቁጥር ካልተሞላ) ለግብርና ናሙና ጥናት የተመረጡት የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ብዛት ማለትም 25 (ከዓምድ 8 መጨረሻ) ይወሰድና የግብርና የግል ባለይዞታ ካላቸው ቤተሰቦች ውስጥ ለቤተሰብ ገቢ፤ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት ለሚያስፈልጉት ቤተሰቦች ብዛት (ማለትም ከላይ በተገለፀው መሠረት ለ12) ይካፈላል። በዚህ ስሌት የተገኘው ቁጥር/ኢንቲጀር/ ካልሆነ ክፍልፋዩን ትቶ ሙሉው ቁጥር ይወሰዳል። ይህ ቁጥር «መ» ነው እንበል። ከዚህ በኋላ «መ»ን በመያዝ የራንደም ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-«መ» ካሉት ቁጥሮች መካከል በመጀመሪያ የተገኘው ቁጥር /«1» እና «መ»ን ጨምሮ/ ይመረጣል። ይህም የተመረጠው ቁጥር በመጀመሪያ የተመረጠውን የግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያለውን ቤተሰብ ያመለክታል። በዚህም መሠረት ቤተሰቡ መጀመሪያ መመረጡን ለማመልከት በቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 8 ላይ የተሰጠው ተከታታይ ተራ ቁጥር ይከበብና በዚሁ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 9 በተመረጠው ቤተሰብ አንዣር «01» ተብሎ ይዣፋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠውን የግብርና የግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያለውን ቤተሰብ ለማግኘት በመጀመሪያ ለተመረጠው ቤተሰብ በዓምድ 8 የተከበበው ተራ ቁጥር ላይ «መ» ይደመርና የሚገኘውን ቁጥር በዓምድ 8 ከተዘረዘሩት ተራ ቁጥሮች የያዘው ቤተሰብ

ተራ ቁጥር ተከቦ በዓምድ 9 «02» ይፃፋል:: ይህ አሠራር በጥናቱ የሚሸፈኑ (12) የግብርና ግል ባለይዞታ የቤተሰብ አባል ያላቸው ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል ማለት ነው::

ነገር ግን በቆጠራ ቦታው ከተመዘገቡት ቤተሰቦች መካከል በግብርና የተሠማራ የቤተሰብ አባል የሌላቸው ቤተሰቦች ካጋጠሙ (በዓምድ 4 ተከታታይ ቁጥር ተሞልቶ ከሆነ ለቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጭ እና ኢኩኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት ከሚመረጡት ቤተሰቦች አንዱ በክፍል 2 ዓምድ 4 ከተመዘገቡት ቤተሰቦች ውስጥ ይሆናል:: በዚህም መሠረት አመራረጡ ለጥናቱ የሚፈለጉት 11 ቤተሰቦች የግብርና የግል ባለይዞታ ካላቸው ቤተሰቦች መካከል የሚመረጡ ሲሆን ምርጫውም ከላይ በተገለፀው መሠረት ለግብርና ናሙና ጥናት ከተመረጡት 25 ቤተሰቦች ውስጥ ይሆናል:: ቀሪው አንድ ቤተሰብ ደግሞ የሚመረጠው በክፍል 2 ዓምድ 4 መጨረሻ የተሰጠውን ተከታታይ ቁጥር በመውሰድ በአንድና በዚህ ቁጥር መካከል አንድንና የመጨረሻውን ቁጥር ጨምሮ ከራንደም ዊንጠረኘር መጀመሪያ የተገኘውን ቁጥር በመውሰድ ሲሆን ተመራጩ ቤተሰብም በዓምድ 4 ከራንደም ዊንጠረኘር የተገኘውን ቁጥር የያዘው ቤተሰብ ይሆናል:: በመሆኑም ከዓምድ 4 ላይ የተመረጠውን ቤተሰብ ለማመልከት በዓምድ 4 ከራንደም የተገኘውን ቁጥር የያዘው ቤተሰብ ይመረጥና በአንፃሩ ደግሞ በዓምድ 9 12 ይፃፋል::

5.5 የ1996 በገጠርና በከተማ የቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጪ እና ኢኩኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት ቅጽ 96/1 አሞላል መመሪያ

በዚህ ቅጽ ላይ ለቤተሰብ ገቢ፤ ፍጆታና ወጪ እና ኢኩኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት የተመረጡት በከተማ 16፤ በገጠር ደግሞ 12 ቤተሰቦች እንደ አመራረጥ ቅደም ተከተላቸው ከቅጽ 96/ከ/0 እና 96/ገ/0 በማወራረስ ይመዘገባሉ:: የእነዚህን የተመረጡትን 16ና 12 ቤተሰቦች መረጃ መረጃ ሰብሳቢው ከቤት ወደ ቤት ተዘዋውሮ በመጠየቅ ይሰበስባል::

ክፍል 1 የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1-3 ክልል፤ ዞንና ወረዳ

በዝህ ዓምዶች ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፤ ዞን፤ እና ወረዳ ስምና ኮድ ለከተማ ከቅፅ 96/ከ/0፤ ለገጠር ደግሞ ከቅጽ 96/ገ/0 ዓምድ ፤ 2 እና 3 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 4 ከተማ

ይህ ዓምድ ለከተማ ጥናቱ የሚካሄድበት ከተማ ስምና ኮድ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 1 ዓምድ 4 በመውሰድ ሲሞላ ለገጠር ግን በሠረዝ ይታለፋል:: በካርድ ኮሰሙ (በንዑስ ዓምዱ) ለከተማው የተሰጠው ኮድ ሲወራረስ ለገጠር ደግሞ ኮድ 8 ይመዘገባል::

ዓምድ 5 ክፍለ ከተማ/ክፍተኛ/ወረዳ

ይህ ዓምድ የሚሞላው ለከተማ መጠይቆች ቢሆንም ለገጠሩ መጠይቅ በንዑስ በካርድ ኮለሞቹ ኮድ 88 ይሞላለታል። ለከተማ ይህ ዓምድና ንዑስ ዓምድ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 1 ዓምድ 5 የሚገለበጥ ይሆናል።

ዓምድ 6 ቀበሌ/ገበሬ ማኅበር

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ቀበሌ/ገበሬ ማኅበር መለያ ስም/ቁጥር ለከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 1 ዓምድ 6 ለገጠር ከቅጽ 96/0 ክፍል 1 ዓምድ 4 በመውሰድ ይሞላል። ካርድ ኮለሞቹም እንዲሁ ከተጠቀሱት ዓምዶች የሚወራረሱ ይሆናሉ።

ዓምድ 7 የቆጠራ ቦታ ኮድ

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ ኮድ ለከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ዓምድ 7 ለገጠር ደግሞ ከቅጽ 96/0 ክፍል 1 ዓምድ 5 በመውሰድ ይሞላል።

ክፍል 2 የተመረጡ ቤተሰቦች ዝርዝር

ዓምድ 8 የቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር

ለከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 11 በመውሰድ ይሞላል። ለገጠር ደግሞ ከቅጽ 96/0 ከክፍል 2 ዓምድ 1 በመውሰድ ይሞላል።

ዓምድ 9 የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ከነአያት

በዚህ ዓምድ ለጥናቱ የተመረጠው የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ከነአያት ለከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ዓምድ 12 ሲወሰድ ለገጠሩ ከቅጽ 96/ገ/0 ከክፍል 2 ዓምድ 2 በመውሰድ ይመዘገባል።

ዓምድ 10 የአመራረጥ ቅደም ተከተል

የተመረጡት ቤተሰቦች የአመራረጥ ቅደም ተከተል ለከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 13 ሲወሰድ ለገጠር ከቅጽ 96/ገ/0 ከክፍል 2 ዓምድ 9 በግብርና የተሰማራ የቤተሰብ አባል ላላቸው ቤተሰቦችና በግብርና የተሰማራ የቤተሰብ አባል ለሌላቸው ቤተሰቦች ደግሞ የመጨረሻው ተራ ቁጥር ማለትም 12 ይሰጣቸዋል።

ዓምድ 11 አስተያየት

በዚህ ዓምድ ቅጹን ለመሙላት ያጋጠሙ ችግሮችና ሌሎች አስፈላጊና መገለጽ ያለባቸው አስተያየቶች ይሠፍራሉ።

በመጨረሻም የመረጃ ስብሰቢው፤ የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪውና የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ስለስራው ትክክለኛነት ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበትን/የታየበትን ቀን በተገቢው ቦታ ማስፈር አለባቸው::

<u>ማስታወሻ</u>:- ለበለጠ ግንዛቤ ከዚህ ቀጥሎ የተሰጠውን የቅጽ 96/ገ/0 እና ቅጽ 96/1 ምሳሌ ተመልከት/ች::

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የ1996 የቤተሰብ ዝ፡ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት
የተመረጡ ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ

ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ

1	2	3	4	5	6	7
ክልል	ዞን	ወረዳ	ከተማ	ክ.ከ/ክፍተኛ/ወረዳ	ቀበሌ/ገ/ማኅበር	የቆጠራ ቦታ

ክፍል 2 - የተመረጡት ቤተሰቦች ዝርዝር

8	9	10	11
የቤተሰብ መለያ ቁጥር ከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 11 ገጠር ከቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 1	የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ከነአያት ከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 12 ገጠር ከቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 2	የአመራረጥ ቅደም ተከተል ከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 13 ገጠር ከቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 9	አስተያየት

	ስም	ፊርማ	ቀን
መረጃ ሰብሳቢ			
መስክ ተቆጣጣሪ			
የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ			

ገጽ ____ ከ ____ ገጾች

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የ1996 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት
የገጠር ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ

ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ

1	2	3	4	5
ክልል	ዞን	ወረዳ	ገበሬ ማኅበር	ቆጠራ ቦታ
ኦሮሚያ	ሸርሌ	ኤሚኛ	ቀሌሩ	02
04	08	11	015	02

ክፍል 2 - የቤተሰቦችና የግብርና የግል ባለይዞታዎች ዝርዝርና የምርጫ ቅደም ተከተል

1	2	3		4	5	6	7	8	9
ቤተሰብ መለያ ቁጥር	የቤተሰብ ኃላፊ ስም ከነአያት	በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ባለይዞታ አለ 1 የለም 2	ኮድ	የማጀና ግል ባለይዞታ የሌላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር (ዓምድ 3 ኮድ 2 ለተሞላላቸው)	በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና የግል ይዞታ ያላቸው ባለይዞታዎች ተከታታይ ቁጥር (ዓምድ 3 ኮድ 1 ለተሞላላቸው)	የባለይዞታው ሙሉ ስም	የግብርና የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር	የአመራረጥ ቅደም ተከተል ለግብርና ጥናት	ለቤተሰብ በጀት ጥናት
001	ሰለሺ ሽሌኽዙ	አለ	1	-	1	ሰለሺ ሽሌ	001		
		የለም	2	-	2	ዝነቡ ፋጠና	-		
002	አለሙ-ታዬ ወላሩ	አለ	1	-	1	አለሙ- ታዬ	002	01	
003	ነጋ ለማ ነጋ	የለም	2	001	-	-	-	12	
004	አሊ ኮን ባዶ	አለ	1	-	1	አሊ ኮን	003		
005	ገዳ ሽጋ ዋሲ	የለም	2	002	-	-	-		
006	ዳኮ ካሳ አየለ	አለ	1	-	1	ዳኮ ካሳ	004		
			-		2	አየለ በቀለ	-		
016	ጀርሶ ችለዴማ	አለ	1	-	1	ጀርሶ ችለ	009	02	
〃									
〃									
023	አየለ ተሬራ ቸሩ	አለ	1	-	1	አየለ ተሬራ	016	03	
024	አልዩ ሙሳ ዘሩ	አለ	1	-	1	አልዩ ሙሳ	017		
〃									
〃									
030	ሀሰን ደዲ ሮባ	አለ	1	-	1	ሀሰን ደዲ	023	04	01
〃									
〃									
037	ለማ ቸሩ ዘሩ	አለ	1	-	1	ለማ ቸሩ	030	06	02
〃									
044	አለሙ-አሊ ካሳ	አለ	1		1	አለሙ-አሊ	037	09	
〃									
100	ሃጸሉ ወሩ ገዶ	የለም	2	009	-	-	-		
〃									
168	አለሙ ገለጻ ክበዴ	አለ	1	-	1	አለሙ ገለጻ	170	25	
〃									
〃									
200	ኸበዴ ገዶ ዋቆ	አለ	1	-	1	ኸበዴ ገዶ	191		

ራንደም ስታርት ክለም 2 ራንደም ስታርት 2 ራንደም ኢንተርቫል 7

1. የግል ባለይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት 191

2. የግል ባለይዞታ የሌላቸው ቤተሰቦች ጠቅላላ ብዛት 4

	ስም	ፊርማ	ቀን
መረጃ ሰብሳቢ	ኸበዴ ችለሣ		13/08/96
መሰክ ተቆጣጣሪ	ወዳኝሽ ግሩማ		15/08/96
የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ	ሽብንጎ ለማ		20/08/96

ገጽ 1 ከ 3 ገጾች

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የ1996 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት
የተመረጡ ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ

ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ

1	2	3	4	5	6	7
ክልል	ዞን	ወረዳ	ከተማ	ክ.ከ/ከፍተኛ/ወረዳ	ቀበሌ/ገ/ማኅበር	የቆጠራ ቦታ
ጨመረያ	ጨርሲ	ጨሪኛ	-	-	ቀራ ፋ	02
04	08	11			015	02

ክፍል 2 - የተመረጡት ቤተሰቦች ዝርዝር

8	9	10	11
የቤተሰብ መለያ ቁጥር ከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 11 ገጠር ከቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 1	የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ከነአያት ከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 12 ገጠር ከቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 2	የአመራረጥ ቅደም ተከተል ከተማ ከቅጽ 96/ከ/0 ክፍል 2 ዓምድ 13 ገጠር ከቅጽ 96/ገ/0 ክፍል 2 ዓምድ 9	አስተያየት
030	ሀሰን ጀዲ ሮግ	01	
037	ለማ ቻፋ ዘፋ	02	
>>	>>	>>	
>>	>>	>>	
>>	>>	>>	
>>	>>	>>	
>>	>>	>>	
003	ገጋ ለማ ጎጋ	12	

	ስም	ፊርማ	ቀን
መረጃ ሰብሳቢ	ገበሬ ችለሣ		13/08/96
መስክ ተቆጣጣሪ	ወለጋ ሀሩሣ	Gtm	15/08/96
የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ	አብነህ ለማ	ዝጠ	20/09/96

ገጽ 1 ከ 1 ገጾች

ቅፅ 1:- የቤተሰብ የሥነ ህዝብ ባህሪያትና የሥራ ሁኔታ

በዚህ ክፍል ውስጥ ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ መደበኛ የቤተሰብ አባላት ዝርዝር፤ ከቤተሰቡ ሃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና ፆታ፤ ዕድሜ፤ ሃይማኖት፤ እንዲሁም ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የጋብቻ ሁኔታና የስራ ሁኔታ መረጃ ይሰበሰባል።

ክፍል 1:- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻና የግብርና ቤተሰብ መለያ

ዓምድ 1:- የጥናቱ መለያ

ጥናቱ መለያ ቁጥር)ሥግሸመዕ አስቀድሞ በንዑስ ዓምዶች 1፤ 2፤ 53 ስለተሞላ ምንም ይሞላል ::

ዓምድ 2:- ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም የሚመዘገብበት ነው። በዚህ ዓምድ ንዑስ ዓምድ 4 እና 3 ምንም ነገር አይሞላም።

ዓምድ 3 እና 4:- ዞንና ወረዳ:-

በናሙና የተመረጠው ቤተሰብ የሚኖርበት ዞንና ወረዳ ስሞች/ቁጥሮች በተሰጡት ክፍት ቦታዎች የሚመዘገቡ ሲሆን በንዑስ ዓምድ 6 እና 7 እንዲሁም በንዑስ ዓምድ 8 እና 9 ምንም ነገር አይሞላም።

ዓምድ 5:- ከተማ:-

ለከተማ ጥናቱ የሚመለከተው ከተማ ስም የሚሞላ ሲሆን ለገጠር ግን ባዶውን ይተዋል። ንዑስ ዓምድ 10 ምንም ነገር አይሞላም። ይሁን እንጂ ለገጠር በንዑስ ዓምድ 10 ላይ ኮድ 8 ይሞላበታል።

ዓምድ 6:- ክፍለ ከተማ/ ከፍተኛ /ወረዳ:-

ለከተማ ጥናቱ የሚመለከተው ክፈለ ከተማ ወይም ከፍተኛ /ወረዳ ስም ወይም ቁጥር ሲሞላ ለገጠር ግን ባዶውን ይተዋል። ንዑስ ዓምድ 4 እና 12 ለከተማ ምንም ነገር የማይሞላበት ሲሆን ለገጠር መጠይቅ ግን በንዑስ ዓምዶች 11 እና 12 ውስጥ ኮድ 88 ይሞላበታል።

ማሳሰቢያ:- አንዳንድ ከተሞች በወረዳ ውስጥ ሳይሆኑ የራሳቸው አስተዳደር ያላቸው ሆነው የተሸነሸኑት ደግሞ በክፍተኛ ሳይሆን በወረዳ ወይም በክፍለ ከተማ ይሆናል:: በዚህን ጊዜ በዓምድ 4 የተመዘገበው ስም/ቁጥር ተደግሞ በዓምድ 6 የወረዳው ቁጥር/ስም ይመዘገባል ማለት ነው:: ሌሎች ከተሞች ደግሞ በወረዳ ሥር ስለሚሆኑ በዓምድ 4 የሚገኙበት ወረዳ ስም ሲሞላላቸው በዓምድ 6 ደግሞ «ክፍተኛው» ይሞላል ማለት ነው:: ይሁን እንጂ አዲስ አበባ ከተማ በክፍለ ከተማ የተሸነሸነ ስለሆነ ወረዳ በሚለው ዓምድ 4 እና በዓምድ 6 ላይ የክፍለ ከተማው ስም ይመዘገባል::

ዓምድ 7:- ቀበሌ ገበሬ ማህበር:-

በዚህ ዓምድ ለከተማ የቀበሌው ቁጥር(ስም) ሲሞላ ለገጠሩ ደግሞ የገበሬ ማኅበሩ ስም (ቁጥር) ይሞላል:: ይሁን እንጂ በትግራይ በገበሬ ማኅበር ምትክ የማዘጋጃ ስም ይሞላል ማለት ነው:: በንዑስ ዓምዶች ከ13-15 ምንም ነገር አይሞላም::

ዓምድ 8:- የቆጠራ ቦታ ኮድ:-

በዚህ ዓምድ ሥር በንዑስ ዓምድ 16 እና 17 ውስጥ ለጥናቱ ለተመረጠው የቆጠራ ቦታ የተሰጠው የመለያ ኮድ ይሞላል::

ዓምድ 9:- የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር:-

በዚህ ዓምድ በንዑስ ዓምዶች 18 እና 19 ጥናቱ የሚመለከተው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር ይሞላል:: ይህ ተራ ቁጥር ከቅፅ 96/1 ክፍል 2 ዓምድ 10 የሚገለበጥ ነው::

ዓምድ 10:- የቤተሰብ አባላት ብዛት:-

በዚህ ዓምድ በንዑስ ዓምዶች 20 እና 21 ውስጥ ቤተሰቡ ያሉት መደበኛ አባላት ብዛት ተጠይቆ ይሞላል:: ይህ ቁጥር በክፍል 2 ዓምድ 13 ካለው በንዑስ በዓምድ 23 እና 24 ከተመዘገበው የቤተሰቡ የመጨረሻ አባል ከሚሰጠው የመጨረሻ ተራ ቁጥር ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል::

ዓምድ 11 የግብርና ይዞታ:-

በቤተሰቡ ውስጥ የግብርና ግል ይዞታ ያለው አባል ያለው መሆኑንና አለመሆኑን አጣርቶ በመጠየቅ ካለው ኮድ 1 ከሌለው ደግሞ ኮድ 2 በንዑስ ዓምድ 22 ላይ ይሞላል::

ዓምድ 12:- የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም ከነአያት:-

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የቤተሰቡ ኃላፊ ማን እንደሆነ አጣርቶ በመጠየቅ ስሙ፤ የአባቱ ስምና የአያት ስም ጭምር መመዝገብ ይኖርበታል። ይህ የቤተሰብ ኃላፊ በክፍል 2 ዓምድ 14 ላይ መጀመሪያ የሚመዘገብ ይሆናል።

ክፍል 2:- ስለ ቤተሰብ አባላት የስነ ሕዝብና የስራ ሁኔታ

ዓምድ 13 - የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር - ይህ ዓምድ በቅድሚያ ከ01 በመጀመር እስከ አሥራ አምስት ለሚሆኑ የቤተሰቡ አባላት ተራ ቁጥር የተሰጠበት ነው። በቤተሰቡ ውስጥ ከ15 አባላት በላይ ሌላ ቅፅ አንድ በመጠቀም "01" ን በ16፤ "02"ን በ17 እየተተካ ተራ ቁጥር የሚሰጥ ሊሆን ነገር ግን በመጀመሪያው መጠይቅ ክፍል 1 (ቅጽ 1) ያለውን መረጃ እንዳለ ወደ 2ኛው መጠይቅ (ቅጽ 1) ክፍል 1 ይተላለፋል።

ዓምድ 14 - የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም:- በዚህ መመሪያ ገጽ 4 እና 5 ላይ ለቤተሰብና ለመደበኛ ቤተሰብ አባል የተሰጠውን ትርጉምና ጽንሰ ሃሳብ መሠረት በማድረግ የቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም ተጠይቆ በአምዱ ስር ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ በሚከተለው ቅደም ተከተል ይመዘገባል:-

-የቤተሰብ ሃላፊ፤

-የኃላፊው ሚስት/ባል፤

-ያላገቡ ልጆች በዕድሜ ቅደም ተከተል (ከትልቅ ወደ ትንሽ)፤

-ያገቡ ልጆችና እዚሁ ቤት አብረው የሚኖሩ የቤተሰባቸው አባላት፤

-ሌሎች ዘመዶች፤

-ቅጥር የቤት ሰራተኛና ቅጥር የጥበቃ (ዘበኛ) ሰራተኛ

-ዘመድ ያልሆኑ አባላት።

ማሳሰቢያ፤

1. በቅርብ የተወለዱ ህፃናት፤ የዕድሜ ባለፀጋ ሰዎች፤ የቤት ሠራተኞች፤ ዘበኞች ... ወዘተ እንዳይረሱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ዓምድ 15 - ከቤተሰቡ ሃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና

በዓምድ 14 ስር ባሉት ክፍት ቦታዎች ወስጥ የቤተሰቡ አባላት ዝርዝር በሚዘጋጅበት (በሚመዘገቡበት) ጊዜ በመጀመሪያው ተራ ቁጥር የሚመዘገበው ሁልጊዜ የቤተሰቡ ኃላፊ ይሆናል። ስለዚህ በዓምድ 15 ስር ባለው ክፍት ቦታ በቤተሰቡ "ኃላፊ" ትይዩ ኃላፊ ተብሎ ከተሃፈ በኋላ ንዑስ ዓምድ 25 እና 26 ውስጥ ለኃላፊ የተሰጠውን የዝምድና ኮድ (Code) "00" እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና እየተጠየቀ በክፍት ቦታው ላይ የሚፃፍ ሲሆን ለዝምድናው ዓይነት መለያ የተሰጠው ኮድ ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 25 እና 26 ላይ ይሞላል።

ምሳሌ:- ከቤተሰቡ ኃላፊ ቀጥሳ የተመዘገበችው የቤተሰቡ ኃላፊ ሚስት ከሆነች በክፍት ቦታው ሚስት ብሎ በመፃፍ በካርድ ኮለሙ ኮድ 01 ይመዘገባል። የቤተሰቡ ኃላፊ ከአንድ በላይ ሚስት ካለውና ሚስቶቹ የርሱ ቤተሰብ አባላት ከሆኑ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና ተመሳሳይ ስለሚሆን 1ኛ ሚስት 2ኛ ሚስት እየተባለ በመፃፍ በንዑስ ዓምዶቹ ደግሞ እየተደጋገመ ኮድ 01 ይሞላላቸዋል። ይሁን እንጂ ለምን በተደጋጋሚ ኮድ 01 እንደተሰጠ በመጠይቁ ግርጌ ማስታወሻ መፃፍ ያስፈልጋል።

የቤተሰቡ መደበኛ አባላት ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና አጣርቶ በመጠየቅ ትክክለኛውን የዝምድና ዓይነት መመዝገብ ያስፈልጋል። ከዓምዱ ሥር የተዘረዘሩት የተለያዩ የዝምድና ዓይነቶችና የመለያ ቁጥራቸው (Codes) የሚከተሉት ናቸው።

ኮድ	ዝምድና
00	የቤተሰብ ኃላፊ
01	ባል/ሚስት
02	የኃላፊና የባለቤት ልጅ
03	የኃላፊ ልጅ
04	የባለቤት ልጅ
05	የኃላፊ /የባለቤት እናት ወይም አባት
06	የኃላፊ /የባለቤት ወንድም ወይም እህት
07	ሌላ ዘመድ (የሥጋና የጋብቻ ዝምድና፤ የማደጎና የክርስትና ልጅ ... ወዘተ)
08	ቅጥር የቤት ሠራተኛ
09	ቅጥር የጥበቃ (ዘበኛ) ሰራተኛ
10	ዘመድ ያልሆኑ አባላት

ማሳሰቢያ

1.ቅጥር የቤት ሠራተኛ ለዚህ ጥናት ቅጥር የቤት ሠራተኛ ማለት በገንዘብም ሆነ በዓይነት ደመወዝ/ምንዳ እየተከፈለው/ላት (በወር፤ በዓመት... ወዘተ) ቤተሰቡን ለማገልገል የተቀጠረች የቤተሰቡ አባል ማለት ነው።

ምሳሌ፦ የቤተሰቡን ምግብ የምታዘጋጅ፤ የቤተሰቡን የዕዳት ተግባራት የምታከናውን፤ ህፃናት የምትንከባከብ፤ ለቤተሰቡ ምግብ የሚሆን እህል የምትፈጭ፤ ወዘተ ናቸው። ይሁን እንጂ ጠላ ጠምቆ ለመሸጥ፤ ለንግድ የሚሆን እንጀራ ለመጋገር፤ እንጨት ለቅሞ ለመሸጥ፤ ... ወዘተ ተብሎ ተቀጥረው የሚሰሩ እንደ ቅጥር የቤት ሠራተኛ አይቆጠሩም። ምክንያቱም አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉት ለቤተሰቡ ሳይሆን ለቤተሰቡ ድርጅት በመሆናቸው ነው።

2. ቅጥር የጥበቃ ሠራተኛ (ዘበኛ)

ለዚህ ጥናት ቅጥር የጥበቃ ሠራተኛ (ዘበኛ) ማለት የቤተሰቡን ቤትና ንብረት ለመጠበቅ በአይነትም ሆነ በገንዘብ መልክ ደመወዝ/ምንዳ የሚከፈለው (በወር፤ በዓመት፤ ... ወዘተ) ተቀጣሪ የቤተሰብ አባል ማለት ነዉ። ይሁን እንጂ የቤተሰቡን የኢኮኖሚ ድርጅት ደህንነት ለመጠበቅ የተቀጠረ እንደ ቅጥር የጥበቃ ሠራተኛ (ዘበኛ) አይቆጠርም።
ምሳሌ፦ እረኛ፤ የሱቅ ጠባቂ፤ ... ወዘተ እንደ የቤተሰብ ቅጥር የጥበቃ ሠራተኛ አይቆጠሩም።

3. የቤት ሠራተኛ / ዘበኛው ከቤተሰቡ ጎላፊ ጋር የሥጋ/የጋብቻ ዝምድና ቢኖራቸውም ኮድ 08 ወይም ኮድ 09 ይሰጣቸዋል እንጂ በዝምድና ኮድ መመዝገብ የለባቸውም፡

ዓምድ 16 - ዕድ

- የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ዕድውን አጣርቶ በመጠየቅ በእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ስም አንዣር ዕድው ወንድ ከሆነ ኮድ "1" ሴት ከሆነች ደግሞ ኮድ "2" በንዑስ ዓምድ 27 ላይ ይሞላል። በስም ብቻ ዕድው ምን እንደሆነ ማወቅ ስለማይቻል የእያንዳንዱን አባል ጾታ ጠይቆ መሣፍ ያስፈልጋል። ምክንያቱም የአንዳንድ ሰዎች ስም ለሁለቱም ጾታዎች ሊያገለግል ስለሚችል (ምሳሌ ዓድቃን) ፀሐይ፤ ማስረሻ፤ ሃይማኖት፤... ወዘተ) የአባላቱን ስም ብቻ መሠረት በማድረግ ዕድቸውን በግምት ማስፈር ስህተት ስለሚያስከትል ነው። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ወንዶች በሴት ስም እንዲሁም ሴቶች በወንድ ስም ስለሚጠሩ ዕድ በሚጠየቅበት ጊዜ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ዓምድ 17 <u>ዕድሜ በሙሉ ዓመት</u>

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ይህ ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት (በጨረሱት ዓመት) በስሙ አንፀር በካርድ ኮለሞች 28 እና 29 ውስጥ ይሞላል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ የሙሉ ዓመቱን ብዛት ብቻ መመዝገብ ማለት ነው። ለምሳሌ የአንድ ሰው ዕድሜ 15 ዓመት ከ11 ወር ከ29 ቀን ቢሆን መመዝገብ ያለበት 15 ዓመት ብቻ ይሆናል እንጂ 16 ዓመት ሊሞላው አንድ ቀን ስለቀረው 16 ዓመት ተብሎ መሞላት የለበትም። የአንድ ህፃን ዕድሜ ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ «00» ይመዘገባል። እንዲሁም የአንድ ሰው ዕድሜ 97 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ «97» ብቻ ይመዘገባል።

ዕድሜያቸውን በትክክል የማያውቁ ወይም ዕድሜያቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች እንደሚያጋጥሙ ይገመታል። ስለዚህ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ትክክለኛ ዕድሜ ለማግኘት በተቻለ መጠን ባለመሰልቸት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚያስችሉት ዘዴዎች መካከል ቀጥሎ የተመለከቱትን ማጤን ይገባል።

ሀ. መልስ ሰጪው በተወለደበት ጊዜ/አካባቢ በብሄራዊ ደረጃ ወይም በሚኖርበት አካባቢ የተፈፀመ ታሪካዊ ድርጊት እንዳለና ቀጥሎም መልስ ሰጪው ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ ዕድሜው ምን ያህል እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ በመጠየቅና ከዚያም ይህንን መረጃ መሠረት በማድረግ የግለሰቡን ዕድሜ ለመገመት መሞከር ያስፈልጋል።

<u>ለምሳሌ</u>:- ግለሰቡ የ1966 አብዮት ከመፈንዳቱ 10 ዓመት ቀድሞ የተወለደ ከሆነ የግለሰቡ ዕድሜ በ1996 ዓ.ም. ከሞላ ጎደል (1996-1966)+10= 40 ዓመት ተብሎ ይመዘገባል። ስለዚህ የአንድን ግለሰብ የተወለደበት ዓመት ታሪካዊ ድርጊቶች ከተፈፀሙበት ዓመተ ምሕረት ጋር በማነፃፀር ዕድሜውን ለመገመት ስለሚቻል ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈፀሙበት ዓመተ ምሕረት ዝርዝር ከዚህ ክፍል ቀጥሎ ይገኛል።

ለ. አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ወይም በአካባቢው የሚኖሩ ግለሰቦች ዕድሜያቸውን በትክክል ሊያውቁና ሊናገሩ ይችሉ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ዕድሜያቸውን የማያውቁትን ሰዎች ዕድሜ ከነዚህ ዕድሜያቸውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል።

ሐ. ከቤተሰቡ አባላት መካከል የአንዱ ዕድሜ በትክክል ከታወቀ፣ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ይቻል ይሆናል። ለምሳሌ የአንድ ቤተሰብ የመጀመሪያው ልጅ ዕድሜው 13 ዓመት መሆኑ ከታወቀና የእናቱን ዕድሜ ለማወቅ ቢፈለግ የእናቱ ዕድሜ ቢያንስ 29 ዓመት ብሎ ለመገመት ይቻላል። ይህም ሊገኝ የሚቻለው እናቶች አብዛኛውን ጊዜ በ16 ዓመት የመጀመሪያውን ልጅ ይወልዳሉ ተብሎ ስለሚገመት የእናትየዋ ዕድሜ 16+13 = 29 ይሆናል። የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የአንዱን ዕድሜ ከሌላው በማነፃፀር ዕድሜያቸውን ለመገመት ይቻላል። ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ እናቶች በየሁለት በየሁለት ዓመት ይወልዳሉ። የትንሹ ልጅ ዕድሜ 7 ዓመት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የታላቁ ልጅ ዕድሜ 9 ዓመት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም አንድ አባል ባገባበት ጊዜዕድሜው ስንት እንደነበረና በጋብቻ ስንት ዓመት እንደቆየ ከታወቀ ዕድሜውን ለመገመት ይቻላል። ዕድሜያቸው የገፋ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ዕድሜያቸውን በጣም ከፍ ያደርጉታል። የነኚህን ሰዎች ዕድሜ ከመጀመሪያው ልጃቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል። ስለዚህ የአንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ከታወቀ ከሌላው አባል ጋር በማዛመድ በተቻለ መጠን ትክክለኛ የሆነውን ገምቶ መፃፍ ያስፈልጋል።

መ. አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች ለመናገር ይፈልጋሉ ወይም ይቀላቸዋል። ስለዚህ ዕድሜያቸውን መግለፅ የሚገባቸው ለመናገር በሚቀላቸው ወይም በሚፈልጉት ሳይሆን፣ ትክክለኛውን ዕድሜ ለማግኘት መሞከር ያስፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች በእርግጥ ዕድሜያቸው 10፣ 15፣ 20፣ 25፣ ... ወዘተ ሊሆን ይችላል።

ሠ. ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት ያላለፈ ሕፃናት ልጆች የተወለዱበትን ጊዜ ወላጆቹ ሊያስታውሱት ስለሚችሉ የሕፃናትና ትናንሽ ልጆች ዕድሜ በሙሉ ዓመት በትክክል መፃፍ አለበት። አልፎ አልፎ የሕፃናትን ትክክለኛ ዕድሜ ለማግኘት ቀላል የማይሆንበት ሁኔታ ካጋጠመም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ትክክለኛውን ዕድሜ መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህ በላይ የተሰጡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ዕድሜ ለማግኘት ትክክለኛ መልሶችን ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማቅረብና በማስላት በቂ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

ዋና ዋና የታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር

ተራ ቁ.	ታሪካዊ ድርጊቶች	ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት	ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1996 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት
1	የዓድዋ ድል የተገኘበት	1888	108
2	ንጉሥ ተክለሃይማኖት ያረፉበት	1893	103
3	ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጋራ ሙለታ ደጃዝማች ተብለው የተሾሙበት	1897	99
4	ልዑል ራስ መኮንን ያረፉበት	1898	98
5	ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዳሞ የተሾሙበት	1900	96
6	ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረርጌ የተሾሙበት	1902	94
7	አጼ ምኒልክ ያረፉበት (ልጅ ኢያሱ የነገሱበት)	1906	90
8	ራስ ሚካኤል በወሎ፡ በትግራና በጎጃም የነገሱበት	1907	89
9	ንግሥት ዘውዲቱ የነገሱበት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ የሆኑበት	1909	87
10	የሰገሌ ጦርነት የተካሄደበት	1909	87
11	እቴጌ ጣይቱ ያረፉበት	1910	86
12	የጎጃር በሽታ የነበረበት	1911	85
13	ልጅ ኢያሱ የተያዙበት	1913	83
14	ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል የሆነችበት (League of Nations)	1916	80
15	የባሪያ ነጻነት ደንብ የወጣበት	1916	80
16	ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት	1917	79
17	ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ያረፉበት	1918	78
18	አቡነ ማቴዎስ ያረፉበት	1919	77
19	ንግሥት ዘውዲቱ ያረፉበት	1922	74
20	ራስ ጉግሳ ወሌ በጎንደር የሞቱበት	1922	74
21	ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የነገሱበት	1923	73
22	የወልወል ግጭት የተደረገበት	1927	69
23	የማይጨው ጦርነት የተካሄደበት ኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት	1928	68
24	የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን	1929	67

ተራ ቁጥር	ታሪካዊ ድርጊቶች	ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት	ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1996 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት
25	በጂማ ገነቴ ላይ የአርበኞች ውጊያ የተደረገበት	1930	66
26	እንግሊዝ ኢጣልያን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የመጣበት	1933	63
27	ኢጣሊያን ድል የተመታችበት	1933	63
28	የመጀመሪያ ወያነ	1935	61
29	ለኢትዮጵያ ሰማዕታት ሀውልት የተሰራበት	1937	59
30	አቡነ ባስሊዎስ ሊቀ ጳጳስ የሆኑበት	1943	53
31	ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የተዋሃደችበት	1943	53
32	የሸንቁጤ ረሀብ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የገባበት	1950	46
33	ዘመነ አንበጣ	1951	45
34	አጄኔራል መንግሥቱ ነዋይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለመፈንቀል ሙከራ ያደረጉበት	1953	43
35	ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሐደችበት	1955	41
36	የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት	1955	41
37	ኮሌራ በሽታ የገባበት	1963	33
38	የወሎ ድርቅ	1965	31
39	የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት	1966	30
40	ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን የወረዱበት	1967	29
41 42	የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በዓል የታወጀበት	1967	29
43	የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት	1967	29
44	የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት	1967	29
45	ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያረፉበት	1967	29
46	የራሳ ዘመቻ የታወጀበት	1969	27
47	የሱማሌ ዘመቻ	1969	27
48	ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. የተመሠረተበት	1972	24
49	የቀይ ኮከብ ዘመቻ	1974	22

ተራ ቁጥር	ታሪካዊ ድርጊቶች	ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት	ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1996 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት
50	ብሔራዊ ውትድርና የታወጀበት	1975	21
51	የመጀመሪያው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደበት	1976	20
52	በትግራይና በወሎ ከፍተኛ ረሀብ የገባበት	1977	19
53	የኢ.ሠ.ፓ. ምሥረታና የ10ኛው አብዮት በዓል የተከበረበት	1977	19
54	የሰፈራ ፕሮግራም የታወጀበት	1978	16
55	የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሥት	1981	15
56	ኢሕአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት	1983	13
57	ሁለተኛው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የተካሄደበት	1987	9
58	የሽግግር መንግሥት ያከተመበት	1987	9
59	ኤርትራ ኢትዮጵያን የወረረችበት	1990	6
60	ዘመቻ ወሐይ ግባት የተጠናቀቀበት	1991	5
61	የኤርትራ ወረራ ሙሉ በሙሉ የከሸፈበት	1992	4

ዓምድ 18 - <u>የጋብቻ ሁኔታ</u>

ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት በስማቸው አንጻር የጋብቻ ሁኔታ በመጠየቅ ከተሰጡት ኮዶች ውስጥ ትክክለኛውን መርጦ በንዑስ ዓምድ 30 ይሞላል::

<u>ማሳሰቢያ</u>:- *ጋብቻ ማለት አንድ ወንድና ሴት በሕጋዊ፣ በባሕላዊ ወይም በኃይማኖታዊ መንገድ የጋብቻ ሥነ ስርዓት ፈጽመው እንደ ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ነው:: የጋብቻውን ሁኔታ ለማመልከት ከዚህ በታች የተመለከቱት የጋብቻ ዓይነቶችና ኮዶቻቸው ተሰጥተዋል::*

የጋብቻ ዓይነት	ኮድ	መግለጫ
አግብተው የሚያውቁ	1	ፈጽሞ ያላገባች/ያላገባ ማለት እስከ ጥናቱ ቀን ድረስ የትዳርን ነገር ያልሞከሩ ማለትም አግብታ የማታውቅ /አግብቶ የማያውቅ ማለት ነው።
ባለትዳር	2	ባለትዳር ማለት በጥናቱ ወቅት በጋብቻ ላይ ያለች ወይም ያለ የቤተሰብ አባል ማለት ነው።
የተፋቱ	3	ከጥናቱ ቀን በፊት አግብታ ወይም አግብቶ የነበረች/የነበረ ነገር ግን ከጥናቱ ቀን በፊት በሕጋዊ/በባሕላዊ ወይም በኃይማኖታዊ መንገድ የተፋታች/የተፋታ የቤተሰብ አባል ነው።
የተለያዩ	4	ባልና ሚስት ባለመግባባት ምክንያት ጉዳያቸው በሽማግሌዎች በመታየት ላይ ያለ ወይም ፍርድ ቤት በቀጠሮ ላይ የሚገኝ።
የሞቱባቸው	5	ባል የሞተባት ወይም ሚስት የሞተችበት ሆነው ከሞቱባቸው በኋላ እስከ ጥናቱ ቀን ድረስ ያላገቡ የቤተሰብ አባላት ማለት ነው።

ከዓምድ 19 - 23 የሥራ ሁኔታ: ዕድሜያቸው (10 ዓመትና በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት ብቻ) የሚጠየቅ

በዚህ ክፍል የሚሰበሰበው መረጃ ከጥናቱ ቀን በፊት ከነበሩት 7 ቀናት ውስጥ ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ በሆናቸው የቤተሰብ አባላት ሲከናወኑ የነበሩ የስራ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ይሆናሉ። መረጃ ሰብሳቢው ይህንን ክፍል ከመሙላቱ በፊት ዓምድ "17"ን በማየት 10 ዓመትና በላይ የሆነ ዕድሜ የተመዘገበላቸውን መለየት ይኖርበታል። ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች የሆኑ የቤተሰብ አባላት ዓምድ 18 ጀምሮ እስከ ዓምድ 23 ድረስ በሰረገዝ ይታለፋል። መረጃ ሰብሳቢው ለመልስ ሰጪው "ባለፉት 7 ቀናት ከ_____ ቀን እስከ_____ቀን ሠርተሃል" ወይ በማለት ቀኑን በመጥቀስ እየጠራ ጥያቄውን ማቅረብ ይኖርበታል። ይህንን ክፍል ለማጠናቀቅ መረጃ ሰብሳቢው በቅድሚያ የምርታማ ሥራን ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል።

ምርታማ ሥራ:- ማለት የሥራው ውጤት የሆነውን ምርት ወይም አገልግሎት በክፈል ወይም በጠቅላላ በመገንዘብ ወይም በዓይነት በመለወጥ ገቢ ለማግኘት ለገበያ ለማቅረብ ሲቻል ነው። ይህም ማለት በራስ፤ በቤተሰብ ይዞታ፤ በመንግሥታዊ፤ በሕዝባዊ ወይም በግለሰብ ድርጅት፤ በቀን፤ በሣምንት፤ በወር ወይም በሰሩት መጠን ክፍያ ወይም ገቢ ለማግኘት ሥራ ሲሰሩ ነው።

በምርታማ ሥራ ውስጥ የሚጠቃለሉ የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባራት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፦

ሀ. ትርፍ ለማስገኘት ዕቃዎችን ማምረት ለምሳሌ የፋብሪካ ውጤቶች፤ የሽክራ ሥራ፤ ...ወዘተ ወይም አገልግሎቶችን ማቅረብ ለምሳሌ ፀጉር ማስተካከል፤ የሽመና ሥራ፤ የአረቄ ንግድ ...ወዘተ፤

ለ. ለመንግሥት፤ ለሌላ ድርጅት ወይም ለግለሰብ በክፍያ የሚሰሩ ሥራዎች (ለምሳሌ ሕክምና፤ ትምህርት፤ ...)፤ በተጨማሪ ያለክፍያ ለመረዳዳት ወይም በዘመቻ የሚሰሩ (ለምሳሌ ምግብ ለሥራ፤ የደን ተከላ፤ የደቦ ሥራ ... ወዘተ)፤

ሐ. ለራስ የምግብ ፍጆታ ወይም ለሽያጭ ወይም ቋሚ ንብረት ለማከማቸት ሲባል የማምረት ተግባር እነርሱም፦

1. ለራስ የምግብ ፍጆታ ሲባል ቀዳሚ ውጤቶችን (Primary Products) የማምረት ተግባር፤ ለምሳሌ ለተለያዩ ሰብሎች (ጥራጥሬ፤ ፍራፍሬ፤ ጥጥ፤ ...ወዘተ) ማምረት፤

2. ከላይ (በተራ ቁጥር 1) ያመረቱትን ምርት ወደ ሌላ ዓይነት ምርት የመለወጥ ተግባር፤ ለምሳሌ ፈትል መፍተል ወይም ሌላ ቁሳቁሶችን ለሽያጭ ማዘጋጀት፤

3. ለራስ የምግብ ፍጆታ የሚመረቱ፤ ለምሳሌ ጠላ ጠምቀው (ከፊሉን ቢጠጡም) የሚሸጡ፤

4. ቋሚ ንብረቶችን (ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል ግልጋሎት መስጠት የሚችሉ) ለራስ ጥቅም ሲባል ማምረት፤ ለምሳሌ የራስን ግቢ ወይም አካባቢ ማንባታ፤ የእርሻ ውጤት ማከማቻ መጋዘኖችንና የእርሻ መሣሪያዎችን መሥራት፤ ሌሎች መሣሪያዎችን ማምረት ናቸው።

ከላይ የተገለፁትን ምርቶች በማምረትና ግልጋሎት በማቅረብ ተግባር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች በምርታማ ሥራ ላይ እንደተሰማሩ ይቆጠራል። ከላይ ከተጠቀሱት የማምረት ወይም ግልጋሎት የመስጠት ተግባራት ውስጥ ሊጠቃለሉ የማይችሉ ሥራዎች በጠቅላላ ምርታማ ያልሆኑ ሥራዎች በመባል ይታወቃሉ። የቤተሰቡ አባላት ያለ ክፍያ ለቤተሰብ ግልጋሎት የሚውሉ ሥራዎችን ለምሳሌ ልጆችን ማስተማር፤ ማሳደግ፤ ቤተሰቡ የሚመገበውን ምግብና መጠጥ ማዘጋጀት፤ የራሳቸውን አጥር፤ ቤት ...ወዘተ አነስተኛ የጥገና ተግባር ማከናወን፤ በበጎ ፈቃደኛነት ለአካባቢው ኅብረሰብ በተለያዩ ማኅበራዊ (ሌላ ሥራ እያላቸው) ግልጋሎት መስጠት ...ወዘተ እንደምርታማ ሥራ አይቆጠሩም። ሆኖም ከላይ የተገለፁት የቤት ውስጥ ሥራዎች ለክፍያ ተብለው እስከተከናወኑ ድረስ በምርታማ ሥራ ክፍል ይመደባሉ። በልመና፤

ሴተኛ አዳሪነት (መጠጥ ደርድረው ሆነ ሳይደረድሩ) የሚተዳደሩ ምርታማ ሥራ እንደሚሰሩ አይቆጠሩም። የቡና ቤት አሻሻጮች፤ በሴተኛ አዳሪነት ተግባር ከተሰማሩ ምርታማ ሥራ እንደሰሩ አይቆጠሩም። ነገር ግን በቡና ቤት ውስጥ ተቀጥረው የሚያገለግሉ ሌሎች ሠራተኞች ለምሳሌ አልጋ አንጣፊ፤ ገንዘብ ተቀባይ፤ ቡናና ሻይ የሚያፈሉ (ባሬስታ)፤ ወጥ ቤት፤ የቡና ቤት ባለቤቶች፤ በትላልቅ ሆቴሎች በአስተናጋጅነት ተቀጥረው የሚሰሩትን በምርታማ ሥራ እንደተሰማሩ ይቆጠራሉ። በተጨማሪም ሳይከፈላቸው የሥራ ልምምድ (በኪሮ፤ በጋራዥ፤ ...ወዘተ) የሚያደርጉ የሚሰሩት ሥራ እንደ ምርታማ ሥራ ይቆጠራል።

ዓምድ 19 - <u>ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በኢኮኖሚያዊ በምርታማ ተግባር (ለክፍያ፤ ለትርፍ ወይም ለቤተሰብ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ) ተሰማርተው ነበርን?</u>

በዚህ ጥያቄ ለማወቅ የተፈለገው የቤተሰቡ አባላት ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ከላይ የቀረበውን የምርታማ ሥራ ትርጉም በሚያሟላ ተግባር ላይ መሠማራት አለመሠማራታቸውን ነው። ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በኢኮኖሚያዊ ምርታማ ተግባር ላይ መሠማራት አለመሠማራታቸውን ለመለየት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በሚከተሉት ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች አማካኝነት አጣርቶ መጠየቅ ያስፈልጋል። እነዚህም፦

- በመንግሥት ወይም በግል ድርጅት ተቀጥረው ሠርተዋል?
- በንግድ ሥራ ተሠማርተው ነበር?
- በቅጥርም ሆነ በግል በክፍያ አገልግሎት በመስጠት ተሰማርተው ነበር?
- በግብርና ሥራ ተሰማርተው ነበር?
- ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎች አምርተው ነበር?
- ለቤተሰቡ ቋሚ ንብረት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ሰርተው ነበር?
- ያለ ክፍያ ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር?
- ከላይ ከተጠቀሱት ውጪ ሌላ ምርታማ ሥራ ሰርተዋልን? ለምሳሌ፦ በተለማማጅነት

ከነዚህ የሥራ ዘርፎች በአንዱ እንኳን ከተሳተፈ በኢኮኖሚያ በምርታማ ተግባር እንደተሠማራ ተቆጥሮ አዎ ተብሎ በመግፍ በንዑስ ዓምድ 31 ላይ ኮድ "1" ተብሎ መዛግ ሲገባ ካልተሳተፈ/ች ደግሞ የለም በማለት ኮድ "2" በካርድ ኮለሙ ይዛፋል ::

ለዚህ ጥናት አንድ ሰው ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በኢኮኖሚያ ምርታማ ተግባር ተሰማርቶ ነበር የሚባለው ቢያንስ ለአንድ ቀን ያህል በኢኮኖሚያ ምርታማ ተግባር የተሰማራ ከሆነ ሲሆን አንድ ቀን ማለት ደግሞ 4 ሰዓትና በላይ የሆነ ጊዜ ነው።

ዓምድ 20 - <u>በአምድ 19 የለም ለመለሱ ያልሠሩበት ምክንያት</u>

ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ ምንም ዓይነት ተሳትፎ ላላደረጉት ማለትም በዓምድ 19 ላይ ኮድ "2" ለተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት በሙሉ ያልሰሩበት ዋናው ምክንያት በመጠየቅና የሚገኘው መልስ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ጋር

በማዛመድ ትክክለኛውን ምክንያት በመለየት በዓምድ ስር ባለው ክፍት ቦታ በመፃፍ የመለያ ኮድ ደግሞ በንዑስ ዓምድ 32 ውስጥ ይሞላል።

ኮድ1. <u>ሥራ እያላቸዉ ያልሰሩ፡-</u> ስራ እያላቸው ያልሰሩ የሚባሉት ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በዓመት ፈቃድ፤ በወሊድ ፈቃድ፤ በሕመም፤ በትምህርት ወይም ስልጠና ላይ ስለሆኑ፤ ለጊዜው ሥራው በተለያየ ምክንያት ስለቆመ (ለምሳሌ ዕድሳት፤ የጥሬ ዕቃ እጥረት፤ የመብራት አለመኖር የመሳሰሉት) የሥራ ወቅት ባለመሆኑ (seasonal) ምክንያት ያልሠሩ ነገር ግን ችግሩ ሲቃለል ወይም ጉዳያቸው ሲያበቃ ወደ ሥራቸው የሚመለሱ መሆን አለባቸው። እነዚህም፦

በቅጥር የሚሰሩ ከሆነ በቀሩበት ወቅት ሙሉ ወይም ከፊል ክፍያ የሚያገኙ፤ ወይም ከሥራ ያስቀራቸው ምክንያት ሲቃለል ወደ ቀድሞ ሥራቸው የሚመለሱ መሆን አለባቸው፤

በግል ለሚተዳደሩ፡- እነሱ ከሥራ ቢቀሩም ድርጅታቸው ያልተዘጋ ወይም ለጊዜው ተዘግቶ ተመልሶ የሚከፈት መሆን አለበት።

ኮድ 2. <u>ሥራ አጥ፡-</u> ለዚህ ጥናት ሥራ አጥ ማለት ወደ መሥሪያ ቤቶች፤ ድርጅቶችና ግለሰቦች እየሄደ ማመልከቻ በማስገባትና በቃል በማነጋገር ሥራ በመፈለግ ላይ የሚገኝ ወይም የሥራ ማስታወቂያዎችን በመገናኛ ብዙሃንና በማስታወቂያዎች በመከታተል ላይ የሚገኝ ወይም ሥራ አፈላላጎ በማጣት እና የተስፋ የቆረጠ ቢሆንም ሥራ ቢያገኝ ግን ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ ነው።

ኮድ 3.<u>ሥራ ፈት፡-</u> ለዚህ ጥናት ስራ ፈት ማለት ስራ ፈልጎ በማጣት ተስፋ ቆርጠ ሥራ መፈለጉን የተወ/ሥራ ቢያገኝም ለመስራት ፈቃደኛ ያለሆነ፤ ወይም ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረገ ወይም ሥራ ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆነ ነው።

ኮድ 4. <u>ተማሪ፡-</u> በዚህ ክፍል የሚካተቱት ቀን ቀን ትምህርት በመከታተላቸው የተነሳ ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ስራ ላይ ያልተሰማሩ ናቸው። ሆኖም ግን ተማሪዎች ሆነው ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ተግባር ጊዜያቸውን ያሳለፉ ከሆነ ስራ እንደሰሩ ይቆጠራሉ።

ኮድ 5. <u>የቤት ውስጥ ሥራ፤</u> በዚህ ጥናት የቤት ውስጥ ሥራ የሚያመለክተው ክፍያ ሳያገኙ ለቤተሰቡ አገልግሎት በመስጠት ብቻ የሚኖሩትን የቤት እመቤት፤ አገልጋዮች፤ ሌሎች የመሳሰሉት የሚያከናውኑትን ተግባር ነው። እነዚህም የቤተሰቡ ምግብ ማዘጋጀት

ልጆችን መንከባከብ ፤ ለቤተሰቡ ውኃ ማምጣት፤ እንጨት መሰብሰብ ... ወዘተ ሥራዎች ይሆናል። ይህን በሚመለከት የሚከተሉትን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሀ. የአንድ ቤተሰብ አባላት ለሌላ ቤተሰብ በማገልገል በሚያገኙት ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩ ከሆነ በምርታማ ተግባር እንደተሰማሩ ይቆጠራል።

ለ. ነገር ግን የተመረጠው ቤተሰብ አባላት በመሆን ቤተሰቡን ያለ ክፍያ የሚያገለግሉ ከሆነ በምርታማ ተግባር እንደተሰማሩ አይቆጠርም። የቤት ውስጥ ሥራ የሚባለው ሥራው ወይም አገልግሎቱ ለቤተሰቡ ፍጆታ/ግልጋሎት የዋለ ብቻ መሆኑ መታወቅ አለበት። ሥራው/አገልግሎቱ የተከናወነው ውጤቱን በገበያ ለማቅረብ ከሆነ ምርታማ ሥራ ነው።

ኮድ 6. <u>ጡረተኛ ወይም በተቆራጭ የሚተዳደር</u>:- በጡረታ ምክንያት ከሥራው ተገልሎ ጡረታ የሚያገኝ ፡ በከተማ ቦታና ቅርፍ ቤት አዋጅ መሠረት አበል የሚያገኝ ወይም ከቤተሰብ በተገኘ ተቆራጭ ገንዘብ የሚተዳደርን ይመለከታል።

ኮድ 7. <u>እርጅና</u>:- በጡረታ፤ በአበል ወይም በተቆራጭ የማይተዳደር ሆኖ ሥራ ያልሰራው በዕድሜ መግፋት ምክንያት ሲሆን ነው።

ኮድ 8. <u>በሽተኛ</u>:- እነዚህ ግለሰቦች ታማሚ ወይም የአካል ጉዳተኞች ወይም የአዕምሮ በሽተኞች የሆኑና በምርታማ ስራ እንዳይሰማሩ ያገዳቸው ምክንያት በሽተኝነታቸው ሲሆን ነው።

<u>አካል ጉዳተኛ</u>:- ማለት የሰውነት ወይም የአእምሮ ጉዳት ነው። አካሉ የተጎዳ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መስማት የተሳነው፤ ማየት የተሳነው ወይም ከሰውነቱ አንዱ አካል የጎደለ፤ ሽባነት፤ ቁምጥናና የስጋ ደዌ፤ የልብ በሽተኛ ... ወዘተ ነው።

<u>ማሳሰቢያ</u>፤ አንዳንድ ግለሰቦች ምንም እንኳን የአካል ጉዳተኞች ወይም የአእምሮ በሽተኞች ቢሆኑም የተሰጠውን «የምርታማ ስራ» ትርጉም የሚያሟላ ስራ ከሰሩ ስራ እንደሰሩ ይቆጠራሉ።

ኮድ 9. <u>ሌላ</u>:- ሌተኛ አዳሪ፤ በልመና የሚተዳደር ፤ እስረኛ የነበረ፤ 10 ዓመት ቢሞላውም ልጅ ነኝ ላለ ... ወዘተ ሌላ በሚለው ሥር ይጠቃለላሉ።

ከዓምድ 19 ኮድ 1 ወይም ዓምድ 20 ኮድ 1 ለተሞላላቸው የሚጠየቅ

ዓምድ 21 - የቅጥር ሁኔታ (ለዋና ሥራዎ)

በዚህ ዓምድ በምርታማ ሥራ ላይ ተሠማርተው የነበሩት በዓምድ 19 ኮድ 1 እንዲሁም በዓምድ 20 ላይ ኮድ 1 ለተሞላላቸው ሰዎች የዋነኛ ሥራቸውን ማለትም ይበልጡን ጊዜ ያሳለፉበትን (የሚያሳልፉበትን) የሥራ ዓይነት መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አስር ዓይነት የቅጥር ሁኔታዎች ውስጥ ትክክለኛውን በመለየት በዓምዱ ስር ሲመዘገብ ተስማሚውን ኮድ በንዑስ ዓምድ 33 እና 34 መመላት ያስፈልጋል::

ኮድ 01.ቀጣሪ:- በራሱ ድርጅት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሰው ቀጥሮ በማሰራት የሚተዳደር ቀጣሪ ይባላል:: በድርጅታቸው ቀጥረው የሚያሰሩ ሁሉ በሥራው ላይ አብረው ቢሰማሩም እንደ ቀጣሪ ይቆጠራሉ::

ኮድ 02. የግል ሥራ መደበኛ በሆነ የሥራ ዘርፍ:- የንግድ/የሥራ ፈቃድ ባለው የግል ሥራ ወይም ድርጅታቸው ውስጥ የሚሠሩ ነገር ግን ምንም ተቀጣሪ የሌላቸው ናቸው:: የቤተሰብ አባላትን ያለ ክፍያ በማስተባበር ሥራቸውን የሚያካሂዱ ኃላፊዎች በዚህ ኮድ ይካተታሉ::

ኮድ 03. የግል ሥራ መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ:- የንግድ/የሥራ ፈቃድ በሌለው የግል ሥራ የሚተዳደሩ ሆነው ነገር ግን ምንም ተቀጣሪ የሌላቸው ናቸው:

ኮድ 04.ተቀጣሪ የግል ድርጅት (መደበኛ በሆነ የሥራ ዘርፍ):- የግል ድርጅት (መደበኛ በሆነ የሥራ ዘርፍ) ተቀጥረው በክፍያ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሠሩ ከሆነ በዚህ ይጠቃለላሉ::

ኮድ 05 ተቀጣሪ የግል ድርጅት (መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ):- በማንኛውም የግል ድርጅት መደበኛ ባልሆነ የስራ ዘርፍ ተቀጥረው በክፍያ የሚሰሩ ከሆነ በዚህ ይጠቃለላሉ::

ኮድ 06. ተቀጣሪ/ መንግሥት የልማት ድርጅት:- በመንግሥት የልማት ድርጅት ውስጥ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ደመወዝ ወይም ምንዳ እየተከፈለቸው የሚሰሩትን ያጠቃልላል:: እነዚህም አምራች ድርጅቶችና አገልግሎት ሰጪ ሆነው በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሕግና ደንብ የሚተዳደሩ ናቸው:: በሀገሪቱ ውስጥ ወደ 145 የሚሆኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አሉ:: ቴሌኮሙኒኬሽን፡ መብራት ኃይል የመሳሰሉት በዚህ ይመደባሉ::

ኮድ 07. ተቀጣሪ መንግሥት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት:- የልማት ድርጅት ባልሆነና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሕግ የሚተዳደሩ መንግስታዊ መ/ቤት ተቀጥሮ የሚሰራ:: የሚኒስቴር መ/ቤቶች፤ ኮሚሽኖች፤ የመንግሥት አስተዳደር (ከቀበሌን ጨምሮ)፤ የባለሥልጣን መ/ቤቶች... ወዘተ (በልማት ድርጅት ሥራ የሆኑትን ሳይጨምር) በዚህ ክፍል ይመደባሉ::

ኮድ 08.ተቀጣሪ በግብረ-ሰናይ ድርጅቶች:- መንግሥታዊ ባልሆነ የዕርዳታ/የልማት ድርጅት ውስጥ (በበጎ አድራጎት ድርጅቶች፤ በሕዝባውያን ድርጅቶች፤ በሃይማኖት ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች፤) የሚሰራና በጥሬ ገንዘብ ወይም በዕቃ መልክ ደመወዝ ወይም ምንዳ የሚከፈለው ሰው መንግሥታዊ ባልሆነ የዕርዳታ/የልማት ድርጅት ውስጥ ተቀጣሪ ይባላል::

ኮድ 09.ተቀጣሪ ለቤተሰብ/ለግለሰብ:- እየተከፈላቸው ቤተሰቡን በማገልገል ላይ የሚገኙ የቤት ሠራተኞች፤ ዘበኞች፤ አትክልተኞች፤ የቤተሰቡ ሾፌሮች ...ወዘተ በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ:: እነዚህ ሰዎች በማገልገል የሚገኙት የቤተሰቡን ድርጅት ሳይሆን ቤተሰቡ ራሱን መሆን ይኖርባቸዋል::

ኮድ 10.ሳይከፈለው ለቤተሰቡ ድርጅት የሚሠሩ:- ያለ ምንም ክፍያ በቤተሰቡ ድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ናቸው:: ሱቅ ላይ በመሸጥና በመለወጥ፤ በእረኝነት፤ በአራሽነት ሳይከፈላቸው የሚያገለግሉ ልጆች እንዳይዘነጉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

ኮድ 11.ሌላ:- ከተዘረዘሩት የቅጥር ሁኔታዎች በአንዱም ሊካተት ያልቻለ በዚህ ኮድ ይጠቃለላል:: ለምሳሌ ሳይከፈላቸው ሥራ የሚለማመዱ፤ ለበጎ አድራጎት ድርጅት፤ ለሕዝባውያን ድርጅት፤ ለሃይማኖት ድርጅት የሚሰሩና ምንም ክፍያ የማይሰጣቸው... ወዘተ::

ማሳሰቢያ:- ምንም እንኳን ፎርማሊቲ ባሟላ መልኩ የተሰጠ የሥራ ፈቃድ ባይኖረውም የግብርና ሥራ መደበኛ የሆነ የሥራ ዘርፍ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 22:- ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ዋና ስራዎ ምን ነበር?

ለዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ተግባር ላይ ሲሳተፉ የነበሩ ሰዎች (በዓምድ 19 ኮድ 1 ወይም በዓምድ 20 ኮድ 1 ለተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት የሥራ/ሙያ ዓይነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: ኮዱ በዋናው መ/ቤት የሚሞላ በመሆኑ ባዶ ይተዋል::

የሥራ/ሙያ ዓይነት ተብሎ የሚመዘገበው ግለሰቡ በአብዛኛው በድርጅቱ በሥራ ሰዓት ላይ እያከናወነ ያለውን የሥራ ዓይነት እንጂ የሚሰራበት ደረጃ/የሥራ መስክ የሚያመርተውን የምርት ዓይነት መሆን የለበትም:: ለምሳሌ አንድ በታይፒስትነት

ለምታገለግል ሠራተኛ የሥራ ቦታዋ ሆስፒታልም ይሁን ፋብሪካ፤ ት/ቤት፤... ወዘተ ሁልጊዜም የሚመዘገብላት ታይፒስት የሚለው የሥራ ዓይነት ነው። በዚህ ዓምድ የግለሰቡ የሥራ/ሙያ ዓይነት በሚሞላበት ጊዜ ዝርዝርና ግልፅ በሆነ መንገድ በቢሮ ውስጥ ተገቢውን የሙያ/የሥራ ኮድ ለመሙላት በሚያሻማ ሁኔታ በጥንቃቄ መሣፍ አለበት።

ከአንድ በላይ ሥራ ለነበራቸው አባላት የሚጠየቅላቸው ስለዋናው ሥራቸው ማለትም ከሌሎች የበለጠ ጊዜ የወሰደውን/የሚወስደውን ይሆናል። <u>ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ላልሰሩ</u> ዋነኛ ሥራ ተብሎ የሚመዘገብላቸው ከሥራ ከመቅረታቸው በፊት ይሰሩት የነበረውን ዋነኛ ሥራ ነው።

<u>ለዓምድ 22 በምሳሌነት የቀረቡ የሥራ/ሙያ ዓይነት</u>

ሚኒስትር	የኪዮስክ አሻሻጭ	እረኛ
የሀገ ባለሥልጣን	ጉልት ሻጭ	የእንጀራ ጋጋሪ
የወረዳ ባለሥልጣን	የሱቅ ሻጭ	ቆሎ አሣሪ
የፖለቲካ ድርጅት ባለሥልጣን	ወጉር አስተካካይ	ጠላ ጠማቂ
ዋና ሥራ አስኪያጅ	ሻይ ለንግድ አምራች	አረቄ አውጪ
የመምሪያ ኃላፊ	ሰብል ለንግድ አምራች	የአውቶብስ ሹፌር
የአገልግሎት ኃላፊ	ከብት ለንግድ አምራች	የትራክተር ሹፌር
ኬሚስት	የግብርና ዕውቀት ያላቸው ገበሬ	ጋዜጣ አሣሪ
ኢንጂነር	ሸክላ ሰሪ	የቤት ሠራተኛ
የሕክምና ዶክተር	ግንበኛ	የቡና ቤት ሣህን አጣቢ
የቄስ ት/ቤት መምህር	ሽማኔ	የቡና ቤት አልጋ አንጣፊ
የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር	ፊታይ	ዘበኛ
የታይፕ መምህር	ልብስ ሰፊ	ተላላኪ
ቄስ	ጫማ ሰፊ	የጦር ኃይል አባል
ሸክ	ገንዘብ ተቀባይ	ገንዘብ ክፉይ

ዓምድ 23 - <u>በለዋና ሥራዎ የኢንደስትሪ ዓይነት/የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት</u>

በዚህ ዓምድ ግለሰቡ የሚሰራበት ድርጅት የሚያመርተው ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት በመጠየቅ ከተሰጡት 15 አማራጭ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ ሊካተት የሚችልበትን ተስማሚ ኮድ በመምረጥ መሙላት ያስፈልጋል ኮዱም በመጠይቁ ጀርባ ላይ ይገኛል። ድርጅት ሲባል የተለየ ክፍል ወይም ቦታ ሳይኖራቸው በመኖሪያ ቤት ውስጥ በበረንዳ፤ በትናንሽ ገበያዎች/ጉልቶች፤ በመንገድ ላይ ...ወዘተ ከሚከናወኑ ጥቃቅን ሥራዎች አንስቶ የተለየ አድራሻና አደረጃጀት ያላቸውን ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎችን ያጠቃልል።

ግለሰቡ የሚሰራበት ድርጅት በየትኛው የኢንዱስትሪ ዘርፍ መካተት እንደሚገባው ለማወቅ እንዲረዳ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት የኢንዱስትሪ አዓይነቶች ዝርዝር መግለጫ በመመሪያው የመጨረሻ ክፍል የሚገኘውን ዕዝል 1 ይመልከቱ::

ኮድ 01. ግብርና፤ አደን፤ ደንህብትና ዓሣ ማስገር

ኮድ 02. ማዕድን ድንጋይና አሸዋ ማውጣት

ኮድ 03. ማምረት (ማኒፋክቸሪንግ)

ኮድ 04. ኤሌክትሪክ፤ ጋዝና ውሃ አቅርቦት

ኮድ 05. ኮንስትራክሽን

ኮድ 06. የጅምላና ችርቻሮ ንግድ፤ መኪናዎች፤ሞተር ብስክሌት፤ የግልና ቤት ውስጥ ዕቃዎች መጠገን

ኮድ 07. ሆቴሎች እና ምግብ ቤቶች

ኮድ 08. ትራንስፖርት የመጋዘን አገልግሎትና መገናኛ

ኮድ 09.የፋይናንስ/የገንዘብ እንቅስቃሴ (ዝውውር)

ኮድ 10. የማይንቀሳቀስ ንብረት፤ኪራይና ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎች

ኮድ11. የመንግስት አስተዳደርና መከላከያ የማህበራዊ ዋስትና (ጡረታ) አገልግሎት

ኮድ 12. የትምህርት፤ የጤና ማህበራዊ አገልግሎት

ኮድ 13. ሌሎች የማህበራዊ ፤ የባህል፤ የመዝናኛ፤ የግልና የቤተሰብ ግልጋሎቶች

ኮድ 14. ቅጥር ሠራተኞች ያሏቸው ቤተሰቦች

ኮድ15. የውጭ ድርጅቶች

ቅፅ 2 - የትምህርት

ክፍል 1: የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ 1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው:: (ከዓምድ 2-12)

ክፍል 2: የትምህርት ሁኔታ:- (5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ የሚሞላ)

ይህ ክፍል ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑት የቤተሰቡ አባላትየትምህርት ሁኔታ በዝርዝር የሚጠየቅበት ነው:: ለአስራር አመቺ በመሆኑ ለእያንዳንዱ አባል ከአምድ 15-28 ባሉት ዓምዶች መሠረት እየተጠየቀ ከተጠናቀቁ በኋላ ወደሚቀጥለው የቤተሰቡ አባል መሸጋገር ያስፈልጋል::

ዓምድ 13: ተራ ቁጥር ከቅጽ 1 ዓምድ 13 እንዳለ ዕድሜው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ አባል በቅደም ተከተል ይገለበጣል::

ዓምድ 14: 5 ዓመትና በላይ የሆናቸውየቤተሰቡ አባላት ዝርዝር:- ዕድሜአቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ብቻ ከቅፅ 1 ክፍል 2 ዓምድ 14 እንዳለ በቅደም ተከተል ከነተራ ቁጥሩ መገልበጥ ይኖርበታል::

ዓምድ 15: ማንበብና መፃፍ ይችላሉ:- በዚህ ዓምድ እያንዳንዱ 5 ዓመትና በላይ የሆነው የቤተሰቡ አባል ማንበብና መፃፍ መቻል አለመቻሉ ተጠይቆ "አዎን" ወይም "የለም" እየተባለ ይመዘገብና በንዑስ ዓምድ 25 ደግሞ ኮድ "1" ወይም ኮድ "2" ይፃፋል:: አንድ ግለሰብ ማንበብና መፃፍ ይችላል የሚባለው ግለሰቡ በሚያውቀው ቋንቋ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ሲችል ነው:: ሆኖም ግን የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮች ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም:: እንዲሁም ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ጎይማኖት ክፍ የሆኑ ዐረፍተ ነገሮች ብቻ ማንብነብ የሚችሉ ነገር ግን መፃፍ የማይችሉ ከሆነ የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም::

ዓምድ 16: አራቱን የሂሣብ መደብ ይችላሉ?

በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ አባላት አራቱን የሂሣብ መደቦች በቃልና በፅሑፍ (መደመር፡ መቀነስ፡ ማባዛትና ማካፈል) መቻልና አለመቻላቸውን አጣርቶ በመጠየቅ የሚችሉ ከሆነ አዎ በማለት ኮድ 1 እንዲሁም የማይችሉ ከሆነ ደግሞ የለም በመፃፍ ኮድ 2 በንዑስ አምድ 26 ላይ ይሞላል::

አንድ ሰው አራቱን የሂሣብ መደቦች ይችላል የሚባለው መደመር፡ መቀነስ፡ ማባዛትና ማካፈል በቃልና በፅሑፍ ማስላት ሲቻል ነው:: ስለሆነም አራቱን የሂሣብ መደቦች በቃላቸው የሚችሉ ሆነው በፅሑፍ ግን የማይችሉ ከሆነ ፡ እንዲሁም ከአራቱ የሂሣብ መደቦች መካከል አንድ የማይችሉት (ለምሳሌ ማባዛት) የሂሣብ መደብ ቢኖር አራቱን የሂሣብ መደብ እንደሚችሉ አይቆጠርም::

ዓምድ 17: መደበኛ ትምህርት ተከታትለው ያውቃሉ?

እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል ማንበብና መፃፍ ቢችልም ባይችልም በሕይወቱ ውስጥ መደበኛ ትምህርት ለመከታተል ተመዝግቦና ትምህርት ተከታትሎ ያውቅ እንደሆነ ተጠይቆ "አዎን" ወይም "የለም" እየተባለ ይመዘገብና በንዑስ ዓምድ 27 ደግሞ "አዎ" ላለ ኮድ "1" የለም የሚል መልስ ለሰጠ ደግሞ ኮድ "2" ይፃፋል::

ዓምድ 18: በአምድ 17 የለም ለመለሱ መደበኛ ትምህርት ያልተከታተሉበት ዋነኛው ምክንያት ምንድን ነው?

ለዚህ ዓምድ መደበኛ ትምህርት ተከታትለው እንደማያውቁ ገልፀው በዓምድ 17 ኮድ 2 የተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት በሙሉ መደበኛ ትምህርት እንዳይከታተሉ ያደረጋቸው ዋነኛ ምክንያት ተጠይቆ የሚሰጡት መልስ በዓምዱ ስር በተሰጠው ክፍት ቦታ የሚሞላ ሲሆን ለተሰጠው ዋና ምክንያት ተስማሚ የሆነ ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለም 28 እና 29 ይሞላል:: ዋና ዋና ምክንያቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል::

ዋና ምክንያት	ኮድ	መግለጫ
መስራት ፈልጌ	01	ካለማንም ግፊት/አስገዳጅነት በራሱ ተነሳሽነት በቅጥርም ሆነ በግል ሥራ ለመስራት መደበኛ ትምህርት ያልተከታተለ በዚህ ኮድ ይጠቃለላል::
ቤተሰቦቼ ስለአላስተማሩኝ	02	በቤተሰብ ፍላጎት/ግፊት መደበኛ ትምህርት ያልተከታተለ በዚህ ኮድ ይጠቃለላል::
የገንዘብ አቅም ስለሌለኝ	03	ለት/ቤት የሚከፈል ልዩ ልዩ ክፍያ ማለትም ወርሃዊ ክፍያ፡ ልዩ ልዩ መዋጮ ለመክፈል ያለመቻል እንዲሁም የትምህርት ቁሳቁስ ማለትም መማሕፍት፡ የፅሕፈት መሣሪያዎች ፡ የደንብ ልብስ ... ወዘተ ለማሟላት የገንዘብ አቅም የለንም ላሉ::
ት/ቤት በአካባቢው ስለሌለ/ስላልነበረ	04	ት/ቤት በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው ባለመኖሩ ወይም አባሉ ለመማር በፈለገበት ጊዜ ያለነበረ በመሆኑ መደበኛ ትምህርት ያልተከታተሉ::

ትዳር	05	ለራስ ፍላጎት በቤተሰብ ፍላጎት ወይም በጠለፋ አማካኝነት ትዳር በመመስረታቸው መደበኛ ትምህርት መከታተል ያልቻሉ በዚህ ዓምድ ይካተታሉ
ቋሚ ህመም	06	በተለያዩ የአዕምሮ ወይም የአካል ሕመሞች ምክንያት ትምህርት መከታተል ያልቻሉ::
አካል ጉዳተኛ	07	በአካል ጉዳት ምክንያት ትምትርት ያልተከታተሉ::
የትምህርትን ጥቅም ስለማላውቅ	08	ትምህርት ይጠቅመኛል/ያስፈልገኛል ብሎ ባለማመን መደበኛ ትምህርት መከታተል ያልቻሉ በዚህ ኮድ ይካተታሉ::
ዕድሜዬ ለትምህርት ስላልደረሰ	09	ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ሆነው ነገር ግን ዕድሜዮ ለትምህርት አልደረሰም በሚል መደበኛ ትምህርት መከታተል ያልቻሉ በዚህ ኮድ ይካተታሉ::
የትምህርት ዕድሜዬ ስላለፈ	10	መማር ብፈልግም የትምህርት ዕድሜያቸው በማለፉ ምክንያት መደበኛ ትምህርት መከታተል ያልቻሉ በዚህ ኮድ ይካተታሉ::

ዓምድ 19: *<u>የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው? (በዓምድ 15 "አዎን" ለመለሱ)</u>*

በዓምድ 15 ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ ገልፀው በዓምድ 15 ኮድ 1 የተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት በሙሉ የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል ተጠይቆ የሚገኘው መልስ ከዚህ በታች በቀረበው ማብራሪያና የኮድ ዝርዝር መሠረት የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል በዓምዱ ሥር ባለው ክፍት ቦታ የሚሞላ ሲሆን ተስማሚውን ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለም 30 እና 31 ውስጥ ይሞላል::

የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ሲባል ግለሰቡ በአዲሱ ስርዓት ትምህርትም ሆነ በቀድሞው ስርዓተ ትምህርት መሠረት በመደበኛ ትምህርት ቤት፤ በኮሌጅ፤ በዩኒቨርስቲ፤ በማሰልጠኛ ተቋምና በመሳሰሉት በመማር ላይ ላሉት አሁን ካሉበት የክፍል ደረጃ በፊት ያለው ክፍል ሲሆን ከጥናቱ በፊት በአዲሱም ሆነ በቀድሞው ሥርዓት ትምህርት ሲማሩ ቆይተውና ፈተና ወስደው <u>ካለፉ ብቻ ያ የነበሩበት</u> ክፍል እነደ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ይወሰዳል:: ለምሳሌ 9ኛ ክፍል እየተማረ ላለ 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ሲባል 9ኛ ክፍል ተምሮና ፈተና ወስዶ ለወደቀ ያጠናቀቀው ከፍተኛ ክፍል 9ኛ ሳይሆን 8ኛ ሲሆን የ9ኛ ክፍል የመጨረሻ ፈተና አልፎ ከሆነ 9ኛ ያጠናቀቀ ይባላል:: ይሁን እንጂ በአዲሱ ስርዓት ትምህርት የ10ኛ እንዲሁም በቀድሞው ሥርዓተ ትምህርት የ12ኛ መልቀቂያ ፈተና የወሰዱ ቢወድቁም እንዳጠናቀቁ ይቆጠራሉ::

ማሳሰቢያ:- 1.በሰኔ በሚጠኑ ቤተሰቦች የሚገኙ አባላት፤ የ8ኛ ክፍልና የ10ኛ ክፍል ፈተናዎች የወሰዱ ከሆነ ምንም እንኳን ውጤታቸውን ባያውቁም የ8ኛ ወይም የ10ኛ ክፍል ትምህርት እንዳጠናቀቁ መቆጠር ይኖርባቸዋል::

2. በአሁኑ ወቅት የመማር ማስተማር ስርዓቱ በመከናወን ላይ ያለው በአዲሱ ስርዓት ትምህርት መሠረት መሆኑ ይታወቃል:: ስለሆነም የቀድሞ ከ1ኛ-8ኛ ከአዲሱ ከ1-8ኛ ጋር እኩል በመሆናቸው በቀድሞ ስርዓተ ትምህርት መሠረት ለተማሩትም ሆነ በአዲሱ

ለተማሩት አንድ አይነት ኮድ ይሰጣቸዋል። ነገር ግን በቀድሞው ስርዓተ ትምህርት መሠረት ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ላሉት ክፍሎች በተናጠል መመዝገብና የየራሳቸውን ኮድ መስጠት ያስፈልጋል። የጨረሱት ከፍተኛ ክፍልና ኮዶቻቸው ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል።

የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ኮድ

ያጠናቀቁት የክፍል ደረጃ	ኮድ	የክፍል መረጃ መግለጫ
ክፍል 1 በሁለቱም ስርዓት ትምህርቶች መሠረት		
መዋዕለ ሕፃናት	00	የመዋዕለ ህፃናት (KG)፤ ዜሮ ክፍል (ቅድመዝግጅት) ኑርሰሪ በመባል የሚታወቁ እንዲሁም በትምህርት ዘመኑ አንደኛ ክፍል በመከታተል ላይ የሚገኙ (ማንበብና መፃፍ ቢችሉም ባይችሉም)
1ኛ	01	ማንበብና መፃፍ ቢችሉም ባይችሉም 1ኛ ክፍል ያጠናቀቁ
2ኛ	02	ማንበብና መፃፍ ቢችሉም ባይችሉም 2ኛ ክፍል ያጠናቀቁ
3ኛ	03	ማንበብና መፃፍ ቢችሉም ባይችሉም 3ኛ ክፍል ያጠናቀቁ
4ኛ	04	ማንበብና መፃፍ ቢችሉም ባይችሉም 4ኛ ክፍል ያጠናቀቁ
5ኛ	05	የ5ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
6ኛ	06	የ6ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
7ኛ	07	የ7ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
8ኛ	08	የ8ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
ክፍል 2 - በቀድሞው ስርዓተ ትምህርት መሠረት		
9ኛ	09	የ9ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
10ኛ	10	የ10ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
11ኛ	11	የ11ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
12ኛ	12	የ12ኛ ክፍል ትምህርት አጠናቅቀው የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተፈትነው ቢያልፉም/ባያልፍም
ሰርተፊኬት	13	ከ12ኛ ክፍል በላይ ለሆነ ትምህርት በአገር አቀፍም ሆነ በውጭ አገር በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ወይም የከፍተኛ ትምህርት መስጫ ተቋማት (ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ወይም አቻ ተቋማት) ውስጥ ዲፕሎማና ከ4 በላይ ለማስገኘት ባልታቀደ ፕሮግራም በመሳተፍ ቢያንስ የአንድ የትምህርት ዘመን ተከታትለው በማጠናቀቅ ሰርተፍኬት ላገኙ ሁሉ።
የመምህራን ማሰልጠኛ ሰርተፊኬት	14	ከመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም የተገኘ ሰርተፊኬት
1ኛ ዓመት ኮሌጅ	15	በከፍተኛ ትምህርት መስጫነት በታወቀ ተቋም (ኮሌጅ፤ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ኢንስቲትዩት፤.... ወዘተ) ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ውስጥ ዲፕሎም ወይም ከዛ በላይ ለማስገኘት በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በመከታተል የ1ኛ ዓመት ትምህርት (ኮርስ) ያጠናቀቁ
2ኛ ዓመት ኮሌጅ	16	በከፍተኛ ትምህርት መስጫነት በታወቀ ተቋም (ኮሌጅ፤ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ኮሌጅ፤ ዩኒቨርስቲ፤ ኢንስቲትዩት፤.... ወዘተ) ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ውስጥ ዲፕሎም ወይም ከዛ በላይ ለማስገኘት በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በመከታተል የ2ኛ ዓመት ትምህርት (ኮርስ) ያጠናቀቁ
ዲፕሎማ	17	12ኛ ክፍል በማጠናቀቅ በከፍተኛ ትምህርት መስጫነት በታወቀ ተቋም (ኮሌጅ፤ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፤ ዩኒቨርስቲ፤ ኢንስቲትዩት፤.... ወዘተ) ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ውስጥ በመሳተፍ ዲፕሎም ላገኙ ሁሉ
3ኛ ዓመት ዩኒቨርስቲ	18	በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ተቋም በመግባት በዲፕሎም በላይ ለሆነ የትምህርት ደረጃ በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም የ3ኛ ዓመት ትምህርት (ኮርስ) ያጠናቀቁ
የመጀመሪያ ዲግሪ BA,BSc,	19	ከከፍተኛ የትምህርት መስጫ ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ያገኙ (በተለየ የትምህርት ዘርፍ ያልተካኑ (Non-Specialized) የህክምና ደክቶሮችን ጨምሮ በዚህ ይመደባሉ።

BLL ወዘተ		
ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ	20	ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ የሆነ የትምህርት ደረጃ ያላቸው በሙሉ (የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ የማስተሬት ዲግሪ፤ PHD ፣ Mphil.... ወዘተ)
ክፍል 3 - በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሠረት		
9ኛ	21	የ9ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
10ኛ	22	የ10ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
11ኛ ቅድመ ዝግጅት	23	ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባት በሚያስችለው የትምህርት መርሃ ግብር ላይ በመሳተፍ የ11ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ
12 ቅደመ ዝግጅት	24	ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባት በሚያስችለው የትምህርት መርሃ ግብር ላይ በመሳተፍ የ12ኛ ክፍል የትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ
ሰርተፍኬት በ10+1 የሙያና የቴክኒክ መርሃ ግብር	25	በ10+1 የሙያና የቴክኒክ መርሃ ግብር ትምህርት በመሳተፍ ሰርተፊኬት ያገኙ
10+1 10+2 መርሃ ግብር	26	10+2 የሙያና የቴክኒክ ትምህርት መርሃ ግብር በመሳተፍ የ10+1 (የአንድ ዓመት ትምህርት) ያጠናቀቁ
ሰርተፍኬት በ10+2 መርሃ ግብር	27	በ10+2 የሙያና የቴክኒክ ትምህርት መርሃ ግብር በመሳተፍ ሰርተፍኬት ያገኙ
10+1 በ10+3 መርሃ ግብር	28	በ10+3 የትምህርት መርሃ ግብር የአንድ ዓመት ትምህርት (10+1) ያጠናቀቁ
10+2 በ10+3 መርሃ ግብር	29	በ10+3 የትምህርት መርሃ ግብር የሁለት ዓመት ትምህርት (10+2) ያጠናቀቁ
ዲፕሎም	30	በ10+3 ፕሮግራም የሚሰጠውን ትምህርት አጠናቅቀው ዲፕሎም ያገኙ
1ኛ ዓመት ኮሌጅ		በተለያዩ ኮሌጆች/ዩኒቨርስቲዎች አማካኝነት የመጀመሪያ ዲግሪ በሚያስገኝ መርሃ ግብር የአንደኛ ዓመት ትምህርት (ኮርስ) ወስደው ያጠናቀቁ
2ኛ ዓመት ኮሌጅ	32	በተለያዩ ኮሌጆች/ዩኒቨርስቲዎች አማካኝነት የመጀመሪያ ዲግሪ በሚያስገኝ መርሃ ግብር ሁለተኛ ዓመት ትምህርት (ኮርስ) ወስደው ያጠናቀቁ
3ኛ ዓመት እና በላይ የኮሌጅ ትምህርት	33	በተለያዩ ኮሌጆች/ዩኒቨርስቲዎች አማካኝነት የመጀመሪያ ዲግሪ በሚያስገኝ መርሃ ግብር የሦስተኛ ዓመት እና በላይ የሆነ ትምህርት (ኮርስ) ወስደው ያጠናቀቁ ነገር ግን የመጀመሪያ ዲግሪ ያላገኙ
የመጀመሪያ ዲግሪ	34	በተለያዩ ኮሌጆች/ዩኒቨርስቲዎች አማካኝነት የሚሰጥ ትምህርት ፕሮግራም የመጀመሪያ ዲግሪ ያገኙ
ሌላ	98	መደበኛ ባልሆነ ትምህርት አማካኝነት ማንበብና መፃፍ የቻሉ ሁሉ (በቴሸ፤ በቁርአን፤ እቤታቸው በመማር በመሠረተ ትምህርት፤ በጎልማሳ ትምህርት ...ወዘተ

ዓምድ 20: **በያዝነው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት ለመከታተል ተመዝግበው ነበር?**

ይህ ዓምድ የቤተሰብ አባል በያዝነው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት ለመከታተል መመዝገቡንና አለመመዝገቡ የሚጠየቅበት ነው። ስለሆነም *የመደበኛ ትምህርት ለመከታተል የተመዘገቡ* የቤተሰብ አባላት ተጠይቀው የሚሰጡት መልስ

ክፍት በተተወ ቦታ ሲመዘገብ ተሰማሚውን ኮድ በመምረጥ "አዎን" ለሚለው ኮድ 1፡ "የለም" ለሚለው ደግሞ ኮድ 2 በንዑስ ዓምድ 32 ላይ ይጻፉል::

(ከዓምድ 21-23)<u>በዓምድ 20 አዎን ለመለሱ አባላት</u>

<u>ዓምድ 21: በያዝነው የትምህርት ዓመት ተመዝግበው ከነበረ ስንተኛ ክፍል?:-</u>

ይህ ዓምድ ከዓምድ 20 ጋር የተያያዘ ነው:: ጥናቱ በሚካሄድበት የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት ለመከታተል ተመዝግበናል ያሉ የቤተሰብ አባላት (ዓምድ 20 ላይ «አዎን» ለመለሱ) ስንተኛ ክፍል እንደተመዘገቡ ተጠይቀው በንዑስ ዓምድ 33 እና 34 ተሰማሚው ኮድ ይሞላል:: በአምድ 20 «የለም» ለመለሱት ግን ይህ ዓምድ በሠረዝ « - » ይታለፋል:: የክፍሉ ደረጃ ለማወቅ በዓምድ 19 የተሰጠውን መመሪያ መከተል ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 22: ትምህርት ለመከታተል የተመዘገቡበት ት/ቤት ዓይነት የትኛው ነው?</u>

ጥናቱ በሚካሄድበት ዓመት ባለው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት ለመከታተል ተመዝግበናል ያሉ የቤተሰብ አባላት (ዓምድ 19 ላይ «አዎን» ለመለሱ) የተመዘገቡበትን ት/ቤት ዓይነት ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ በዓምዱ ሥር በተተወው ባዶ ቦታ በመፃፍ በንዑስ ዓምድ 35 ደግሞ ተሰማሚው ኮድ ይሞላል:: በዓምድ 20 «የለም» ለመለሱት ግን በሠረዝ «- » እንደሚታለፍ መታወቅ አለበት::

<u>መደበኛ የትምህርት ቤቶችን ዓይነት ለመለየት የሚከተሉትን አጭር መግለጫ ይጠቀሙ::</u>

ኮድ 1. <u>የመንግሥት ት/ቤቶች</u>:- የሚባሉት በትምህርት ሚኒስቴር፡ በግብርና ሚኒስቴር፡ በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር፡ በማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ በመከላከያ ሚኒስቴር እንዲሁም እነዚህን በመሳሰሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ቁጥጥር ሥር የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶችን፡ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆችን ያጠቃልላል::

ኮድ 2. <u>የሚሲዮን/ግብረ-ሰናይ ድርጅት ት/ቤቶች (በክፍያ)</u>:-እነዚህ የመንግሥት ዕርዳታ በማግኘትም ሆነ ባለማግኘት በቤተክህነት ወይም በሃይማኖታዊ ሚሲዮን ድርጅት ወይም ሙስሊም ድርጅት ሥር እየተዳደሩ በክፍያ መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ናቸው:: መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች (መያድ/NGO) የሚደገፉና የሚተዳደሩ በክፍያ መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ ት/ቤቶች በሙሉ በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ::

ኮድ 3. <u>የሚሲዮን/ማብረ-ሰናይ ድርጅት ት/ቤቶች (በነዓ)</u> እነዚህ የመንግሥት ዕርዳታ ለማግኘት ሆነ ባለማግኘት በቤተክህነት ወይም በሃይማኖታዊ ሚሲዮን ድርጅት ወይም ሙስሊም ድርጅት ሥራ እየተዳደሩ በነዓ መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ ት/ቤቶች ናቸው መንግስታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች (መያድ/NGO) የሚደገፉና የሚተዳደሩ በነዓ መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ መደበኛ ት/ቤቶች በሙሉ በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ::

ኮድ 4. <u>የግል ት/ቤቶች:</u> የሚባሉት ከሃይማኖት ነክ ድርጅቶች: ከመንግሥትና ከማብረ-ሰናይ ድርጅቶች (NGO) ዕርዳታ ውጪ ሙሉ በሙሉ በሌሎች መንግሥታዊ ባልሆኑ በግል ወይም በሽርክና ለትርፍ ተብለው የተቋቋሙና መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ ት/ቤቶች ናቸው::

ኮድ 5. <u>የሕዝብ ትምህርት ቤቶች:-</u> የሚባሉት የመንግሥት ዕርዳታ በማግኘትም ሆነ ባለማግኘት በውስጣቸው የሚማሩ ተማሪዎች በሚያደርጉት ክፍያና በየአካባቢያቸው በሚገኘው ተገልጋይ ሕዝብ ሙሉ ቁጥጥር በመተዳደር መደበኛ ትምህርት የሚሰጥባቸው ናቸው::

ኮድ 5. <u>ሌላ /ይገለፅ/:-</u> በልዩ ልዩ የውጭ አገር መንግሥታት እየተረዱ ወይም ሳይረዱ ለዜጎቻቸው ልጆች መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ የውጭ ኮሚኒቲ ትምህርት ቤቶችና እንዲሁም ሌሎች ከላይ ከተራ ቁጥር 1-5 ውጪ ያሉት በሙሉ በዚህ ክፍል የሚመደቡ ሲሆን ምን ዓይነትና የማን ትምህርት ቤት እንደሆነ ደግሞ መገለፅ ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 23: ትምህርት እየተከታተሉ ባሉበት ት/ቤት ችግር አጋጠመዎታል?</u>

ይህ ጥያቄ ተማሪው በመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥመው ችግር ካለ ለመዳሰስ የሚያስችል ነው:: ጥያቄው የሚመለከተው በያዝነው የትምህርት ዘመን በመማር ላይ ያሉትን የቤተሰብ አባላት ብቻ ሲሆን አጠያየቁ በሚከተሉት ዘዴዎች መሠረት መከናወን ይኖርበታል::

- በመጀመሪያ በደፈናው ያጋጠመው (ለመማር እንቅፋት የሆነው) ችግር/ሮች ካለ/ሉ እንዲገለፅ ማድረግና የገለፃቸው ችግሮች ዋና ዋና ችግሮች ተብለው ከተዘረዘሩት ጋር ማዛመድ::

መልስ ሰጪው የቀረበለትን ጥያቄ በትክክል ካልገባው አልያም የሚያጋጥመው ችግር ለመግለፅ የሚያዳግተው ከሆነ ከዚህ በታች የተሰጡትን ዋና ዋና የችግር አይነቶች

በመጠቆም መንገድ መክፈትና ማውጣጣት ያስፈልጋል። በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የችግር አይነት አንፃር "ችግር ካጋጠማቸው "ኮድ 1" ምንም ዓይነት ችግር ካላጋጠማቸው ደግሞ ኮድ 2 መሞላት ይኖርበታል።

የችግሩ ዓይነት	መግለጫ
የመጽሐፍ እጥረት	እያንዳንዱን የትምህርት ዓይነት ለመከታተል የሚያስችል መፅሐፍ ባለመኖሩ ወይም እጥረት በመኖሩ ምክንያት ተማሪው ትምህርቱን ለመከታተል እየፈለገ በትምህርቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሮበት ከሆነ የችግሩን መኖር ለማመልከት በዓምዱ ስር ከተዘረዘሩት የችግር አይነቶች መካከል የመፅሐፍ እጥረት ከሚለው ስር ባለው ካርድ ኮለም 36 ውስጥ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን መፅሐፍን አስመልክቶ የጎላ ችግር የለኝም የሚል ከሆነ ደግሞ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 ይሞላል።
ደካማ የማስተማር ዘዴ	በአስተማሪዎች (በአብዛኛው) የሚሰጠው ትምህርት ተማሪውን በሚ.ያሳትፍና በሚያነቃቃ መልኩ ሳይሆን (የተለያዩ ምሳሌዎች፤ በተግባር የተደገፉ ሙከራዎች በመጠቀም፤ በጥያቄና መልስ አማካኝነት የተማሪውን ተሳትፎ በማነቃቃት፤ የክፍል፤ የቤት ስራዎች በመስጠትና በማረም ... ወዘተ ካልተደገፉ) በትምህርት ክፍል ጊዜው ውስጥ እንዲጠናቀቁ ብቻ የተሰጣቸውን እርእስቶች ገረፍ ገረፍ በማድረግ ብቻ የሚከናወን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ካተኮረና እነዚህን ችግሮች የበማሰብ ት/ቤቱ ደካማ የማስተማር ዘዴ ይከተላል ላሉ ሁሉ ካርድ ኮለም 37 ላይ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ችግሩ ከሌለ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል።
የመምህራን እጥረት	የመምህርራን እጥረት መኖሩን እንደ ችግር የሚገልፅ ከሆነ በንዑስ አምድ 38 ውስጥ ኮድ 1 ሲሞላ ችግር ከሌለ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል።
የክፍል መጨናነቅ	በአንድ ክፍል ውስጥ መኖር ከሚገባው የተማሪ ብዛት በላይ በመጨናነቅ ተማሪው ትምህርቱን በሚገባ ለመከታተል ተፅእኖ አሳድሮበት ከሆነ በካርድ ኮለም 39 ውስጥ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን የለም ከተባለ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል።
የትምህርት ቤቱ የመገልገያዎች ችግር	ቤተመፃህፍት አለመኖር / በተገቢው አገልግሎት አለመስጠት፤/ የተሟላ አለመሆን፤ የቤተሙከራ (ላብራቶሪ) አለመኖር/ ተገቢው አገልግሎት አለመስጠት፤ የወንበርና ጠረጴዛ እጥረት/ ለመማር አመቺ አለመሆን፤ የሰሌዳ አለመኖር ወይም ለመፃፍያነት አመቺ አለመሆን ፤ በት/ቤቱ መፀዳጃ ቤት አለመኖር /አመቺ አለመሆን/ ፤ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አለመኖር፤... ወዘተ የመሳሰሉት ችግሮች መኖር አለመኖር ሲሆን ችግሩ ካለ በካርድ ኮለም 40 ውስጥ ኮድ 1 ሲሞላ ችግሩ ከሌለ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል።
ደህንነት የማጣት ችግር/ስጋት	ተማሪው ትምህርቱ በሚገባ እንዳይከታተል የሚያውክ የፀጥታ ችግር መኖር ፤ ከት/ቤቱ ውጭ በሚመጡ ሰዎች አማካኝነት የሚደርስ

	የድብደባ፤ የማስፈራራት ፤ የንጥቂያ ችግር (በተለይ በሴቶች ወይም በግል የሚያደርሰው) የሚባል ከሆነ ኮድ 1 ከሌለ ደግሞ ኮድ 2 በንዑስ ዓምድ 41 ላይ ይሞላል።
ሌላ	ከላይ ከተጠቀሱት የችግር አይነቶች የተለየ ችግር በንዑስ ዓምድ 41 ውስጥ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ከሌለ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል።

ዓምድ 24: ባለፈው የትምህርት ዓመት ትምህርት ለመከታተል ተመዘግበው ነበር?

ጥናቱ ከሚካሄድበት የትምህርት ዓመት በፊት በነበረው የትምህርት ዘመን (በ1995) የመደበኛ ትምህርት ለመከታተል የተመዘገቡ የቤተሰብ አባላት ተጠይቀው የሚሰጡት መልስ ክፍት በተተው ቦታ ሲመዘገብ ተስማሚውን ኮድ በመምረጥ "አዎን" ለሚለው ኮድ 1፤ "የለም" ለሚለው ኮድ 2 በንዑስ ዓምድ 43 ውስጥ ይጻፋል።

ዓምድ 25:- (በዓምድ 24 «አዎን» ለመለሱ) ባለፈው የትምህርት ዓመት (1995) ተመዝግበው ከነበሩ ስንተኛ ክፍል?

ጥናቱ ከሚካሄድበት የትምህርት ዓመት በፊት በነበረው የትምህርት ዘመን (1995) ለመማር የተመዘገቡ የቤተሰብ አባላት (በዓምድ 24 «አዎን» ለመለሱ) ስንተኛ ክፍል ተመዝግበው እንደነበር ተጠይቀው በንዑስ ዓምድ 44 እና 45 ይጻፋል። ሆኖም በዓምድ 24 የለም ብለው ኮድ 2 ከተመዘገበ ይህ ዓምድ በስረዝ ይታለፋል። ስንተኛ ክፍል ተመዝግበው እንደነበሩ ለማወቅ ለዓምድ 19 የተሰጠውን መመሪያ መከተል ያስፈልጋል።

ዓምድ 26: ባለፈው የትምህርት ዓመት ተመዝግበው ከነበረ የመጨረሻ ፈተና ወሰዱ?

በ1995 ለመማር የተመዘገቡ የቤተሰብ አባላት በመጀመሪያ ደረጃ የዓመቱ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚሰጠውን የመጨረሻ ፈተና መውሰዳቸውና አለመውሰዳቸው ይጠየቅላቸዋል። ፈተናውን ወስደናል ለሚሉ በንዑስ አምድ 46 ላይ ኮድ 1 ሲሞላላቸው የመጨረሻ ፈተና ካልወሰዱ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላላቸዋል።

ዓምድ 27: ባለፈው የትምህርት ዘመን የመጨረሻ ፈተና ከወሰዱስ ፈተናውን አለፉ?

በዓምድ 26 ላይ የዓመቱን ትምህርት አጠናቅቀው የመጨረሻ ፈተና በመውሰዳቸው ኮድ 1 የተሞላላቸው አባላት የወሰዱት ፈተና ማለፋቸውና አለማለፋቸውን በመጠየቅ ካለፉ ኮድ 1 ከወደቁ ደግሞ ኮድ 2 በንዑስ ዓምድ 47 ላይ ይሞላል።

ዓምድ 28፡ (በአምድ) 26 የለም ለመለሰ ባለፈው የትምህርት ዓመት የጀመሩትን ክፍል ያላጠናቀቁበት ወይም የመጨረሻ ፈተና ያልወሰዱበት ምክንያት ምንድን ነው?

በ1995 የትምህርት ዘመን ትምህርት ለመማር ተመዝግበው ሲያበቁ በተለያዩ ምክንያት ሳቢያ የዓመቱን ትምህርት ማጠናቀቂያ የመጨረሻ ፈተና ያልወሰዱበት ዋና ምክንያት ምን እንደሆነ በመጠየቅ የሚሰጡት መልስ በዓምዱ ስር በተሰጠው ክፍት ቦታ መሙላት ሲሆን ለተሰጠው ዋና ምክንያት ተስማሚ የሆነ ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለም 48 እና 49 ይሞላል። ትምህርት ለማቋረጥ ዋና ዋና ምክንያቶች ከዚህ በታች ተሰጥቷል።

ዋና ምክንያት	ኮድ	መ ግ ለ ጫ
በሥራ ምክንያት	01	የዓመቱን ትምህርት አጠናቅቀው የመጨረሻ ፈተና መውሰድ ሲገባቸው ተቀጥረው ሥራ ለመስራት፤ የግል ሥራ ለመስራት፤ ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት (ለማገዝ)... ወዘተ ሲሉ የዓመቱን የመጨረሻ ፈተና ከመስጠቱ በፊት ትምህርታቸውን ያቋረጡ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ።
ክፍያውን ስለማልችል	02	ለት/ቤት የሚከፈል ልዩ ልዩ ክፍያ ማለትም ወርሃዊ ክፍያ፤ ልዩ ልዩ መዋጮ ፤ ... ወዘተ ለመክፈል ባለመቻል (አቅም በማጣት) ለመጨረሻው ፈተና ያልበቁ የቤተሰብ አባላት በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ።
የትምህርት ቁሳቁስ ባለማግኘት	03	የትምህርት ቁሳቁስ ማለትም መፃህፍት፤ የፅሕፈት መሳሪያዎች፤ የደንብ ልብስ ... ወዘተ ለማሟላት ባለመቻላቸው ከመጨረሻ ፈተና በፊት ትምህርታቸውን ያቋረጡ አባላት በዚህ ካድ ይጠቃለላሉ።
ትምህርት ቤቱ ስለራቀ	04	ት/ቤት በአካባቢው ባለመኖሩ ርቆኝ ነው ያቋረጥኩት ላሉ ሁሉ
የትምህርት ጥራት ስለቀነሰ	05	የትምህርት ጥራት መቀነስ ማለት የመምህራን ጥራት ጉድለት፤ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ጉድለት፤ የመማር ማስተማር ሂደት ደካማ መሆን፤ ወዘተ በሚል ምክንያት በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ።
ከመጨረሻው ፈተና በፊት ስለወደቅኩ	06	ትምህርት ለማቋረጥ ዋና ምክንያት የሆናቸው የመጨረሻው ፈተና ከመሰጠቱ በፊት በተሰጡ ፈተናዎች ላይ በመውደቃቸው ምክንያት ወይም ደግሞ ባመጡት ውጤት አነስተኛ መሆን ምክንያት ተስፋ ቆርጠው ትምህርታቸውን ያቋረጡ እንደሆነ ነው።
ጋብቻ በፍላጎት/ትዳር/	07	በራስ ፍላጎት ጋብቻ ፈፅመው ትምህርታቸውን ለማቋረጥ የተገደዱ በዚህ ይጠቃለላሉ።
ጋብቻ በጠለፋ/ትዳር/	08	ጋብቻ በጠለፋ ማለት ግለሰቧ ሳትፈልግ ከአቅሟ በላይ በሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ስትጠለፍ ነው።
በህመም	09	በህመም ወይም በአደጋ ምክንያት የመጨረሻውን ፈተና ለመውሰድ የተሳናቸው የቤተሰብ አባላት በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ።
እርግዝና/ ወሊድ	10	በእርግዝና ወይም በወሊድ ምክንያትር ያቋረጡ
የተፈጥሮ አደጋ	11	በአካባቢው ድርቅ በመከሰቱ በድርቅ፤ በጎርፍ፤ ወረሽኝ፤ የመሬት መንቀጥቀጥ ወዘተ ምክንያት ያቋረጡትን ሁሉ ያጠቃልላል።

ሰው ሰራሽ አደጋ	12	በጦርነት ምክንያት በመፈናቀል፤ የአካባቢው ሰላም በመደፍረሱ ምክንያት በመፈናቀል፤ ከቤት ወደ ት/ቤት ለመሄድ የሚያስችል አስተማማኝ ወጥ ባለመኖሩ... ወዘተ ምክንያት ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ በሙሉ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ።
ከዚህ በላይ ትምህርት ስለማያስፈልገኝ	13	የተማረው ትምህርት በቂ እንደሆነ በማመን ያቋረጠ።
ተምሬ ስራ አገኛለሁ ብዬ ስለማላምን (ተስፋ መቁረጥ)	14	"ተምሬ የት እደርሳለሁ" በሚል ሰበብ ማቋረጥ፤ ትምህርት ለመከታተል አለመፈለግ፤ መሰላቸት፤... በመሳሰሉት ምክንያት የመጨረሻ ፈተና ከመስጠቱ በፊት ያቋረጠ።
ሌላ	15	ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውጭ የቤተሰብ አባላት የሰጡት ምክንያት በመመዝገብ ኮድ 15 ይመዘገብላቸዋል።

ቅፅ 3 - ጤና

ክፍል 1: የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ 1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው::

ክፍል 2: የጤና ሁኔታ (ለሁሉም የቤተሰቡ አባላት የሚሞላ)

ዓምድ 13: ተራ ቁጥር ከ1-15 ተራ ቁጥር በቀጥታ ከቅፅ 1 ክፍል 2 ዓምድ 13 ተወራርሷል::

ዓምድ 14: መደበኛ የቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም

በቅፅ 1 ዓምድ 14 የተመዘገቡት የቤተሰብ አባላት በሙሉ ተከታታይ ተራ ቁጥራቸው ሳይዛባ ወደዚህ ዓምድ በቀጥታ ይገለበጣሉ::

ዓምድ 15: ባለፉት 2 ወራት ውስጥ ህመም ወይም አደጋ አጋጥምዎት ነበር?

ይህ ጥያቄ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚቀርብ ነው:: የቤተሰቡ አባላት ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ የጤና መታወክ (ሕክምና ሊወስዱም ላይወስዱም ይችላሉ) ወይም አደጋ አጋጥሞት ከነበረ በዓምዱ ስር "አዎን" የሚለው ተመዝግቦ በካርድ ኮለም 25 ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ምንም የጤና ችግር ካላጋጠመው ደግሞ "የለም" የሚለው ተመዝግቦ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 ይሞላለታል::

የቤተሰቡ አባል የጤና ችግር አላጋጠመኝም ካለ ማለትም "የለም" የሚለው ተመዝግቦ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 ከተሞላለት ዓምድ 16 እና 17 ስለማይመለከተው በቀጥታ ወደ ዓምድ 18 ይታለፋል::

ማስታወሻ:-

1. ባለፉት ሁለት ወራት ሲባል መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡን ከጎበኘበት ቀን በፊት ካለው ቀን ጀምሮ ወደ ኋላ ሁለት ወራት በመቁጠር ያለውን ጊዜ ነው::

ለምሳሌ:- መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡን የጎበኘው ሰኔ 10 ቀን ቢሆን ባለፉት ሁለት ወራት የሚመለከተው ጊዜ ከሚያዝያ 10 ቀን እስከ ሰኔ 9 ቀን ይሆናል ማለት ነው::

2. አንድ ሰው የጤና ችግር ወይም አደጋ አጋጥሞታል የሚባለው ታሞ ወይም አደጋ ደርሶበት የጤና መታወክ ሲያጋጥመው ነው::

3. ሕመም ማለት የአካል ወይም የአዕምሮ ደህንነት መጓደል ማለት ሲሆን ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ለአጭር ጊዜ/ቢያንስ ለአንድ ሰዓት/ታሞ ከነበረ የጤና ችግር እንዳጋጠመው ይወሰዳል::

4. አንድ ሰው በአደጋ ምክንያት የጤና ችግር አጋጥሞታል የሚባለው በጉዳቱ ምክንያት ቢያንስ ለአንድ ሙሉ ቀን የዘወትር ተግባሩን ለማከናወን ካልቻለ፤ አደጋው ባደረሰው ጉዳት ምክንያት ሕክምና ያደረገ፤ ወይም በአደጋው ምክንያት ሕክምና አስፈልጎት ያጣን ግለሰብ ያጠቃልላል::

ዓምድ 16: ህመም/አደጋ ካጋጠመዎት ዋነኛ ህመሙ ወይም አደጋው ምን ነበር?

በዓምድ 15 ላይ ህመም ወይም አደጋ አጋጥሞናል ላሉ የቤተሰቡ አባላት ዋነኛ የህመማቸው ወይም የአደጋውን ዓይነት በመጠየቅ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የበሽታ ዓይነቶች ጋር በማዛመድ ትክክለኛውን መልስ ይሞላላቸዋል:: ለግለሰቡ (የቤተሰቡ አባል) ባለፉት 2 ወራት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆነ የህመም ዓይነት ሊያጋጥመው ስለሚችል በጥንቃቄ ጠይቆ ከህመሞቹ ወይም አደጋዎቹ ዋነኛውን በመጠየቅ ይህንኑ በዓምዱ መዝግቦ ተገቢውን ኮድ በካርድ ከለም 26 ማስፈር ያስፈልጋል::

የህመም ዓይነቶች ዝርዝር እና ኮዶቻቸው

ወባ =1
ተቅማጥ =2
አደጋ =3
የጥርስ ህመም =4
የአይን ህመም=5
የቆዳ በሽታ=6
የጆሮ፤ የአፍንጫ ወይም የጉሮሮ ህመም =7
የሰንባ ነቀርሳ በሽታ = 8
ሌላ(ይገለፅ) =9

ዓምድ 17: በህመሙ/አደጋ ምክንያት ባለፉት 2 ወራት ከመደበኛ ተግባርዎ ለምን ያህል ቀናት አቋረጡ?

በዓምድ 15 ህመም/አደጋ አጋጥሞናል ላሉ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በህመሙ/በደረሰበት አደጋ ምክንያት ባለፉት 2 ወራት ለምን ያህል ቀናት ከመደበኛ ሥራ እንደተስተጓጎለ ወይም ትምህርት እንዳቋረጠ ወይም ጨዋታ እንዳቋረጠ (ለሕፃናት) ተጠይቆ ትክክለኛውን መልስ በካርድ ከለሞች 27-28

ይመዘገብለታል። በዚህም መሠረት ምንም እንኳን ቢታመምም ከመደበኛ ተግባሩ (ሥራ/ትምህርት) ካልተስተጓጎለ "00" በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ይሞላለታል። ሆኖም አደጋ አጋጥሞኝ ነበር ላሉ የቤተሰብ አባላት በዚህ ጥያቄ ቢያንስ 1 ቀን ከመደበኛ ሥራቸው/ትምህርታቸው ሊያቋርጡ እንደሚችሉ ማስተዋል ያስፈልጋል።

ዓምድ 18: ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ወደ ህክምና ተቋም ወይም በህላዊ ሐኪም ሄደው አገልግሎት አግኝተው ነበር? (ቢታመሙም ባይታመሙም)

ጥያቄው የሚመለከታቸው የቤተሰቡ አባላት የጤና ችግር አጋጥሟቸው ወይም የጤና ችግር ባያጋጥማቸውም የጤናቸው ሁኔታ ለመከታተል ሲሉ ወደ ዘመናዊ ህክምና መስጫ ወይም ወደ ባህላዊ የህክምና ሰጪ በመሄድ ምርመራ ካደረጉ "አዎን" የሚለው ተመዝግቦ በካርድ ኮለም 29 ኮድ 1 የሚሞላላቸው ሲሆን ምርመራ ያላደረጉ ከሆነ ግን በዓምዱ ስር "የለም" የሚለው ተመዝግቦ ኮድ 2 በካርድ ኮለሙ ይሞላላቸዋል። አንድ ሰው ክትትል (ምርመራ) አድርጓል የሚባለው በዘመናዊ የሕክምና ማዕከሎች ማለትም እንደ ሆስፒታል፤ ጤና ጣቢያ፤ ክሊኒክ ከመሳሰሉት እንዲሁም ዘመናዊ የሕክምና መገልገያዎችን በመጠቀም በቤታቸውም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ሕክምና ከሚሰጡ ግለሰቦች፤ ከባሕላዊ አካሚዎችና ከመሳሰሉት ምርመራ ከተደረገለት ወይም የምክር አገልግሎት ካገኘ ነው። ነገር ግን <u>የጥንቆላ ተግባር ከሚያከናውኑ፤ ከበሮ ከሚመቱ፤ ፈሊ ከሚጥሉት ሰይጣን እናወጣለን ከሚሉ፤ መንፈሳዊ ሰበካ ከሚያደረጉ፤ የጠበልና የእምነት አገልግሎት ከሚሰጡና</u> ከመሳሰሉት የሚገኘው አገልግሎት <u>በዚህ ጥናት</u> እንደ ሕክምና አገልግሎት አይቆጠርም። ስለሆነም በዚህ ጥናት የሚካተቱ ባህላዊ አካሚዎች በጤና ጥበቃ ሚ/ር (ቢሮ) ዕውቅና የተሰጣቸው ብቻ ናቸው።

<u>በዓምድ 18 አዎን ለመለሱ</u>

<u>ዓምድ 19:</u> **<u>የህክምና ዕርዳታ ያገኙበት ዋነኛው የህክምና ተቋም የቱ ነው?</u>**

የቤተሰቡ አባል ባለፉት 2 ወራት ውስጥ የህክምና አገልግሎት አግኝቶ ከሆነ የሕክምና አገልግሎት ያገኙበትን ተቋም ከተዘረዘሩት አስር አማራጮች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በይበልጥ የጎበኘው/አብዛኛውን ሕክምና ያደረገበትን/ አንድ ተቋም በመለየት በዓምዱ ይመዘገባል። ለምሳሌ:- የሕክምና አገልግሎት የተገኘበት/የጎበኘው የሕክምና ተቋም በሚሲዩን ቢሆን ሚሲዩን የሚለው በዓምዱ ተመዝግቦ ኮድ 6 በካርድ ኮለም 30 ይመዘገብለታል።

የሕክምና ተቋማት	ኮድ
- ከባሕል ሐኪም(ፈቃድ ያለው)	0
- ሆስፒታል (የመንግስት)	1
- የጤና ጣቢያ (የመንግስት)	2
- ክሊኒክ (የመንግስት)	3
- የጤና ኬላ (የመንግስት)	4
- የግል ጤና ተቋም	5
- የሚስዮን/ግብረ-ሰናይ ጤና ተቋም	6
- ግለሰብ (የጤና ባለሙያ)	7
- ፋርማሲ	8
- ሌላ(ይገለፅ)	9

ማሳሰቢያ፡- የሕክምና ተቋማትን ለመለየት የሚከተለውን ማብራሪያ መከተል ያስፈልጋል፡-

ሀ. የግል ሆስፒታል፡- በግል/በማህበር/ በሽርክና የሚገኙ/ የመንግስት ያልሆኑ ሆስፒታሎች ናቸው። ለትርፍ የተቋቋሙ የሐይማኖት ድርጅቶች፡ ሆስፒታሎችና ሌሎች ሆስፒታሎች በዚህ ይመደባሉ። በጤና ጥበቃ መስፈርት መሠረት የእነዚህ ሆስፒታሎች ደረጃ መለስተኛ፡ መካከለኛ፡ ከፍተኛና ልዩ ሆስፒታል በመባል ይታወቃል።

ለ. የግል ክሊኒክ፡- በግል/በማህበር/ በሽርክና የሚገኙ/ የመንግስት ያልሆኑ ክሊኒኮች ናቸው። ለትርፍ የተቋቋሙ የሐይማኖት ድርጅቶች ክሊኒኮችና ሌሎች መሰል ክሊኒኮች በዚህ ይመደባሉ። የነዚህም ክሊኒኮች ደረጃ መለስተኛ፡ መካከለኛ፡ ከፍተኛና ልዩ ክሊኒክ በመባል ይታወቃል።

ሐ. የሚስዮን/ግብረ ሰናይ፡- ከመንግስት ይዞታ ውጭ የሆኑና ትርፍ ለማግኘት ያልተቋቋሙ የሐይማኖት ድርጅቶች እና ሌሎች የሕክምና ተቋማትን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህ ተቋማት በሆስፒታል፡ በክሊኒክ፡ በጤና ጣቢያና በመሳሰሉት ደረጃዎች የሚገኙ ሊሆኑ ይችላሉ።

ምሳሌ፡- በካቶሊክ ሚሲዮን፡ በመካነ ኢየሱስ፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፡ የእስልምና ሐይማኖት ድርጅቶች ...ወዘተ. የተቋቋሙ የሕክምና ማዕከላት በዚህ ይካተታሉ።

መ. ግለሰብ፡- (የጤና ባለሙያ) ምንም ዓይነት የጤና ተቋም ሳይኖራቸው በግል በቤታቸው ወይንም በጤና ተቋም ባልሆነ ሌላ ቦታ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ በዚህ ይመደባል።

ሠ. ፋርማሲ፡- ምንም እንኳን ፋርማሲ በሐኪም የታዘዘ መድኃኒት በመሸጥ ተግባር የተሰማራ ድርጅት ቢሆንም የሕክምና አገልግሎት ጭምር እንደሚሰጡ ይታወቃል። ስለሆነም ሐኪም ሳያማክሩ በቀጥታ የፋርማሲ ሠራተኞችን በማማከር የሕክምና አገልግሎት ያገኙ የቤተሰብ አባላት በዚህ ይካተታሉ።

ረ. <u>የባሕል አካሚ</u>:- ባሕላዊ መድኃኒቶችን (ቅጠላ ቅጠሎች፤ ሥራ ሥሮች ...ወዘተ.) ተጠቅመው የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። በዚህ ጥናት መሠረት የባህል ሐኪም የሚባሉት ፈቃድ ያላቸው ብቻ ሲሆኑ ፈቃድ የሌላቸው ከሆነ "ሌላ" በሚለው ውስጥ እንደሚካተቱ መታወቅ አለበት።

ሰ. <u>ሌላ</u>:- ከላይ ከ1ኛ እስከ 8ኛ ተራ ቁጥር ከተጠቀሱት የሕክምና ተቋማት ውጭ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ ሁሉ በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ። በመንግሥት/በግል ድርጅቶች፤ በፋብሪካዎች፤ ...ወዘተ. ለሠራተኞቻቸው የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ፤ የተይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ የሕክምና አገልግሎቶች ...ወዘተ. በዚህ ይካተታሉ። እንዲሁም የሕክምና ባለሙያ ቢሆኑም ባይሆኑም ሕመም በተሰማው ጊዜ ራሱን በራሱ ያከመ በዚህ ይመደባል።

<u>ዓምድ 20 የህክምና እርዳታ ባገኙበት ተቋም ያጋጠመዎት ችግር ነበር?</u>

የህክምና አገልግሎት ባገኙበት ተቋም ችግር አጋጥሞአቸው ለነበሩ የቤተሰቡ አባላት በዓምዱ ስር የለም የሚለው ተሞልቶ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ችግር አላጋጠመንም ለሚሉ ደግሞ የለም የሚለው ተሞልቶ ኮድ 2 በካርድ ክለም 31 ይሞላል።

<u>ዓምድ 21</u>: *<u>በዓምድ 20 አምን ከመለሱ የህክምና አገልግሎት ባገኙበት ተቋም ያጋጠመዎት ችግር ምን ነበር?</u>*

የሕክምና አገልግሎት ባገኙበት ተቋም ችግር አጋጥሞን ነበር ለሚሉ የቤተሰብ አባላት ችግር አጋጥሟቸው ከነበረ የችግሩ ዓይነት በመጠየቅና በመጠይቁ ከተሰጡት የችግር ዓይነቶች ጋር በማገናዘብ አለ ለሚሉ ኮድ 1 አላጋጠመንም ለሚሉ ደግሞ ኮድ 2 በእያንዳንዱ የችግር ዓይነት ሥር ባለው ካርድ ክለም ይሞላል።

የችግር ዓይነቶች ዝርዝር
ተቋሙ ንፅህና የለውም
ረጅም የወረፋ ጊዜ አለው
የህክምና ባለሙያዎች እጥረት
አገልግሎቱ ውድ ነው
የመድሃኒት አለመኖር/እጥረት
የላብራቶሪ አለመኖር
የአገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች እጥረት
የተቋሙ ሰራተኞች ትብብር ጉድለት
ሌላ(ይገለፅ)

ዓምድ 22: በዓምድ 18 የለም ከመለሱ ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ በህክምና አገልግሎት ያልተጠቀሙበት ዋነኛ ምክንያት ምን ነበር?

በዓምድ 18 ላይ "የለም" የሚል መልስ ለሰጡ ግለትም ወደ ህክምና ተቋም/ባህል ሃኪም አልሄድኩም ላሉ የቤተሰቡ አባላት በዚህ አምድ ወደ ተቋሙ ያልሄዱበት ዋና ምክንያት ይጠየቅላቸዋል። የቤተሰቡ አባላት ካልታመሙ ወይም ህመም ሲያጋጥማቸውም ህክምና አያስፈልጋቸውም የሚል መልስ ከሰጡ የሰጡት ምክንያት በዓምዱ ተመዝግቦ በካርድ ኮለም 41 ላይ ደግሞ ኮድ 1 ይሞላል። ይሁን እንጂ ታሞ የነበረ የቤተሰብ አባል ወደ ህክምና መስጫ ተቋም ለምን እንዳልሄደ አጣርቶ በመጠየቅ የሚገኘው ዋነኛ ምክንያት በዓምዱ ስር ተመዝግቦ ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማዛመድ ተስማሚው ኮድ በንዑስ ዓምድ 41 ይሞላል።

ምክንያቶች	ኮድ
ህክምና አላስፈልገኝ	1
የገንዘብ አቅም ስለሌለኝ	2
ውድ ስለሆነ	3
ርቀት ስላለው	4
ጥራቱ ስለማላምን	5
ህክምና ያድናል ብዬ ስለማላምን	6
የህክምና ባለሙያዎች እጥረት	7
የአገልግሎት ጥራት ማነስ የመሣሪያዎች አለመሟላት	8
ሌላ(ይገለፅ)	9

ዓምድ 23: *ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ የህክምና አገልግሎት አገኙ? (ቢታመሙም ባይታመሙም)*

የቤተሰቡ አባላት ባለፉት 12 ወራት ውስጥ (ቢታመሙ ባይታመሙም) ለምን ያህል ጊዜ በህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋም እንደተጠቀሙ ተጠይቆ ብዛቱ ይመዘገባል። አንድ ሰው የህክምና ተቋሙን ስንት ጊዜ እንደጎበኘው ወይም እንደተገለገለበት የሚቆጠረው አንድ ጊዜ ካርድ አውጥቶ የተመላለሰበትን ቀናት በመቁጠር ሳይሆን ካርድ ለማውጣት ወይም እንደ አዲስ ለማሻሸር የሄደባቸውን ቀናት ብቻ በመቁጠር ነው። ስለዚህ ግለሰቡ ለምን ያህል ጊዜ የሕክምና አገልግሎት እንዳገኘ ተጠይቆ ብዛቱ በካርድ ኮለም 42 እና 43 ይመዘገባል።

ዓምድ 24 -25: ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ሴቶች ብቻ የሚጠየቅ

ዓምድ 24: ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ፅንስ ይዘው/አርግዘው ነበር?

እድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆናቸው ሴቶች ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ፅንስ ይዘው/አርግዘው ከሆነ አጣርቶ በመጠየቅ አዎ የሚል መልስ ከተገኘ መልሱ በአምዱ ስር ባለ ክፍት ቦታ በመግፍ ኮድ 1 ደግሞ በካርድ ኮለም 44 የሚሞላ ሲሆን የለም የሚል ከሆነ ደግሞ በዓምዱ ስር የለም በመግፍ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 መሙላት ያስፈልጋል:: መረጃው ወንዶችን በሙሉና ከሴቶች ደግሞ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆነውን ስለማይመለከት ጥያቄውን ሳያቀርቡ ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ሲያጋጥም ሰረዝ በማድረግ በቀጥታ ወደሚቀጥለው የቤተሰብ አባል ማለፍ ያስፈልጋል::

ዓምድ 25: በዓምድ 24 "አዎን" ለመለሱ በእርግዝና ወቅት የቅድመ-ወሊድ የጤና ምርመራ አድርገው ነበርን?

በዚህ ጥያቄ ላይ በዓምድ 24 ላይ አዎን ለመለሱ ሴቶች በእርግዝናቸው ወቅት ለህፃኑና ለእናት ጤንነት አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ-ወሊድ የጤና ምርመራዎች ማድረጋቸውና አለማድረጋቸው የሚጠየቅበት ነው:: ለቅድመ-ወሊድ ምርመራ ሲባል በእርግዝና ወቅት የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን ለማወቅ የሚረዳ የደም፡ የሽንት፡ የደም ግፊት እና የመሳሰሉ የጤና ምርመራዎችን አድርገው ከነበረ እንዲሁም ለሕፃኑ ጤንነት ሲባል በእርግዝና ወቅት የመንጋጋ ቆልፍ (ቴታነስ) ክትባት (Tetanus Toxid TT) የወሰዱትን የሚያጠቃልል የጤና ምርመራ ነው:: ነገር ግን በወሊድ ወቅት የተከናወነው የማዋለድ ተግባር እንደ ቅድመ-ወሊድ ምርመራ እንደማይቆጠር መገንዘብ ያስፈልጋል:: በመሆኑም የቅድመ ወሊድ የጤና ምረመራ ሳደረጉት በዓምዱ ሥር ባለው ክፍት ቦታ አዎ ብሎ በመግፍ በንዑስ ዓምድ 45 ላይ ኮድ 1 ሲሞላላቸው ላላደረጉት ደግሞ የለም በመግፍ ኮድ 2 ይሞላል::

ዓምድ 26 -29: ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ የሚጠየቅ

ዓምድ 26: የ_____ አባት በሕይወት አሉ?

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች (ከ0-17 ዓመት ላሉ) የሆኑ የቤተሰብ አባላት አባታቸው በሕይወት መኖር አለመኖራቸው ተጠይቆ በሕይወት ካሉ በካርድ ኮለም 46 ኮድ 1 የሚሞላላቸው ሲሆን በሕይወት ከሌሉ ደግሞ ኮድ 2 በካርድ ኮለሙ ይሞላላቸዋል::

ዓምድ 27: የ_____ አባት ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ ናቸው?

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ በዓምድ 26 ላይ አባታቸው በሕይወት አሉ ከተባለ አባታቸው ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ መሆኑ አለመሆኑ ተጠይቆ አባት ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ ከሆነ በካርድ ኮለም 47 ኮድ 1 የሚሞላላቸው ሲሆን አባት ከቤተሰቡ ጋር የማይኖር ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 በካርድ ኮለሙ ይሞላላቸዋል::

ዓምድ 28: የ_____ እናት በሕይወት አሉ?

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ የቤተሰብ አባላት እናታቸው በሕይወት መኖር አለመኖራቸው ተጠይቆ በሕይወት ካሉ በካርድ ኮለም 48 ኮድ 1 የሚሞላላቸው ሲሆን በሕይወት ከሌሉ ደግሞ ኮድ 2 በካርድ ኮለሙ ይሞላላቸዋል::

ዓምድ 29: የ_____እናት በሕይወት ካሉ ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ ናቸው?

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ በዓምድ 28 ላይ እናታቸው በሕይወት አሉ ከተባለ እናታቸው ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ መሆኑ አለመሆኑ ተጠይቆ እናት ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ ከሆነ በካርድ ኮለም 49 ኮድ 1 የሚሞላላቸው ሲሆን እናት ከቤተሰቡ ጋር የማትኖር ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 በካርድ ኮለሙ ይሞላላቸዋል::

ቅጽ 4፦ ዕድሜያቸው ከ 5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ክብደትና ቁመት ልክቶሽና የጤና ሁኔታ

ክፍል 1፦ የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ 1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው።

ክፍል 2፦ ዕድሜያቸው ከ 5 ዓመት በታች የሆኑ የሕፃናት ክብደትና ቁመት ልክቶሽና የጤና ሁኔታ

ዕድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት የሚባሉት ጥናቱ በተካሄደበት ቀን ዕድሜአቸው ከ"4" ዓመት ከ11 ወር ከ29 ቀን የሚደርስ ሕፃናትና ገና አዲስ የተወለዱትን ያጠቃልላል።

ዓምድ 13፦ የሕፃኑ ተራ ቁጥር

በዚህ ዓምድ የሚመዘገበው ከቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 13 ለእያንዳንዱ መደበኛ አባል ከተሰጠው ተራ ቁጥር መካከል ዕድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት ብቻ (ከቅጽ 1 ዓምድ 17 ዕድሜውን በማየት) የሕፃኑን ተራ ቁጥር ከዓምድ 13 በተጥታ በማስተላለፍ ነው። ሕፃናት በቅፅ 1 ላይ ሲመዘገቡ ተከታታይ በሆነ መንገድ ላይሆን ስለሚችል ወደዚህ ዓምድ ሲተላለፍም ቀድሞ የተመዘገበው ተራ ቁጥር ምንም ዓይነት ማስተካከያ ሳይደረግበት እንዳለ ነው።

ለምሳሌ፦ በቅጽ 1 በክፍል 2 ዓምድ 13 ለሕፃኑ የተሰጠው ተራ ቁጥር "06" ቢሆን በቅጽ 4 ክፍል 2 ዓምድ 13 ለሕፃኑ የሚሰጠው ተራ ቁጥር "06" ይሆናል ማለት ነው።

ዓምድ 14፦ የዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ስም ዝርዝር፦

ይህ ዓምድ ከቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 13 ወደ ቅጽ 4 ክፍል 2 ዓምድ 13 ተራ ቁጥሩ ለተላለፈለት ሕፃን ሙሉ ስም ከቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 14 የሚገለበጥ ነው። የሕፃናቱ ስምና ተ.ቁ. እንደይሳሳት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

ዓምድ 15: የሕፃኑ ወላጅ እናት ተራ ቁጥር

በዓምድ 14 የተጠቀሰው ሕፃን ወላጅ እናት መጀመሪያ የቤተሰቡ አባል መሆን አለመሆኗን በመጠየቅ መልሱ "አዎን" ከሆነ ከቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 13 ለሕፃኑ ወላጅ እናት የተሰጠውን ተራ ቁጥር ምንም ዓይነት ማስተካከያ ሳይደረግበት በቅጽ 4 ክፍል 2 ዓምድ 15 በካርድ ኮለም 25 እና 26 በሕፃኑ ትይዩ ይመዘገባል:: የሕፃኑ እናት የቤተሰብ አባል ካልሆነች ካርድ ኮለሙ "00" ይፃፍ::

ዓምድ 16: የሕፃኑ ዕድሜ (በወራት)

ይህ ዓምድ በቅጽ 4 ዓምድ 13 እና 14 መረጃ የተሞላለት ሕፃን ዕድሜ በሙሉ ወራት ተጠይቆና ተሰልቶ የሚመዘገብበት ነው:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 17 የተመዘገበው ዕድሜ በሙሉ ዓመት ስለሆነና ለዚህ ጥናት የሚፈለገው የሕፃኑ ዕድሜ ግን በወራት በመሆኑ የህፃኑ ዕድሜ በወራት ምን ያህል እንደሆነ ቤተሰቡ ተጠይቆ መሞላት አለበት:: ቤተሰቡ የሰጠውን ዕድሜም በቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 17 ከተመዘገበው ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ነው:: <u>ሆኖም በቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 17 ላይ በዓመት የተሰጠውን ዕድሜ በምንም ዓይነት በ12 በማባዛት ወደ ቅጽ 4 ክፍል 2 ዓምድ 16 ማወራረስ አይቻልም</u>:: ምክንያቱም በቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 17 ላይ በዓመት የተሰጠው ዕድሜ 4 ዓመት ቢል ይህ 4 ዓመት ማለት 4X12 = 48 ወራት ማለት ብቻ ላይሆን ይችላል:: ለምሳሌ በቅጽ 1 ዕድሜ በሙሉ ዓመት ስለሚሞላ እስከ 11 ወራት ያህል ልዩነት ሊኖረው ይችላል:: በመሆኑም እድሜው በወራት ተጠይቆ መሞላት አለበት:: እንጂ በምንም አይነት ተአምር በ12 ተባዝቶ መቀመጥ የለበትም::

<u>ምሳሌ</u>:- ቤተሰቡ የሕፃኑ ዕድሜ 3 ዓመት ከ11 ወራት ነው የሚል መልስ ቢሰጥ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለም 27 እና 28 የሚመዘገበው /3x12/+11 = 47 ተብሎ ነው:: ሆኖም በቅጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 17 የሕፃኑ ዕድሜ በሙሉ ዓመት ስለሚፃፍ 3 ዓመት በመውሰድ እና በ12 አባዝቶ ማስቀመጥ ምን ያህል ስህተት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል:: በተጨማሪም የህፃኑ ዕድሜ ሙሉ ወራት በተጨማሪ ከ1-29 ቀናት ቢኖሩት (ለምሳሌ 3 ዓመት 11 ወር ከ29 ቀን ቢሆነው) የሚመዘገበው ዕድሜ በሙሉ ወር 47 ይሆናል::

ከዓምድ 17-27 ላሉ ዓምዶች የሚጠየቀው ዕድሚያቸው ከ00-59 ወራት ለሆናቸው ህፃናት በሙሉ ነው::

ዓምድ 17: **ህፃኑ የት ተወለደ?**

ዕድሜው ከ5 ዓመት በታች (ከ0-59 ወራት) የሆነው ህፃን የት እንደተወለደ እናቱን ወይም አሳዳጊውን በመጠየቅ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛው የተወለደበት ቦታ በዓምዱ ስር በመመዝገብ አስፈላጊው ኮድ ደግሞ *በካርድ ኮለም 29 በሕፃኑ ትይዩ ይመዘገባል::* ሆኖም ህፃኑ የተወለደው በጤና ተቋማት ወይም በመኖሪያ ቤት ውስጥ ካልሆነ "ሌላ" የሚለው አማራጭ ኮድ ይሞላል::

የህፃኑ የመወለጃ ቦታዎች	**ኮድ**
ሆስፒታል	=1
ክሊኒክ	=2
ጤና ጣቢያ	=3
ጤና ኬላ	=4
በመኖሪያ ቤት ውስጥ	=5
ሌላ ቦታ(ይገለፅ)	=6

ማሳሰቢያ:-1. ከላይ የተዘረዘሩት የጤና ተቋማት የመንግስት፤ የግል፤...ወዘተ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማስተዋል ያስፈልጋል:: ስለሆነም የሚፈለገው የህክምና የተቋማቱ ደረጃ እንጂ ባለቤታቸውን አይደለም::

2. ለዚህ ጥናት አንድ ህፃን በመኖሪያ ቤት ውስጥ ተወለደ የሚባለው የተወለደበት ቦታ በወላጅ እናቱ መኖሪያ ቤት ውስጥ ፤ በአያቶቹ መኖሪያ ቤት ውስጥ ፤ በቤተሰቡ መኖሪያ ቤት ውስጥ ወይም ደግሞ በማንኛውም ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ውስጥ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ከመኖሪያ ቤት ውጭ ከተወለደ የተወለደበት ቦታ ተገልፆ ኮድ 6 ይሰጠዋል::

ለምሳሌ:- በጉዞ ላይ ሆነው በድንገተኛ ምጥ በመያዛቸው በመንገድ በተገኘ ቤት ውስጥ ቢወልዱ፤ በአይሮፕላን፤ በመኪና፤ ... ወዘተ ቢወልዱ እንዲሁም በአንዳንድ ሰዎች እንደሚደረገው የመውለጃ ወቅት ሲደርስ ከቤታቸው ውጭ መጠለያ ተዘጋጅቶላቸውም ሆነ ሳይዘጋጅላቸው ያለ ምንም እርዳታ የሚወልዱ ሴቶች በሙሉ በኮድ 6 ውስጥ ይጠቃለላሉ::

ዓምድ 18: ህፃኑን ማን አዋለደው?

ህፃኑን ማን እንዳዋለደው እናቱን/አሳዳጊውን በመጠየቅ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በዓምዱ ስር በመመዝገብ አስፈላጊው ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለም 30 በሕፃኑ ትይዩ ይመዘገባል::

አዋላጅ	ኮድ
የጤና ባለሙያ	=1
አዋላጅ ነርስ	=2
የሰለጠነች የልምድ አዋላጅ	=3
ያልሰለጠነች የልምድ አዋላጅ	=4
እራሴ ወለድኩ	=5
ሌላ	=6

ማሳሰቢያ:-
- የጤና ባለሙያ ማለት ዶክተር ነርስ (ከአዋላጅ ነርስ ሌላ) ጤና ረዳት ... ወዘተ የሚያጠቃልል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::
- የሰለጠነች የልምድ አዋላጅ ማለት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በማዋለድ ሥልጠና ወስዳ ማስረጃ ያላት የልምድ አዋላጅ ማለት ነዉ
- ያለሰለጠነች የልምድ አዋላጅ ማለት ደግሞ በየአካባቢው በልምድ አዋላጅነት የታወቀች ነገር ግን ስልጠና ያልወሰዱ ናቸው::

ዓምድ 19 የሕፃኑ የክትባት ካርድ አለ?

ሕፃኑ የክትባት ካርድ እንዳለው ተጠይቆና ናሙና ካርድ በማሳየት ካርዱን ቤተሰቡ እንዲያሳይ መጠየቅ ያስፈልጋል:: መረጃው በካርድ ላይ ስላለ ከዚያ ላይ አይቶና አረጋግጠ መሙላት ይረዳል:: ነገር ግን ካርዱን የሌለው ወይም የጠፋባቸው ውይም በየጤና ተቋም የሚቀመጥበት ሁኔታ ስለሚኖር እንደሁኔታው የተሰጡትን አማራጭ ኮዳች መሙላት ያስፈልጋል:: አማራጮቻም:-

የሕፃኑ ካርድ

አለ=1

ጠፍቷል=2

የጤና ተቋም ነው ያለው=3

አላወጡም/ካርድ የለውም=4

ከዓምድ 20-23: ሕፃኑ የ-------ክትባት ወስዷል?

ዕድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ ለአንዳንድ በሽታዎች መከላከያ የሚሆኑ ክትባቶች መውሰዳቸውን /አለመውሰዳቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎች በእዚህ ዓምዶች ውስጥ ይሰበሰባል። አብዛኛው ቤተሰብ ልጆቻቸው ክትባት መውሰዳቸውን የሚያረጋግጥ የመከታተያ ካርድ ሊኖራቸው ስለሚችል ለሀፃኑ የተሰጠውን የክትባት ዓይነት ከካርዱ በማየት ማረጋገጥ ይቻላል።

ዓምድ 20: ሕፃኑ የኩፍኝ (ወተቴ) Measels/ ክትባት ወስዷል?

ይህ ዓምድ በተለይ ሕፃናትን ስለሚያጠቃው ኩፍኝ ስለሚባለው በሽታ መከላከያ ክትባት መሰጠቱን ወይም አለመሰጠቱን የሚገልጽ መረጃ የሚሰበሰብበት ነው። ክትባቱ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ነው። ሕፃኑ የኩፍኝ /Measels/ ክትባት ወስዶ ከሆነ የክትባቱን ካርድ በማየት አረጋግጦ ወይም ተጠይቆ የተሰጠው ምላሽ በዓምዱ "አዎን" የሚለው ተጽፎ ኮድ 1፡ "የለም" ለሚለው ተጽፎ ኮድ 2፡ በካርድ ኮለም 32 ይመዘገባል። የኩፍኝ በሽታ በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች ወተቴ ተብሎ እንደሚጠራ ማስታወስ የሚያስፈልግ ሲሆን በየብሔረሰቡ ቋንቋ ደግሞ የተለያየ ስም ያለው በመሆኑ የክትባቱ ዓይነት የኩፍኝ ለመሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

> ማሳሰቢያ:- የኩፍኝ ክትባት የሚሰጠው በክንድ ላይ ሲሆን ምንም ዓይነት ምልክት/ጠባሳ አያስቀርም።

ዓምድ 21: ሕፃኑ የሳንባ ነቀርሳ (BCG) ክትባት ወስዷል?

ለሳንባ ነቀርሳ መከላከያ /Anti-Tuberculosis/ የሚሆን አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ክትባት ነው። ሕፃኑ የቢ.ሲ.ጂ /BCG/ ክትባት ወስዶ ከሆነ ተጠይቆ ወይም የክትባት ካርዱን በማየት "አዎን" ለሚለው በዓምዱ ተጽፎ ኮድ 1፡ "የለም" ለሚለው ተጽፎ ኮድ 2 በካርድ ኮለም 33 ይመዘገባል።

> ማስታወሻ:- የሳንባ ነቀርሳ ክትባት በግራ ትከሻ ላይ የሚሰጥ ሲሆን በግልጽ የሚታይ ጠባሳየሚተው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 22: ሕፃኑ የዘጌ አናፋ፡ ትክትክ፡ መንጋጋ ቆልፍ (DPT) ክትባት ወስዷል?

ለዘጌ አናፋ፡ ለትክትክና ለመንጋጋ ቆልፍ Diptheria, pertusis and Tetanus(DPT) መከላከያ የሚሆን በተወሰነ የጊዜ ርቀት ለሦስት ጊዜ የሚሰጥ ክትባት ነው። ሕፃኑ የዲ.ፒ.ቲ. /D.P.T/ (ከD.P.T1 እስከ D.P.T3) ክትባት ወስዷል ከተባለ የክትባት ካርዱን በማየት ወይም በመጠየቅ መልሱ "አዎን" ከሆነ ኮድ 1 ፣ "የለም" ከሆነ ኮድ 2 ፣ በየአንዳንዱ የዲ.ፒ.ቲ. (ከD.P.T1 እስከ D.P.T3) ክትባት ደረጃ በተናጠል በካርድ ኮለም 34-36 ይመዘገባል።

> ማሳሰቢያ:- ይህ የዲ.ፒ.ቲ. ክትባት የሚሰጠው በሕፃኑ መተመጫ ወይም ታሳ በኩል ነው። የዐረ-6 ክትባት ካርድ ሳሳቸው ሕፃናት ይህ ክትባት መሰጠቱ በግልጽ ሰፍሯል።

ዓምድ 23: ሕፃኑ የልምሻ (Polio) ክትባት ወስዷል?

ለልጅነት ልመሻ (Polio) መከላከያ የሚሆን በተወሰነ የጊዜ ርቀት ለሦስት ወይም ለአራት ጊዜ የሚሰጥ ክትባት ነው። ሕፃኑ የልጅነት ልምሻ (Polio) (ከpolio0 እስከ polio3) ክትባት ተሰጥቶት ከሆነ የክትባቱን ካርድ በማየት ወይም በመጠየቅ አረጋግጠ መልሱ "አዎን" የሚል ከሆነ በእያንዳንዱ የክትባት ደረጃ መሠረት በየካርድ ኮለሙ ኮድ "1" ፣ "የለም" ከሆነ ደግሞ ኮድ "2" ፣ ይመዘገባል። ይህም ማለት ለፖሊዮ 0 በካርድ ኮለም 37፡ ለፖሊዮ 1 በካርድ ኮለም 38 ፣ ለፖሊዮ 2 በካርድ ኮለም 39 እና ለፖሊዮ 3 ደግሞ በካርድ ኮለም 40 እንደሁም በካርድ ኮለም 41 ደግሞ ክትባቱን በዘመቻ መልክ ለወሰዱ ህፃናት በሙሉ ተጠይቆ ይሞላሳቸዋል። የፖሊዮ ክትባት በፈሳሽ መልክ በአፍ የሚሰጥ ሲሆን ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1996 ዓ.ም. በጥቅምትና ህዳር ወራት በሰፈው በዘመቻ መልክ ሲሰጥ የነበረ እና ከ1990 በፊትም ክትባቱ በዘመቻ መልክ ይሰጥ እንደነበር መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 24: ሕፃኑ ስንት ጊዜ ቫይታሚን ኤ (Vit.A) እንክብሎች ወስዷል?

ለቤተሰቡ የቫይታሚን ኤ (Vitamin A) ናሙና እንክብሎች (ካፕሱሎች) በማሳየት ለሕፃኑ ተሰጥቶ ይታወቅ እንደሆነ በመጠየቅ "አዎን" የሚል መልስ ከተገኘ ሕፃኑ ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ስንት ጊዜ እንደወሰደ ተጠይቆ በካርድ ኮለም 42 ቁጥሩ ብቻ ይመዘገባል::

ዓምድ 25: ሕፃኑ አመጋገብ /የክብደት ቁጥጥር ፕሮግራም ተሳታፊ ነበርን?

ህፃኑ በ"Nutrition program" የገንቢ ምግብ ፕሮግራም ወይም የክብደት ቁጥጥር ፕሮግራም ተሳታፊ ሆኖ እንደሆነ እናቱን ወይም አሳዳጊውን በመጠየቅ ተሳታፊ ከሆነ "አዎን" የሚል ተዕፎ ኮድ 1 በካርድ ኮለም 43 ምሚመዘገብ ሲሆን ተሳታፊ ካልነበረ ደግሞ "የለም" በማለት ኮድ 2 በካርድ ኮለሙ ይመዘገባል::

ዓምድ 26: ሕፃኑ/ኗ ባለፉት 2 ሳምንታት ውስጥ ተቅማጥ፡ ትኩሳት ታሞ/ማ ነበር?

ሕፃኑ/ኗ ባለፉት 2 ሳምንታት ውስጥ ትኩሳት "ሳል፡ ተቅማጥ ታሞ/ማ እንደነበርና እንዳልነበር በመጠየቅ በዓምዱ ሥር በተዘረዘሩት የህመም ዓይነቶች መሠረት "አዎ" የሚል መልስ ከተሰጠ በትክክለኛው ካርድ ኮለም ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ያልታመመ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል ::

ይህ ጥያቄ የሚቀርበው ለእያንዳንዱ የህመም አይነት በተናጠል በመሆኑ የሚገኝው መልስ ለተቅማጥ፡ ለትኩሳት እንዲሁም ለሳል በተናጠል መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል:: ምሳሌ:- አንድ ህፃን ሳልና ትኩሳት በአንድ ጊዜ ታሞ ወይም ባለፉት 2 ሳምንታት በተለያየ ጊዜያት ሳልና ትኩሳት ታሞ ከነበረና ተቅማጥ ያልታመመ ከሆነ ኮድ 1 የሚሞላለት በሳል ስር ባለው ካርድ ኮለም 46 እና በትኩሳት ስር ባለው ካርድ ኮለም 45 ውስጥ ሲሆን በተቅማጥ በተሰጠው ካርድ ኮለም ግን ኮድ 2 ይሞላለታል ማለት ነው::

ዓምድ 27:-ህፃኑ በተቅማጥ በሽታ ተጠቅቶ/ታሞ ከነበረ ምን ተደረገለት/ተሰጠው?

በዓምድ 26 ላይ ህፃኑ ተቅማጥ :: ሳል :: ትኩሳት ወይም የእነዚህ ቅልቅል በሆነ በሽታ ተጠቅቶ (ታሞ) ከነበረ የተደረገለትን ዕርዳታ በመጠየቅ ህፃኑ ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱ ይሞላል:: ኦአርኤስ (ORS) ወሰደ ከሆነ :: በቤት ውስጥ የተሰራ ኦ..ኦር.ኤስ. (ውኃ፡ጨው፡ስኳር ወዘተ) ተጨምሮ በመመሪያው መሠረት የተዘጋጀ :: ሌሎች ፈሳሾች

ተሰጥተው ከሆነ፤ ወደ ዘመናዊ ጤና ተቋም ተወስዶ እንደሆነ ወይም በባህላዊ ሕክምና (የባሕል አካሚ ማሳየት፤ ቅጠላቅጠል መስጠት ...ወዘተ) ተሰርቶ ከሆነ ቤተሰቡን በመጠየቅ አስፈላጊውን ኮድና ስም በተሰጡት አምዶች መመዝገብ ያስፈልጋል። ሕፃኑ ምንም እርዳታ ካልተደረገለት ኮድ 6 ይሞላለታል። አለመውሰዱን አጣርቶ በመጠየቅ መውሰዱ ከተረጋገጠ በዓምዱ ስር አ.አር.ኤስ በመሙላት ኮድ 1፤ ሌሎች የተደረጉለትን ዕርዳታዎች ከተሰጡት አማራጮች አጣርቶ በመጠየቅ በአምዱ ስር የተደረገለት ዕርዳታ ተጽፎ በካርድ ክለም 47 ደግሞ ተስማሚው ኮድ ይሞላል።

ማሳሰቢያ፡- በአሁኑ ወቅት በየቦታው የሚሰጠው ለምለም የተባለ ነገር አአርኤስ (ORS) መሆኑ ማስተዋል ያስፈልጋል።

ክዓምድ 28-29: ዕድሜአቸው ከ3 ወር እስከ 59 ወር ለሆናቸው ሕፃናት ብቻ የሚሞላ የሕፃናት ክብደትና ቁመት አለካክ

ከ3 ወር እስከ 59 ወር ባለው የዕድሜ ገደብ ውስጥ የሆነ የማንኛውም ሕፃን ቁመትና ክብደት በትክክል ተለክተው በእነዚህ ዓምዶች ይሰፍራሉ። ዝርዝር የአለካክ መመሪያው የመረጃ አሰባሰብ መመሪያው በስተመጨረሻ በዕዝል 2 ተገጿል።

ጥብቅ ማሳሰቢያ፡-ዓምድ 28 እና 29 ዓምዶች የሚሞሉት ማለትም የክብደቱና የቁመቱ ልኬት መከናወን ያለበት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት መጠይቅ ቅጾች በሙሉ (እስከ ቅፅ 9 ያሉት) ተሞልተው ከተጠናቀቁ በኋላ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 28: የሕፃኑ ክብደት (በግራም)

ዕድሜአቸው ከ3-59 ወራት የሆናቸው ሕፃናት በሙሉ ለዚህ ጥናት በተዘጋጀው ሚዛን በመመዘን የሚገኘው ክብደት በግራም ከ48-52 ባሉት ካርድ ክለሞች ይመዘገባል።

ዓምድ 29: የሕፃኑ ቁመት በሳንቲሜትር

ለዚሁ በተሰጠው የቁመት መለኪያ በመጠቀም የህፃኑ ቁመት በሳንቲ ሜትር በመለካት በካርድ ክለም 53-55 ውስጥ ይሞላል። የህፃናት ቁመት ሲለካ በሚከተለው መንገድ መሆን ይኖርበታል። ለማንኛውም ዕድሜው ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ሕፃን የቁመት መለኪያውን ከግድግዳ አስጠግቶ ጠፍጣፋ መሬት

ላይ ማቆምና ከዚያም ሕፃኑን ማቆሚያው ላይ እግሩን ገጥሞ ቀና አድርጎ በማቆም ኳድሮው የሕፃኑን አናት እስኪነካ ከላይ ተነ ብሎ ሜን ማለት ቁመቱ በትክክል በሙሉ ሴንቲ ሜትር አንብቦ መመዝገብ ያስፈልጋል። ሕፃኑ ቀጥ ብሎ ሲቆም ተረከዙ ራሱና መላ ቁመቱ ሳይንቀጥ ሚትሩ የተለጠፈበትን እንጨት መንካት ያለባቸው ከመሆናቸው በላይ እግሮቹ ፍፁም ቀጥ ያሉ ወይም የተገተሩ መሆን ሲገባቸው የሕፃኑ እይታ ፊት ለፊት ቀጥ ያለ መሆን አለበት። ይህም ማለት ሕፃኑ መሬት ሳያይ ወይም ወደ ላይ ሳያንጋጥጥ ማለት ነው።

ለማንኛውም <u>ዕድሜው ከሁለት ዓመት በታች ለሆነ ሕፃን</u> ደግሞ ቁመቱ የሚለካው የቁመት መለኪያውን ወጣ ገባ በሌለበት ጠፍጣፋና ጠንካራ ከሆነ ወለል፣ ጠረጴዛ፣ ...ወዘተ. ላይ በማስተኛት ነው። ከዚያም ሕፃኑን በመደገፍ በመለኪያ መሳሪያው ላይ የሕፃኑን ጭንቅላት /አናት ወደ መለኪያ መሳሪያው መቆሚያ በማድረግ ቀጥ አድርጎ በጀርባው በማስተኛት ነው። ልኬቱም ከመከለሉ በፊት የሕፃኑ አናት የመለኪያ መሳሪያውን መቆሚያ በሚገባ ማስነካትና የሕፃኑን ጀርባ ግንድ በእጅ ደግፎ ሕፃኑ በሚገባ ወደ ላይ መመልከቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በመጨረሻ የሕፃኑን እግሮች አንድ ላይ ገጥሞ ቀጥ ብለው የተዘረጉ መሆናቸውን ጉልበቱን በእጅ በመጫንና እግሮቹን በእጅ በመግጠም ጭምር ካረጋገጡ በኋላ ኳድሮው መሀል ለመሀል ማስረገጥና ትክክለኛውን መመዝገብ ነው። ርዝመቱ በሚመዘገብበት ጊዜ የሕፃኑ ቁመት ከ100 ሳንቲ ሜትር ያነሰ ከሆነ በቁጥሩ በስተግራ "0" በመጨመር ባለ ሶስት ዲጂት ቁጥር አድርጎ መፃፍ አለበት።

<u>ምሳሌ</u>:- የህፃኑ ቁመት 89 ሳንቲ ሜትር ቢሆን በካርድ ላለም 53 ውስጥ "0" በመፃፍ በካርድ ላለም 54 እና 55 ደግሞ "89" ይሞላል ማለት ነው።

ቅጽ 5:- ቤተሰቡ ቤት ውስጥ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች

ቅጽ 5 አያንዳንዱን የቤተሰብ አባላት የሚመለከት ሳይሆን በአጠቃላይ ቤተሰቡን በማስመልከት የሚሞላ መጠይቅ ነው:: ቅፅ 5 በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ክፍል 1 እንደተለመደው የአካባቢ መለያ አድራሻ የሚሞላበት ነው:: በክፍል 2 ደግሞ ቤተሰቡ በቤት ውስጥ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች አስመልክቶ በየዓምዱ በቀረቡት ጥያቄዎች መሠረት መረጃ የሚሰበሰብባቸው ናቸው::

ክፍል 1:- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ 1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው::

ክፍል 2:- ቤተሰቡ በቤት ውስጥ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች

በዚህ ክፍል የቤተሰቡ መኖሪያ ቤት ሁኔታ፡ የቤተሰቡ የሚጠቀምበት የማገዶና የመብራት ዓይነትና ሁኔታ አስመልክቶ መረጃ ይሰበሰባል:: ስለቤተሰቡ የመኖሪያ ቤት ሁኔታ መረጃ ለመሰብሰብ እንዲቻል የቤትን ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ግድ ስለሚል የቤት ትርጉም ቀጥሎ ተሰጥቷል::

ቤት ሲባል ሁሪያውን ከወለል እስከጣሪያ ድረስ አንድ አዋቂ ሰው ለማስቆም በሚደርስ ግድግዳ የተከበበና ቢያንስ አራት ካሬ ሜትር የሆነ ስፋት ኖሮት ለአንድ አዋቂ ሰው አልጋ ለማስዘርጋት የሚበቃ ስፍራ ያለው ነው:: ቤቱ ከተለያዩ የሕንፃ መሳሪያዎች የተሰራ ሊሆን ይችላል:: ማለትም ከድንጋይ፡ ከሸክላ፡ ከብሎኬት፡ ከሲሚንቶ፡ ከእንጨት፡ ወይም ከሌሎች ከአካባቢው ከተገኙ የሕንፃ መሳሪያዎች ሊሰራ ይችላል:: ይሁን እንጂ ለዚህ ጥናት በጊዜያዊነት የሚሰሩ ቤቶች ማለትም አሰራራቸው ለጊዜያዊ መጠለያ ተብለው እንጨት በመሬት በመትከል ቋሚነት በሌለው ግድግዳ እንዲሁም በካርቶን፡ በፕላስቲክ፡ ...ወዘተ. የተሰሩትን አያጠቃልልም:: ይሁን እንጂ በአንዳንድ አካባቢ ቤቶች በአሰራራቸው ቋሚ ስለማይመስሉ እንደ ቤት ሳይቆጠሩ እንዳይታለፉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

ዓምድ 13: ተራ ቁጥር:- ይህ ዓምድ አስቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም::

ዓምድ 14: ቤተሰቡ ከ12 ወራት በፊት ነበርን?

ቤተሰቡ ከ12 ወራት በፊት ከነበረ በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ "አዎን" ተፅፎ በንዑስ ዓምድ 25 ኮድ "1" ይሞላል። ካልነበረ ግን "የለም" ተሞልቶ በንዑስ ዓምድ 25 ኮድ "2" ይጻፋል። ይህም ማለት ቤተሰቡ አሁን ባለበት መኖሪያ ቤቱ ማለት ብቻ ሳይሆን በየትም ቦታ ቢሆን የቤተሰብ ትርጉም በሚያሟላ መልኩ ተመስርቶ መኖሩንና አለመኖሩን ለማወቅ ነው።

ምሳሌ:- 1. አንድ ወጣት ሚስት በማግባቱ ምክንያት ባለፈው ወር ከነበረበት ቤተሰብ ተለይቶ አሁን ያለበትን ቤት በመከራየት ከሚስቱ ጋር የሚኖር ከሆነ ይህ ቤተሰብ ከ12 ወራት በፊት ያልነበረ በመሆኑ "የለም" ተብሎ ይሞላል።

2. አንድ ወንደላጤ ለረጅም አመታት ብቻውን ሲኖር ቆይቶ ባለፈው ወር ትዳር መስርቶ የሚኖር ከሆነ "ይህ ቤተሰብ ከ12 ወራት በፊት ነበርን?" ለሚለው ጥያቄ መልሱ "አዎን" ይሆናል። ምክንያቱም ጋብቻው ከመፈጸሙ በፊትም ቢሆን አንድ አባል ያለው ቤተሰብ ነበርና ነው። ከጋብቻው በኋላ የተከሰተው ነገር ቢኖር የቤተሰብ አባላት መጨመር ብቻ ነው።

ዓምድ 15: ቤተሰቡ በዚህ መኖሪያ ቤቱ ምን ያህል ጊዜ ኖሯል?

ቤተሰቡ አሁን በሚኖርበት ቤት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደኖረ ተጠይቆ በዓመትና በወር ተለይቶ ይመዘገባል። ቤተሰቡ አሁን በሚኖርበት ቤት ሁለት ዓመት ከአስራ አንድ ወራት ተቀምጦ ቢሆን በንዑስ ዓምዶች 26 እና 27 "02" ሲሞላ በንዑስ ዓምዶች 28 እና 29 ደግሞ "11" ይሞላል ማለት ነው።

ለ16 - 18 እና ከ20 - 22 ላሉ ዓምዶች:

ማሳሰቢያ:-የዚህ ክፍል የአጠያየቅ ስልት ለየት ባለ መልኩ ማለትም የአሁኑንና ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት የነበረውን ሁኔታ ጎን ለጎን የሚጠይቁ በመሆኑ ጥንቃቄ ሚድረግ ያስፈልጋል። በየዓምዱ የቀረቡት ጥያቄዎች ከየዓምዱ ግርጌ ከተሰጡት ሦስት ወቅቶች (ማለትም "በጥናቱ ዓመት" እና "ከ12 ወራት በፊት" እና ከ4 ዓመት በፊት) ከነበረው ጋር በማዛመድ ቤተሰቡ ከተጠየቀ በኋላ የተገቢው መልስ ኮድ ከየወቅቱ አንፃር በተሰጡት ንዑስ ዓምዶች ውስጥ ይሞላል። "አሁን" ማለት መረጃ ሰብሳቢው

ቤተሰቡን በሚጎበኝበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ ሲሆን:: "ከ12 ወራት በፊት" ማለት ደግሞ ከጥናቱ ቀን ጀምሮ ወደ ኋላ ካሉት 12 ወራት በፊት "የዛሬ አንድ ዓመት" (አምና) ያለው ሁኔታ ማለት ሲሆን ከ4 ዓመት በፊት ማለት ደግሞ ጥናቱ ከሚካሂድበት ዓመት 4 ዓመት በፊት የዛሬ 5 ዓመት ያለው ሁኔታ ማለት ነው:: ቤተሰቡ በአሁኑ ጊዜ የሚገኘው አገልግሎት ከ12 ወራት በፊትና ከ4 ዓመት በፊት ከሚያገኘው የተለየ ሊሆን እንደሚችል በመገንዘብ ጠይቆ ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከ12 ወራት በፊት ኖሮ ከ4 ዓመት በፊት ቤተሰቡ ያልነበረ ከሆነ ግን በጥናቱ ወቅት የሚለውና ከ12 ወራት በፊት የሚለው ተጠይቀው ይሞላና ከ4 ዓመት በፊት የሚለው በ(-) ይታለፋል::

ዓምድ 16: ቤተሰቡ መኖሪያ ቤቱን በምን መልኩ ነው የያዘው?

ቤተሰቡ የሚኖርበትን ቤት በጥናቱ "ከ12 ወራት በፊት" እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት በምን መልኩ እንደያዘው በመጠየቅ በዓምዱ ሥር ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በጥናቱ ዓመት የተጠቀሙን መልስ ኮድ በመምረጥ በንዑስ ዓምድ 30 ሥር በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ይመዘግባል:: አማራጭ ኮዶቹም የሚከተሉት ናቸው::

የመኖሪያ ቤት ይዞታ ዓይነቶች	ኮድ
በባለቤትነት	0
ከቀጣሪው ለተቀጣሪው ቤተሰብ በነፃ የተሰጠ ወይም በኪራይ የሚከራይበት	1
ከዘመድ በነፃ የተሰጠ ወይም በኪራይ የሚከራይበት	2
ከአሰሪው ድርጅት የተከራየው	3
ከኪራይ ቤቶች ድርጅት የተከራየው	4
ከቀበሌ የተከራየው	5
መንግሥታዊ ካልሆነ ከአከራይ ድርጅት የተከራየው	6
ከዘመድ የተከራየው	7
ዘመድ ካልሆነ ቤተሰብ የተከራየው	8
ሌላ ይገለፃል	9

ለምሳሌ፦ በዓምድ 16 ቤተሰቡ አሁን/በጥናቱ ወቅት የሚኖርበትን ቤት በምን መልኩ እንደያዘው ሲጠየቅ በባለቤትነት የሚል መልስ ሰጥቶ ከ12 ወራት በፊት ግን ቤተሰቡ ከቀበሌ በኪራይ መልክ ይዞት የነበረ ከ4 ዓመት በፊት ደግሞ ያለነበረ ቤተሰብ ሊሆን ይችላል። በዚህ ዓምድ በጥናቱ ወቅት ለሚለው በባለቤትነት (ኮድ 0) ፣ ከ12 ወራት በፊት ለሚለው ከቀበሌ የተከራየው (ኮድ 5) እና ከ4 ዓመት በፊት ለሚለው ሠረዝ ("-") ይደረጋል ማለት ነው።

ዓምድ 17: ቤቱ ስንት ክፍሎች አሉት?

ቤተሰቡ አሁን የሚኖርበትን ቤት ስንት ክፍሎች እንዳሉት ተጠይቆ በንዑስ ዓምዶች 31 እና 32 የቤቱ ክፍሎች ብዛት ይመዘገባል። የቤቱ ክፍሎች ሲባል ማድቤትና መፀዳጃ ቤት እንደማይጨምር መታወቅ ይኖርበታል።

ዓምድ 18: የቤቱ ግድግዳ በአብዛኛው የተሰራው ከምንድን ነው?

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ አሁን የሚኖርበትን ቤት ሁኔታ የቤቱ ግድግዳ በአብዛኛው ከምን እንደተሰራ ተጠይቆ በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ተስማሚውን በመምረጥ በንዑስ ዓምድ 33 በተጠቀሱት ጊዜያቶች አቅጣጫ የኮድ ቁጥሩ ይሞላል።

የቤቱ ግድግዳ የተሰራበት ዕቃ	ኮድ
ከእንጨትና ከጭቃ	1
ከእንጨትና ሰንበሌጥ	2
ቀርቀሃ/ሸንበቆ	3
ጭቃና ድንጋይ	4
ሲሚንቶና ድንጋይ	5
ብሎኬት	6
ጡብ	7
ሌሎች	8

ዓምድ 19: የቤቱ ጣሪያ በአብዛኛው የተሰራው ከምንድን ነው?

ቤተሰቡ አሁን የሚኖርበትን ቤት የቤቱ ጣሪያ በአብዛኛው ከምን እንደተሰራ ተጠይቆ በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ተስማሚውን በመምረጥ

"በጥናቱ ወቅት"፡ ከ12 ወራት በፊት እና ከ4 ዓመት በፊት ያለው ሁኔታ በንዑስ ዓምድ 34 ኮዱቹ ብቻ ይመዘገባሉ::

የቤቱ ጣሪያ የተሰራበት ዕቃ	ኮድ
ቆርቆሮ	1
ሰንበሌጥ /ሳር/	2
ዕንጨትና ጭቃ	3
ተርቀሃ/ሸንበቆ	4
ሸክላ	5
ሌላ ይገለፅ	6

ዓምድ 20፡ ቤተሰቡ ለቤቱ በዋነኛነት/በአብዛኛው የሚጠቀመው የመብራት ዓይነት ምንድን ነው?

የቤተሰቡ ዋነኛ የመብራት ዓይነት ተጠይቆ በዓምዱ ከተዘረዘሩት አማራጮች አንዱንና ዋናውን በመምረጥ ከዓምዱ ግርጌ ከተሰጡት "በጥናቱ ዓመት"ና "ከ12 ወራት በፊት" እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት ለሚለው በመለየት በየአንዳራቸው በንዑስ ዓምድ 35 ሥር በተሰጠው ቦታ ተገቢውን ኮድ መመዝገብ ያስፈልጋል::

የመብራት ዓይነት	ኮድ
ኩራዝ/ፋኖስ	1
ኤሌክትሪክ/ቆጣሪ/በግል	2
ኤሌክትሪክ/ቆጣሪ/በጋራ	3
ሜኖሶ /እንጨት፡ቅጠል፡እንዳ ...ወዘተ	4
ሻማ/ሟሟ	5
ሌላ /ይገለጽ	6

ዓምድ 21: ቤተሰቡ ባለፈው ሳምንት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ከአንድ ሰዓት ለበለጠ ጊዜ መብራት መቋረጥ አጋጠመው?

በዚህ ዓምድ ለማወቅ የተፈለገው የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት ያላቸው ቤተሰቦች የመብራት መቋረጥ እያጋጠማቸው መሆኑና አለመሆኑን ለማወቅ ነው። ስለሆነም ከጥናቱ ቀን በፊት ካለው ቀን ጀምሮ ወደ ኋላ በመቁጠር እያንዳንዱ ቤተሰብ ባለፈው ሳምንት ውስጥ (ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ) ከአንድ ሰዓት ለበለጠ ጊዜ የቆየ የመብራት መቋረጥ ድግግሞሽ ለስንት ጊዜ እንዳጋጠመው ይጠየቅለታል።

ለምሳሌ:- አንድ ቤተሰብ ባለፈው ሳምንት ውስጥ ከነበሩት 7 ቀናት መካከል በ2ኛውና በ5ኛ ቀናት ቢቋረጥበትና የመቋረጡ ክስተትም በ2ኛው ቀን ከጠዋቱ ከ3:00 ሰዓት ጀምሮ እስከ 6:00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ደግሞ ከ11:00 ሰዓት ጀምሮ እስከ 12:30 ሰዓት ቢሆን፤ በ5ኛው ቀን ደግሞ ከ8:30 ሰዓት እስከ 9:50 ሰዓት ቢሆን ቤተሰቡ በጠቅላላ የመብራት መቋረጥ ያጋጠመው 3 ጊዜ መሆኑ ነው።

የመብራት መቋረጥ ክስተት	ኮድ
ቤተሰቡ መብራት የለውም	1
ምንም የመብራት መቋረጥ አላጋጠመውም	2
አንድ ጊዜ ብቻ (የመብራት መቋረጥ አጋጥሞናል)	3
ሁለት ጊዜ ብቻ (የመብራት መቋረጥ አጋጥሞናል)	4
ከሁለት ጊዜ በላይ (የመብራት መቋረጥ አጋጥሞናል)	5

ስለሆነም ቤተሰቡ የመብራት መኖር ፣ የመብራት መቋረጥ ክስተት ሁኔታና ክስተቱ ካለ የድግግሞሽ ብዛት በተሰጡት የመለያ ኮዶች መሠረት ትክክለኛው መልስ በንዑስ ዓምድ 36 ውስጥ መሞላት ይኖርበታል።

ዓምድ 22: ቤተሰቡ በዋነኛነት የሚጠቀምበት የማገዶ ዓይነት ምንድን ነው?

ቤተሰቡ "ባዮጋዙ ወቅት" እና "ከ12 ወራት በፊት" እንዲሁም ከ ዓመት በፊት በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች ውስጥ በዋነኛነት የሚጠቀመው የማገዶ ዓይነት ተጠይቆ ተገቢው ኮድ በንዑስ ዓምድ 37 ሥር ይሰፍራል::

የማገዶ ዓይነት	ኮድ
የተሰበሰበ እንጨት	1
የተገዛ እንጨት	2
ከሰል	3
ኑሮ ጋዝ	4
ቡታ ጋዝ/የሲሊንደር/	5
ኤሌክትሪክ	6
ቅጠል/ኩበት/ሰጋቱራ	7
ምንም አይጠቀምም	8
ሌላ ይገለጽ	9

ክፍል 2 (የቀጠለ):- ቤተሰቡ በቤት ውስጥ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች

ይህ ክፍል የክፍል 2 ተከታይ ሲሆን ቤተሰቡን በሚመለከት የሚሞላ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 23: ተራ ቁጥር ይህ ዓምድ አስቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነክም::

ዓምድ 24: በክረምት ወቅት ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውኃ የሚያገኘው ከየት ነው? ቤተሰቡ በጥናቱ ዓመት :' ከ (12 ወራት በፊት) እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት በክረምት ወቅት የመጠጥ ውኃ የሚያገኘው ከየት እንደሆነ በመጠየቅ የተነገረውን መልስ በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማመዛዘን በንዑስ ዓምድ 40 ውስጥ ተገቢውን ኮድ ማስፈር ያስፈልጋል::

የመጠጥ ውሃ ምንጮች	ኮድ
ከቤት ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ	1
ከግቢ ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ/የግል	2
ከግቢ ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ/የጋራ	3
ከግቢ ውጭ ካለ የቧንቧ ውኃ/የጋራ	4
ከተጠበቀ የጉድጓድ /ምንጭ ውኃ	5
ካልተጠበቀ የጉድጓድ/ምንጭ ውኃ	6
የዝናብ ውኃ	7
ከወንዝ :' ሐይቅ:' ኩሬ:' ... ወዘተ	8

የተጠበቀ ጉድጓድ ወይም ምንጭ

1. በጉድጓዱ ወይም በምንጩ ዙሪያ በሲሚንቶ የተገነባ ግንብ መኖር አለበት:: ይኸውም:-

   ሀ. ጉድጓድ ከሆነ ጉድጓዱ በሚገኝበት የአፈር ሁኔታ መሠረት ግንቡ ቢያንስ ከ2 እስከ 4 ሜትር ወደ መሬት ውስጥ የገባ እና 70 ሳንቲ ሜትር ያህል ደግሞ ከመሬት ወደ ላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል::

ሰ. ምንጭ ከሆነ ግንቡ ጠንካራ መሬት ወይም አለት እስከሚገኝበት ድረስ መሬት ውስጥ የገባና እንደ አስፈላጊነቱ ከመሬት በላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል። ግንቡ በአንድ በኩል ውኃ ማውጫ ክፍት ቧንቧ ያለው መሆን አለበት።

2. በጉድጓድም ሆነ በምንጭ ዙሪያ የተገነባው ግንብ ከላይ ከሲሚንቶ የተሰራ ወይም ሌላ ዓይነት ጥብቅ ክዳን እንዲኖረው ያስፈልጋል።

3. ወደ ጉድጓዱ ወይም ምንጩ ጎርፍ እንዳይገባ የጎርፉን አቅጣጫ የሚቀይር ተስማሚ በይ ጎርፍ ሊመጣ ከሚችልበት አካባቢ ወይም አቅጣጫ መኖር አለበት።

4. እንደ መጸዳጃ ቤት ከመሳሰሉት ውኃውን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች ጉድጓዱም ሆነ ምንጩ ቢያንስ ቢያንስ ከ25 እስከ 30 ሜትር የራቀ መሆን አለበት።

5. በተራ ቁጥር 4 የተገለፀው በኳይ ቆሻሻ ዓይነት የውኃው ጉድጓድ ወይም ምንጩ ከሚገኝበት ከፍ ባለ ቦታ ቢኖር ርቀቱ በተራ ቁጥር 4 ላይ ከተጠቀሰው ርቀት ብዙ መብለጥ ይኖርበታል።

ስለዚህ ቤተሰቡ ውኃ የሚያገኘው ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በሚያሟላ ሁኔታ ከተጠበቀ ጉድጓድ ወይም ምንጭ ከሆነ ከተጠበቀ ውኃ እንደተጠቀመ ይቆጠራል። በሚንቧ የሚመጣ ውኃ ካልሆነ በስተቀር ከወንዝ ወይም ከሐይቅ እየተቀዳ የሚገኘው ውኃ በአጠቃላይ ያልተጠበቀ ነው ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ከወንዝ፣ ከሐይቅ ወይም ከኩሬ እየቀዳ የሚጠቀም ቤተሰብ በተጠበቀ ውኃ አይጠቀምም ማለት ነው። ከሚንቧ የሚገኝ ውኃ ግን በአጠቃላይ እንደተጠበቀ ይቆጠራል። ውኃው ግን ወደ ተጠቃሚዎቹ ቤት የሚደርሰው በሰው ጉልበት ወይም በጋማ ከብቶች ሊሆን ይችላል።

<u>ዓ/ም 25: በበጋ ወቅት ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውኃ የሚያገኘው ከየት ነው?</u>

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ፣ ከ"12 ወራት በፊት፣ እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት በበጋ ወቅት የመጠጥ ውኃ የሚያገኘው ከየት እንደሆነ በመጠየቅ የተሰጠውን መልስ ከዓ/ም ሥር

ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማዛመድ በንዑስ ዓምድ 41 ውስጥ ተገቢውን ኮድ ማስፈር ያስፈልጋል::

የመጠጥ ውሃ ምንጭ	ኮድ
ከቤት ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ	1
ከግቢ ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ /የግል	2
ከግቢ ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ/የጋራ	3
ከግቢ ውጭ ካለ የቧንቧ ውኃ/የጋራ	4
ከተጠበቀ የጉድጓድ /ምንጭ ውኃ	5
ካልተጠበቀ የጉድጓድ /ምንጭ ውኃ	6
ከወንዝ፡ ሐይቅ፡ ኩሬ፡ ...ወዘተ	7

ዓምድ 26: ቤተሰቡ ተፈልቶ የቀዘቀዘ ውኃ የመጠጣት ልምድ አለው?

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ለ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት ተፈልቶ የቀዘቀዘ ውኃ የመጠጣት ልምድ መኖር አለመኖሩ ተጠይቆ በዓምዱ ግርጌ "በጥናቱ ወቅት፡ ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት ከሚለው አቅጣጫ በንዑስ ዓምድ 42 በተሰጠው ቦታ ተገቢው ኮድ ይመዘገባል:: "አዎን" ለሚለው ኮድ "1" ፣ "የለም" ለሚለው ደግሞ ኮድ "2" ይሞላል ማለት ነው::

ዓምድ 27: ቤተሰቡ በምግብነት የሚጠቀመው ጨው አዮዲን አለው?

ቤተሰቡ "በጥና ወቅት" በምግብነት የሚጠቀመውን ጨው በመጠየቅ አስፈላጊውን ምርመራ ከተደረገ በኋላ አዮዲን እንዳለው እና እንደሌለው በማረጋገጥ በዓምዱ ግርጌ "በጥናቱ ወቅት" ለሚለው አቅጣጫ በንዑስ ዓምድ 43 በተሰጠው ቦታ ተገቢው ኮድ ይመዘገባል::

ቤተሰቡ የሚመገበው ጨው አዮዲን እንዳለው ወይም እንደሌለው ለማወቅ በሚከተለው አኳኋን ምርመራው ይከሄዳል::

1. አንድ የሻይ ማንኪያ ጨው በጠፍጣፋና ደረቅ ዕቃ/ሳህን፡ ድንጋይ ...ወዘተ./ ላይ ይደረጋል::
2. ሁለት ጠብታ ኬሹን መመርመሪያ ፈሳሽ (Testing solution) በጨው ላይ ማፍሰስ::
3. ወዲያውኑ የቀለም ለውጥ በጨው ላይ እንዳለ መከታተል::

ሀ. የውኃ ሰማያዊ ወይም ሀምራዊ ቀለም ከታየ ጨው አዮዲን ያለው ሲሆን፤

ለ. ምንም የቀለም ለውጥ ካልታየ ቀዩን ፈሳሽ በመጨመር የቀለም ለውጥ እንደሚያመጣ መከታተል አሁንም የቀለም ለውጥ ካልታየ ጨው አዮዲን የሌለው በመሆኑ "የለውም" የሚለው ኮድ 2 ይመዘገባል ማለት ነው::

ማስታወሻ:- መመርመሪያ ፈሳሹ ጨው ከመጨመሩ በፊት በደንብ መነቅነቅ አለበት::

("Shake well before use")

ዓ/ም 28: ቤተሰቡ በዋነኛነት የሚጠቀምበት የመፀዳጃ ዓይነት ምንድን ነው?

ቤተሰቡ "በጥናቱ ወቅት" እና "ከ12 ወራት በፊት" እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት በዋነኛነት የሚጠቀምበት የመፀዳጃ ዓይነት በዓ/ዱ ሥር ከተሰጡት አማራጮች ተጠይቆ ተገቢው ኮድ በንዑስ ዓ/ድ 44 ሥር ይሰፍራል::

የመፀዳጃ ዓይነት	ኮድ
በውኃ የሚወርድ መፀዳጃ/የግል	1
በውኃ የሚወርድ መፀዳጃ/የጋራ	2
የጉድጓድ መፀዳጃ/የግል	3
የጉድጓድ መፀዳጃ/የጋራ	4
የቤት ሰቀ (ባልዲ/ፖፖ)	5
ሜዳ /ጫካ	6
ሌላ /ይገለጽ/...	7

ዓ/ም 29: ቤተሰቡ ደረቅ ቆሻሻ ለመጣል በዋነኛነት የሚጠቀምበት ዘዴ ምንድን ነው?

ቤተሰቡ "በጥናቱ ወቅት" እና "ከ12 ወራት በፊት" እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት በዓ/ዱ ሥር ደረቅ ቆሻሻ ለመጣል በዋነኛነት/በአብዛኛው የሚጠቀምበት ዘዴ ከተሰጡት አማራጮች ተጠይቆ ተገቢው ኮድ በንዑስ ዓ/ድ 45 ሥር ይሰፍራል::

የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴ	ኮድ
ቆሻሻ በሚሰበሰብ መኪና (በቆሻሻ ማጠራቀሚያ) መኪና	1
ቆሻሻ በሚሰበሰብ ሰዎች (በቆሻሻ ማጠራቀሚያ) ዕቃ	2
ጉድጓድ ቆፍሮ መጣል	3
ቆሻሻውን ሜዳ ላይ መጣል	4
ለማዳበሪያ መጠቀም	5
ቆሻሻውን ማቃጠል	6
ሌላ/ይገለጽ	7

ቅጽ 6:- የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የርቀትና የአጠቃቀም ሁኔታ

በዚህ ቅጽ የሚሰበሰበው መረጃ በጥናቱ የሚሸፈኑት ቤተሰቦች ከሚገኙበት አካባቢ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ርቀት ምን ያህል እንደሆነ፤ የአጠቃቀም ሁኔታ፤ በአገልግሎቱ የማይጠቀሙ ከሆነ ዋናው ምክንያትና ከድርጅቶቹ የሚገኘው አገልግሎት እርካታ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመገምገም የሚያስችል ነው::

ክፍል 1: የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ 1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው::

ክፍል 2: የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የርቀትና የአጠቃቀም ሁኔታ

ዓምድ 13: ተራ ቁጥር:- ከ01-25 አስቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነክም::

ዓምድ 14: የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት:-

በዚህ ዓምድ ዋና ዋናዎቹ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተዘርዝረዋል:: ከዓምድ 15-20 ያሉት ዓምዶች መረጃ የሚሞላላቸው በዓምድ 14 በተዘረዘሩት የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መሠረት መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 15: ቤተሰቡ በቅርብ የሚያገኘው _____ ርቀቱ ምን ያህል ነው?

በዚህ ዓምድ በዓምድ 14 የተዘረዘሩት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ቤተሰቡ ቢጠቀምም ባይጠቀምም በቅርብ የሚገኘው ድርጅት ቤተሰቡ ካለበት ቦታ ያለው ርቀት ተጠይቆ መሞላት ይኖርበታል:: ስለዚህ ይህ ዓምድ በምንም መልኩ ባዶ ሊሆን አይችልም:: ይህም ርቀት የሚሞላው ወደ ሙሉ ኪሎ ሜትር በማጣጋትና በስንት ደቂቃ የሚወሰደውን ጊዜ በመጠየቅ ነው:: ከአንድ ኪሎ ሜትር በታች ከሆነ በንዑስ ዓምድ 25-27 "000" ይሞላል:: አሞላሉም በሚከተለው ሁኔታ ነው::

ማስታወሻ:

- ቤተሰቡ የአገልግሎት ሰጪ ተቋሙን ርቀት በሰዓት ብቻ የሚያውቅ ከሆነ ምን ያህል ሰዓትና ደቂቃ እንደሚጓዝ የሚመዘገብ ሲሆን በኪ.ሜትር መመዝገቢያ ሳጥን ላይ ባዶ ይተዋል::

- ቤተሰቡ የአገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ርቀት በኪ.ሜትር ብቻ የሚያውቅ ከሆነ ለሰዓትና ደቂቃ መሃፊያ በተሰጠው ቦታ ላይ ባዶ በመተው ርቀቱ በኪ.ሜትር ብቻ ይመዘገባል::

- ቤተሰቡ የአገልግሎት ሰጪ ተቋሙን ርቀት በሁለቱም የመለኪያ አይነቶች (በሰዓትና በኪ.ሜትር) መናገር የሚችል ከሆነ ሰዓትና ደቂቃ በሚለው አንዣር ሰዓት እና ደቂቃውን ኪ.ሜትር በሚለው አንዣር ደግሞ ርቀቱ በኪ.ሜትር ይመዘገባል::

ዓምድ 16: ቤተሰቡ በ_____ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ምን ያክል ይጠቀማል?

በዚህ ዓምድ በዓምድ 14 የተዘረዘሩትን እያንዳንዱን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት አስመልክቶ የአጠቃቀም ሁኔታው የሚጠየቅ ሲሆን ለጥያቄው ተስማሚውን መልስ ከተሰጡት ምርጫዎች መካከል በመምረጥ በንዑስ ዓምድ 32 ላይ ኮዱ ይመዘገባል::

አማራጭ መልሶች	ኮድ
ምንም አይጠቀምም	=1
አልፎ አልፎ ይጠቀማል	=2
አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማል	=3
ሁልጊዜ ይጠቀማል	=4

ዓምድ 17: በዓምድ 16 ኮድ 1 ወይም 2 ለተሞላላቸው ቤተሰቡ በ_____ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ምንም አልጠቀምም/ አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ ካለ ዋና ምክንያቱ ምንድን ነው?

በዚህ ዓምድ በዓምድ 14 የተዘረዘሩትን እያንዳንዱን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት አስመልክቶ ቤተሰቡ አልጠቀምም (ኮድ 1) ወይም አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ (ኮድ 2) ካለ የማይጠቀምበት ዋናው ምክንያት ምን እንደሆነ ተጠይቆ የተሰጠው መልስ በዓምዱ ሥር

ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማዛመድ ኮድ 1 በንዑስ ዓምድ 33 -39 ውስጥ ሲሞላ ቤተሰቡ ላለጠቀሳቸው ምክንያቶች ደግሞ በንዑስ ዓምዶቹ ውስጥ ኮድ 2 ይሞላል::

አማራጭ ምክንያቶች:-
ርቀት ስላለው
ውድ ስለሆነ
የአገልግሎት ጥራት ዝቅተኛ ስለሆነ
ሠራተኛ/መሣሪያ ስለሌለው
አገልግሎት የተሟላ ባለመሆኑ (ዕቃዎች፤ ሠራተኞች ...ወዘተ)
ስለማያስፈልገው/ስለማይመለከተው
ሌላ ይገለፅ

ዓምድ 18: ቤተሰቡ ባገኘው አገልግሎት ረክቷል?

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በዓምድ 16 ኮድ 2 /አልፎ አልፎ/፤ ኮድ 3/ አብዛኛውን ጊዜ/ ወይም ኮድ 4/ሁልጊዜ/ እጠቀማለሁ ተብሎ ለተሞላላቸው የአገልግሎት ዓይነቶች ሲሆን ቤተሰቡ አገልግሎት ባገኘባቸው የአገልግሎት ዓይነቶች መርካት /መደሰት/ ወይም አለመርካቱ/አለመደሰቱ/ ተጠይቆ ረክቻለሁ/ተደስቻለሁ ካለ በዓምዱ ስር አዎን በመባሉ ኮድ 1፤ አልረካሁም/አልተደሰትኩም ካለ ደግሞ በዓምዱ ስር የለም በመባሉ ኮድ 2 በንዑስ ዓምድ 40 ላይ ይመዘገባል:: ነገር ግን በዓምድ 16 ላይ ኮድ 1 /ምንም አልጠቀምም ካለ/ ይህ ዓምድ በሠረገዝ ይታለፋል::

ዓምድ 19: ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ከአገልግሎት ሰጪው ድርጅት ያገኘው አገልግሎት የጥራት ደረጃ ምን አይነት ለውጥ አሳይቷል?

ይህ ዓምድ የሚጠየቀው በዓምድ 16 ኮድ 2 ፣ 3 ወይም 4 ለተሞላላቸው (በአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ለተጠቀሙ) ቤተሰቦች ነው:: ስለሆነም ባለፉት 12 ወራት ቤተሰቡ ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ያገኘው አገልግሎት የጥራት ደረጃ አሁን ካለው ጋር በማነፃፀር የሚጠየቅ ሲሆን ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ጋር በማገናዘብ/በማዛመድ በዓምዱ ተገቢው መልስ ተመዝግቦ ተስማሚው ኮድ ደግሞ በንዑስ ዓምድ 41 ላይ ይመዘገባል::

አማራጭ መልሶችም:-	ኮድ
ዝቅተኛ እየሆነ ነው (እየዘቀጠ ነው)	=1
ምንም ለውጥ የለውም	=2
እየተሻሻለ መጥቷል	=3
አላውቅም	=4

ማስታወሻ:- በዓምድ 16 ኮድ 1 ከተሞላ ይህ ዓምድ (በሰረዝ ይታለፋል)::

ዓምድ 20: ቤተሰቡ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለመድረስ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው የመጓጓዣ አይነት ምንድን ነው?

በዓምድ 16 ኮድ 2 ፡ኮድ 3 ወይም ኮድ 4 ለመለሱ ቤተሰቦች በዓምድ 14 በተዘረዘሩት የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መሠረት ወደ ድርጅቶቹ ለመድረስ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት የመጓጓዣ አይነት ምን እንደሆነ ይጠየቅላቸዋል:: በመሆኑም ቤተሰቡ በሚሰጡት መልስ መሠረት በዓምዱ ሥር የመጓጓዣ አይነት የሚሞላ ሲሆን በንዑስ አምድ 42 ደግሞ ተስማሚው ኮድ ተመርጦ ይሞላል:: ይሁን እንጂ በአምድ 16 ላይ ምንም እንደማይጠቀሙ ለገለፁለት የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት ይህ አምድ በሰረዝ ይታለፋል:: የመጓጓዣ አይነቶችና ኮዶቻቸው ከዚህ በታች የተሰጡት ናቸው::

የመጓጓዣ ዓይነት	ኮድ
በእግር	1
በብስክሌት	2
በሞተር ሳይክል(ሞተር/ ብስክሌት)	3
በዜት መኪና	4
በሕዝብ መጓጓዣ(አውቶቡስ፡ ታክሲ)	5
በመስሪያ ቤት መኪና(ሰርቪስ)	6
በጋሪ/በከብት	7
ሌላ (ይገለፅ)	8

ቅጽ 7:- የቤተሰቡ የቤትና የመሬት ይዞታ እና ሌሎች

ቋሚ ንብረቶች ሁኔታ

በዚህ ቅጽ የሚሰበሰቡት መረጃዎች ስለቤተሰቡ የቤትና የመሬት ይዞታ ሁኔታዎችንና የቋሚ ንብረቶች ሁኔታ ሲሆኑ በክፍል 2 የቤትና የመሬት ይዞታ እንዲሁም በክፍል 3 ደግሞ በተዘረዘሩት ሌሎች ቋሚ ንብረቶች መሰረት መረጃው ይሰበሰባል::

ክፍል 1: የተመረጠው ቤተሰብ አደራሻ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ 1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው::

ክፍል 2 : የቤተሰቡ የቤትና የመሬት ይዞታ ሁኔታ

በዚህ ክፍል ቤተሰቡ ከ12 ወራት በፊት መኖሩና አለመኖሩን (በቅፅ 5 ክፍል 2 ዓምድ 14 የተሰጠውን መልስ ይመልከቱ)፡ የቤተሰቡ የቤት ሁኔታ የቤተሰቡ የመሬት ይዞታ ሁኔታና የመሬቱ ስፋት እንዲሁም የራሱ ባይሆንም ቤተሰቡ የሚጠቀምበት መሬት ሁኔታና ስፋት መረጃዎች ይሰበሰባሉ::

በዚህ ቅጽ በጥናቱ ወቅት ማለት መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡን በነበኘበት ጊዜ ማለት ነው::
ከ12 ወራት በፊት ማለት ደግሞ የዛሬ አንድ ዓመት ወይም አምና ማለት ነው::
ከ4 ዓመት በፊት ማለት ደግሞ የዛሬ 5 ዓመት ማለት ነው::

ዓምድ 13:- ተራ ቁጥር

በዚህ ዓምድ ስር የጥናቱ ወቅት፡ ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት የነበሩትን ወቅቶች ለመለየት ሲባል 01 ፣ 02 እና 03 ተብለው አስቀድመው የተሞሉ ስለሆኑ አይነኩም::

ዓምድ 14:- ቤተሰቡ ከ12 ወራት በፊት ነበርን?

ይህ ዓምድ ከቅጽ 5 ክፍል 2 አምድ 14 በቀጥታ የሚወራረስ ነው::

ዓምድ 15: ከቤተሰቡ መካከል /ንላፊውን ጨምሮ/ የራሱ የሆነ መኖሪያ ቤት ወይም ሌላ ቤት ያለው አለ?

ከቤተሰቡ አባላት መካከል/ንላፊን ጨምሮ/ በጥናቱ ወቅት፡ "ከ12 ወራት በፊት" እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት ቢያንስ አንድ አባል ቤት ካለው/ከነበረው በጥናቱ ወቅት፡ ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት በሚሉት አቅጣጫ በንዑስ ዓምድ 26 ኮድ 1 ይሞላለታል። ከቤተሰቡ አባላት መካከል አንዱም እንኳን ቤት ከሌለው በዓምዱ ስር በንዑስ ዓምድ 26 ኮድ 2 ይሞላል። በተጠቀሱት ወቅቶች ከቤተሰቡ አባላት መሃከል አንዳቸውም ቤት ከሌሎቸው ወደ ዓምድ 17 ይታለፋል።

ማሳሰቢያ:-

1. ቤቱ የሚገኝበት ቦታ ጥናቱ ከሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ ክልል ውጪ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ቤቱ የቤተሰቡ አባል /አባላት የግል ንብረት መሆን እንዳለበት መታወቅ አለበት።

2. ቤቱን በማከራየ መልክ በብድር ቢሰራውም በዚህ ይጠቃለላል።ይሁን እንጂ ከሌላ ቤተሰብ ጋር በሽርክና የያዛቸው ቋሚ ንብረቶች በጥናቱ አይሸፈኑም።

3. በቅጽ 5 ዓምድ 16 ቤተሰቡ ቤቱን በባለቤትነት ይዣዋለሁ የሚል መልስ ከሰጠ ቢያንስ አንድ ቤት እንዳለው መታወቅ አለበት።

ዓምድ 16: ቤተሰቡ በአጠቃላይ ስንት የራሱ የሆነ የመኖሪያ ቤቶችና ሌሎች ቤቶች አሉት?

በዓምድ 15 "አዎን" የሚል መልስ ከተሰጠ የግድ በዓምድ 16 ብዛቱ መሞላት ይኖርበታል። ስለዚህ በዚህ ዓምድ "00" ሊሞላ እንደሚችል መታወቅ አለበት። እንዲሁም በዓምድ 15 የተጠየቀው ከቤተሰቡ አባላት መካከል በጥናቱ ወቅት፡ ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት ቢያንስ አንዱ አባል ቤት ያለው/የነበረው መሆኑን ሲሆን በዓምድ 16 ግን በአጠቃላይ በጥናቱ ወቅት፡ ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት ቤተሰቡ ያሉት የቤቶች ብዛት ነው። ይህንን ብዛት ለማግኘት ከቤተሰቡ አባላት መካከል ስንቶቹ ቤት እንዳላቸው ጠይቆ በማጣራት

ጠቅላላ ደምራቸውን በዓመቱ ሥር ከጥናቱ ወቅት ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም "ከ4 ዓመት በፊት" በሚለው አቅጣጫ በንዑስ ዓምድ 27 - 28 ይሞላል::

ለምሳሌ:- ቤተሰቡ 2 የመኖሪያ ቤቶች፡ አንድ የንግድ ቤት፡ 2 ለማምረቻ የሚጠቀምባቸው ቤቶች ቢኖሩት በአጠቃላይ 5 ቤቶች አሉት ማለት ነው:: አሞላሉም በዓመቱ ሥር ባለው ክፍት ቦታ በጥናቱ ወቅት ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም "ከ4 ዓመት በፊት" ከሆነ በመለየት በንዑስ ዓምድ 27 - 28 "05 ተብሎ ይሞላል::

ዓምድ 17: ከቤተሰቡ አባላት መካከል ኃለፊውን ሜምር የራሱ የሆነ የእርሻ ወይም ሌላ መሬት ያለው አለ?

አንድ የቤተሰብ አባል መሬት አለው የሚባለው በገጠርም ሆነ በከተማ ቤት ያረፈበት ቦታ ፡ ለእርሻ ሥራና የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ላላቸው ተግባራት የሚውል (ለሊዝ፡ በግዥ፡ በውርስ ወይም በሌላ መንገድ) በንብረትነት የያዘው ቦታ ማለት ነው:: በጥናቱ ወቅት፡ ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት ከቤተሰቡ አባላት መካከል አንድ አባል እንኳን ከላይ የተጠቀሰው መሬት ካለው በዓመቱ ሥር በተሰጠው ንዑስ ዓምድ 29 ኮድ 1 በየወቅቶቹ እንዣር እየተጠየቀና እየተጣራ የሚሞላ ሲሆን መልሱ የለም የሚል ከሆነ የሚለው ኮድ 2 በየወቅቶቹ እንዣር እየተጠየቀና እየተጣራ ይሞላል::

ማሳሰቢያ:- ቤተሰቡ መሬት አለው የሚባለው በመኖሪያ አካባቢው ብቻ ሳይሆን ከአካባቢው ውጭ (በወረዳ፡ በዞን፡ በክልሉ ወይም ከክልሉ ውጭ) ሊሆን እንደሚችል መታወቅ አለበት::

ምሳሌ:- አንድ ቤተሰብ ከ4 ዓመት በፊት የራሱ የሆነ መሬት ያልነበረውና የዛሬ አንድ ዓመት ግን ቤት ቢገዛ እና አሁንም ያለው ቢሆን በዚህ ዓምድ በንዑስ ዓምድ 29 በጥናቱ ወቅት በሚለው ትይዩ ከ12 ወራት በፊት በሚለው ትይዩ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ከ4 ዓመት በፊት በሚለው ትይዩ ግን 2 ይሞላል::

ዓምድ 18: በአምድ 17 "አዎን" ለመለሱ ቤተሰቡ የራሱ የሆነ ስንት ማሳና በሌላ የመሬት አጠቃቀም የተያዘ ቦታ አለው?

ይህ ዓምድ የሚጠየቅላቸው ቤተሰቦች በዓምድ 17 (በጥናቱ ወቅት ፡ ከ12 ወራት በፊትና ከ4 ዓመት በፊት) የራሳቸው የሆነ መሬት አላቸው ተብሎ ኮድ 1 ለተሞላላቸው ነው። በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት፡ ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት ምን ያህል መሬት / ማሳዎች እንደሚጠቀም ወይም ይጠቀም እንደነበር ተጠይቆ ብዛቱ በቁጥር በዓምዱ ስር በተሰጡት ንዑስ ዓምድ 30 እና 31 ይሞላል። ለዚህ ጥናት ማሳ ማለት ባለይዞታው "ማሳ" ብሎ የሚያውቀው ሲሆን ይህም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ቋሚና ጊዜያዊ ሰብሎች ድብልቅ ሊያዝ እንደሚችል መታወቅ አለበት። በሌላ የመሬት አጠቃቀም ማለት በጊዜያዊ ሆነ በቋሚ ሰብሎች ያልተያዘ የቤተሰቡ መሬት ማለት ነው።ይህም በረት፡ የግጦሽ ቦታ፡ የደን ቦታ ወዘተ ሊሆን ይችላል።

ዓምድ 19: አጠቃላይ የመሬት ስፋት በአካባቢው መለኪያ

በዚህ ዓምድ ለመስብሰብ የተፈለገው መረጃ በዓምድ 17 ላይ መሬት እንዳላቸው ለገለፁ ቤተሰቦች የመሬቱ ስፋት በአንድ በአካባቢው በታወቀ የአካባቢ መለኪያ መሠረት ምን ያህል እንደሆነ ነው። ስለሆነም "በአካባቢ መለኪያ" በሚለው ስር ለስም በተሰጠው ቦታ የአካባቢው መለኪያ ስም ሲፃፍ የአካባቢው መለኪያ ስም ኮዱ ደግሞ በንዑስ ዓምድ 32 እና 33 በቢሮ ደረጃ የሚሞላ ስለሆነ ምንም አይነካም። ስፋቱ ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 34-37 ይሞላሉታል።

ማስታወሻ:- የመሬቱ ስፋት በአካባቢው መለኪያ በሚሞፍበት ወቅት በሙሉ ቁጥርና በክፍልፋይ ተለያይቶ መፃፍ /መሞላት እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል።

ምሳሌ:- አንድ ለጥናቱ የተመረጠ ቤተሰብ ውስጥ 3 መሬት ያላቸው አባላት ቢኖሩና አንደኛው አባል ሦስት ተኩል ጥማድ፡ ሁለተኛው አባል ሲሶ ጥማድ እንዲሁም ሦስተኛው አባል ደግሞ ሩብ ጥማድ እንዳላቸው ቢናገሩ ይህ ቤተሰብ በጥቅሉ ያለው መሬት ስፋት በጥማድ (3.50 + 0.33 + 0.25 = 4.08) ስለሆነ 4ትን ለሙሉ ቁጥር መፃፊያ በተሰጠው ቦታ (በንዑስ ዓምድ 34 እና 35) ሲፃፍ 0 እና 8ትን ደግሞ በክፍልፋይ መፃፊያ በተሰጠው ንዑስ ዓምድ 36 "0" ይፃፍና በንዑስ ዓምድ 37 ደግሞ "8" ይፃፉል ማለት ነው።

መግለጫ

1. በአንድ የቆጠራ ቦታ ውስጥ ለሚጠኑ ቤተሰቦች በሙሉ የሚመዘገበው የአካባቢ መለኪያ አንድ ዓይነት መሆን ይኖርበታል። ይኸውም ቤተሰቦቹ የተለያየ

የአካባቢ መለኪያ የሚጠቀሙ ቢሆን እንኳን ለሁሉም ቤተሰቦች መመዝገብ ያለበት የአካባቢ መለኪያ በቆጠራ ቦታው ውስጥ በአብዛኛው የሚታወቀው (አብዛኛው ህበረተሰብ የሚጠቀምበት) ተጠይቆ መሞላት ይኖርበታል። በዚህ መሠረት ለሁሉም ቤተሰቦች ወጥ የሆነ የአካባቢ መለኪያ ከተመዘገበ በኋላ እያንዳንዱ በጥናቱ የታቀፈ ቤተሰብ የመሬቱን ስፋት ሲጠየቅ ከተመዘገበው ውጭ በሌላ የአካባቢ መለኪያ መሰረት የመሬቱ ስፋት ቢናገር እንኳን ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር አወዳድሮ የመሬቱ ስፋት እንዲናገር ማድረግ ያስፈልጋል።

2. የመሬታቸው ስፋት በአካባቢው መለኪያና በስታንደርድ መለኪያ (በሁለቱም) ለሚያውቁ ቤተሰቦች መረጃ የሚሰበሰበው የሁለቱን መሆን ይኖርበታል።
3. ከሁለቱ መለኪያዎች አንዱን ብቻ የሚያውቁ ከሆነ ግን በሚያውቁት የስፋት መለኪያ መሠረት መረጃው ይሰበሰባል።

በአንድ የቆጠራ ቦታ አብዛኛው ቤተሰብ የሚጠቀመው የአካባቢ መለኪያ "ቀርጥ" ነው እንበል። በቆጠራ ቦታው ከተመረጡት ቤተሰቦች ውስጥ አንዱ ቤተሰብ በጥማድ ቢናገር " በቀርጥ" ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ቤተሰቡን በመጠየቅ በአካባቢው መለኪያ ዓምድ ስር ስሙ "ቀርጥ" ተብሎ ስፋቱ በቀርጥ ይመዘገባል ማለት ነው።

ዓምድ 20: አጠቃላይ የመሬት ስፋት በስታንደርድ መለኪያ

በዚህ ዓምድ በቤተሰቡ የራሱ የሆነ መሬት ጠቅላላ ስፋት ዓለም አቀፍ እውቅና ባለው የሜትሪክ /ስታንደርድ/ መለኪያ መሠረት የሚሞላ ነው። እነዚህም መለኪያዎች ሄክታርና ስኳዌር ሜትር ናቸው። የስታንደርድ መለኪያው ስም በአምዱ ስር ባለው ክፍት ቦታ የሚሞላ ሲሆን ኮድ በሚለው ስር በንዑስ ዓምድ 38 እና 39 በዚሮ ደረጃ የሚሞላ ስለሆነ ክፍት ይተዋል። የመሬቱ ስፋት አስቀድሞ ስሙ በተገለፀው ስታንደርድ መለኪያ መሠረት ተጠይቆ ሙሉ ቁጥሩን በንዑስ ዓምድ 40-44 እና ክፍልፋዩን በዓምድ 45 መመዝገብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 21፡ቤተሰቡ የራሱ የሆነ መሬት ማሳዎች ብዛት ካለፈው 12 ወራት ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?

ቤተሰቡ በአሁኑ ወቅት (በጥናቱ ወቅት) ያለው አጠቃላይ የመሬት / የማሳዎች ብዛት ፡ ከ12 ወራት በፊት ጋር ሲነፃፀር ምን እንደሚመስል ተጠይቆ የሚሰጠውን መልስ ከተሰጠት አማራጮች ጋር በማገናዘብ በጥናቱ ወቅት በሚለው ትይዩ በንዑስ ዓምድ 46 ተሰማሚው ኮድ መመዝገብ ይገባል። አማራጭ መልሶችና ኮዳቸው ከዚህ በታች ተመልክተዋል።

አማራጭ መልሶች	ኮድ
አሁን ቀንሷል	=1
ተመሣሣይ ነው	=2
አሁን ጨምሯል	=3
አላውቅም	=4

ዓምድ 22፡ ቤተሰቡ የራሱ ያልሆነ መሬት / ማሳዎች አጠቃቀም ምን ይመስላል?

ይህ ዓምድ ሁሉንም ቤተሰቦች የሚመለከት (በዓምድ 17 መሬት አለን ላሉ ይሁን የለንም ላሉ በሙሉ) ሲሆን ቤተሰቡ የራሱ ያልሆነ መሬት/ማሳ በተለያየ መልክ አማኝቶ እየተጠቀመበት መሆኑና አለመሆኑን እንዲሁም እየተጠቀመ ከሆነ በምን መልኩ እንዳገኘው በመጠየቅ የሚገኘውን መልስ በዓምዱ ሥር ካሉት ሁኔታዎች ጋር በማመዛዘን ትክክለኛውን ኮድ በካርድ ቁጥር 47 ውስጥ ይሞላል። ይህ ጥያቄ የሚቀርበው በጥናቱ ወቅት፡ ከ12 ወራት በፊት እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት በነበረው ሁኔታ ላይ በማተኮር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ ዓምድ የሚገኙ መልሶችና ኮዶቻቸው ከዚህ በታች የተሰጡት ናቸው።

የአጠቃቀም ሁኔታ	ኮድ
አይጠቀምም	1
በኪራይ ይጠቀማል (ሊዝ ፌምር)	2
ከባለመሬቱ ምርት በመከፋፈል ይጠቀማል	3
በነፃ ይጠቀማል	4
በሌላ	5

<u>በዓምድ 22 ከኮድ 2-5 ለመለሱ/ቤተሰብ የራሱ ያልሆነ መሬት የሚጠቀም ከሆነ/</u>

<u>ዓምድ 23 - ቤተሰቡ የራሱ ያልሆነ ስንት ማሳዎችና በሌላ የመሬት አጠቃቀም</u>

<u>የተያዘ ቦታ አለው?</u>

ቤተሰቡ የራሱ ያልሆነ መሬት / ማሳዎች መጠቀሙ ከተረጋገጠ (በዓምድ 22 ከኮድ 2 - 5 ከተሞላ) በዚህ ዓምድ በተናጠል በየወቅቱ (በጥናቱ ወቅት ፤ "ከ12 ወራት በፊት" እንዲሁም ከ4 ዓመት በፊት) የራሱ ያልሆነ ምን ያህል መሬት / ማሳዎች እንደሚጠቀም/ይጠቀም እንደነበር አጣሪዉ በመጠየቅ የሚገኘው መልስ በቁጥር በንዑስ ዓምዶች 48 እና 49 ይሞላል።

<u>ዓምድ 24: ቤተሰቡ የራሱ ያልሆነ መሬት/ ማሳዎች ብዛት ካለፈው 12 ወራት ጋር</u>

<u>ሲነፃፀር ምን ይመስላል?</u>

ቤተሰቡ አሁን የሚጠቀምበት የራሱ ያልሆነ መሬት/የማሳዎች ብዛት ካለፈው ከ12 ወራት ጋር ሲነፃፀር ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብ በንዑስ ዓምድ 50 መመዝገብ ይኖበል። አማራጭ መልሶችና ኮዳቸው ከዚህ በታች ተመልክተዋል።

አማራጭ መልሶች	ኮድ
አዎን ቀንሷል	=1
ተመሣሣይ ነው	=2
አዎን ጨምሯል	=3
አላውቅም	=4

ዓምድ 25: አጠቃላይ የመሬት ስፋት በአካባቢው መለኪያ ምን ያህል ነው?

በዚህ ዓምድ በዓምድ 22 ላይ የራሳቸው ያልሆነ መሬት እንደሚጠቀሙ ለገለፁ ቤተሰቦች (በዓምድ 22 ከኮድ 2-5 ለተሞላላቸው) የመሬቱ ስፋት በአንድ በአካባቢው በታወቀ የአካባቢ መለኪያ መሠረት ምን ያህል እንደሆነ ይመዘገባል። ከላይ ለአምድ 19 የተገለፀውን ተመልከት።

ማስታወሻ፡- የመሬቱ ስፋት በአካባቢው መለኪያ በሚዛፍበት ወቅት በሙሉ ቁጥርና በክፍልፋይ ተለያይቶ መዛፍ /መሞላት እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 26: ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት የራሱ ያልሆነ መሬት የሚጠቀም ከሆነ የመሬቱ ስፋት በስታንደርድ መለኪያ ምን ያህል ነው ?

በዚህ ዓምድ የሚጠየቀው መረጃ በዓምድ 22 ላይ የራሳቸው ያልሆነ መሬት እንደሚጠቀሙ ለገለፁ ቤተሰቦች (በዓምድ 22 በኮድ 2 - 5 ለተሞላላቸው) የመሬቱ ጠቅላላ ስፋት በወጥነቱ ዓለም አቀፍ እውቅና ባለው የሜትሪክ /ስታንደርድ/ መለኪያ (ሄክታር ወይንም በስኩዌር ሜትር ነው። አሞላሉ ከላይ በዓምድ 20 ከተሰጠው ጋር ተመሳሳይ ነው።

ክፍል 3: የቤተሰቡ ሌሎች ቋሚ ንብረቶች

ዓምድ 27: ተራ ቁጥር:- ይህ ዓምድ ከ01 በመጀመር እስከ 29 ድረስ አስቀድሞ ተራ ቁጥር የተሰጠው ስለሆነ አይነካም::

ዓምድ 28: የንብረት ዓይነቶች:- በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ሊኖሩት የሚችሉ የቋሚ ንብረት ዓይነቶች ተዘርዝረዋል:: ስለሆነም ከዓምድ 29-31 ያሉት መረጃዎች የሚሞሉት በዓምድ 28 በተዘረዘሩት ንብረቶች መሠረት መሆን ይኖርባቸዋል::

ዓምድ 29: በአሁኑ ጊዜ ቤተሰቡ_____ አለው?

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በዓምድ 28 የተዘረዘሩትን እያንዳንዱን ንብረት አስመልክቶ በአሁኑ ጊዜ ያለው መሆኑና አለመሆኑን ይጠየቃል:: ለእያንዳንዱ በዓምድ 28 ለተዘረዘሩት ንብረቶች ቤተሰቡ ተጠይቆ አለኝ የሚል ከሆነ በዓምድ 29 ሥር ባለው ክፍት ቦታ "አዎን" የሚል መልስ ተመዝግቦ በንዑስ ዓምድ 67 ላይ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን የለኝም በሚላቸው ንብረቶች ትይዩ ደግሞ "የለም" የሚል ተሞልቶ በንዑስ ዓምድ 67 ኮድ 2 ይሞላለታል:: "አይመለከተውም የሚሞላላቸው በግብርና ሥራ ላይ ያልተሰማሩ ቤተሰቦች ሆነው ለግብርና ቋሚ ዕቃዎች ከተራ ቁጥር 01-11 ብቻ ነው::

ዓምድ30 :በዓምድ 29 አዎን ለመለሱ ቤተሰቡ ስንት_____አለው?

ቤተሰቡ በዓምድ 28 ለተዘረዘሩት የንብረት ዓይነቶች በአሁኑ ጊዜ አለኝ ካለ በዓምድ 29 "አዎን" የሚል መልስ ከሰጠ (ኮድ "1" ከተሞላ) በዚህ ዓምድ በቁጥር ስንት እንዳለው ተጠይቆ በዓምዱ ሥር የንብረቱ ብዛት በፊደል ይፃፍና በንዑስ ዓምድ 68-70 ውስጥ ደግሞ በአሃዝ ይሞላል:: ሆኖም ማን በዓምድ 29 የለም ተብሎ ኮድ "2" ከተሞላ ይህ ዓምድ በሰረዝ "-" ይታለፋል

ዓምድ 31: አሁን ካለው ብዛት ጋር ሲነፃፀር ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በ___ ላይ የታየ ለውጥ ምን ይመስላል?

በዚህ ዓምድ በዓምድ 28 ለተዘረዘሩት ለእያንዳንዱ ቋሚ የቤተሰቡ ንብረት አሁን/በጥናቱ ወቅት/ ካለው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የታየውን ለውጥ እንዲያነፃፅር ቤተሰቡን በመጠየቅ መረጃው ይሞላል። ይኸውም ጨምሯል የሚል ከሆነ በዓምዱ ሥር ባለው ክፍት ቦታ "ጨምሯል" ተብሎ ይፃፍና በንዑስ ዓምድ 71 ላይ ኮድ 1 ይሞላል፣ ለውጥ ከሌለ "ለውጥ የለውም" በማለት ይፃፍና ኮድ 2 ሲሞላለት፣ ቀንሷል የሚል መልስ ከሰጠ "ቀንሷል" በማለት ይፃፍና ኮድ 3 ይሞላለታል። እንዲሁም ጥያቄው የማይመለከተው ቤተሰብ ከሆነ አይመለከተውም ተብሎ በንዑስ ዓምዱ ኮድ 4 ይሞላለታል። "አይመለከተውም ሊሞላላቸው የሚችለው በግብርና ሥራ ላይ ያልተሰማሩ ቤተሰቦች የግብርና ቋሚ ንብረቶች (ከተራ ቁጥር 01 - 11) በተመለከተ ብቻ ነው። በሌላው ቋሚ ንብረት በሙሉ አይመለከተውም ሊሞላለት አይችልም።

ማሳሰቢያ:- 1. በዚህ ቅጽ ከዓምድ 29-31 ባሉት ጥያቄዎች "አሁን" ማለት የጥናቱን ወቅት /መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡን በአነጋገረበት ጊዜ ያለው ሁኔታ ነው/።

ይህ አምድ ቤተሰቡ በአሁኑ ወቅት ቋሚ ንብረት ቢኖረውም ባይኖረውም እንደሚጠየቅ መታወቅ አለበት። አንድ ቤተሰብ በአሁኑ ወቅት ንብረቱን ባይኖረውም ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ሊኖረው እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። ባለፉት 12 ወራት ውስጥም ሆነ አሁን ንብረቱ ባይኖረው "ለውጥ የለውም" የሚለው አማራጭ እንዲሞላለት ያስፈልጋል። አሁን ባይኖረው ነገር ግን ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ኖሮት ከሆነ "ቀንሷል" የሚለው አማራጭ ይመዘገብለታል። ነገር ግን ቤተሰቡ በአሁኑ ጊዜ ከሌለው "ጨምሯል" የሚለው አማራጭ ሊሞላ እንደሚይችል መታወቅ አለበት።

ቅጽ 8:- ጠቅሚ የኑሮ ደረጃ መለኪያዎች

ክፍል 1: የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ 1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው::

ክፍል 2: ጠቋሚ የኑሮ ደረጃ መለኪያዎች

ይህ ክፍል የሚመለከተው የቤተሰቡን አባላት አንድ በአንድ በመጠየቅ ሳይሆን ስለ ቤተሰቡ አጠቃላይ ሁኔታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 13: ተራ ቁጥር:- ተራ ቁጥር የተሞላ ስለሆነ በዚህ ዓምድ ምንም አይፃፍም::

ዓምድ 14: ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የምግብ እጥረት አጋጥሞት ነበርን ?

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የምግብ እጥረት ደርሶበት እንደነበረ ወይም እንዳልደረሰበት የሚጠየቅበት ነው:: ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት የምግብ እጥረት አጋጥሞት ከነበረ በዓምዱ ስር በተተወ ክፍት ቦታ አዎን የሚለው መልስ ይጻፍና በካርድ ኮለም 25 ደግሞ ኮድ 1 ይሞላል:: ቤተሰቡ የምግብ እጥረት አጋጥሞት ያልነበረ ከሆነ የለም ተብሎ ኮድ 2 በተሰማሚው ቦታ ይመዘገባል::

ለዚህ ጥናት አንድ ቤተሰብ የምግብ እጥረት አጋጠመው የሚባለው ከተለያየ ምንጭ በሚያገኘው ገቢ (በማምረት፤ ከእርሻ መገልገያ እንስሳት በስተቀር ያሉ እንስሳትና ውጤታቸውን በመሸጥ በተለየ ምርታማ ሥራዎች በማከናወን... ወዘተ የተገኘ ገቢ) ቤተሰቡን ከወር እስከ ወር ለመመገብ ያልቻለ እንደሆነ ነው:: ቤተሰቡ በዚህም ምክንያት ለተለያዩ ችግሮች ሲጋለጥ ይችላል::

ምሳሌ

- በምግብ እጦት ምክንያት ከቀየው መፈናቀል፤
- ለዕርዳታ መዳረግ፤
- በችግሩ ምክንያት የእርሻ እንስሳት ለመሸጥ መገደድ፤
- በምግብ እጦት ምክንያት ለአራጣ(የገንዘብ ወይም የዓይነት) መዳረግ፤
- የእርሻ መሳሪያዎች ለመሸጥ መገደድ፤
- የቤተሰቡን ቋሚ ዕቃዎች ለመሸጥ መገደድ፤
- የቤተሰቡን የቤት ቁሳቁሶች ወይም የግል ዕቃዎች ለመሸጥ መገደድ፤
- የቤተሰቡን የቤት ቋሚ ንብረቶች፤ የቤት ቁሳቁሶች ወይም የግል ዕቃዎች በወለድ አገድ

መልክ (በተወሰነ የጊዜ ገደብ ካልመለሰ ውርስ መሆን) ለማስያዝ መገደድ፤
- የቤተሰቡን የምግብ እጥረት/ችግር/ ለመሸፈን ሲባል ብቻ ቤተሰቡ/ የቤተሰቡን አባላት ምርታማ ባልሆነ ተግባር ለማሰማራት መገደድ (ልመና፡ስርቆትና ዝርፊያ፡ ሴተኛ አዳሪነት፡ ወዘተ)

ዓምድ 15: <u>ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ለምን ያህል ወራት የምግብ እጥረት አጋጠመው?</u>

ይህ ዓምድ የሚመለከታቸው ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የምግብ እጥረት አጋጥሞን ነበር ብለው በዓምድ 14 አዎን ለመለሱና ኮድ 1 ለተሞላላቸው ቤተሰቦች ነው። ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ለምን ያህል ወራት የምግብ እጥረት አጋጥሞት እንደነበር በመጠየቅ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ በወራት ብዛት በንዑስ ዓምድ 26-27 መሳፍ ይገበዋል።

<u>ማስታወሻ:-</u> አንድ ቤተሰብ በአንድ ወር ውስጥ የምግብ እጥረት አጋጥሞታል የሚባለው በወር ውስጥ <u>ቢያንስ ለ5 ቀናት</u> የምግብ እጥረት ካጋጠመው ነው።

<u>ምሳሌ:-</u> በገጠር የሚኖር አንድ የተመረጠ ቤተሰብ በ1995 ዓ.ም. የምርት ዘመን ያመረተው ምርት ቤተሰቡን ለ8 ወራት መግቧል እንበል የ1996 ዓ.ም. ምርት እስከሚደርስበት ጊዜ ድረስ የ4 ወር የምግብ እጥረት ቢያጋጥመው "04" በተሰጠው ሳጥኖች ውስጥ ያሞላሉ ማለት ነው። በተጨማሪም በሰኔ ወር ለ10 ቀን፡ በሐምሌ ወር 15 ቀን፡ በሌሎቹ ወራት ምንም እጥረት ባያጋጥመው ይህ ቤተሰብ ላለፉት 12 ወራት ውስጥ በሁለት ወራት የምግብ እጥረት ያጋጠመው በመሆኑ በአምዱ 02 ይሞላለታል።

ዓምድ 16: <u>በአሁኑ ወቅት (ዘንደሮ) ያለው የቤተሰቡ የምግብ ሁኔታ ከአምናው ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?</u>

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ አሁን ያለውን የቤተሰቡን የምግብ ሁኔታ አምና ከነበረው ሁኔታ ጋር በማነፃፀር ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግቦ ተገቢውን ኮድ ደግሞ በንዑስ ዓምድ 28 መጨላት ያስፈልጋል።

አማራጭ መልሶች	ኮድ
በጣም ብሶበታል	=1
በመጠኑ ቀንሷል	=2
ተመሣሣይ ነው	=3
በመጠኑ ጨምሯል	=4
በጣም ጨምሯል	=5

ዓምድ 17: በአሁኑ ወቅት ያለው የቤተሰቡ የልብስ ሁኔታ ባለፉት 12 ወራት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል::

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ በጥናቱ ወቅት ያለውን የቤተሰቡን የልብስ ሁኔታ ባለፉት 12 ወራት ከነበረው ሁኔታ ጋር በማነፃፀር በአሁኑ ወቅት ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግበ ተገቢውን ኮድ ደግሞ በካርድ ክለም 29 ውስጥ መጻፍ ያስፈልጋል::

አማራጭ መልሶች	ኮድ
በጣም ብሶበታል	=1
በመጠኑ ቀንሷል	=2
ተመሣሣይ ነው	=3
በመጠኑ ጨምሯል	=4
በጣም ጨምሯል	=5

ዓምድ 18: በአሁኑ ወቅት ያለው አጠቃላይ የቤተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ከአምናው ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ያለው አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ከአምናው ጋር በማነፃፀር ኑሮው ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከተሠጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግበ ተገቢው ኮድ ደግሞ በንዑስ ዓምድ 30 ውስጥ ይጻፋል::

አማራጭ መልሶች	ኮድ
በጣም ብሰበታል	=1
በመጠኑ ቀንሷል	=2
ተመሣሣይ ነው	=3
በመጠኑ ጨምሯል	=4
በጣም ጨምሯል	=5

ዓምድ 19: በአሁኑ ወቅት ያለው የአካባቢው ሕብረተሰብ አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ከአምናው ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት የአካባቢው ሕብረተሰብ አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታን ከአምናው ጋር በማነፃፀር ምን እንደሚመስል ተጠይቆ የሚሰጠውን መልስ ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ተስማሚውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግቦ ተገቢው ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለም 31 ይሞላል::

አማራጭ መልሶች	ኮድ
በጣም ብሰበታል	=1
በመጠኑ ቀንሷል	=2
ተመሣሣይ ነው	=3
በመጠኑ ጨምሯል	=4
በጣም ጨምሯል	=5
አላውቅም	=6

ዓምድ 20: በዚህ ዓመት ያመረትከው የሰብል ምርት ለምን ያህል ወራት ይበቃሃል?

ቤተሰቡ በዚህ ዓመት ያመረተው ሰብል ለምን ያህል ወራት እንደሚበቃው/እንደበቃው ተጠይቆ የሚሰጠውን መልስ በወራት ብዛት በካርድ ኮለም 32 እና 33 መሙላት ያስፈልጋል:: ቤተሰቡ ሰብል የማያመርት ከሆነ ወይም በዚህ ዓመት ሰብል ያላመረተ እንደሆነ በካርድ ኮለሞቹ "-" ይሞላል::

ዓምድ 21: ቤተሰቡ ያልተጠበቀ ችግር ቢያጋጥመው 100 ብር በአንድ ሣምንት ሊያገኝ ይችላል?

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ያልተጠበቀ ችግር ቢያጋጥመው በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ 100 ብር ማግኘት ይችል ወይም አይችል እንደሆነ በመጠየቅ እችላለሁ ካለ "አዎን" የሚለው በዓምዱ ስር ተመዝግቦ ኮድ 1 በንዑስ ዓምድ 34 ሥር ሲመዘገብ አልችልም ካለ ደግሞ የለም የሚለው በዓምዱ ተመዝግቦ ኮድ 2 በንዑስ ዓምድ 34 ሥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 22: በአምድ 21 "አዎን" ለመለሱ የሚያገኙ ከሆነ በዋንኛነት/በቅድሚያ ከየት ሊያገኙ ይችላሉ?

በዓምድ 21 ቤተሰቡ ያልተጠበቀ ችግር ቢገጠመኝ 100 ብር በአንድ ሣምንት ውስጥ ማግኘት እችላለሁ ብሎ ኮድ 1 ከተሞላለት በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በቅድሚያ/በዋንኛነት ከየት ማግኘት እንደሚችል በመጠየቅ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን መልስ በዓምዱ ስር በተተወው ባዶ ቦታ መፃፍና ተገቢውን ኮድ ደግሞ በካርድ ክለሞች 35 እና 36 መሙላት ይገባል::

አማራጭ መልሶች	ኮዶች
የቤት እንስሳትና ውጤታቸውን በመሸጥ	01
የእርሻ ውጤቶችን በመሸጥ	02
የደን ውጤቶችን በመሸጥ	03
ካለኝ ጥሬ ገንዘብ	04
ከባንክ/ከቁጠባ በማውጣት	05
ከዕቁብ	06
ከዕድር	07
ከባንክ/አበዳሪ ድርጅት/ በመበደር	08
ከዘመድ በመበደር	09
ከዘመድ በስጦታ መልክ	10
ዘመድ ካልሆነ ሰው በመበደር	11
ዘመድ ካልሆነ ሰው በስጦታ ማግኘት	12
የቤት ቋሚ ዕቃዎች በመሸጥ	13
የግል ዕቃዎች በመሸጥ(ጌጣጌጥና የመሳሰሉት)	14
ሌላ (ይገለፅ)	15

ዓምድ 23፡የቤተሰቡ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ምንድን ነው? (በጥሬ ገንዘብና በዓይነት)

በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ወይም ዋና መተዳደሪያው ምን እንደሆነ ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠው መልስ ከዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ተስማሚውን በመምረጥ በዓምዱ ስር በተተው ክፍት ቦታ መዝግቦ ትክክለኛውን ኮድ ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 37 እና 38 መመዝገብ ይገባል።

የቤተሰብ ገቢዎች ዋና ዋና ምንጮች

ኮድ

- ከቤተሰቡ የግብርና ውጤት የተገኘ (እንሰሳትና ውጤታቸውን ይጨምራል)--- 01
- ከቤተሰቡ ድርጅት (ከግብርና ሌላ) የተገኘ---------- 02
- መንግስታዊ ከሆኑ ድርጅቶች በእርዳታ/በስጦታ የተገኘ----------03
- መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በእርዳታ/በስጦታ የተገኘ---------- 04
- ከቤተሰቦች/ግለሰቦች በተቆራጭ/በስጦታ የተገኘ---------- 05
- ከውጭ ተቆራጭ/በስጦታ የተገኘ ---------- 06
- በነፃ የተገኘ /ከሜካ የተሰበሰበ፤ በአደን የተገኘ፤ በነፃ ከተገኙ የደን ውጤቶች ሽያጭ የተገኙ ምግቦችና መጠጦች፤ በልመና የተገኘ ... ወዘተ----- 07
- ከደመወዝ፤ ምንዳ፤ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፤ ውሎ አበል፤ አልዋንሽ፤ ቦነስ፤ ኮሚሽን፤---------- 08
- ከጡረታና ማህበራዊ ዋስትና የተገኘ ---------- 09
- ከተቀጣጭ የወጣ (ከባንክ፤ ከቁጠባ ... ወዘተ ---------- 10
- ከወለድና Royalties ከመሳሰሉት የተገኘ ---------- 11
- ከአክስዮን (ከትርፍ ክፍፍል) የተገኘ ---------- 12
- ከቤት ኪራይ የተገኘ ----------13
- ከቤት ኪራይ ውጭ ከሆኑ ዕቃዎች ኪራይ የተገኘ (የእቃ፤ መጋዘን፤ የእንሰሳት፤ ማሽነሪ----------14
- ከቋሚ የቤትና የግል ዕቃዎች ሽያጭ የተገኘ፤ ---------- 15
- ከሌላ ምንጭ የተገኘ (ከእቁብ፤ ከእድር፤ ለቤተሰቡ ፍጆታ የተበደረው፤ ከቤተሰቡ ፍጆታ አበድሮት ከነበረው የተቀበለው፤ ከኢንሹራንስ፤ ከካሳ፤ ከውርስ፤ ከሎተሪ አሸናፊነት፤ ከሴተኛ አዳሪነት ተግባር... ወዘተ)----------16

ማሳሰቢያ፡-የቤተሰቡ ዋነኛ የገቢ ምንጮች የሚባሉት በዋነኛነት የሚተዳደርባቸው የሥራ ወይም የድርጅት አይነቶች ወይም በዋነኛነት የሚተዳደርባቸውና ገቢ የሚያገኝባቸው መንገዶች ናቸው:: ቤተሰቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የገቢ ምንጮች ቢኖሩት ወይም የተለያዩ የገቢ ምንጭ ያላቸው የቤተሰብ አባላት ቢኖሩት መወሰድ ያለበት በአብዛኛው ቤተሰቡን ለማኖር ያስቻለ የገቢ ምንጭ መሆን ይኖርበታል:: ስለሆነም ዋናው የገቢ ምንጭ የትኛው እንደሆነ በመጠየቅ ተጣርቶ ዋናውን የገቢ ምንጭ መመዝገብ ይኖርበታል::

ዓምድ 24: ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የኑሮ ሁኔታውን የሚያናጋ ችግር/አደጋ አጋጥሞት ነበር?

ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የኑሮ ሁኔታውን የሚያናጋ አደጋ/ችግር ማለትም በመጠይቁ ዓምድ የተዘረዘሩት የችግር/አደጋ አይነቶች ደርሰበት/አጋጥሞት እንደነበር ወይም እንዳልነበረ ለማወቅ እያንዳንዱ የተዘረዘሩት አደጋዎች/ችግሮች እየጠቀሱ በመጠየቅ "አጋጥሞኝ ነበር" ለሚለው አደጋ/ችግር በአደጋው/በችግሩ ትይዩ በንዑስ ዓምድ 39 ውስጥ ኮድ 1 ሲሞላ "አላጋጠመኝም" ካለ ደግሞ በአደጋው/ችግሩ ትይዩ ኮድ 2 በንዑስ ዓምድ 39 ይሞላል::

የአደጋ/ችግር ዓይነቶች ዝርዝር

- ሞት
- የቤተሰብ አባል ህመም
- የቤተሰቡ አባል ከሥራ መፈናቀል/መሰናበት
- የምግብ እጥረት
- የድርቅ አደጋ
- የጎርፍ አደጋ
- ከፍተኛ የሆነ የሰብል መውደም
- የቤት እንስሳት ሞት
- ከፍተኛ የሆነ የዋጋ መርከስ (መውደቅ)
- ሌላ (ይገለፅ)

ምሳሌ:- አንድ ገበሬ የእርሻ ሰብሉን በረዶ ቢመታበት ነገር ግን ቤተሰቡ ይህ ሰብል በበረዶ በመመታቱ ምክንያት ምንም አይነት የኑሮ መናጋት/ችግር ካለጋጠመው "ከፍተኛ የሆነ የሰብል መውደም" በሚለው ትይዩ በዓምድ 24 በንዑስ ዓምድ 39 "የለም" ተብሎ ኮድ 2 ይሞላል:: ነገር ግን የሰብል ውድመቱ ቤተሰቡን በጣም የጎዳው ከሆነ እዎን ተብሎ ኮድ 1 ይመዘገባል:: ስለዚህ የጉዳቱን መጠን ከመልስ ሰጪው በጥልቀት ጠይቆ መረዳት ያስፈልጋል:: ለሌሎችም ችግሮች ተመሳሳይ አጠያየቅ መከተል ያስፈልጋል::

ዓምድ 25: በአምድ 24 "አዎን" ለመለሱ ብቻ ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ለደረሰበት ---አደጋ/ችግር ከታች የተዘረዘሩትን አማራጮች በመፍትሄ ተጠቅሟል?

ይህ ዓምድ የሚመለከታቸው በዓምድ 24 የቤተሰቡን የኑሮ ሁኔታ የሚያናጋ አደጋ/ችግር አጋጥሞኝ ነበር ብለው በንዑስ ዓምድ 39 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ብቻ ነው:: በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ አጋጥሞኝ ነበር ብሎ በዓምድ 24 ኮድ 1 በተሞላለት አደጋ /ችግር ትይዩ ቤተሰቡ አደጋውን/ችግሩን ለመቋቋም ያጣናውን/የሰጠውን መፍትሄ በመጠየቅ በዓምዱ ስር ከተዘረዘሩት የመፍትሄ ዓይነቶች ጋር በማገናዘብና የተዘረዘረው እያንዳንዱ የመፍትሄ አይነት ለቤተሰቡ ችግር ለመፍታት የተጠቀመበት ከሆነ ኮድ 1 በመፍትሄነት ካልተገለገለበት ደግሞ ኮድ 2 በእያንዳንዱ ኮለም ይሞላል::

ዋና ዋና አማራጭ መፍትሄዎች

የምግብ ዕርዳታ
የቤት እንስሳትና ውጤታቸውን በመሸጥ
ሌሎች የእርሻ ውጤቶች በመሸጥ
የቤት ዕቃዎችን በመሸጥ
ካለኝ ጥሬ ገንዘብ
ሌላ ይገለፅ

ዓምድ 26: ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ ቤተሰቡ ----- ችግር /አደጋ ምን ያህል ጊዜ አጋጥማት ነበር?

ቤተሰቡ በዓምድ 24 የተዘረዘሩት አደጋዎች/ችግሮች በእያንዳንዳቸው አንፃር ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንዳጋጠመው/እንደደጋገመው በመጠየቅ የሚሰጠውን መልስ በዓምድ 24 በተዘረዘረው አደጋ/ችግር ትይዩ በንዑስ አምድ 46 እና 47 ይሞላል::

ማሳሰቢያ:- አንድ ችግር/አደጋ ተደጋገመ የሚባለው በአንድ ወቅት ተከስቶ በተለያዩ ዘዴዎች ከተፈታ በኋላ እንደገና በድጋሚ ከተከሰተ ነው::

የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት መጠይቅ

ቅጽ.9 የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ሁኔታ

በዚህ ክፍል መረጃ ሰጪዎች ስለ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ያላቸውን ግንዛቤና የስርጭት ሁኔታ የሚመለከት መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን በተቻለ መጠን መረጃውን ከቤተሰብ ኃላፊ ብቻ መሰብሰብ ያስፈልጋል::

የዚህ ክፍል ጥያቄዎች ልዩ ጥንቃቄ የሚፈልጉ በመሆኑ መረጃ ሰብሳቢው ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት::

ክፍል 1:- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ 1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው::

ክፍል 2:- የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ሁኔታ

ዓምድ 13:- ተራ ቁጥር

ተራ ቁጥር አስቀድሞ ከ01 -03 ተሞልቷል::

ዓምድ 14:- ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ስለመኖሩ ያውቃሉ ?

በዚህ ዓምድ ለመረጃ ሰጪው ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መኖሩን ማወቅ አለማወቁ ተጠይቆ "አዎን" ወይም "የለም" እየተባለ ይመዘገብና በንዑስ ዓምድ 25 ደግሞ ኮድ 1 ወይም ኮድ "2" ይመዘገባል:: መልስ ሰጪው "የለም" አላውቅም ካለ የሚቀጥሉት ጥያቄዎች ስለማይመለክቱት ሌላ ጥያቄ አይጠየቅም::

በዓምድ 14 ኮድ 1 ለመለሱ

ዓምድ 15:- የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ያውቃሉ ?

በዓምድ 14 ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ስለመኖሩ አውቃለሁ ብለው መልስ ለሰጡ ቤተሰቦች በዓምድ 15 ስተዘረዘሩት አማራጮች ወይም መተላለፊያ መንገዶች ተጠይቀው

የሚሰጡትን መልስ "አውቃለሁ" ከሆነ ኮድ 1 "አላውቅም" ከሆነ ኮድ 2 በካርድ ኮለም 26 - 28 በየምክንያቶቹ ይመዘገባል።

<u>የመተላለፊያ መንገዶቹ ዝርዝር</u>

በልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት
በደም
ከእናት ወደ ልጅ

ዓምድ 16:- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በቀበሌም በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ (የታመሙ/በሞት የተለዩ) ሰዎች አሉ ?

መረጃ ሰጪው በሚኖርበት ቀበሌ ውስጥ በኤች.አይ.ቪ ኤድስ የተጠቁ (የታመሙ/በሞት የተለዩ) ሰዎችን የሚያውቁ እንደሆነ ተጠይቆ መልሱ ይመዘገብና በንዑስ ዓምድ 29 ደግሞ ተገቢው ኮድ ይጻፋል። በቀበሌያቸው በበሽታው የታመሙ/የሞቱ ሰዎችን ለመለየት ከዚህ በታች የተገለጹት አማራጮች ቀርበዋል።

አዎን . . . . ኮድ 1
የለም . . . . » 2
አላውቅም. . » 3
መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለሁም. . . ኮድ 4

በዓምድ 16 አዎን ለመለሱ

ዓምድ 17:- እባክዎን ስም ሳይጠቅሱ በቀበሌም ባለፈው 12 ወራት ውስጥ በኤች.አይ.ቪ. (የታመሙ/የሞቱ) ሰዎች ብዛት ምን ያህል እንደሆነ ቢገልፁልን ?

ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ የታመሙ/የሞቱ ሰዎች እንዳሉ ለገለፁ ቤተሰቦች (በዓምድ 16 ኮድ 1 የተሞላላቸው) ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በቀበሌያቸው በኤች.አይ.ቪ ኤድስ የታመሙ/የሞቱ ሰዎችን ብዛት በጾታና በዕድሜ በመከፋፈል እንዲናገሩ በመጠይቅ ብዛታቸውን በዓምዱ መመዝገብ ይኖርበታል።

"ዕድሜያቸው ከ15 በታች፣ ከ15 - 64 እንዲሁም ከ64 ዓመት በላይ" የሆኑና ወንድ የኤች.አይ.ቪ ታማሚዎች የተባሉትን ብዛት በንዑስ ዓምድ 30 እና 31 ሲመዘገብ

ሴት የኤች.አይ.ቪ ታማሚዎች ደግሞ በንዑስ ዓምድ 32 እና 33 ብዛታቸው ይመዘገባል።

ዕድሜያቸው "ከ15 በታች፣ ከ15 - 64 ዓመት እንዲሁም ከ64 ዓመት በላይ" የሆኑና በኤች.አይ.ቪ ኤድስ ሞቱ የተባሉ ወንዶች ብዛታቸው በንዑስ ዓምድ 34 ና 35 ሲመዘገብ በኤች.አይ.ቪ ኤድስ የሞቱ ሴቶች ብዛት ደግሞ በንዑስ ዓምድ 36 እና 37 ይመዘገባል።

ዓምድ 18፡-ከሚከተሉት የኤች.አይ.ቪ. የመከላከያ ዘዴዎች የትኛውን ያውቃሉ?

በዚህ ዓምድ መረጃ ሰጪው የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያ ዘዴዎችን ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ በመጠይቁ ከተሰጡት 3 የመከላከያ ዘዴዎች ጋር በማገናዘብ አዎን እናውቃለን ለሚሉ ኮድ "1" አናውቅም "የለም" ለሚሉ ደግሞ ኮድ 2 ሲሞላ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ደግሞ ኮድ 3 በእያንዳንድ የመከላከያ ዘዴ ሥር ባሉት ካርድ ኮለሞች ተስማሚ ኮድ ይሞላል።

የመከላከያ ዘዴዎች ዝርዝር
በአንድ መወሰን
መታቀብ/ምንም ግንኙነት አለማድረግ
ኮንደም መጠቀም

በዓምድ 18 ኮድ 1 ለተሞላላቸው የሚጠየቅ

ዓምድ 19:- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የኤድስ የመከላከያ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል?

በዓምድ 18 ላይ የተገለፁት የኤድስ መከላከያ ዘዴዎች (በአንድ መወሰን፣ መታቀብ፣ ኮንደም) አውቃለሁ ላሉት ቤተሰቦች የኤድስ መከላከያ ዘዴዎችን ባላፉት 12 ወራት መጠቀም/አለመጠቀማቸው ተጠይቆ ተጠቅሜአለሁ ላሉ አዎን ተብሎ ይመዘገብና በንዑስ ዓምድ 41 ኮድ 1 ሲሞላ አልተጠቀምኩም ላሉ ደግሞ የለም ተብሎ ይመዘገብና በንዑስ ዓምዱ ኮድ 2 ይሞላል። ነገር ግን መልስ ለመስጠት ፍቀደኛ ካልሆኑ ፍቃደኛ አይደሉም ተብሎ ይመዘገብና በንዑስ ዓምዱ ኮድ 3 ይሞላል።

ዓምድ 20፡- የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከያ ዘዴዎችን ከተጠቀሙ አጠቃቀምዎ ምን ይመስላል ?

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት የኤድስ መከላከያ ዘዴዎችን መጠቀማቸውን ለገለፁ መረጃ ሰጪዎች (በዓምድ 19 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) ለእያንዳንዱ ዋና ዋና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከያ ዘዴዎች (በአንድ መወሰን፣ መታቀብና ኮንደም መጠቀም) አንባር የመረጃ ሰጪው አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ሁልጊዜ የሚጠቀም ከሆነ ኮድ 1፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀም ከሆነ ኮድ 2 እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀም ከሆነ ኮድ 3 ለእያንዳንዱ የመከላከያ ዘዴ በንዑስ ዓምድ 42 ይመዘገባል።

የቆጠራ ቦታ ካርታ አጠቃቀም

በከተማ ለቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጭ እና ኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የምንጠቀምባቸዉ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች በ 1996 ዓ.ም በተካሄደዉ የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ወቅት ወቅታዊ የተደረጉ ናቸዉ። ይሁንና ወቅታዊ ሲደረጉ ከፊሎቹ መግለጫቸዉ ከነቆጠራ ቦታ ካርታ ድንበሮቻቸዉ፣ ከፊሎቹ ደግሞ በካርታ መግለጫ (U-5) ብቻ ወቅታዊ እንዲሆኑ ተደርጓል። ስለሆነም እያንዳንዱ መረጃ ሠብሣቢ ይህንን በመገንዘብ የካርታ ማኅለሉን የሚያከናዉነዉ በአብዛኛዉ መግለጫዉን (U-5) በመጠቀም መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል።

በተጨማሪም ለጥናቱ በተመረጠ ቆጠራ ቦታ የሚመደብ መረጃ ሰብሳቢ ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት በተቆጣጣሪው አማካኝነት የተመደበበትን የቆጠራ ቦታ ካርታ እና ስለ ቆጠራ ቦታዉ የሚገልጽ የቆጠራ ቦታ መግለጫ ጽሁፍ ከተረከበ በኋላ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መግለጫዎች መሠረት ስለቆጠራ ቦታዉ ካርታ በዝርዝር ማወቅ ይገባዋል።

1. መረጃ ሰብሳቢው የተመደበበትን የቆጠራ ቦታ በሚገባ ለማወቅ ይችል ዘንድ ለ ገጠር ለሁሉም የ ቆጠራ ቦታዎች፣ለ ከተማ ደግሞ የቆጠራ ቦታዉ በኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ወቅት ያልተሸነሸነ ከሆነ በመጀመሪያ የተሰጠውን የቆጠራ ቦታ ካርታ ማጥናት ይኖርበታል። ለዚህም የተመደበበት የቆጠራ ቦታ ካርታ ይዘት ምን እንደሆነ በሚቀጥሉት ገጾች ውስጥ የተዘረዘሩትን ማጥናት አለበት።

2. መረጃ ሰብሳቢው ከካርታው ጋር የተያያዘውን የካርታ መግለጫ ጽሁፍ በሰሜን፣በምሥራቅ፣በደቡብ እና በምዕራብ አቅጣጫዎች የቆጠራ ቦታውን የወሰን መግለጫ ደጋግሞ በማንበብ በካርታው የሚታዩትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮች መሬት ላይ ካሉት ጋር ማገናዘብ ይኖርበታል። በአብዛኛዉ በከተማ ድንበር አካባቢ የነበሩ የቀድሞ የቆጠራ ቦታዎች ወቅታዊ ሲደረጉ የተሸነሸኑ በመሆናቸዉ እና ሽንሸናዉም በመግለጫ (U-5) አማካኝነት ብቻ የተካሄደ በመሆኑ ለዚህ ጥናት መግለጫዉ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለዉ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

3. በቆጠራ ቦታ ካርታ ላይ ከሚገኙ ዓብይ ነጥቦች ውስጥ አንዱ የቆጠራ ቦታው ድንበር ነው። የድንበሩ ዓላማ መረጃ ሰብሳቢው ከተወሰነለት ክልል

እንዳይወጣ እና በክልሉ ውስጥ ያሉትን ቤተሰቦችና ቤቶች ለመመዝገብ እንዲችል ነው::: መረጃ ሰብሳቢው ይህን በመረዳት በቆጠራ ቦታዉ ካርታ ላይ የተገለጸውን ድንበር ጠንቅቆ በማወቅና በመሬት ላይም ለመለየት መቻል አለበት:: በአንዳንድ የቆጠራ ቦታ ካርታ ላይ የተገለጸው ድንበር ምናልባት በአካባቢው ያሉትን ቋሚ ነገሮች ሳይጠቅስ ሊቀር ይችላል:: ይህን እና ይህን የመሳሰሉ ችግሮች ለማስወገድ መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታውን እየተዘዋወረ በሚያጠናበት ወቅት የቀበሌ ሊቀመንበር ወይም ተወካይ አብሮ መዞርና ዳር ድንበሩን ማሳየትና ማረጋገጥ አለበት::

4. መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታውን ድንበር በአመቺ መንገድ ለማወቅ ይችል ዘንድ ከቆጠራ ቦታ ካርታው ጋር አብሮ ከሚሰጠው የካርታ መግለጫ ላይ በተገለጸው መሠረት ከሰሜን በመነሳት ጉዞውን ይጀምራል:: ይህን ለማድረግ ለመረጃ ሰብሳቢው በካርታው ላይ የሰፈሩትን የሕንጻ፣ የት/ቤት፣ የቤተክርስቲያን፣ የመስጊድ፣ የመንገድና ወዘተ ስሞች፣ የወንዝ ስም ካለ፣ ለምልክትነት የተጻፉ የግለሰቦች ቤት የቆጠራ ቦታውን የሚያዋስኑ ቀበሌ ወረዳ፣ ቆጠራ ቦታ . . . ወዘተ. እየጠየቀና እያገናዘበ ቦታዎቹን ለይቶ ማወቅ አለበት::

አንድ መረጃ ሰብሳቢ በተመደበበት የቆጠራ ክልል በሚዘዋወርበት ወቅት ልዩ ልዩ ችግሮች ሊያጋጥሙት ይችላሉ:: ይኸውም የካርታው ሥራ በሚሠራበት ወቅት ምንም ያልተሸፈነ ቦታ ሳይተው ወይም ቦታዎች ሳይደራረቡ እንዲሠሩ ከፍተኛ ሙከራ ቢደረግም አንዳንድ ጊዜ በቆጠራ ቦታዉ እና በአዋሳኝ የቆጠራ ቦታ መሀከል ያልተሸፈኑ ቦታዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: እንዲሁም በሁለት የቆጠራ ቦታዎች መሀከል ያለ ቦታ በሁለት የቆጠራ ቦታዎች ውስጥ ሊደራረብ ይችላል::

የዚህ ዓይነት ችግር በሁለት የቆጠራ ቦታዎች ድንበር ላይ በሚያጋጥም ወቅት መረጃ ሰብሳቢው ይህን ችግር ለተቆጣጣሪው በማስታወቅ እቦታው ድረስ በመሄድ ድንበሩን ማስተከከል ይኖርባቸዋል:: ይህን ዓይነቱ ሥራ መረጃ ሰብሳቢው የቤተሰብ ምዝገባ ከማድረጉ በፊት መሆን አለበት:: መረጃ ሰብሳቢው በሚሰጠው የቆጠራ ቦታ ካርታ በመጠቀም የቆጠራ ቦታዎችን ድንበር በሚገባ አውቆ ከለየ በኋላ የቤተሰብ ምዝገባ ሊጀምር ይችላል::

ካርታው የጎላ ስህተት ከታየበት እርማት ማድረግ የሚቻለው ከተቆጣጣሪው ጋር በመወያየት ብቻ ነው:: ስለ ቆጠራ ካርታ ይዘት በሚገባ ለመረዳት በሚከተሉት ገጾች ተያይዘው የቀረቡትን ካርታዎችና መግለጫዎች መመልከት ያስፈልጋል::

የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ይዘት፡-

ሀ. የከተማ ቆጠራ ቦታ ካርታዎች ይዘት

1. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት የክልል፣ የዞንና የወረዳ ስም

2. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ከተማ ስም እና ክ.ከተማ/ከፍተኛ/ወረዳ ስም ወይም ቁጥር

3. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ቀበሌ ቁጥር/ስም

4. የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር (ኮድ)

5. የቆጠራ ቦታው ግምታዊ ስፋት

6. በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚገኙ የቤቶችና ቤተሰቦች ብዛት

7. የቆጠራ ቦታው ትክክለኛ ድንበር፡- የድንበሩ ዓላማ ቆጣሪው ከተወሰነለት ክልል እንዳይወጣ እና በክልሉ ውስጥ ያሉትን ቤቶች እና ቤተሰቦች ብቻ ለመመዝገብ እንዲችል ነው።

8. የካርታው ሰሜናዊ አቅጣጫ መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታ ድንበሩን በአመቺ መንገድ ለማወቅ ይችል ዘንድ ከቆጠራ ቦታ ካርታው ጋር አብሮ ከሚሰጠው የካርታ መግለጫ ላይ በተገለጸው መሠረት ከሰሜን በመነሳት ከዚያ ወደ ምሥራቅ ከዚያ ወደ ደቡብ ከዚያ ወደ ሰሜን እየተጓዘ የቆጠራ ቦታውን ዙሪያ ይጨርሳል።

9. በካርታው ውስጥ በስዕላዊ መልክ የተሰጡ ምልክቶች (Legend) በካርታው ውስጥ የሚታዩትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮች ብሎክ/ሕንጻ፣ ወንዝ፣ መንገድ፣ለምልክትነት የተባሉ የግለሰቦች ቤት . . . ወዘተ መረጃ ሰብሳቢው መሬት ላይ ካሉት ጋር ማገናዘብ ይኖርበታል።

10. የካርታው መስፈርት

11. የቆጠራ ቦታውን የሚያዋስኑ የክልል፣የዞን፣የወረዳ፣ ክፍለ ከተማ፣ ከፍተኛ ፣ቀበሌ. . . ወዘተ ስም ሊሆኑ ይችላሉ።

ለ. <u>የገጠር ቆጠራ ቦታ ካርታዎች ይዘት</u>

1. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ ና ገበሬ ማህበር ስም/ቁጥር

2. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት የ ገበሬ ማህበር ሊቀመንበር ስም

3. የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር (ኮድ)

4. በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች ብዛት

5. የቆጠራ ቦታው ግምታዊ ስፋት

6. <u>የቆጠራ ቦታው ትክክለኛ ድንበር፡-</u> የድንበሩ ዓላማ ቆጣሪው ከተወሰነለት ክልል እንዳይወጣ እና በክልሉ ውስጥ ያሉትን ቤቶች እና ቤተሰቦች ብቻ ለመመዘገብ እንዲችል ነው።

7. <u>የካርታው ሰሜናዊ አቅጣጫ</u> መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታ ድንበሩን በአመቺ መንገድ ለማወቅ ይችል ዘንድ ከቆጠራ ቦታ ካርታው ጋር አብሮ ከሚሰጠው የካርታ መግለጫ ላይ በተገለጸው መሠረት ከሰሜን በመነሳት ከዚያ ወደ ምሥራቅ ከዚያ ወደ ደቡብ ከዚያ ወደ ሰሜን እየተጓዘ የቆጠራ ቦታውን ዙሪያ ይጨርሳል።

8. <u>በካርታው ውስጥ በስዕላዊ መልክ የተሰጡ ምልክቶች (Legend)</u> በካርታው ውስጥ የሚታዩትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮች ብሎክ/ሕንጻ፣ መንገድ፣ለምልክትነት የተሳሉ የግለሰቦች ቤት . . . ወዘተ መረጃ ሰብሳቢው መሬት ላይ ካሉት ጋር ማገናዘብ ይኖርበታል።


9. የካርታው መስፈርት

10. የቆጠራ ቦታውን የሚያዋስኑ የክልል፣የዞን፣የወረዳ፣ ክፍለ ከተማ፣ ከፍተኛ ፣ቀበሌ. . . ወዘተ ስም ሊሆኑ ይችላሉ።

በተጨማሪም እያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ የድንበር መግለጫ ዕሁፍ አለው። ይህ ዕሁፍ ካርታውን በበለጠ ስለሚያብራራ መረጃ ሰብሳቢው ከካርታው ጋር በአንድነት መረዳት አለበት። ለአብነት ያህል አንድ የከተማ ካርታ ከነመግለጫው ከዚህ ቀጥሎ ተሰጥቷል።

ክልል	አሮሚያ
ዞን	ምሥ. ሸዋ
ወረዳ	ቦሰት
ከተማ	ደኒ

የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር	01-01
የቤቶች ብዛት	206
የቤተሰብ ሀላፊ ብዛት	191
ግምታዊ ስፋት	0·26 ኪ.ሜ^2



መፍቻ	
ሶልጢ ዋደ ቤት	3
የሀይሉ ቱቱ ቤት	2
የቦራ ዑስማን ቤት	6
የዑመር ሁሴን "	7
የቃደ መሀመድ ቤት	8
የቀበሌ ሻደ ቤት	9
የታየች ቸሬ ቤት	10
ደወታ ሮሮ	13
ከሣሁን አዘነ	11

መስፈርት 1: 5,000

መግለጫ

- የገበሬ ማህበር ወሰን
- የቆጠራ ቦታ ወሰን
- የዘወትር መኪና መንገድ
- የበጋ መኪና መንገድ
- የእግር መንገድ
- ትቤት መስሪድ
- ቆርቆሮ ሣር ቤቶች
- የገበያ ቦታ
- የእስላም መቃብር
- 01-01 የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር

ስም	ደረጃ	ፊርማ	ቀን
ቦና ገጸ	ሬ·ካርታ ሠራተኛ		24/05/96
ገጸ ኢደ	ተቆጣጣሪ		24/05/96

CENTRAL STATISTICAL AUTHORITY
FORM FOR DESCRIBING URBAN ENUMERATION AREA

JOB ID	1	2	3

FORM U-5

PART 1: AREA IDENTIFICATION

1	2	3	4	5	6	7
KILIL	ZONE	WEREDA	URBAN CENTER	KEFTEGNA/KIF KETEMA	KEBELE	E.A. CODE
ሃዲያ	ሜኦ/ደቡ	ቦሰጋ	ሻሸ	—	ዐ1	ዐ1-ዐ1

PART 2: E.A. DESCRIPTION

DESCRIBE THE IDENTIFIABLE BOUNDARIES FROM NORTH AND COMPLETE IN CLOCKWISE DIRECTION

ሰሜን:- ቃሉ የቆመሩ ቦታ የሸፈርነ ዋቄን ቤተ መዛ መንገድ: የኋችኛዉ ፖክነ ቤተ መዛ መስጅ ኻዲርነ በመሃላ ኻቆመናቷዉን መዛ ሰሜን በመቄሊን ትንሽ ኻንቄዛ መዛ ቆሞቤ የማመስዛው የበነመነ መንገዳን በመቄሊን ኻቆመናቷዉን መዛ ምሥራቅ ኻዲርነ በመሃላ የጋራ ካ ኻንን ቤተ መዛ መንገድ: የሲሰመቱ ጉንን ቤተ መዛ መስጅ በመተመ በሊቄመ- ካዛኔ ገበያ ጋር ኻየተዋሰን የቆጠነ ሀቄን ቤተ መዛ መስጅ: የኻመቱ ሮሮን ቤተ መዛ መንገድ በመተመ ካንጠነ ገበያ መሰን ሲዓርነ ያቆማሳል::

ምሥራቅ:- የሰሜን መሰን ካቆመነበት በመሃላ ኻዛኔ ገበያ በመገንጠል የቆጠነ ሀቄን ቤተ መዛ መስጅ: የኻመቱ ሮሮን ቤተ መዛ መንገድ: በመተመ ኻቆመናቷዉን መዛ ኻሰጉ ኻዲርነ ካንጠነ ገበያ ጋር ኻየተዋሰን ሄዛመ- የካሃሀ ኻዘንተ ቤተ መዛ መስጅ: የታቦቷ ቸሀንጭ ቤተ መዛ መስጅ ኻዲርነ መዛ ፖጠነ የማመስዛው የዘመር መንገዳ ሲዓርነ የምሥራቅ መስን ቀቆማሳል::

ኻሰጉ:- የምሥራቅ መሰን ካቆመነበት በመሃላ ካንጠነ ገበያ ተገንጥሎመ የታቦቷ ቸሀን ቤተ መዛ መስጅ በመተመ መዛ ቦታ የማሄዛው የመሃሉ መንገዳ ተሰንተመ በሊቄመ በመጋዝ የቆመነ ኻዲ ቤትን መዛ መስጅ: የቄሳ መሠመቱን ቤተ መዛ መሰጅ ተተመ የሰሜ ገበያ ኻንበር ሰሄርነ የኻሰጉ መሰን ያቆማሳል::

ምዕራብ:- መዛ ቦቄ ካማሄዛው የዘመር መንገድ በመገንጠል ኻቆመናቷዉን መዛ ሰሜን ሮ- ቃሉ ኻዲርነ ኻቆመነ ኻዲ ቤትን መዛ መስጅ: የቄሳ ማሠመቱን ቤተ መዛ መሰጅ: የሸማሪ ሊሆን ቤተ መዛ መስጅ የሰሩ ቄሰማን ቤተ መዛ መስጅ: የጋሰን ቦታ መስጅ: የኻዛ ሮጆን ቤተ መሰጅ: የሰሪሶ ቄዛን ቤተ መስጅ: የቃንኬ ከሰንን ቤተ መዛ መሰጅ: የሰሪሶ ዋኻን ቤተ መስጅ ተተመ ኻቆመናቷዉን መዛ ሰሜን ካንሪሰ የዛሰር መንገዳን ታሰንተመ ኻንቨ ካንሸሄዛ የኻሰን ካሰሪን ቤተ መዛ መስጅ በመተመ መንገዱን ኻቄመ መሰጅ-ከሰዓሊት ካሰቦ ገበያ ካንጠነ ቄሰማን ቄሰማን ኻቄመ ካቆመናቷዉን መዛ ሰሜን ሮ- ቃሉ ኻዲርነ ካዛኔ ገበያ ጋር ኻየተዋሰን የሮጎ ዋቄን ቤተ መስጅ: የኻመቱ ተሰን ቤተ መዛ መስጅ ኻዲርነ መዛ ካተሃሳሰን የሰሜን ጀመሪ ሲዓርነ ያጠቃልል::

NB:- USE ADDITIONAL FORM IF NEEDED
ATTACH THIS FORM TO E.A. MAP

NAME OF G.A. Bona Geda SIGNATURE Bnak DATE 24/05/98
NAME OF SUPERVISOR Geda Edo SIGNATURE DATE 24/05/98

ዕዝል 1

የሥራ ዓይነት ምደባ መለያ ኮድ ዝርዝር

መግቢያ

የሥራ ዓይነት ምደባ የሰው ኃይልን በሚመለከት ልዩ ልዩ መረጃዎችን በማስገኘት ፕላን ለማውጣት ይረዳል። የሰው ኃይልን ለመገመት፣ የትምህርትና የማሠልጠኛ ፕሮግራሞችን ለማውጣት፣ ለአስተዳደር አገልግሎት፣...ወዘተ. በአጠቃላይ ከፍተኛ ጥቅም ያለው መረጃን ያስገኛል።

የአንድ ግለሰብ የሥራ ዓይነት የሚመደበው ግለሰቡ በድርጅቱ ውስጥ በሚሠራው በአንድ በተወሰነ ወይም በዋነኛ ሥራው ነው። ለምሳሌ በአንድ ሆስፒታል በታይፒስትነት የምትሠራ ግለሰብ ሥራሽ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ በዓምድ 31 ታይፒስት ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን። ይህ የሥራ ዓይነት የጽሕፈትና ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ሠራተኞች ምደባ ውስጥ ስለሆነ ትክክለኛውን ኮድ ከተሰጠው የሥራ ዓይነት መለያ ኮድ ዝርዝር ከገጽ 5 ከዋና ክፍል 4 ከንዑስ ክፍል 41 በመምረጥ በካርድ ኮለሞቹ ኮድ 411 ይሞላል።

የግብርና ዕውቀት ያለው በግል ለሌላ በግብርና ለተሠማራ ግለሰብ ሥራህ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ የግብርና ዕውቀት ያለው የግል ገበሬ ተብሎ ተሞልቶ ከሆነ ትክክለኛውን ኮድ ከተሰጠው የኮድ ዝርዝር ከገጽ 7 ከዋና ክፍል 62 በመምረጥ ኮድ 621 በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል።

በዓምድ 31 የዋነኛ ሥራዎ ዓይነት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ፣ ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት በሙሉ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው። ነገር ግን ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ ሆኖ ዓምዱ ያልተሞላላቸው ግለሰቦች ቢገኙ መረጃው መሞላት ሲገባው ያልተሞላ መሆኑን ለማመልከት ኮድ 999 በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል።

ዋና ክፍል 1-
ሕግ አውጭዎች፣ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ሥራ አስኪያጆች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች አብዛኛዎቹ ተግባራት ፖሊሲን መቅረፅና መወሰን እንዲሁም ሕጎችንና የሕዝብ መተዳደሪያዎች፣ አፈፃፀማቸውን መከታተል፣ መንግስትን መወከልና እንደ መንግስት መሥራት፣ የኢንተርፕራይዞችንና የመምሪያዎችን ተግባራት ማቀድ፣ መምራትና ማስተባበርን ያጠቃልላሉ። ዋና ክፍሉም የማዕከላዊ መንግሥት፣ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ ሕግና ደንብ አውጭዎችና አስፈጻሚዎችን፣ የድርጅቶችን አመራር አካላትና የዋና ክፍል የክፍልና የአገልግሎት ኃላፊዎች ያጠቃልላል። በዚህ ዋና ክፍል ውስጥ የተለያዩ የትምህርትና የሙያ ደረጃ ያላቸው አብረው ይገኛሉ።

11. ሕግ አውጭዎችና ከፍተኛ ባለሥልጣናት

111. ሕግ አውጭዎች
/የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ ምክር ቤት ሊቀመናብርት፣ የፓርላማ ወይም ሸንጎ አባላት፣ ከሕግ ማውጣትና ማስፈጸም ጋር ግንኙነት ያላቸው ልዩ ፀሐፊዎች/

112. የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት
/የብሔራዊ፣ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ ምክር ቤት አባላት፣ አምባሳደሮች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ሬጅስትራሮች/

113. የቀበሌ አመራር አካላትና የጎሣ መሪዎች
/የከተማ የቀበሌና ክፍተኞች፣ የገጠር ገ/ማህበራት አመራሮችና የጎሣ መሪዎች/

114. የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች፣ የአሠሪዎች፣ የሠራተኞች፣ የሙያና የራሳቸው የሆነ የኢኮኖሚ ፍላጎት ያላቸው ማሕበራት፣ የሰብዓዊና መሰል ድርጅቶች ከፍተኛ ባለስልጣናች /ፕሬዝዳንቶች፣ መሪዎችና የአመራሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት/

12. ሥራ አስኪያጆችና መምሪያ ኃላፊዎች

121. መንግሥታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ትላልቅ የምርት ማምረቻና አገልግሎት መስጫ ምሳሌ:- የትራንስፖርት፣ የኮንስትራክሽን፣ የትምህርት፣ የጤና ...ወዘተ አገልግሎት መስጫ) ድርጅቶችና ተቋማት፣ ዋና ሥራ አስኪያጆች (ዋና ኃላፊዎች)፣ ሥራ አስኪያጆችና የመምሪያ ኃላፊዎች፣ ዋና ፀሐፊዎች፣ የክሊጆች፣ የተቋማትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተሮች እዚህ ይጠቃለላሉ።

13. የሥራ ኃላፊዎች፣ የዋና ክፍል፣ የክፍልና የአገልግሎት ኃላፊዎች

131. የሥራ ኃላፊዎች፣ የዋና ክፍል፣ የክፍልና፣ የአገልግሎት ኃላፊዎች፣ (መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባለሆኑ መለስተኛ ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች፣ በትላልቅና በመለስተኛ ድርጅቶች የዋና ክፍል፣ የክፍልና የአገልግሎት ኃላፊዎች የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ዳይሬክተሮች) ኮንትራክተሮች

132. የአነስተኛ የግል የጅምላና የችርቻሮ ንግድ፣ የምግብ ቤቶችና ሆቴሎች ባለቤቶችና የሥራ ኃላፊዎች፣ እንዲሁም ሌሎች በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የአነስተኛ የግል የንግድና አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ኃላፊዎች በዚህ የሚጠቃለሉ ሲሆን፣ እነዚህ ባለሙያዎች በአብዛኛው የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ የማቀድ፣ የማስተባበርና የመምራት ተግባርን የሚያከናውኑ ናቸው።

ዋና ክፍል 2

ፕሮፌሽናሎች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች ተግባራቸው፣ በፊዚካል፣ በሕይወት፣ በማህበራዊ ሳይንስና በሰብዓዊ ትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ የዩኒቨርስቲ ዲግሪ ወይም ተመሣሣይ የሆነ የትምህርት ደረጃ የሚጠይቁ የስራ ዓይነቶች ናቸው። በዋና ክፍሉ የሚካተቱ ተግባሮችም፣ ያለውን የዕውቀት ክምችት ማዳበርና ማሳደግ፣ ሳይንሳዊ ዕንስሃሳቦችንና መላምቶችን በመጠቀም ምርምሮችን ማካሄድ፣የምርምር ውጤት የሆኑትን ግኝቶች በሥራ ላይ የማዋልና የማስተማር፣ሌሎች ሙያን የሚጠይቁ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስጠት ናቸው።

21. የፊዚካል ሳይንስ፣ የማቲማቲክስ፣ የምሕንድስና ሳይንስ ፕሮፌሽናሎች

211. ፊዚሲስቶችና የስነክዋክብት ተመራማሪዎች፣ ኬሚስቶች፣ ሜትሮሎጂስቶች፣ ጂኦሎጂስቶች፣ ጂኦፊዚስቶችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች

212. ማቲማቲሽያኖች፣ ስታቲስቲሽያኖችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች የመድህን ዋስትና ተንታኞችን፣ አክቾዋሊስትስ፣ ዲሞግራፊሮችን ያጠቃልላል

213. የኮምፒዩተር ፕሮግራመሮችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች፣ ኮምፒውተር ሲስተም ድዛይነሮችንና አናሊስቶችን፣ የኮምፒውተር ሲስተም ኢንጂነሮችንና የዳታ ቤዝ አድሚንስትሬተሮችን ያጠቃልላል

214. አርክቴክቶች፣ ኢንጅነሮችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች የሲቪል፣ የኤሌክትሪክ፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ ሜካኒካል፣ ኬሚካል፣ የማዕድን ሥራ መሐንዲሶችና የቅየሳና የካርታ ሥራ ፕሮፌሽናሎች

22. የሕይወት ሳይንስና የጤና ፕሮፌሽናሎች

221. አግሮኖሚስቶች፣ ባዮለጂስቶች፣ ፋርማኮሎጂስቶችና የመሳሰሉት የደንና የአፈር ተመራማሪዎችን፣ ቦታኒስቶችን፣ ኢክሎጂስቶችን፣ ዙኦሎጂስቶችን፣ ፓቶሊጂስቶችን፣ ባዮኬሚስቶችንና ባዮፊዚስቶችን፣ አናቶሚስቶችንና መሰል ባለሙያዎችን ያጠቃልላል።

222. የሕክምና ዶክተሮች፣ ዴንቲስቶች፣ ፋርማሲስቶች፣ የእንስሳ ሕክምና ዶክተሮችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች (ነርሶችና ድሬሰሮች በዚህ አይጠቃለሉም)

223. የጤና መከንናች፣ ስፔሻላይዝድ ያደረጉ ነርሶችና አዋላጅ ፕሮፌሽናሎች (የልምድ አዋላጆችን አይጨምርም)

23. የማስተማር ፕሮፌሽናሎች

231. የኮሌጆች፣ ዩኒቨርስቲዎችና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራን

232. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን

233. ኢንስፔክተሮች፣ የትምህርት ካሪኩለም አዘጋጆችና የመሳሰሉት (የልዩ ትምህርት፡ የዓይነ ስውራን፣ መስማት የተሳናቸው ...ወዘተ ካሪኩለም አዘጋጆች እዚህ ይጠቃለላሉ)

24. ሌሎች ፕሮፌሽናሎች

241. አካውንታንቶች፣ አዲተሮችና የመሳሰሉት ፕሮፌሽናሎች

242. ዳኞች፣ ጠበቆችና የመሳሰሉት የወረዳ ዐቃቤ ሕግ

243. የቤተመጻሕፍት፣ የሙዚየምና የመሳሰሉት ሥራ ፕሮፌሽናሎች

244. ኢኮኖሚስቶች፣ ሶሾሎጂስቶች፣ ሂስቶሪያኖች፣ ሳይኮሎጂስቶች የሶሻል ወርክና የመሳሰሉት የሶሻል ሳይንስ ፕሮፌሽናሎች

245. የሙዚቃ የትያትር የፊልም ሥራ ፕሮፌሽናሎች፣ የስዕልና የቅርፃ ቅርፅ ሥራ፣ የጋዜጠኝነትና የፀሐፊነት ፕሮፌሽናሎች፣ ደራስያንና የመሳሰሉት

246. የሐይማኖት ፕሮፌሽናሎች/ጳጳሶች፣ ኢማሞች ...ወዘተ/

ዋና ክፍል 3
ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች ቴክኒካዊ ዕውቀትና የሥራ ልምድ የሚጠይቁና በአብዛኛው ከ12ኛ ክፍል በላይ በሆኑ ተቋሞች፣ ኮሌጆች፣ ...ወዘተ የሚሰጥ የትምህርት ደረጃ ወይም ተመሳሳይ የሆነ ደረጃ የሚጠይቁ ናቸው። በዋና ክፍሉ የሚካተቱት አብዛኞቹ ተግባራቶች ከፊዚካል ሳይንስ፣ ከተፈጥሮ ሳይንስና ከሶሻል ሳይንስ ጋር የተያያዙ ቴክኒካዊ ሥራዎችን ማከናወንና የማስተማር ናቸው።

31. የምሕንድስናና የፊዚካል ሳይንስ ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

311. የምሕንድስናና የፊዚካል ሳይንስ ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች (የኬሚካል፣ የሲቪል፣ የኤሌክትሪካል፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የሜካኒካል፣ የማዕድን ሥራ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎችና ቴክኒሽያኖች ቀያሾች፣ የንድፍ ሥራ ባለሙያዎች፣ የሕንፃ ኢንስፔክተሮች የካርታ ሠራተኞች፣ የኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ ቴክኒሽያኖችና የመሳሰሉት)

312. የኮምፒዩተር ኦፕሬተሮች፣ ረዳት ፕሮግራመሮችና የመሳሰሉት

313. የፎቶግራፍ፣ የድምፅ፣ የምስል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የሕክምና መሣሪያዎች ኦፕሬተሮችና የመሳሰሉት ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

314. የአውሮፕላን የአየር መቆጣጠሪያና የመርከብ ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች፣ ፓይለቶች፣ የመርከብ ነጂዎች፣ ... ወዘተ

315. የስራ ደህንነትና የስራ ጥራት ኢንስፔክተሮች፣ ለምሳሌ፣ የሕንፃና የእሳት አደጋ መከላከያ ኢንስፔክተሮች፣ የአካባቢ ጤንነት ኢንስፔክተሮች (ሳኒተሪን አይጨምርም) የምርት ጥራት ኢንስፔክተሮችና የመኪና ደህንነት ኢንስፔክተሮች

32. የሕይወት ሳይንስና የጤና ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

321. የግብርና፣ የአፈር፣ የደን፣ የፊርማኮሎጂ፣ የባዮኬሚስትሪ፣ የባዮሎጂ፣ የደምና የመሳሰሉት ቴክኒሽያኖችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች (የግብርና አማካሪዎችና የግብርና የሠርቶ ማሳያ ባለሙያዎች እዚህ ይጠቃለላሉ።)

322. ነርሶች፣ የጤና ረዳቶች፣ ድራስሮች፣ ሳኒተሪያኖች፣ የፊዚዮቴራፒ ረዳቶች፣ የጥርስ ሕክምና ረዳቶች፣ የመነፅር ሥራ ረዳቶች፣ የፋርማሲ ረዳቶች፣ የፋርማሲስት ረዳቶች፣ የነርስ ረዳቶች፣ ሶሻል ዎርከሮችና የመሳሰሉት የከብት ሕክምና ረዳቶችና ቴክኒሽያኖች

323. የልምድ አዋላጆችና የባህል ሕክምና አዋቂዎች /በእምነት ላይ በመመርኮዝ ሕመሞችን የሚያድኑ፣ ዘመናዊ ሕክምና ሳይጠቀሙ የተለያዩ ቅጠላ ቅጠልና ሥራሥሮችን በመጠቀም ሕመሞችን የሚያክሙና በእምነት ላይ በመመርኮዝ የአእምሮና የአካል ችግሮችን የሚያክሙ /ቃልቻ፣ ጠንቋይና የመሳሰሉትን አያጠቃልልም/

33. የማስተማር መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

331. የአንደኛና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና የሕፃናት ማሳደጊያዎች መምህራን (የተመሳሳይ ደረጃ ት/ቤቶች ዓይነ ስውራን፣ ...ወዘተ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች)

332. የቁስ ት/ቤቶችና የቁርዓን ት/ቤቶች መምህራን

333. የመኪና መንዳት፣ የታይፕ ትምህርት፣ የመሳሰሉት መምህራን (የበረራ መምህራን እዚህ ይጠቃለላሉ።)

34. ሌሎች መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች

341. ደላሎች/የውጭ ምንዛሪ፣ የዋስትና፣ የክምችትና ሼር፣ የኢንሹራንስ ወኪሎች፣ የጉዞ አማካሪዎችና አቀነባባሪዎች፣ የሪል ኤስቴት፣ ግዢ፣ ሽያጭ፣ ኪራይ አቀነባባሪዎች (አስማሚዎች)፣ የቴክኒክ ዕቃዎች (መሣሪያዎች) ሽያጭ ተወካዮች፣ ኢንተርፕራይዞችንና ድርጅቶች በመወከል ዕቃና አገልግሎት ገዢዎች፣ በኢንሹራንስ የሚሸፈኑ የዕቃዎችና ንብረቶች ኪሳራ ገማቾች፣ አጫራቾች፣ በሌላ ቦታ ያልተገለፀ የፋይናንስና ሽያጭ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች።

342. የንግድ ኤጀንቶችና ደላላዎች፣/ገዥና ሻጭ አገናኞች፣ ሽያጭና ግዢ አደራዳሪዎች/አስማሚዎች/ ሥራና ሠራተኛ አገናኞችና አዋዋዮች፣ ከጉምሩክ ጋር በመገናኘት ዕቃዎች ተገቢውን ፎርማሊቲ አሟልተው እንዲወጡ የማድረግ እንዲሁም የላኪነት/አስመጪነትና የመድህን ፈቃዶች መኖራቸው አረጋጋጮች (የመርከብ ላይ ደላሎች፣ያልተጠቀሱ የንግድና የዕቃ ደላሎች፣ የፎርማሊቲ አጣሪ ተወካዮች እዚህ ይጠቃለላሉ።)

343. የአስተዳደርና የፍርድ ቤት ፀሐፊዎች፣ የሚሣብ መዝገብ ያገሮች፣ የስታቲስቲክስ ማቲማቲክስና ተመሳሳይ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች፣ ኤክሲኪዩቲቭ ሴክሬታሪዎች፣ የማህበራዊ ጉዳይ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎችና የመሳሰሉት፣ እና በሌሎች ቦታ ያልተጠቀሱ የአስተዳደር መለስተኛ ኘሮፌሽናሎች፣

344. የጉምሩክና የብሔራዊ ድንበር ተቆጣጣሪ ሠራተኞች፣ የቀረጥ ሥራ ሠራተኞች፣ የንግድ ፈቃድና የፓስፖርት ሠራተኞችና የመሳሰሉት ለምሳሌ፣ መለስተኛ ኢንስፔክተሮች፣ የዋጋና standard የመለኪያ ትክክለኛነት አጣሪ ኢንስፔክተሮች፣

345. ዘፋኞች፣ የመድረክ ተዋናዮችና ዲክሬተሮች፣ የንግድ/የፋሽን ዲዛይነሮች አስተዋዋቂዎች የሬዲዮና የቴሌቪዥን አንባቢዎች፣ ስፖርተኞች የማስታወቂያና የፅሁፍ ሥራ የመሳሰሉት

346. የኃይማኖት መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች /ቄሶች፣ ሼኮች፣ ዲያቆናት ወንጌላውያን፣ መኳሳት፣ ...

ዋና ክፍል 4

የጽህፈትና ተመሣሣይ ሠራተኞች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች ዋና ተግባራቶች የመረጃ ማደራጀት መመዝገብ፣የገቢና ወጪ ደብዳቤዎችን ብዛት ማስላት መለየት ሲሆን ዕውቀትና ልምድን የሚጠይቁ ናቸው። ዋንኞቹ ሥራዎችም የጽህፈት፣ የታይፒስትነት፣ የመረጃ መመዝገብና የማስላት ከደንበኞች ጋር በአብዛኛው ገንዘብ ነክና ቀጠሮ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ከማስተናገድ ጋር የተያያዙ የሥራ ዓይነቶች ናቸው። በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ

ዓይነቶች በአብዛኛው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሙያ ማሰልጠኛ ተቋም የሙያ ሥልጠና ወይንም ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት ደረጃ ባላቸው የሚከናወኑ ናቸው።

41. የቢሮ የጽህፈት ሠራተኞች

411. ታይፒስቶች፣ በኮምፒዩተር መረጃ ፀሐፊዎችና የመሳሰሉት

412. የሂሣብ መዝገብ ያገሮች፣ የሂሣብ ፀሐፊዎች፣ የስታቲስቲክስና የፋይናንስ ፀሐፊዎችና ለምሳሌ፡- የስታትስቲክስ መረጃ ሰብሳቢዎች፣

413. የዕቃዎች ክምችትና የምርት ፀሐፊዎች፣ የአየር የየብስና የባቡር ትራንስፖርት ፀሐፊዎች የመንገድ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎችና የመሳሰሉት

414. የቤተ መጻሕፍት፣ የፖስታ፣ የፋይል ሥራ ፀሐፊዎች፣ ማመልከቻ ፀሐፊዎችና ሌሎች የቢሮ ጽህፈት ሠራተኞች

42. ደንበኞችን የማስተናገድ የጽህፈት ሥራ ሠራተኞች

421. ገንዘብ ተቀባዮችና ክፋዮች፣ ትኬት ቆራጮች (ከትራንስፖርት የተለየ ነው)፣ የፖስታ ቤት አስተናጋጆች፣ ገንዘብ ሰብሳቢዎች፣ ቆጣሪ አንባቢዎችና የመሳሰሉት

422. እንግዳ ተቀባዮች (የሆቴል፣ የሕክምናና የመሳሰሉት)፣ ቴሌፎን ኦፕሬተሮች ቲኬት ቆራጮች እና የመሳሰሉት

ዋና ክፍል 5

የአገልግሎት የሱቅና የገበያ ሽያጭ ሠራተኞች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ የሥራ ዓይነቶች አብዛኛዎቹ ተግባራቶች ለግለሰቦች አገልግሎት የመስጠትን፣ የመከላከል አገልግሎት የመስጠትን፣ በሱቅና በገበያ ዕቃ የመሸጥ እውቀትን የሚጠይቁ ናቸው። ዋና ክፍሉ በተለይም ከገዛ፣ ከሆቴል፣ ክበና ቤት አገልግሎቶች፣ ከግለሰብ እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ ከግለሰብና ከንብረት ጥበቃ አገልግሎቶች፣ የደንብ ስርዓት ማስከበር አገልግሎቶችና በሱቅና በገበያ የዕቃ ሽያጭ አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ አገልግሎት ሰጭዎችን ያጠቃልላል።

51. ለግለሰብ አገልግሎት ሰጭዎችና የአደጋ/የወንጀል መከላከያ አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች

511. የጉዞ አስተናጋጆችና የመሳሰሉት (የአውሮፕላን፣ የባቡርና የመሳሰሉት አስተናጋጆች፣ አስጎብኝዎችና የመሳሰሉት)

512. የጠላ ቤት፣ የአረቄ ቤት፣የጠጅ ቤት፣ ሌሎች መጠጥ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ሻይ ቤቶች፣ ሬስቶራንቶች፣ ሆቴሎችና የመሳሰሉት አገልግሎት ሠራተኞችና ምግብ አብሳዮች (የጠላ ቤት፣አረቄ ቤቶች የቡና ቤት አስተናጋጆች፣ ወጥ ቤቶች፣ ባፊስታዎችና የመሳሰሉት)

513. ፀጉር ቆራጮች የውበት ሳሎን ሠራተኞች በሕፃናት ማሳደጊያዎች ተንከባካቢዎችና ሌሎች ለግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎችና የእነዚህ ሠራተኞች ተቆጣጣሪዎች

514. ፖሊሶች፣ የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች፣ የወንጀል ምርመራ የደህንነት ሠራተኞችና የመሳሰሉት

52. የሱቅና የጉልት ሽያጭ ሠራተኞችና ሞዴሎች

521. የፋሽንና የሥነ ጥበብ ሞዴሎች

522. የሱቅና የኪዮስክ አሻሻጮችና ቤንዚን ቀጂዎች (የጅምላና የችርቻሮ ንግድ በሚከሄድባቸው ሱቆች ውስጥ ዕቃ የሚሸጡ፣ የሚደረድሩና የሚያሻሽጡ)

523. በጉሊት፣ ሜዳ ላይ ባለ ገበያ እንዲሁም በመንገድ ላይ /ተቀምጠው/ ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ የሚሸጡ፣ የማገዶ እንጨት ነጋዴዎች

ዋና ክፍል 6

የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎችና ዓሣ አስጋሪዎች

በዚህ ክፍል የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው (ማለትም:- የማረስ፣ የመዝራት፣ የማረም፣ የመሰብሰብና የመሳሰሉት ተግባራት የሚከናወኑበትን ወቅትና ሁኔታ የሚያውቁ) አራሾች፣ የከብት ማርባት ዕውቀት ያላቸው ከብት አርቢዎች፣ የዓሣ ማጥመድ ሙያ ያላቸው ዓሣ አጥማጆች በዚህ ክፍል ይጠቃለላሉ። በተጨማሪም በዚህ ክፍል ለንግድ ተግባር የሚያገለግሉ የሰብል፣ የከብት፣ የጥጥ፣ የሸንኮራ፣ የትምባሆ፣ ...ወዘተ ምርቶችን የሚያመርቱ በሥራው ላይ ተገቢው ዕውቀት ያላቸው ሠራተኞችን ያጠቃልላል። በዚህ ክፍል የሚመደቡ ሠራተኞች የተለያዩ የዕውቀት ደረጃ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

61. ለንግድ በተቋቋሙ እርሻዎችና ድርጅቶች የሚሠሩ የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎች:-

611. የሰብል፣ ጥጥ፣ ሸንኮራ፣ ሻይ፣ ወይንና የመሳሰሉትን ለንግድ የሚያመርቱ ዕውቀቱ ያላቸው ገበሬዎች፣

612. የከብት፣ የዶሮና የመሳሰሉትን ለንግድ የሚያመርቱ ዕዉቀቱ ያላቸው ገበሬዎች

613. በደንና በከሰል ሥራ የተሠማሩ ዕውቀት ያላቸው ሠራተኞች

614. በዓሣ ማስገር በአደንና በመሳሰሉት የተሠማሩ ዕውቀቱ ያላቸው ሠራተኞች

62. በግልና በቤተሰብ እርሻ የተሠማሩ የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎችና ዓሣ አስጋሪዎች:-

621. በግልና በቤተሰብ እርሻ የተሰማሩ የግብርና ሥራ ዕውቀት ያላቸው ገበሬዎች፣ ከብት አርቢዎችና ዓሣ አስጋሪዎች (የማሳ አዘገጃጀት፣ አስተራረስ፣ የሚዘራበትን ሠዓትና ለግብርና አስፈላጊ የሆነውን ዕውቀት ከወላጅ ወይም ከልምድ የቀሰሙና በሥራው የተሠማሩ ገበሬዎች፣ የከብት እርባታ እውቀት ያላቸው ከብት አርቢዎች የዓሣ ማጥመድ ሙያ ያላቸው ዓሣ አጥማጆች)

ዋና ክፍል 7

የዕደጥበብና ተመሳሳይ ሠራተኞች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡት ሠራተኞች የዕደ ጥበብ ሙያ ያላቸውና ለዚህ ተግባር በጥቅም ላይ በሚውሉ መሣሪያዎች የመጠቀም ችሎታ ያላቸው የዕደ ጥበብ ምርቱን ለማምረት የሚያስፈልጉ ሥራዎችን ዓይነት በትክክል የሚረዱና የምርቱንም ጥቅም የተረዱ ሠራተኞች ናቸው። በዚህ ክፍል የሚመደቡት ሠራተኞች በማዕድን ማውጣት፣ የሕንፃ ሥራ ፣የተለያዩ የዕደ ጥበብ ውጤቶችን በማምረት ተግባር ላይ የተሠማሩ ናቸው።

71. የማዕድን አውጭዎችና የሕንፃ ሥራ ሠራተኞች

711. የማዕድን፣ የድንጋይ፣ የአሸዋና የመሳሰሉት አውጭዎችና የድንጋይ ጠራቢዎች (ዲማሚት አፈንጂዎች፣ የክባ ሠራተኞች በዚህ ክፍል ይጠቃለላሉ።)

712. ግንበኞች፣ አናፂዎች የመሳሰሉትና ባህላዊ ቤቶችን ፣ ጎጆዎችን ...ወዘተ ሠሪዎች። (የእንጨት ጀልባና ታንኳ ሠሪዎች እዚህ ይጠቃለላሉ።)

713. ለሳኞች፣ የቧንቧ ሥራ ሠራተኞች፣ የጣሪያ ሥራ ሠራተኞች (የጣሪያ አዋቂዎች)፣ የመስታወት ሠራተኞች፣ የሕንፃ ኤሌክትሪሺያኖችና የመሳሰሉት የሕንፃና የራኒሽንግ ወይም የማጠናቀቅ ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች

714. ቀለም ቀቢዎች (የሕንፃዎችና፣ ሌሎች በሌላ ቦታ ያልተገለፀው የተመረቱ ቁሳቁሶች ለምሳሌ የመኪና ቀለም መቀባትን ያጠቃልላል)

72. የብረት፣ የማሽኖችና ተመሳሳይ ሠራተኞች

721. ብረት በያጆች፣ ብረት አቅላጮች፣ የጠፍጣፋ ብረት ሠራተኞች፣ የመሠረትና የምሶሶ የሚሆን ፌሮ ብረት አዘጋጆችና ብረት ወጣሪዎች፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ የዕደጥበብ ሠራተኞችና

722. ቀጥቃጮች፣ የብረታ ብረት የዕደጥበብ ምርት አምራቾችና የመሳሰሉት

723. የመኪና ሜካኒኮች፣ የአውሮፕላን ኢንጂን ሜካኒኮችና ገጣሚዎች፣ ጎሚስታዎች፣ ላቫጆ (የዘይትና ግሪሲንግ የሚያደርጉ)ና ሌሎች ተመሳሳይ ሠራተኞች።

724. የኤሌክትሪካልና የኤሌክትሮኒክስ ሚካኒኮች፣ የቴሌፎን መሥመር ዘርጊዎች፣ ጠጋኞችና ኬብል አገናኞች፣ የጋራዥ ኤሌክትሪሽያንና የመሳሰሉት። (የሬድዮ፣ ቴሌቪዥንንና የመሳሰሉት አዳሾች እዚህ ይጠቃለላሉ።)

73. አንጥረኞች፣ የሽክላ ሠራተኞች፣ የእንጨትና የቆዳ ዕደጥበብ ሠራተኞችና የጎትመት ሠራተኞች:- (የዕደጥበብ ውጤቶች)

731. አንጥረኞች፣ ወርቅ፣ ሠዓትና ተመሳሳይ የሆኑ ጥንቃቄ የሚፈልጉ መሣሪያዎች ሠሪዎችና ጠጋኞች (የመዚቃ መሳሪያ ሠሪዎች እዚህ ይጠቃለላሉ።)

732. ሽክላ፣ መስታወት፣ ሠሪዎችና የሽክላ መስታወትና ሲራሚክስ ምርቶችን ቀለም ቀቢዎችና ተመሳሳይ ሠራተኞች።

733. የእንጨት፣ የቀርከሃ፣ የቃጫ፣ የጨርቅና የቆዳ ቁሳቁሶች የዕደጥበብ ውጤቶች ሰሪዎች

734. የቀላል የጎትመት ሥራ ሰሪዎች፣ ፎቶግራፍ አንሺዎችና የፊልም አጣቢዎች፣ የመጽሐፍ ጠራዢዎችና የመሳሰሉት (አታሚዎች፣ ፊደል ለቃሚዎች፣ ስቴሪዮና ኤሌክትሮ ታይፐሮች፣ ብረት ላይ አታሚዎች፣ ጨርቃጨርቅ ላይ አታሚዎች እና የመሳሰሉት እዚህ ይጠቃለላሉ)

74. ሌሎች የዕደጥበብና ተመሳሳይ ሥራዎች:-

741. ጠላ ጠማቂዎች፣ አረቄ አውጪዎች፣ እንጀራና ዳቦ ጋጋሪዎች፣ የኬክና ሌሎች ጣፋጭ ምግብ ዝግጅት ሠራተኞች፣ የልኪንዳ ሠራተኞች ቅቤና ዓይብ አውጭዎች፣ የትምባሆ አዘጋጆች፣ በርበሬ ለቅማ የምትሸጥና የመሳሰሉት፣ የምግብና መጠጥ ቀማሾችና ደረጃ ሠጪዎች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች ሳይበላሹ ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ አድራጊዎችና ምግብ አዘጋጆች የመሳሰሉት።

742. ሰሊንና ዘንቢል ሠሪዎች፣ ቁምሳጥኖችን ቡሩሾችንና ሌሎች የእንጨት ቁሳቁሶችን የሚያመርቱ፣ ኪስ ወረቀት የሚሠሩ፣

743. ሸማኔዎች፣ ፈታዮች፣ ልብስ ሠፊዎች ሥጋጃ ሠሪዎች ፍራሽ አዳሽ፣ ሶፋ አዳሽ፣ ታፒስሪና የመሳሰሉት

744. ሩቂዎች፣ ጫማ ሠፊዎች፣ ጫማ ጠጋኝና የመሳሰሉት

ዋና ክፍል 8

የማምረቻ መሣሪያዎች አፕሬተሮችና ገጣጣሚዎች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ ሠራተኞች በአብዛኛው ትላልቅ ማሽነሪዎችን የማንቀሳቀስና የመጠቀም (አፕሬት የማድረግ) ዕውቀት ያላቸው ናቸው። አብዛኛዎቹም የሥራ ዓይነቶች ማዕድን አውጭዎች የማምረቻ መሣሪያዎች አፕሬተሮች፣ ሾፌሮች ናቸው።

81. በቋሚነት የተተከሉ መሣሪያዎችና የመሳሰሉት አፕሬተሮች

811. የማዕድን ማውጫና ማጣሪያ ማሽኖች አፕሬተሮች

812. የብረት ማቅለጫና ተመሳሳይ ማሽኖች አፕሬተሮች

813. የመስታወት፣ የሴራሚክስና ተመሣሣይ ማሽነሪዎች አፕሬተሮች

814. የእንጨት መሰንጠቂያና የወረቀት ማምረቻ ማሽነሪዎች አፕሬተሮች

815. የኬሚካል፣ የፔትሮሊየምና የተፈጥሮ ጋዝ ማሽኖች አፕሬተሮች

816. የኤሌክትሪክና ሌሎች የኃይል ማመንጫ መሳሪያዎች አፕሬተሮች

817. የመገጣጠሚያ ማሽነሪ አፕሬተሮች

82. ማሽን ኦፕሬተሮችና ገጣጣሚዎች

821. የሲሚንቶ፣ የብረት ቅርፅ ማውጣትና የመሳሰሉት የማዕድንና ከማዕድናት ከሚገኙ ንጥረ ነገሮች ጋር የተያያዙ ማሽኖችን ኦፕሬተሮች

822. የኬሚካል፣ ፋርማሲቲካል፣ የመፈንዳት ፀባይ ያላቸው (ፈንጂዎች) እና ሌሎች ከተመሳሳይ የኬሚካል ውጤቶች ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፕሬተሮች (የክብሪት ማምረቻ ማሽነሪ ኦፕሬተሮች፣ የፊልምና ፎቶግራፍ ማሳደጊያ ማሽነሪ ኦፕሬተሮች)

823. ከላስቲክና ከጎማ ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፕሬተሮች

824. የእንጨት ውጤቶች እና ከእንጨት ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፕሬተሮች

825. ከጎትመት፣ ከመለበድና ከወረቀት ውጤቶች ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፕሬተሮች

826. ከድርና ማግ ከጨርቃጨርቅ ምርትና ስፌት፣ ከቆዳና ከጫማ ጋር የተያያዙ ማሽን ኦፕሬተሮች፣ የማቅለምና የላውንደሪ ማሽን ኦፕሬተሮች

827. ከምግብ (ሥጋ፣ ወተት፣ ሰብል፣ ከረሜላ፣ ስኳር፣ ሻይ፣ ቡና፣ ቢራ፣ ለስላሳ፣ ... ወዘተ) ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፕሬተሮች ፣ ወፍጮ ቤት ሠራተኛ

828. ተገጣጥመው የሚሠሩ መኪኖች፣ አውሮፕላኖችን፣ የኤሌክትሪካልና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን ከብረት፣ ከፕላስቲክ፣ ከጎማ፣ ከቆዳ ከእንጨት ወይም ከሌሎች ዕቃዎችን የሚሰሩ ዕቃዎች ገጣጣሚዎች

83. ሾፌሮችና ተንቀሳቃሽ ማሽን ኦፕሬተሮች

831. የባቡርና ተመሳሳይ መሣሪያዎች ነጂዎችና ኦፕሬተሮች

832. የመኪና፣ የታክሲ፣ የአውቶብስ፣ የሞተር ብስክሌት፣ የጭነት መኪኖች ነጂዎች

833. የክሬኖች፣ የዕቃ ማንሻ ተንቀሳቃሽ ማሽን ኦፕሬተሮች፣ ትራክተሮችና ሌሎች ከግብርና ጋር የተያያዙ ማሽኖች ኦፕሬተሮች

834. የመርከብ ላይ ሠራተኞችና ተመሳሳዮች

ዋና ክፍል 9

ዝቅተኛ ሥራ ሠራተኞች

በዚህ ዋና ክፍል የሚመደቡ ሠራተኞች ዝቅተኛ የሆኑ ሥራዎችን የማካሄድ አውቀት ያላቸው ናቸው። በአብዛኛውም በእጅ የሚያዙ መሣሪያዎች በስተቀር የተለየ መሣሪያ የማይጠቀሙ ሲሆን ሥራቸውም በአብዛኛው የግል ጉልበትን በመጠቀም የሚከናወን ነው። በሥራው ላይም ውሳኔ የመስጠታቸው እድል አነስተኛ ነው። አብዛኞቹ በዚህ ክፍል የሚመደቡ ሥራዎች በየመንገዱ የሽያጭ ተግባር የሚያከናውኑ፣ ዘበኝነት፣ የቤት ሠራተኝነት፣ የማዕድን ቁፋራ ወዛደሮች፣ የግብርናና የከብት እርባታ ዝቅተኛ ሠራተኞች፣ የማዕድን ማውጣት የኮንስትራክሽንና የማምረቻ ፋብሪካዎች ተራ ወዛደሮች ናቸው።

91. ዝቅተኛ የሽያጭና የአገልግሎት ሥራ ሠራተኞች

911. ቆሎ አዟሪዎች፣ የልዋጭ ነጋዴዎች፣ ዕቃ በየቤቱ እያዞሩ የሚሸጡ፣ በየመንገዱ እየዞሩ ዕቃ የሚሸጡ፣ ጋዜጣ አዟሪዎችና የመሳሰሉት ዕቃ ሻጮች

912. ሊስትሮዎች፣ በየመንገዱ መኪና የሚያጥቡና የመሳሰሉት በመንገድ አገልግሎት የሚሰጡ

913. የቤት ሠራተኞች፣ ልብስ አጣቢዎች፣ ሹፋባ ሠሪዎች የቡና ቤት ጽዳት ሠራተኞች፣ የቡና ቤት ሣህን አጣቢዎች፣ የቡና ቤት አልጋ አንጣፊዎችና ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ

914. ዘበኞች /የግለሰብ ቤትንም ይጨምራል/፣ ዕቃ ተሸካሚዎች፣ ተላላኪዎች፣ የቢሮ ጽዳት ሠራተኞች፣ መንገድ ጠራጊዎች፣ ቆሻሻ ሰብሳቢዎች፣ በግቢ ውስጥ መኪና አጣቢዎችና ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ

92. ዝቅተኛ የግብርናና የዓሣ ማስገር ሠራተኞች

921. እረኞች፣ ዝቅተኛ የእርሻ ሥራ፣ የዓሣ ማስገርና የደን ሥራ ሠራተኞች (የሥራው ዓይነት የተለየ ዕውቀት የማይጠይቅ ሆኖ ከሌሎች በሥራው ላይ ዕውቀት ካላቸው ዝቡራዎች ጋር በረዳትነት ወይም በአጋዥነት የግብርና ሥራ የሚያካሂዱ ሠራተኞች)

93. የማዕድን ቁፋሮ፣ የሕንፃ ሥራ፣ የማምረቻና የትራንስፖርት ሥራ የቀን ሠራተኞችና ወዛደሮች

931. የማዕድን ቁፋሮ፣ የድንጋይ ማውጣት፣ የኮንስትራክሽንና የጥገና ሥራ ወዛደሮች፣

932. የማምረቻ ፋብሪካዎች ተራ ወዛደሮችና የፋብሪካ ቡና ለቃሚዎች

933. በእጅ ወይም በፔዳል የሚንቀሳቀሱ፣ በእንስሳት የሚጎተቱ /እንደጋሪ/ ተንቀሳቃሾችና መሣሪያዎች ነጅዎች፣ ጭነትና ሌሎች ዣዦችን የሚያስተናግዱ ወዛደሮች /አውታንቲዎች፣ ወያላዎችና የመሳሰሉት በዚህ ይጠቃለላሉ/ ዕቃ ጫኝና አውራጆች፣ በጋማ ከብት ዕቃ የሚያጓጉዙ

ዋና ክፍል 0

የጦር ኃይል አባላት

01. የጦር ኃይል አባላት (ሲቪሎችን አይጨምርም)

011. የጦር ኃይል አባላት

የኢንዱስትሪ ወይም የድርጅት ምርት፣ ንግድ ወይም አገልግሎት ምደባ መለያ ኮድ ዝርዝር

መግቢያ

የኢንዱስትሪ ምደባ ዋና ዓላማ ድርጅቶችን በየእንቅስቃሴአቸው ዓይነት ለመመደብ ሲሆን ትክክለኛ የሆነ የኢንዱስትሪ ምደባም የአንድን አገር ኢኮኖሚ አቋምና ዝንባሌ ለመገምገም ይረዳል።

በአንድ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የተሰማራ ግለሰብ የኢንዱስትሪ ምደባ የሚካሄደው ግለሰቡ በተሰማራበት ድርጅት የመጫረሻ /final/ ዋና ምርት ወይም አገልግሎት መሠረት ነው።

በጥናቱ መጠይቅ ላይ በዓምድ 32 የግለሰቦች የኢንዱስትሪ መደብ ማለትም የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ተፅፎ ይገኛል። የዚህንም ምድብ ኮድ ከተሰጠው የኢንዱስትሪ ኮድ ዝርዝር በመምረጥ በ1996 የክተሞች የስራ ስምሪት ጥናት መጠይቅ በዓምድ 32 በተዘጋጁት ካርድ ኮለሞች ይሞላል።

ለምሳሌ በአንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በገንዘብ ያዥነት የሚሠራ ግለሰብ የኢንዱስትሪ ምደባ እንደሚከተለው ይሆናል። ድርጅቱ ማለትም ትምህርት ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት አገልግሎት ሲሆን ይኸውም በመጠይቁ በዓምድ 32 ተፅፎ እናገኘዋለን። ለዚህም ተገቢው ኮድ በተሰጡት ሦሥት ካርድ ኮለሞች ከገጽ 21 ከዋና ክፍል አስራ ሁለት ከንዑስ ክፍል 80 ተመርጦ ለዚህ ኢንዱስትሪ ዓይነት ተስማሚው ኮድ 802 ስለሆነ ይኸው ኮድ ይሞላል።

የሌላ ግለሰብ የኢንዱስትሪ ዓይነት በዓምድ 32 ጠላ አምርቶ መቸርቸር የሚል ተሞልቶ ከሆነ ጠላውን ጠምቀው በችርቻሮ ለሚሸጡ የኢንዱስትሪ ዓይነት ከኢንዱስትሪ ኮድ ምደባ በገጽ 22 ከዋና ክፍል ስድስት ከንዑስ ክፍል 55 ኮድ 552 ስለሆነ ይኸው ተመርጦ በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል። ነገር ግን ጠላውን በጅምላ ገዝተው በጅምላ የሚሸጡ ከሆነ የግለሰቡ ኢንዱስትሪ በጅምላ ንግድ በመመደብ በካርድ ኮለሞቹ ኮድ 512 ይሞላላቸዋል።

በዓምድ 32 የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምንድን ነው የሚለው ጥያቄ እድሜአቸው አስር ዓመትና በላይ ለሆኑ ግለሰቦች በሙሉ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው። ነገር ግን ዕድሜአቸው አስር ዓመትና በላይ ሆኖ በዓምዱ የኢንዱስትሪ ዓይነት ያልተሞላላቸው ግለሰቦች ቢገኝ መረጃው መሞላት ሲገባው ያልተሞላ መሆኑን ለማመልከት ኮድ 999 በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል።

ዋና ክፍል - አንድ

ግብርና፣ አደን፣ ደን ሀብትና አሣ ማስገር

01. ግብርና፣ አደንና ተመሣሣይ ምርቶችና አገልግሎቶች

011. ቋሚና ጊዜያዊ ሰብሎች የእርሻ ምርት፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች፣ ፍራፍሬ፣ አትክልትና ለገበያ የሚቀርቡ ሰብሎችን ማምረት /ጤፍ፣ ስንዴ፣ ...፣ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ መንደሪን፣ ...፣ ድንች፣ ሽንኩርት፣ ለውዝ፣ ቡና ...ወዘተ/ እንዲሁም የተለያዩ የዘር እህሎችን ማምረትና የአትክልት ችግኞችን ማፍላት እና ሌሎች በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ሰብሎችን ማምረት በዚህ ይጠቃለላሉ።

012. ከብት እርባታ /ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ፈረስ፣ ... ወዘተ ማርባት፣ የዶሮና ንብ እርባታ፣ ወተት፣ የሌሎች እንስሳት እርባታና በሌላ ቦታ ያልተገለፀ የእንስሳት ተዋፅያዎችን (ምሳሌ ፀጉር ...ወዘተ) በእንስሳት አርቢው ማምረት፣ ...ወዘተ/

013. እርሻና ከብት እርባታ /ጥምር ግብርና/ (ሰብሎችን ማምረት ከእንስሳት እርባታ ጋር)

014. የግብርናና ከብት እርባታ አገልግሎት መስጠት የእንስሳት ሕክምናን ሳይጨምር /ፀረ-ሰብልና ፀረ-እንስሳት የሆኑ ተባዮችንና በሽታዎችን መከላከል፣ የእርሻ መሳሪያዎችን ትራክተር፣ ኮምባይነርና የመሣሠሉ ማክራየት (ከኦፕሬተር ጋር)፣ የመስኖ ሥራ፣ ከብቶችን ማዳቀል ሥራ ...ወዘተ/ እንዲሁም ሰብልን ለገበያ ለማቅረብ የማጠብ፣የማድረቅ፣የመፈልፈል... ወዘተ. አገልግሎት መስጠት፣

015. አደን /ለምግብ፣ ለሽያጭ፣ ለምርምር፣ ስጋቸው ፣ ቆዳቸውን ወይም ፀጉራቸውን ለመጠቀም ወይም ለማራባት የአደን ሥራ ወይም ልማት ማካሄድ/

02. የደን ሀብት ምርት ማምረት

020. የደን ሀብት ምርት ማምረት /ደን ማልማት፣ መንከባከብና ጥቅም ላይ ማዋል/ በተፈጥሮና በሰው የሚለሙ ዛፎችን ለማገዶና ለተለያዩ ጥቅሞች እንዲውሉ ማዘጋጀት ለምሳሌ ከሰል ማክሰል፣ ጣውላ ማዘጋጀት ...ወዘተ

05. ዓሣ ማስገር

050. ዓሣ ማስገርና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ከባህር፣ ከሐይቆች፣ ከውቅያኖሶች፣ ...ወዘተ ማምረት፣ ከዓሣ ማምረት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሌሎች የዓሣ ማስገር ሥራዎች አገልግሎቶችን መስጠት

ዋና ክፍል ሁለት

ማዕድን ድንጋይና አሸዋ ማውጣት

10. የድንጋይ ከሰልና የሊግናይት ፒት ማምረት

101. የድንጋይ ከሰል፣ ሊግናይት ፒት ማምረት

11. ያልተጣራ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ ማምረት፣ ዘይትና ጋዝ ለመፈለግ የሚደረጉና ተመሳሳይ አገልግሎቶች /ነገር ግን የቅየሳ ሥራን አይጨምርም/

111. ያልተጣራ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ ማምረት፣ ዘይትና ጋዝ ለመፈለግ የሚደረጉና ተመሳሳይ አገልግሎቶች /ነገር ግን የቅየሳን ሥራን አይጨምርም/

12. የወርቅ የብረትና የመሳሰሉት ማዕድናትን ማምረት

120. የወርቅ የመዳብ እንዲሁም ብረት ነክ የመሳሰሉት ማዕድናትን ማምረት

13. ሌሎች ማዕድን፣ ድንጋይና አሸዋ ማውጣት

131. ድንጋይ፣ አሸዋና ሸክላ ማውጣት (ማምረት)

132. ከዚህ በላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ማዕድናትን ማውጣት /ኬሚካሎች፣ የማዳበሪያ ማዕድናት ጨው፣ ...ወዘተ ማውጣት/

ዋና ክፍል- ሦሥት

ማኒፋክቸሪንግ

ማኒፋክቸሪንግ አንድን ዕቃ ወደ ሌላ አዲስ ዓይነት ዕቃ ወይም ምርት የመለወጥ ተግባር ነው። የመለወጡ ተግባር ዘመናዊ የሞተር ማሽኖችን ወይም በእጅ በመጠቀም በፋብሪካ ወይም በመኖሪያ ቤት ውስጥ ...ወዘተ ሊከናወን ይችላል። በተጨማሪም የተለያዩ ምርቶችን መገጣጠም ወይም የተለያዩ ማሽኖችንና መሣሪያዎችን በንግድ፣ በማዕድንና ሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ገጣጥሞ መትከል እንደ ማምረት ተቆጥሮ የተተከሉት የማሽን ዓይነቶች በሚመደቡበት የማምረት መለያ ኮድ ዉስጥ ይመደባሉ። የተለያዩ የፋብሪካና የንግድ ማሽኖችንና መሳሪያዎችን በዋነኝነት የመጠገን ሥራ እንደ ማምረት ተቆጥሮ ማሽኖቹና መሣሪያዎቹ በሚመደቡበት የማምረት መለያ ኮድ ውስጥ ይመደባሉ። ቀደም ሲል የተመረቱ ምርቶችን በከፍተኛ ደረጃ መለወጥ ወይም እንደገና መስራት እንደ ማምረት ይቆጠራል።

15. የምግብ ውጤቶችን ማምረት

151. የከብት፣ የበግ፣ የዶሮና የመሳሰሉ እንስሳትን ማረድ፣ ሥጋውን ማዘጋጀትና እንዳይበላሽ መጠበቅ /ቁራጮች፣ በቆርቆሮ ወይም በሌላ ዕቃ ሥጋ ማሸግና ማዘጋጀት የመሳሰሉት/

152. ከባሕር፣ ከሐይቆችና ከወንዞች የሚገኙ እንደ ዓሣ የመሳሰሉትን በቆርቆሮ ወይም በሌላ ዕቃ ማሸግ፣ እንዳይበላሹ መጠበቅና ማዘጋጀት

153. ትኩስ፣ ደረቅ ወይም በማቀዝቀዣ የተጠበቀ አትክልትና ፍራፍሬ በቆርቆሮ ወይም በሌላ ማሸግና ማዘጋጀት /በቆርቆሮ የታሸጉ የአትክልትና ፍራፍሬ ጭማቂዎችን ማዘጋጀት ይጨምራል/

154. ከቅባት እህሎች፣ ከአትክልትና ከእንስሳት ዘይትና ስብ (ፋትስ) ማምረት /የዘይት መጭመቂያዎች እዚህ ይመደባሉ/

155. ወተትና የወተት ተዋፅዖ ማዘጋጀት /ቅቤ፣ ቺዝ፣ ማሸግ ...ወዘተ ማዘጋጀት ነገር ግን ወተት በማለብ ለቤታቸው የሚያዘጋጁ በኮድ 012 ወይም 013 ይመደባሉ/

156. እህል በወፍጮ ፈጭቶ ማዘጋጀት /እህል ገዝተው በመፍጨት ለመንግሥት፣ ለነጋዴዎች፣ ለግለሰቦች ወይም ለሌላ ድርጅት የሚያቀርቡ ፋብሪካዎች ወይም ወፍጮ ቤቶች በዚህ ይመደባሉ። ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያ ምግብ ማደራጃና ሆለታ ዱቄት ፋብሪካ የመሳሰሉት፣ ነገር ግን ከግለሰቦች፣ ከቤተሰቦች ወይም ከነጋዴዎች እህል ቀርቦላቸው የአገልግሎት ዋጋ እያስከፈሉ የሚፈጩ በአገልግሎት ዘርፍ ይመደባሉ/፣ ከእህል የእንስሳት መኖ ማዘጋጀት/

157. የጋገራ ውጤቶች ማምረት /እንጀራ፣ ዳቦ፣ ኬክና ብስኩት፣...ወዘተ ማምረት/

158. ስኳርና ከረሜላዎችን ማምረት /ወንጂ ስኳር ፋብሪካ፣ ገነት ከረሜላ ፋብሪካ፣ሸንኮራ ...ወዘተ/

159. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች የምግብ ዓይነቶች ማምረት/ ማኮረኒ፣ ፓስታ፣ ቡና መቁላት፣ መፍጨትና ማሸግ፣ ቅመማቅመምን ፈጭቶና አሽጎ ማዘጋጀት፣ እርሾ ...ወዘተ/

16. ትምባሆና መጠጦችን ማምረት

161. የአልኮል መጠጦች ማምረት /ሞላ ማሩና መርከበኛ የመጠጥ ፋብሪካ የመሳሰሉት/

162. ወይን ጠጅ ማምረት /ከሰምና የመሳሰሉ የወይን ፋብሪካዎች/

163. ቢራ ማምረት /ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ በደሌ፣ ...ወዘተ ቢራ ፋብሪካዎች/

164. ለስላሳ መጠጥ ወይም ሚኒራል ውሃ /የእምቦ ውሃ የመሳሰሉ/ ማምረት

165. ጠላ፣ ቦርዴና የመሳሰሉትን መጥመቅ /በጠማቂው ድርጅት ጠላ በችርቻሮ ከተሸጠ ድርጅቱ በንግድ ዘርፍ ይመደባል፣ ነገር ግን ጠማቂው ድርጅት ጠላውን ለሌላ ነጋዴ ወይም ድርጅት በጅምላ ቢሸጥ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ/

166. ጠጅ መጥመቅ /ከላይ ለጠላ ጠማቂ ድርጅት የተሰጠው ማሳሰቢያ ጠጅንም በሚመለከት ያገለግላል/

167. ካቲካላ መዋመቅ /ከላይ ለጠላ ጠማቂ ድርጅት የተሰጠው ማሳሰቢያ ካቲካላንም በሚመለከት ያገለግላል/

168. የትምባሆ ውጤቶች የሆኑ ሲጋራዎች፣ ሲጋሮች፣ ...ወዘተ ማምረት /የትምባሆ ማብቀልና ቅጠሎችን ማዘጋጀት በግብርና ውስጥ ይመደባሉ/

169. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች መጠጥና ትምባሆ ማምረት

17. ጨርቃ ጨርቅ ማምረት

171. መፈልቀቅ፣ ማዳወር፣ መፍተል፣ ማቅለምና ማጠናቀቅ /አደይ አበባ ጥጥ ፋብሪካ፣ የኢትዮጵያ ክር ፋብሪካና በሽመና የአገር ባሕል ልብሶች ማምረት/

172. ከሚለበሱ ልብሶች በስተቀር ከጨርቃ ጨርቅ እንደ መጋረጃ፣ የአልጋ ልብስ፣ አንሶላ፣ የትራስ ልብስ፣ የመኪና መቀመጫ ልባሶች፣ ድንኳኖች፣ የመኝታ ከረጢት፣ ባንዲራ፣ የቆሻሻ መወልወያ፣ የወለል ምንጣፎች፣ መረብ፣ ገመድ፣ ያልተሰፋ ቆዳ ...ወዘተ ማምረትና እንዲሁም በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን ማምረት

173. አሠራራቸው አንድ ወጥ ሆኖ ሳይገጣጠሙ በቀጥታ ሊለበሱ የሚችሉ በእጅ ወይም በማሽን የሚሰሩ ጥልፎችና ልብሶች ለምሳሌ ስቶኪንጎች፣ ካልሲዎች፣ ሹራቦች፣ ...ወዘተ ማምረት

18. የሚለበሱ ልብሶችን ማምረት፣ ከፀጉር የሚሰሩ ልብሶችን ማቅለምና ማዘጋጀት

181. ከፀጉር ከሚሠሩ ልብሶች በስተቀር የሚለበሱ የጨርቅ ልብሶችን ማምረት /በዚህ ክፍ የሚጠቃለሉ በአጠቃላይ ጨርቁ ተቀዶና ተገጣጥሞ የሚዘጋጅ ሲሆን ነው። በተጨማሪ ጨርቁን ገዝተውና ሰፍተው ወይም አጠናቀው ለሽያጭ የሚያቀርቡ፣ ጨርቅ ቀርበላቸው የአገልግሎት ዋጋ እያስከፈሉ ልብስ የሚሰፉ ሁሉ በዚህ ክፍል ይመደባሉ። የልብሶቹም ዓይነት የወንዶች፣ የሴቶችና የልጆች ሆኖ የውጭ ወይም የውስጥ ልብሶች፣ የሥራ ወይም የስፖርት ልብሶች፣ ኮፍያዎች፣ ቀበቶዎች፣ ከቆዳ የተሠሩ ልብሶች ...ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ።/ ነገር ግን አሠራራቸው አንድ ወጥ ሆኖ ሳይገጣጠሙ በቀጥታ ሊለበሱ የሚችሉ በእጅ ወይም በማሽን የሚሰሩ ጥልፎችና ልብሶች ለምሳሌ ስቶኪንጎች፣ ካልሲዎች፣ ...ወዘተ በክፍ 173 ሥር እንጂ በዚህ አይካተቱም።

182. ከእንስሳት ፀጉርማ ቆዳ የሚሠሩ ልብሶችን ማቅለምና ማዘጋጀት፣ እስከ ፀጉራቸው ካሉ ቆዳዎች ወይም ሌጦዎች ዕቃዎችን ማምረት

19. ቆዳ ማልፋት፣ ማለስለስና ማዘጋጀት፣ በፋብሪካ ወይም በቤት ውስጥ ቆዳ ማዘጋጀት የቆዳ ሻንጣዎች፣ የእጅ ቦርሳዎች፣ ኮርቻዎች፣ የተለያዩ የፈረስ ጌጣጌጦችና ጫማዎች ማምረት

191. ቆዳ ማልፋት፣ ማለስለስና ማዘጋጀት /በፋብሪካ ወይም በቤት ውስጥ ቆዳ ማዘጋጀት ለምሳሌ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ/፣ የቆዳ ሻንጣዎች፣ የእጅ ቦርሳዎች፣ ኮርቻና የኮርቻ ዕቃዎች ማምረት በተጨማሪም የሚለበሱ የቆዳ ልብሶችን ማምረት በዚህ ይከተታሉ

192. ከጨርቅ በስተቀር ከሌሎች ማቴሪያሎች ጫማዎችን ማምረት፣ በተጨማሪም የጫማ ሶሎችንና ሌሎች የጫማ ክፍሎችን ማምረት

20. ከቤትና ከቢሮ ዕቃዎች በስተቀር እንጨትና የእንጨት ውጤቶችንና ቡሽ ማምረት

201. እንጨት መሰንጠቅና ማዘጋጀት /ትላልቅና ትናንሽ የእንጨት መሰንጠቂያና ማዘጋጃ ድርጅቶች/

202. ከቤትና ከቢሮ ዕቃዎች በስተቀር የእንጨት፣ የቀርከሃና የሸምበቆ ውጤቶችን ማምረት /የእናዚ መሣሪያዎች፣ ሳጥኖች፣ በርሚሎች፣ የተለያዩ በእንጨት የተሰሩ የእጅ መሣሪያዎች፣ በእንጨት የተሰሩ የወጥ ቤት ዕቃዎች፣ ...ወዘተ/

21. የወረቀትና የወረቀት ውጤቶችን ማምረት

210. ወረቀት፣ የወረቀት ውጤቶች (ለምሳሌ ሶፍት) የወረቀት ቦርድ /ክርታስና የመሳሰሉ የወረቀት ዕቃዎች/ ማምረት፣

22. ማተም፣ መጠረዝና ማባዛት

221. ማተም /የተዘጋጁ መጻህፍት፣ ጋዜጣዎች፣ ጆርናሎች፣ መጽሔቶች፣ ...ወዘተ ጽሁፎችን መጠረዝና ማተም፣ ማባዛትና ፎቶ ኮፒ ሥራዎችንም ያጠቃልላል/

222. የተቀረጹ ሪኮርዶችን ማባዛት /ካሴቶች፣ ቪዲዮ ቴፖች፣ የኮምፒዩተር ዲስኮችን ከኦሪጅናል ኮፒዎች ላይ ማባዛት፣ ነገር ግን ኦሪጅናል የቪዲዮ ቴፖችና ተንቀሳቃሽ ፊልሞችን ማተም ወይም መቅረጽ በዚህ አይጠቃለሉም/

23. የተጣራ የነዳጅ ውጤቶችን ማምረት

231. የተጣራ የነዳጅ ውጤቶችን ማምረት

24. ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶችን ማምረት

241. ከማዳበሪያ በስተቀር መሠረታዊ የኢንዱስትሪ ኬሚካል ማምረት /የኢንዱስትሪ ጋዝ የመሳሰሉ ማምረት/

242. ማዳበሪያ የናይትሮጅን ኮምፓውንድ ማምረት

243. ፕላስቲክና ፕላስቲክ መሰል ጎማዎችን በቀዳሚነት ማምረት

244. ፀረ-ተባይና ሌሎች የግብርና ኬሚካል ውጤቶችን ማምረት

245. ቀለም፣ ቫርኒሽና የመሳሰሉትን የማቅለሚያ፣ የማተሚያ ቀለሞችንና ማስትሾችን ማምረት

246. የተለያዩ መድሃኒቶችና የመድሃኒት ኬሚካሎች ማምረት /የኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካና የሀገር ባህል መድሃኒት አምራቾች የመሳሰሉ/

247. ሳሙና፣ ሽቶና የንጽህና መጠበቂያ ዕቃዎች እንደ ጥርስ ሳሙና፣ ኒቪያ ክሬም፣ የተለያዩ ሳሙናና ሰንደል የመሳሰሉ ማምረት የጫማ ቀለሞችን፣ ማስቲሾችን፣ ለወለልና ለመሳሰሉት ሰም ማምረት ያካትታል፣

248. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶችን ማምረት /ፈንጂዎች፣ የተለያዩ የቅባት ዘይቶች፣ የመጻፊያ ቀለሞች፣ ...ወዘተ/ ሰው ሰራሽ ክር ማምረት

25. የጎማና ፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት

251. ጎማና ከመነዳሪያ ማምረት /አዲስ ጎማ ፋብሪካና የጎማ ቁጠባ የመሳሰሉ/እንዲሁም በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የጐማ ውጤቶችን ማምረት፣ ነገር ግን የሚከራይ በረባሶ በኮድ 192 ይካተታል።

252. የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት /እንደ ኢትዮ ፕላስቲክ ፋብሪካ የመሳሰሉና ከፕላስቲክ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለምሳሌ ለወለል ምንጣፍ የሚሆን፣ ለመፀዳጃ ቤት የሚሆኑ ልዩ ልዩ ዕቃዎች፣ ለጠረጴዛ መሸፈኛ፣ የዕቃ መጠቅለያዎች፣ ...ወዘተ/

26. ብረት ነክ ያልሆኑ ሌሎች የማዕድን ውጤቶችን ማምረት

261. መስታወትና የመስታወት ውጤቶችን ማምረት

262. ሸክላ፣ ሴራሚክና የሴራሚክ ቁሳቁሶችን ማምረት

263. ሲሚንቶ፣ ኖራና የመሳሰሉ ለሕንፃ ሥራ የሚያገለግሉ የሲሚንቶ ውጤቶችን ማምረት

264. ድንጋይ መጥረብ፣ ቅርጽ ማውጣትና ማዘጋጀት

269. ከላይ ያልተጠቀሱ ከሌሎች ብረት ነክ ካልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ዕቃዎችን ማምረት /አዲስ አበባ አስቤስቶስ ፋብሪካ፣ እብነበረድና የመሳሰሉትን ማምረት/ ለግንባታ የሚረዱ ማጣበቂያዎች ማምረት፣ ለግንባታ የሚረዱ ማጣበቂያዎች ማምረት፣

27. መሠረታዊ ብረታ ብረቶችን ማምረት

271. መሠረታዊ ብረታ ብረት ማምረት

272. የከበሩ ብረቶች (ለምሳሌ ወርቅና ነሐስ ማምረት/ እንዲሁም፣ ብረትነት ከሌላቸው ነገር ግን ብረታ ብረት መሰል ገመዶችን፣ ቱቦዎችን፣ መገጣጠሚያዎችን፣ ...ወዘተ ማምረት

273. ብረታ ብረቶችን ቅርጽ እንዲይዙ ማድረግ፣ የእጅ መሣሪያዎችን ማምረት

28. ከማሽኖችና ሌሎች መሣሪያዎች በስተቀር የብረታ ብረት ውጤቶችን ማምረት

281. ከማሽኖችና ሌሎች መሣሪያዎች በስተቀር የብረታ ብረት ውጤቶችን ማምረት የውኃ ወይም ሌሎች ነገሮች ማከማቻ ታንከሮችን ወይም ሪዘርቨሮች ማምረት፣ የብረት በሮች፣ የብረት ፍሬሞች፣ ለሕንፃ ሥራ የሚውሉና ተመሳሳይ ከብረታ ብረት የተሠሩ ውጤቶችን ማምረት/

29. ማሽኖችና ሌሎች መሣሪያዎችን ማምረት

291. ለአጠቃላይ ሥራ ጥቅም የሚሰጡ ማሽኖችና ሌሎች መሣሪያዎችን ማምረት /የመኪና የአውሮፕላንና የብስክሌት ኢንጂኖችን ሳይጫምር ሌሎች ኢንጂኖችን ማምረት፣ ፓምፖችና ኮምፕሬሰሮች፣ ...ወዘተ ማምረት/

292. ለተለየ ሥራ ጥቅም የሚሰጡ ማሽኖችና መሣሪያዎች ማምረት /ለግብርና ተግባር የሚውሉ፣ ለሕንፃ ሥራ የሚውሉ፣ ...ወዘተ ማሽኖች ማምረት/

293. በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱና ለቤት ውስጥ ግልጋሎት የሚውሉ ኤሌክትሪካል የሆኑ ወይም ያልሆኑ ዕቃዎች ማምረት /ፍሪጆች፣ ፍሪዘሮች፣ የልብስ ማጠቢያዎች፣ የምግብ መፍጫ ማሽኖች፣ ኩኪሮች፣ ...ወዘተ/

30. የቢሮ፣ የሂሳብና የስሌት ማሽኖችን ማምረት

300. የቢሮ፣ የሂሳብና የስሌት ማሽኖችን ማምረት /ለቢሮ ሥራ የሚውሉ የማባዣ ማሽኖች፣ የማተሚያ መሣሪያዎች፣ የጽህፈት መኪና፣ የመረጃ ማቀነባበሪያ መሣሪያዎች፣ ...ወዘተ ማምረት/

31. በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ማምረት

311. በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ማምረት ማለትም የኤሌክትሪክ ሞተር፣ ጀኔሬተር፣ ትራንስፎርመር፣ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ፣ የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች፣ የኤሌክትሪክ ሽቦ፣ ባለልባስና ኬብል ባትሪ፣ የኤሌክትሪክ መብራትና በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የኤሌትሪክ መሣሪያዎችን ማምረት፣

32. ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና የመገናኛ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ማምረት

321. ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና የመገናኛ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ማምረት

33. የሕክምና መሣሪያዎች፣ የዓይን መነፅሮች የተለያዩ ካሜራዎችና ሠዓቶችን ማምረት

331. የሕክምና መሣሪያዎች፣ የዓይን መነፅሮች፣ የፍቶግራፍ መሣሪያዎች፣ ሠዓቶችን ማምረት፣ የመለኪያ (የመመዘኛ) መሣሪያዎችን ማምረት

34. መኪናዎችና ተሳቢዎችን ማምረት

341. መኪናዎችንና ተሳቢዎችን ማምረትና የመኪና መለዋወጫዎችን ማምረት (የመኪና ኤሌክትሪክ ዕቃዎች ማምረትን አይጨምርም - ኮድ 311 ውስጥ ይጠቃለላሉ)

35. ሌሎች የትራንስፖርት መሣሪያዎችን ማምረት

351. ሌሎች የትራንስፖርት ዕቃዎችን ማምረት /መርከቦችንና ጀልባዎችን (የስፖርት ጀልባዎችን ጨምሮ) መሥራትና መጠገን፣ ባቡር፣ አውሮፕላን፣ ሞተር ብስክሌት፣ ብስክሌት ማምረት፣ ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ የትራንስፖርት መሣሪያዎችን ማምረት/

36. የቤትና የቢሮ ዕቃዎችን ማምረት፣ በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ምርቶችን ማምረት

361. የቤት ዕቃዎችን ለቤተሰብ፣ ለቢሮ፣ ለሆቴል፣ ለምግብ ቤትና ለተለያዩ ድርጅቶች /ሆስፒታል፣ ቲያትር ቤቶች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ ት/ቤቶች፣ ...ወዘተ/ ማምረት፣ የቤት ዕቃዎች ከድንጋይና ኮንክሪት በስተቀር ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከቀርከሃ፣ ከመስታወት ወይም ከቆዳ የተሠሩ ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨማሪም የቤት ዕቃዎቹ ለምግብ ማብሰያ፣ ለሳሎን፣ ለመተኛ፣ ለመቀመጫ፣ ለሥራ ...ወዘተ የሚያገለግሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

362. ከከበሩ ማዕድናት (ወርቅ፣ አልማዝ ...ወዘተ) ወይም ከአርቲፊሻሎች ጌጣጌጥና የመሳሰሉ ዕቃዎች ማምረት /ሰንቲሞች፣ ሜዳሊያዎች፣ ቅርፃ ቅርፅ ...ወዘተ ማምረት/

363. የሙዚቃ መሣሪያዎች ማምረት

364. የስፖርት ዕቃዎች ማምረት

369. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ምርቶች /አርሳስ፣ እስክሪፕቶና ሌሎች ለጽሕፈትና ለአርት ባለሙያዎች የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣ አሻንጉሊት፣ ጃንጥላ፣ ቁልፍ፣ መጥረጊያ፣ ብሩሽ፣ የአምፖል መሸፈኛ፣ የማስታወቂያ ጽሁፎች፣ ...ወዘተ የመሳሰሉት ማምረት/

ዋና ክፍል - አራት

ኤሌክትሪክ፣ ጋዝና ውሃ አቅርቦት

40. ኤሌክትሪክ፣ ጋዝ፣ እንፋሎትና ሙቅ ውሃ ማምረት፣ ክምችትና ሥርጭት

401. ኤሌክትሪክ ክምችትና ስርጭት

402. የጋዝ ምርትና ስርጭት

403. እንፋሎትና ሙቅ ውሃ አቅርቦት

41. ውሃ ማከማቸት፣ ማጣራትና ማሠራጫት

410፣ ውሃ ማከማቸት፣ ማጣራትና ማሠራጫት ለምሳሌ ለቤተሰብ፣ ለድርጅቱ ወይንም ለሌሎች

ተቃዋሚዎች በክፍያ ውሃ የማሰራጨት፣ወይም የማከፋፈል አገልግሎት መስጠት፣

ዋና ክፍል - አምስት

ኮንስትራክሽን

45. ኮንስትራክሽን

451. የኮንስትራክሽን ቦታ ማዘጋጀት /የሕንፃ መሥሪያ ቦታዎች ማጽዳት፣ መጥረግና ማስተካከል/

452. በሙሉ ወይም በማሻሽ አጠቃላይ ሕንፃ ሥራ፣ ሲቪል ምሕንድስና ሥራ /አዲስ የሕንፃ ሥራዎች፣ ሙሉ በሙሉ ወይም በማሻሽ የመቀየር ሥራዎች፣ ፕሪፋብችን መገጣጠም፣ እነዚህም መኖሪያዎች፣ መሥሪያ ቤቶች፣ መጋዝኖች፣... መንገዶች፣ ድልድዮች፣ ...ወዘተ ሥራዎችን ያጠቃልላል/

453. በሕንፃዎች የኤሌክትሪክ፣ ውሃና ሌሎች ዕቃዎችን መገጣጠም /ኤሌክትሪክ፣ ውሃ፣ ቴሌፎን፣ አንቴናና ሌሎች ዕቃዎችን መግጠምና እነዚሁት ዕቃዎች መጠገንን ይጨምራል/

454. ሕንፃዎችን የማጠናቀቅ ሥራ /ግድግዳና ጣራ ቀለም ቅብ፣ ወለሎችን ታይል፣ ምንጣፍና የመሳሰሉ ማልበስ፣ በግድግዳ ወረቀት ግድግዳዎችን ማስጌጥ፣ ወዘተ/

455. የሕንፃ መሥሪያ መሣሪያዎች ወይም ማፍረሻ መሣሪያዎችን ከሠራተኞች /ባለሙያዎች/ ጋር ማከራየት

ዋና ክፍል - ስድስት

የጅምላና ችርቻሮ ንግድ፣ መኪናዎች፣ ሞተር ብስክሌቶች፣ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች መጠገን

50. መኪናዎችና ሞተር ሳይክሎች ሽያጭና ጥገና፣ የነዳጅ ችርቻሮ ንግድ

የመኪናዎችና ሞተርሳይክሎች መለዋወጫዎች ሽያጭና ጥገና፣ አሮጌ መኪናዎችን መሸጥ፣ የእጥበት፣ ግሪሲንግና የመሳሰሉ እንዲሁም ነዳጅ በችርቻሮ መሸጥን ያጠቃልላል። (ነገር ግን የግል መኪና ማከራየት በክፍል 60 የሚመደብ እንጂ በዚህ ክፍል አይካተትም)።

501. የመኪናዎች ሽያጭ

502. የመኪናዎች ጥገና፣ እጥበትና ግሪሲንግ

503. የመኪና መለዋወጫዎች ሽያጭ

504. የሞተር ሳይክሎችና መለዋወጫቸው ሽያጭና ጥገና

505. የተሽከርካሪዎች ነዳጅ ችርቻሮ ንግድ /ለማንኛውም ተሽከርካሪ የሚውሉ ነዳጆችና ቅባቶች ሽያጭ፣ የነጭ ጋዝ ሽያጭም በዚሁ ይጠቃልላል/

51. የጅምላ ንግድና ኮሚሽን ንግድ /መኪናዎችና ሞተር ብስክሌት ንግድን አይጨምርም/

511. በክፍያ ወይም በኮንትራት ስምምነት እንደ ባለቤት ሆነው ጅምላ ሽያጮች /ደላላዎች፣ አጫራቾች፣ በኮሚሽን ወኪሎች፣ ...ወዘተ ባለቤቱን በመወከል ጅምላ ሽያጭ የሚያካሂዱ/

512. የእርሻ ውጤቶች /ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬና አትክልት/ ቁም ከብት፣ ምግብ መጠጥና ትምባሆ ጅምላ ንግድ፣ ሰብል ገበያ ድርጅት

513. የቤት ውስጥ ዕቃዎች ጅምላ ንግድ /የቤት ዕቃዎች፣ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ሰዓቶች፣ የሕክምና ዕቃዎች፣ የግል ንፅህና ዕቃዎች፣ መፃህፍት፣ መጽሔቶች፣ መጎፅሮች፣ ጌጣጌጦች፣ የስፖርት ዕቃዎች (ባይስክል ጭምር)፣ ከቆዳ የተሠሩ ዕቃዎች፣ ...ወዘተ ጅምላ ንግድ/

514. ግብርና ነክ ያልሆኑ ምርቶች፣ አሮጌና ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎች /እንደገና የሚሰሩ/ ጅምላ ንግድ /በጠጣር፣ በፈሳሽና በጋዝ መልክ ያሉ ነዳጆችና መሰል ምርቶች፣ ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት፣ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች፣ ጨርቃ ጨርቆችና ከጥቅም ውጪ የሆኑ አሮጌ ዕቃዎች ጅምላ ንግድ/

515. ማሽኖች፣ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ጅምላ ንግድ /ከመኪናዎችና ሞተር ሳይክሎች በስተቀር የኮንስትራክሽን፣ የቢሮ፣ የተለያዩ የጨርቃ ጨርቅ፣ እንጨት፣ ብረትና የመሳሰሉ ኢንዱስትሪዎች ማሽኖችና መሣሪያዎች ጅምላ ንግድ/

519. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች የጅምላ ንግዶች

52. ችርቻሮ ንግድ /መኪናና ሞተር ብስክሌቶችን አይጨምርም/፣ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች መጠገን

521. በተወሰነ የንግድ ዘርፍ ባልተሰማሩ ሱቆች፣ መደብሮች ችርቻሮ ንግድ /አዲስና አሮጌ ለግልና ለቤተሰብ ፍጆታ የሚውሉ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን በሱቆች፣ በገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ/

522. የተዘጋጀ ምግብ፡- መጠጥና ትምባሆ በተወሰነ የንግድ ዘርፍ በተሰማሩ ሱቆች፣ ገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ፣ ለምሳሌ አትክልትና ፍራፍሬ፣ሥጋና የስጋ

ውጤቶች፣እንዲሁም በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ሌሎች ተመሳሳይ ምግብ ነክ የሆኑ የችርቻሮ ንግድ አገልግሎት መስጫዎች በዚህ ይካተታሉ።

523. ሌሎች አዳዲስ ዕቃዎች በተወሰነ ንግድ ዘርፍ በተሠማሩ ሱቆች፣ ገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ /ፋርማሲዎች፣ የሕክምናና የንፅሕና መጠበቂያ ዕቃዎች፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ልብሶች፣ ጫማዎችና የቆዳ ውጤቶች፣ የሕንፃ ቀለሞች፣ ቫርኒሽና የመሳሰሉ፣ የቢሮ ዕቃዎች፣ መጽሐፍት፣ የጽሕፈት መሳሪያዎች፣ የፎቶ ግራፍና የዓይን መነፅር፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ/

524. አሮጌ ዕቃዎችን በሱቆች፣ በገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ

525. በሱቆች፣ በገበያ አዳራሾች፣ ...ወዘተ ሳይሆን በመንገድ ላይ፣ በገበያ ቦታዎች፣ በጉልቶች፣ በትዕዛዝ፣ ...ወዘተ ችርቻሮ ንግድ፣ የጉሊት ሽንኩርት፣ የጉሊት ጫት፣ የልዋጭ ንግድ፣ የማገዶ እንጨት ንግድ

526. የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች ጥገና /ኮማኒፋክቸሪንግ፣ ጅምላ ወይም ችርቻሮ ንግድ ጋር ባልተገናኘ መልኩ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎች ጥገና/ ፍራሽና ጫማ እድሳት፣ሰዓትና ራዲዮ አዳሾች

ዋና ክፍል - ሰባት

ሆቴሎችና ምግብ ቤቶች

55. ሆቴሎችና ምግብ ቤቶች

551. የመኝታ አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎች፣ የካምፕ ቦታዎችና ሌላ ለአጭር ጊዜ ቆይታ የሚያስተናግዱ የንግድ ቤቶች /ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ የት/ቤት ዶርሚተሪዎች፣ የእንግዳ ቤቶች፣ ሆስቴሎችና መጠለያዎች/

552. ምግብ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ሻይ ቤቶችና ክበቦች፣ ጠላ ቤቶች፣ አረቄ ቤቶች፣ /የመኝታ አገልግሎት አይሰጡም/

ዋና ክፍል - ስምንት

ትራንስፖርት፣ የመጋዘን አገልግሎትና መገናኛ

60. የየብስ ትራንስፖርት /ሰው፣ዕቃ ፣በመሬት ላይ ማጓጓዝ/

601. የየብስ ትራንስፖርት (አምቡላንስ አይጨምርም) /የመኪና፣ በሰው/በዕቃት የሚጎተቱ ጋሪዎች፣ መኪና መከራየት፣ መኪና መንዳት አስተማሪ፣ የሽክም ሥራ ዕቃ ማጓጓዝ (ወዝ አደር)/

61. የውሃ ላይ ትራንስፖርት /ሰው፣ ዕቃ፣ በወንዝ፣ በግድቦችና በኃይቆች ላይ ማጓጓዝ/

611. የውሃ ላይ ትራንስፖርት /ሰው፣ ዕቃ፣ በወንዝ፣ በግድቦችና በኃይቆች ላይ ማጓጓዝ/

62. የአየር ትራንስፖርት

621. የአየር ትራንስፖርት

63. ከትራንስፖርት ጋር ግንኙነት ያላቸውና አጋዥ ሥራዎች፣ የጉዞ ወኪል

630. ከትራንስፖርት ጋር ግንኙነት ያላቸውና አጋዥ ሥራዎች፣ የጉዞ ወኪል /የካርጎ አገልግሎት፣ የመጋዘን አገልግሎትና ሌሎች የጉዞ ወኪል ሥራዎች/

64. ፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን

641. የብሔራዊ ፖስታና የፖስታ ወኪሎች አገልግሎት

642. ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት

ዋና ክፍል - ዘጠኝ

የፋይናንስ /የገንዘብ እንቅስቃሴ (ዝውውር)

65. የፋይናንስ /የገንዘብ እንቅስቃሴ (ዝውውር)፣ /የመድህንና የጡረታ ዋስትናን አይጨምርም/

651. የገንዘብ እንቅስቃሴ (ዝውውር) የሚያካሂዱ ድርጅቶች /ብሄራዊ ባንክና ሌሎች የገንዘብ እንቅስቃሴ ተቋሞች/፣ ቤቶችን ለመሥራት ወይም ለመግዛት ብድር የሚሰጡ የገንዘብ ተቋማት የመሳሰሉት

659. ሌሎች የገንዘብ እንቅስቃሴዎች /በጊዜ ገደብ ንብረት በኪራይ የመስጠት፣ ከባንክ አሠራር በተለየ መልክ ብድር መስጠት ...ወዘተ/

66. የመድህንና ጡረታ ዋስትና /እንደ ግዴታ የሚሰበሰቡ የማህበራዊ ዋስትናን አይጨምርም/

660. የመድህንና ጡረታ ዋስትና /የህይወት፣ የንብረትና ሌሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ ዋስትናዎች፣ በጡረታና ዋስትና ኮሚሽን የሚደረገውን እንቅስቃሴ አይጨምርም/

67. ከፋይናንስና መድህን እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች

671. ከፋይናንስና መድህን እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች

ዋና ክፍል - አሥር

የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ ኪራይና ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎች

70. የማይንቀሳቀስ ንብረት የተመለከቱ እንቅስቃሴዎች

701. የማይንቀሳቀስ ንብረት የተመለከቱ እንቅስቃሴዎች፣ ኪራይ ቤቶች አስተዳደር

71. ማሽኖችና መሣሪያዎችን ያለ ኦፕሬተር ማከራየት፣ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ማከራየት

711. ማሽኖችንና መሣሪያዎችን ያለ ኦፕሬተር ማከራየት /የትራንስፖርት፣ የግብርና፣ የኮንስትራክሽን፣ የቢሮ (ኮምፒዩተር ጭምር) እና ሌሎች ማሽኖችና መሣሪያዎች ያለ ኦፕሬተር ማከራየት/

713. ለግለሰብና ለቤት ውስጥ ግልጋሎት የሚውሉ በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ዕቃዎችን የማከራየት አገልግሎት ሰምሳሴ ብስክሌት፣ ጆተኒ፣ ቪዲዮ ቴፖችን፣ሪከርደሮችን ጌጣጌጦችን፣ ጋዜጣና መፅሔት እና የመሳሰሉት የማከራየት አገልግሎት መስጠት፣

72. ኮምፒዩተርና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎች

721. ሐርድ ዌርን በተመለከተ ምክርና እገዛ መስጠት

722. ሶፍት ዌርን በተመለከተ ምክርና አገዛ እንዲሁም አቅርቦት

723. መረጃ በኮምፒዩተር ማቀነባበርና ተመሳሳይ ሥራዎች

724. የቢሮ፣ የሂሳብና የኮምፒዩተር ማሽኖች ጥገና

729. ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ ተመሳሳይ የኮምፒዩተር ሥራዎች

73. ምርምርና ልማት:- በመንግስት አስተዳደር ሥራ የሚንቀሳቀሱ የምርምርና የልማት ሥራዎችን አይጨምርም/

731. በተፈጥሮ ሳይንስና በምህንድስና ላይ የተመረኮዘ ምርምርና ቤተ መከራዎች

732. በሶሻል ሳይንስ፣ በቋንቋ፣ በባህልና በመሳሰሉት ላይ የተመረኮዘ ምርምሮችና ቤተመከራዎች

74. ሌሎች የንግድ ሥራዎች

741. ሕግ ነክና የጥበቅና ሥራዎች፣ የሂሳብ፣ የሂሳብ አያያዝና አዲት ንግድ ሥራዎች፣ ስለታክስ አማካሪዎች፣ የገበያ ጥናትና የሕዝብ አስተያየት አሰባሳቢዎች፣ የንግድና የአስተዳደር ሥራዎች አማካሪዎች /ኮንሰልንታንሲ/ የቀረጥ አማካሪ

742. አርክቴክቸራል፣ የምሕንድስናና ሌሎች የቴክኒክ የማማከር ሥራዎች፣ የዕቃዎችና ምርቶች ኢንስፔክሽን/ቴስቲንግ (ከህክምና መሣሪያዎች በስተቀር)

743. የማስታወቂያ ሥራዎች /በጋዜጦች፣ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢግዚቢሽን፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ ...ወዘተ የማስተዋወቂያ ሥራዎች/

749. ከላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች የንግድ ሥራዎች /ማንኛውንም የመኖሪያና የሥራ ቦታ ሕንፃዎች ጽዳት ሥራ፣ የፎቶ ማንሳትና ማጠብ ሥራ፣ የማሸግ /የሕክምና የውበት መጠበቂያና የመሳሰሉትን ዕቃዎች ማሸግ፣ ስም መለጠፍ ... ወዘተ/ ሥራዎች፣/ ሠራተኛን ከአሰሪ መቅጠር፣ ሌሎች የድለላ ሥራዎች የማጫረት ሥራ፣ የመተርጎም ሥራ፣ የኤግዚቢሽን ሥራ፣ ታይፕ የማድረግና የማረም ሥራ፣ የፋሽን ዲዛይን ማዘጋጀት

ዋና ክፍል - አሥራ አንድ

የመንግስት አስተዳደርና የመከላከያ፣ የማህበራዊ ዋስትና (ጡረታ) አገልግሎት

75. የመንግስት አስተዳደርና መከላከያ፣ የማህበራዊ ዋስትና (ጡረታ) አገልግሎት

751. የመንግስት አስተዳደር፣ የሕብረተሰቡን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች የሚቀይሱ የመንግስት ድርጅቶች /በማዕከልና በተዋረድ የተቋቋሙ እስከ ቀበሌ ድረስ የመንግስት የሚኒስቴር፣ ኮሚሽንና መሰል መሥሪያ ቤቶች፣ የታክስና መሰል ሥራዎችን የሚሰሩ እንደ አገር ውስጥ ገቢና የመሳሰሉ ድርጅቶች፣ የሕብረተሰቡን የትምህርት የጤና፣ የባሕልና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚከታተሉና የሚያካሂዱ መ/ቤቶችና መሰል የመንግስት ድርጅቶች/

752. ሁሉን አቀፍ ግልጋሎት ለህብረተሰቡ የሚሰጠ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ለምሳሌ /የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የፖሊስና የሕብረተሰቡን ደህንነትና ሥርዓት የመጠበቅ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ ፍርድ ቤቶች፣ እሥር ቤቶች፣ ...ወዘተ

753. የጡረታና ዋስትና አገልግሎት /የመንግሥት ጡረታና ዋስትና ኮሚሽን፣ የህመም የአደጋና የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ አገልግሎትን ያካትታል። (ነገር ግን ሌሎች በእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የሚሰጡ እርዳታዎች በክፍል 853 እንጂ በዚህ ክፍል አይመደቡም)

ዋና ክፍል - አሥራ ሁለት

የትምህርት፣ የጤና ማህበራዊ አገልግሎት

80. ትምህርት /የግልና የመንግስት ት/ቤቶችንና በቀንም ሆነ በማታ ትምህርት የሚሰጡትን ያጠቃልላል/

801. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት/የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የመዋዕለ ሕፃናት የሕፃናት ማሳደጊያ ፕሮግራሞችና፣ ወደ አንደኛ ደረጃ ለመግባት የሚያዘጋጁ በዚሁ ይጠቃለላሉ/

802. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት/የመለስተኛ፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ለየት ባለ መልክ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችም በዚሁ ይጠቃለላሉ/

803. የከፍተኛ ትምህርት/ሁለተኛ ደረጃ በላይ ለዩኒቨርስቲ ትምህርት /ዲግሪ ወይም ዲፕሎም የሚያስገኙ/ የሚያዘጋጁ ት/ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች/

804. የመሠረተ ትምህርት ሌሎች መደበኛ ያልሆኑ ትምህርቶች /የመሠረተ ትምህርት፣ የሙያና የቴክኒክ ትምህርት በቀን ወይም በማታ በት/ቤቶች ወይም በተለያዩ ተቋማት ወይም በተልዕኮ ወይም በሬዲዩ፣ በቴሌቪዥን ትምህርት የሚሰጡ ፕሮግራሞች፣ በመደበኛ ትምህርት ሊተረጎም የማይችል እንደ ቂስ፣ ቁርዓን፣ ...ወዘተ ትምህርቶች በሙሉ በዚህ ይጠቃለላሉ::/

85. ጤናና ማህበራዊ ሥራ

851. የሰዎች ጤና የመጠበቅ አገልግሎት /ሆስፒታሎች፣ የጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች፣ /በድርጅቶች፣ ት/ቤቶች፣ ...ወዘተ ውስጥ ያሉትንም ያጠቃልላል፣/ የአምቡላንስና ሌሎች ግልጋሎቶችን የሚሰጡ እንደ ቀይ መስቀል የመሳሰሉት ድርጅቶች፣ የባህል ሕክምናዎች/ የመከላከያ ሕክምና ሥራዎችን አያጠቃልልም::

852. የእንስሳት ሕክምና /የቬትሪናሪ አገልግሎት፣ በእርሻ ቦታዎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ...ወዘተ የእንስሳት ሕክምና አገልግሎት/

853. የማህበራዊ ሥራ /በመጠለያዎች ወይም ከመጠለያ ውጭ የተለየ እንክብካቤ ለሚፈልጉ የማህበረሰብ አባላት ለምሳሌ ለምየት ለተሳናቸው፣ ለመስማት ለተሳናቸዉ፣ ለአእምሮ በሽተኞች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለሕፃናት ለአረጋዊያን ተጧሪዎች፣ ...ወዘተ ማህበራዊ እገዛ የማድረግ አገልግሎት መስጠት በተጨማሪም በመጠለያ ጣቢያዎች፣ የስደተኛ ካምፖች፣ ችግሮቹ ባሉበት ቦታ፣ ...ወዘተ በተለያዩ የመንግስት የግልና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ምክር፣ እገዛና ሌሎች ማህበራዊ እርዳታዎችን መስጠት ለምሳሌ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን፣ ወርልድ ቪዥን፣ ኬር፣ ኤስ ኦኤስ፣ ዝዋይ የሕፃናት አምባ፣ ...ወዘተ/

ዋና ክፍል - አሥራ ሦስት

ሌሎች የማህበራዊ፣ የባህል፣ የመዝናኛ የግልና የቤተሰብ ግልጋሎቶች

90. የቆሻሻ ማስወገጃና ንጽሕና አገልግሎቶች

900. የቆሻሻ ማስወገጃና ንጽሕና አገልግሎቶች/ክቤተሰብ፣ ከኢንዱስትሪዎች፣ ከንግድ ተቋሞችና ከመሳሰሉ ቆሻሻ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝና /በመኪና፣ በቱቦ ወይም በሌላ መልክ ሊሆን ይችላል/ ማስወገድ/

91. በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የመ.ያ፣ የንግድና የሠራተኛ ማህበራት እንቅስቃሴዎች

911. የንግድ የሥራና የሙያ ማህበራት ሥራዎች /የኢትዮጵያ ንግድ ም/ቤት፣ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ማህበር፣ የኢትዮጵያ ኬሚስትሪ ባለሙያዎች ማህበር፣ ...ወዘተ የመሳሰሉ

912. ሥራና ሠራተኛን የሚመለከቱ ማህበራት እንቅስቃሴዎች /የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር፣ በአንድ ሙያ ወይም የሥራ ዘርፍ የተሠማሩ ባለሙያዎችን ወይም ሠራተኞችን ጥቅም ለማስጠበቅ የተቋቋሙ ማህበራት/

919. ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ የሙያና መሰል ማህበራት /የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የወጣት ማህበራት፣ ሌሎች በባሕልና በስፖርት፣ በተለያዩ የመዝናኛና ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ማህበራትና ክበቦች/

92. የመዝናኛ፣ የባሕልና የስፖርት እንቅስቃሴዎችን

921. የሲኒማ፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና የመሳሰሉ የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ማዘጋጀት /በምስል የተቀነባበሩ ቲያትር፣ ሲኒማ፣ ...ወዘተ በቲያትር ቤቶች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ማሠራጫት፣ የቪዲዮ ቴፖች ጥናታዊ ፊልም፣ ...ወዘተ ለድርጅቶች (ለግለሰቦች ማከራየትን አይጨምርም) ማሠራጨትና የመሳሰሉ የመዝናኛ አገልግሎቶች/ ናይት ክለብ ዋና ሥራቸው የሆነ

922. የዜና ስርጭት ድርጅቶች /ዜናዎችና ምስሎችን ለሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና ለመሳሰሉት ማቀበል ወይም ማቅረብ/

923. የቤተመጽሐፍ፣ ሙዝየምና ተመሳሳይ ማህበራዊ አገልግሎቶች

924. የስፖርትና ሌሎች የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች /የእግር ኳስ፣ የቴኒስ፣ የዋና፣ የበክስ፣ ቼዝ፣ ...ወዘተ ክለቦችና ድርጅቶች፣ በተጨማሪም የስፖርት አሰልጣኞች፣ ሠዓት ተቆጣጣሪዎች፣ ዳኞች፣ ...ወዘተ ሥራዎች:/

93. ሌሎች አገልግሎቶች

930. ሌሎች አገልግሎቶች፣ ላውንድሪ፣ ሊስትሮ፣ የመኪና መጠበቅ፣ የታክሲ ወያላ፣ የመኪና ረዳት /የእጥበት (ላጪና ... ወዘተ)፣ የፀጉርና ሌሎች የቁንጅና መስጫዎች፣ የቀብር ስነ-ሥርዓት አስፈፃሚዎች ...ወዘተ እና በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ሌሎች የባሕል፣ የመዝናኛና የስፖርት አገልግሎቶች፣ ዕቃ የማውረድና የመጫን

931. በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የቀን ሠራተኞች፣የጉልበት ሥራ/ሽክም/ አገልግሎት መስጠት፣

ዋና ክፍል - አሥራ አራት

ቅጥር ሠራተኞች ያሏቸው ቤተሰቦች

95. ቅጥር ሠራተኞች ያሏቸው ቤተሰቦች

950. ቅጥር ሠራተኞች ያሏቸው ቤተሰቦች /ለቤት ውስጥ ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች ለምሳሌ የቤት ሠራተኞች፣ የቤት ዘበኞች፣ አስተናጋጆች፣ ሞግዚቶች፣ የቤተሰብ ሾፌሮች፣ ...ወዘተ ያሏቸው ቤተሰቦች/

ዋና ክፍል - አሥራ አምስት

የውጭ ድርጅቶች

99. የውጭ ድርጅቶች

990. የውጭ ድርጅቶች /የተባበሩት መንግሥታት፣ የአህጉር አቀፍና ሌሎች የትብብር ድርጅቶች ለምሳሌ ኢሲኤ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ የአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ የጎዳጅ አምራችና ላኪ አገሮች ድርጅት፣ ...ወዘተ/

ተጨማሪ ማብራሪያዎች

በዓምድ 31 እና ዓምድ 32 ስለሚሰጡ የተወሰኑ ኮዶች ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ

1ኛ የዋና ሥራ ዓይነት

741:- ያመረቱትን እህል መፍጨት (ፈጭቶ ዱቄቱን መሸጥ)፣ ቆጮ መፋቅ፣ መቁረጥ፣ ፍቆ (አዘጋጅቶ) መሸጥ፣ ቅቤ፣ አይብና የመሳሰሉትን አውጥቶ (አዘጋጅቶ) ሻጮች:: ምግብ፣ ጠላ፣ አረቄ አዘጋጅቶ መሸጥ፣ ትምባሆ አዘጋጅቶ መሸጥ፣ ጭማቂ አዘጋጅቶ መሸጥ፣ ጀላቲና የመሳሰሉት ጣፋጭ ምግቦች ማዘጋጀት (አዘጋጅቶ መሸጥ):: የከብት ቆዳ ገፋፊዎች::

524:- (አዲስ) በግል የሚተዳደሩ ነጋዴዎች ቀጣሪ ከሆኑ ወይም ከ10 በላይ የሥራ ተካፋይ ሠራተኞች ካሏቸው::

921:- ኩበት፣ ቅጠል፣ እንጨት፣ ጫት፣ ቡና እና ሌሎች ተመሳሳይ የግብርና የደን ምርቶችን ለቃሚ፣ ፣ ለቅሞ መሸጥ እንዲሁም እንጨት መቁረጥ፣ ቆርጦ መሸጥ፣ ሳር ማጫድ፣ አጫጅ፣ አጭዶ መሸጥ በማለትና በተመሳሳይነት የተጠቀሱ የዋነኛ ሥራ ዓይነቶች

2ኛ የድርጅት ዋነኛ ምርት

011: - ቡና፣ ጫት ለቅሞ የመሸጥ አገልግሎት

012: - ኩበት ለቅሞ የመሸጥ አገልግሎት

020: - እንጨት ለቅሞ የመሸጥ አገልግሎት

- እንጨት ቆርጦ መሸጥ

- ሳር አጭዶ መሸጥ

ማሳሰቢያ:

ከማምረት (ማዘጋጀት) እስከ መሸጥ ድረስ ለተጠቀሱ የዋነኛ ሥራ ወይንም የድርጅት ዋነኛ ምርቶች፣ በዓምድ 31 ላይ ለማምረት (ማዘጋጀት) ቅድሚያ ተሰጥቶ ከዚሁ ጋር የተገናዘበ የዋነኛ ሥራ ዓይነት ኮድ እንዲሰጥ::

ዕዝል 2

የሕፃናት ቁመትና ክብደት ልክቶሽ /Anthropometric Measurements/

ዝርዝር ማብራሪያ

ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆናቸው ሕጻናት ሁሉ መመዘንና መለካት ይኖርባቸዋል። የሕፃናት ክብደትና ቁመት ልክቶሽ በቅጽ 4 ክፍል 2 ዓምድ 28 እና 29 ስር በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ይመዘገባሉ። ቁመትና ክብደት ልክቶሽ ራሱን የቻለና የቤተሰብ መጠይቁ ሲጠናቀቅ የሚከናወን ተግባር ነው። ማሳሰቢያ፡- ከሶስት ወር በታች ለሆኑ ህፃናት ክብደታቸው ብቻ ይለካል።

I. ልክቶሽ ከመጀመሩ በፊት መወሰድ ያለባቸው ቅደም ተከተሎችና ጥንቃቄዎች፡

ሀ. ለኪና ረዳት ያስፈልጋለ፡

እያንዳንዱ የልክቶሽ ተግባር በተወሰኑና በልክቶሹ ላይ በሚሳተፉ ሠራተኞች የሚካሄድ ይሆናል። እነዚህም "ለኪ"፡ "ረዳት"፡ ... ወዘተ እየተባለ ስም ተሰጥቷቸዋል። የሕፃናትን ቁመትና ክብደት ልክቶሽ ለማካሄድ ረዳቱን ማሰልጠን ያስፈልጋል። ለኪው ሕፃኑን በመያዝ ልክቶሹን የሚያካሂደውና ውጤቱን የሚመዘግብ ሲሆን ረዳቱ ሕፃኑን ለመያዝ የሚረዳ ነው። ያልሰለጠነ ረዳት (እንደ እናት፡ ወንድም ...ወዘተ) ከአለ የሰለጠነው ለኪ ያልሰለጠነውን ረዳት ምን በማድረግ እንደሚረዳው ሊገለፅለት ይገባል። ረዳት ከሌለ አንድ ሰው ብቻ የልጁን ክብደት በመለካት መመዝገብ ይችላል። ነገር ግን አስፈላጊው ጥንቃቄ ሁሉ መደረግ አለበት።

ለ. የመለኪያው ጣውላና የመለኪያው አቀማመጥ፡

የመለኪያው ጣውላና መለኪያው የሚቀመጡበትን ቦታ መምረጥ ያስፈልጋል። በቀን ጊዜ ከቤት ውጭ ሜዳ ላይ ልክቶሹን ማከናወን ጠቀሜታ ይኖረዋል። ቅዝቃዜ ከአለ፡ ዝናብ ከሆነ ወይም ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ግር ግር የሚፈጥሩ ከሆነ ልክቶሹን በቤት ውስጥ ማከናወን ተገቢ ይሆናል። ነገር ግን ልክቶሹ በሚካሄድበት ቦታ ሁሉ በቂ ብርሃን መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ሐ. የዕድሜን ሁኔታ በማጤን የአለካኩን ሁኔታ መወሰን፡

ልክቶሹ ከመከናወኑ በፊት የልጁን ዕድሜ ማጤን ያስፈልጋል። የልጁ ዕድሜ ከሁለት ዓመት ያነሰ ከሆነ እርዝመቱን /አስተኝቶ/ መለካት ያስፈልጋል። የልጁ ዕድሜ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ ቁመቱን /አቁሞ/ መለካት ተገቢ ይሆናል። የልጁ ዕድሜ በትክክል የማይታወቅ ከሆነና ቁመቱ ከ85 ሳ.ሜ ያነሰ ከሆነ አስተኝቶ /ዕርዝመቱን/ መለካት የሚገባ ሲሆን ቁመቱ ደግሞ ከ85 ሳ.ሜ እና በላይ ከሆነ ቁመቱን (እንደቆመ) መለካት ተገቢ ይሆናል።

መ. መመዘንና መለካት ያለበት መቼ ነው፡

ልክቶሹ መከናወን ያለበት ሌሎች መጠይቆች ከተጠናቀቁ በኋላ ይሆናል። ይህም የሚጠቅመው ከቤተሰቡ አባላት ጋር አስቀድሞ ለመግባባት ነው። ወዲያውኑ ከቤተሰቡ እንደደረሱ ልክቶሽ ማካሄድ አለመግባባትን ሊፈጥር ስለሚችል ከዚህ ተግባር መቆጠብ ይገባል:

ሠ. በአንድ ጊዜ መለካት ያለበት አንድ ልጅ ብቻ ነው፤

በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከአንድ በላይ ለጥናቱ ብቁ የሆኑ ልጆች ከአሉ በየተራ መለካት ይኖርባቸዋል። ሁሉንም ልጆች በአንድ ላይ መለካት አይቻልም። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ልክቶሾች ከተጠናቁ በኋላ የመለኪያ መሣሪያዎቹ በሙሉ ወዲያውኑ ወደቦታቸው መመለስ ይኖርባቸዋል።

ረ. ልጁን መቆጣጠር፤

ልጁ ሲመዘን ወይም ሲለካ መቆጣጠር ተገቢ ነው። የልጆች ጥንካሬና እንቅስቃሴ፤ (በጣም ሕፃን የሆኑትን ልጆች ጨምሮ) መናቅ የሌለበት ጉዳይ ነው። ልጆችን በምንይዝበት ጊዜ ጥንካሬና የተረጋጋ መንፈስ ይጠበቅብናል። የኛ የመረጋጋትና በራስ የመተማመን ስሜት በእናቶችና በሕፃናት ላይ የመረጋጋት ስሜት እንደሚፈጥር መገንዘብ ያስፈልጋል።

የሕፃናት ልክቶሽ በሚካሄድበት ጊዜ ሕፃኑ እንዳይጠለፍ ወይም እንዳይወድቅ በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝና መቆጣጠር ያስፈልጋል። ሕፃኑን ለብቻው በመሣሪያው ላይ መተው ተገቢ ተግባር አይደለም።

ሰ. ፍርሃትን ማስወገድ፤

ፍርሃትንና ጭንቀትን ለማስወገድና ተቃውሞን ለመቀነስ የአለካኩን ሂደት ለእናታቸው ማስረዳት የሚያስፈልግ ሲሆን፤ ለሕፃናት ደግሞ በጥቂቱ መግለጽ ተገቢ ይሆናል። የእናቶችን ወይም የሕፃናትን የፍርሃት ደረጃ በማጤን የልክቶሹ ተግባር መቼም ያለበት መሆኑን መወሰን ያስፈልጋል። ሕፃናት ልጆች ብዙ ጊዜ አይተባበሩም፤ ያለቅሳሉ፤ ይረብሻሉ፤ ይማታሉ አንድ አንድ ጊዜ ድግሞ ይናከሳሉ። ሕፃኑ በከባድ ፍርሃት የተሞላ ከሆነና በተከታታይ ከባድ ልቅሶ የሚያሰማ ከሆነ ለማባበል መሞከር ያስፈልጋል። ወይም ልክቶሹ ከመካሄዱ በፊት ወደ እናቱ መልሶ በመስጠት ማረጋጋት ያስፈልጋል።

የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተከሰቱ ልጁ መመዘን ወይም መለካት የለበትም፦

ሀ. ልጁ በጣም የታመመ ከሆነ
ለ. ልጁ የአካል ጉዳተኛ በመሆኑ የተነሳ የቁመት የልክቶሹ ሥራ አስቸጋሪ ከሆነ ወይም የተሳሳተ ልክቶሽ የሚሰጥ ከሆነ።

ሸ. የልክቶሹን ውጤት አመዘጋገብ፤

በዚህ ጥናት የልክቶሹ ውጤት በመጀመሪያ ደረጃ በማስታወሻ ላይ ከልጁ እና ከእናቱ ተራ ቁጥር ጋር በጥንቃቄ ይመዘገባል። ከዚያም ወደ ዋናው መጠይቅ በጥንቃቄ ይገለበጣል።

<u>ጥብቅ ማሳሰቢያ</u>፦የሕፃናት ክብደትና ቁመት የመለካት ሥራን እንደ ቀላል ነገር በመውሰድ ያለአግባብ በራስ መተማመን ተገቢ አይደለም። ልክቶሽን ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ካሳከናወነው በቀላሉ ስህተት እንደምንሰራ መታወቅ አለበት።

II. የቁመት ልክቶሽ ቅደም ተከተል

ሀ. የሕፃኑ ቁመት አለካክ (ሥዕል 1)

1. ለኪ ወይም ረዳቱ የመለኪያውን ጣውላ ጠንካራና ጠፍጣፋ በሆነ ግድግዳ፤ ጠረጴዛ፤ ዛፍ፤ ... ወዘተ ላይ ማስቀመጥና:: ጣውላው በትክክል የተቀመጠና ያልተዛነፈ መሆኑን ማረጋገጥ::

2. እናትዬው የልጁን ጫማ እንድታወልቅና በቁመት ልክቶሹ ላይ ችግር የሚያመጣ ነገር ከአለው እንድታስተካክል መጠይቅ:: ልጁን ወደ መለኪያ ጣውላው እንድትወስደውና ልጁ የሚረብሽ ከሆነ ከልጁ አጠገብ ቁጢጥ እንድትል (እረዳት ካለሆነች) ማድርግ::

3. ረዳቱ መጠይቁንና አስክሪብቶውን መረት ላይ በማስቀምጥ በልጁ አካል ቀኝ በኩል መንበርከክ (ቀስት 2)::

4. ለኪው ለመንቀሳቀስ እንዲያመቸው በልጁ በስተግራ በኩል በቀኝ ጉልበቱ መንበርከክ አለበት (ቀስት 3)::

5. ረዳቱ ልጁ እግሮቹን በመግጠምና ጫማውን በትክክል እንዲረግጥ፤ በመለኪያ ጣውላው መሀል ላይ እንዲቆምና በመለኪያ ጣውላው ላይ ወደኋላ ተጠግቶ እንዲቆም አድርግ:: /ቀስት 4 እና 5ን እንዲሁም 6 እና 7ን እይ/የልጁ እግሮች ቀጥ ብለው የቆሙ መሆኑን፤ የእግሩ ተረከዝና ባቱ ወደ መለኪያ ጣውላው የተጠጉ መሆኑን አረጋግጥ::

6. ለኪው ልጁ ፊት ለፊት ቀጥ ብሎ እንዲመለከት ማድረግ (ቀስት 8):: የግራ እጅህን በመክፈት የልጁን አገጭ ደግፎ መያዝ::(ቀስት 9) የልጁ ትከሻዎች ቀጥ ብለው የተስተካከሉ መሆኑን (ቀስት 10)፤ እጆቹ በጉኑ በኩል ያሉ መሆኑን (ቀስት 11) እና ራሱ፤ የትከሻ የመጋጠሚያ አጥንቶችና መቀመጫዎቹ ወደ መለኪያ ጣውላው የተጠጋጉ መሆኑን (ቀስት 12፤ 13 እና 14) ማረጋገጥ:: በልጁ ራስ ላይ የምታርፈውን መለኪያ በልጁ አናት ላይ ቀስ ብለህ በማሳረፍ የልጁን ፀጉር ገፍቶ እንዲይዘው ጫን ማድረግ (ቀስት 15)::

7. ለኪና ረዳት ሁለቱም የልጁን አቋቋም በመመርምር (ቀስት 1-15) አሰፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማንኛውንም ተግባር በድጋሚ ማስተካከል::

8. ለኪው የልጁ አቋቋም ትክክል መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ልክቶሹን ወደ 0.1 ሳሜ በማጣጋት ማንበብ:: ከልጁ አናት ላይ ያረፈውን መለኪያ፤ እና የግራ እጁን ከአገጩ ላይ በማንሳት ልክቶሹ በሚመዘገብበት ጊዜ ልጁን መደገፍ::

9. ረዳቱ የልክቶሹን ውጤት ወዲያውኑ በመመዝገብ ለለኪው ማሳየት::
ማስታወሻ:- ረዳቱ ያልሰለጠነ ከሆነ ለኪው ውጤቱን መመዝገብ አለበት::

10. ለኪው:- የልክቶሹ ውጤት በመጠይቁ ላይ እስከሚገለበጥ ድረስ በማስታወሻ ላይ የልጁንና የእናቱን ተራ ቁጥር የያዘና በትክክል የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ:: ስሕተቶች ከአሉ ወደ ሌላ ሥራ ሳይሄድ ወዲያውኑ ማስተካከል::

ሐ. የሕፃኑ እርዝመት አለካክ (ሥዕል 2)

1. ለኪው ወይም ረዳቱ:- የመለኪያ ጣውላውን ጠንካራና ቀጥታ በሆነ ቦታ ላይ በመሬት ላይ፤ በወለል ላይ፤ በማይንቀሳቀስ ጠረጴዛ ላይ ...ወዘተ ማስቀመጥ::

2. ረዳቱ መጠይቁንና እስክሪቢቶውን መሬት ላይ፤ ወለል ላይ ወይም ጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ (ቀስት 1):: መለኪያ ጣውላው መሬት ላይ ከሆነ ከጣውላው በስተጀርባ በሁለቱም ጉልበቱ መንበርከክ (ቀስት 2)::

3. ለኪው የልጁን የእግር ድጋፍ በቀኝ እጅ ለመያዝ እንዲያመቸው በልጁ የቀኝ አካል በኩል መንበርከክ (ቀስት 3)::

4. ለኪና ረዳት የእናትየዋን እርዳታ በመጠየቅ በሚከተለው መንገድ ልጁን በጣውላው ላይ ለማስተኛት መምከር:: እናትየው ረዳት ካልሆነች በጣውላው ጀርባና ከልጁ ፊት ለፊት በመንበርከክ ልጁን እንድታረጋጋው ማድረግ::
ረዳት:- የልጁን ራስ የኋላ አካል በመደገፍ ቀስ በቀስ በጣውላው ላይ ማጋደም::
ለኪ:- የልጁን ዋናውን የሰውነት አካል በመያዝ መደገፍ::

5. ረዳቱ በልጁ ጆሮዎች አካባቢ በእጆቹ በመያዝ ልጁን ደግፎ (ቀስት 4):: እጆቹን ቀጥ በማድረግና በማመቻቸት (ቀስት 5) የልጁን ራስ ከጣውላው ላይ በቀስታ በማስቀመጥ የልጁ እይታ ቀጥታ ወደ ሰማይ እንዲሆን ማድርግ:: የልጁ የእይታ መስመር በቀጥታ መሬትን በ90° ማቋረጥ ይኖርበታል (ቀስት 6):: ረዳት ከልጁ ራስ ትይዩ በመሆን በቀጥታ የልጁን ዓይን ማየት የሚቻልበት ሁኔታ ላይ ይኖርበታል::

6. ለኪው ልጁ በጣውላው መሀል ላይ ቀጥ ብሎ የተኛ መሆኑን በማረጋገጥ (ቀስት 7) የግራ እጅቹን በልጁ የእግር አገዳ (ከተረከዙ በላይ) ላይ ወይም በጉልበቶቹ ላይ በማስቀመጥ (ቀስት 8) ወደ ጣውላው ገፋ አድርጎ መያዝ:: በቀኝ እጅ ከጫማው ስር ያለውን ጠፍጣፋ መለኪያ ቦርድ ወደ ልጁ ተረከዝ ገፍቶ መያዝ (ቀስት 9)::

7. ለኪና ረዳቱ ልጁ ጣውላው ላይ በትክክል መጋደሙን ማረጋገጥ፤ አስፈላጊ ከሆነ ማንኛውንም ማስተካከያ ማድረግ::

8. ለኪው ልጁ ትክክለኛ ቦታው ላይ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ልክቶሹን ወደ 0.1 ሳሜ አጠጋግቶ ማንበብ:: በልጁ እግር ስር ያለውን ቦርድና ከልጁ የእግር አገዳ ወይም ጉልበቶቹ ላይ ያለውን የግራ እጁን ማንሳትና ውጤቱ በሚመዘገብበት ጊዜ ልጁን መደገፍ::

9. ረዳቱ ወዲያውኑ የልጁን ራስ በመልቀቅ፤ ውጤቱን መዝግቦ ለለኪው ማሳየት::
ማስታወሻ:- ረዳቱ ያልሰለጠነ ከሆነ ውጤቱን ለኪው መመዝገብ አለበት::

10. ለኪ ውጤቱ በመጠይቁ ላይ እስከሚገለበጥ ድረስ በማስታወሻ ላይ የልጁንና የእናቱን ተራ ቁጥር የያዘና በትክክል መመዝገቡን ማረጋገጥ:: ስህተት ካለ ወዲያውኑ ማስተካከል::
ማስታወሻ:- ረዳቱ ያልሰለጠነ ከሆነ (ለምሳሌ እናት) በእርዝመት ልክቶሹ ጊዜ ለኪው ረዳቱን የማገዝ ግዴታ አለበት::

III. የክብደት ልክቶሽ ቅደም ተከተል፡፡

ሀ. የክብደት መለኪያ መሣሪያ

1. ዲጂታል እስኬል (Degetal Scale) (ዩኒሴፍ ኤሌክትሮኒክ እስኬል ወይም ዩኒእስኬል)፡- ይህ መሣሪያ ልጆችና ትልልቅ ሰዎችን ለመመዘን ያገለግላል። እሰኬሉ በ0.1 ኪ.ግ (0.2 ፓውንድ) የተስተካከለ ሲሆን ያለምንም የሂሳብ ስሌት በቀላሉ የልጁን ክብደት ለማንበብ የሚያስችል መሣሪያ ነው። ዩኒስኬል በፀሐይ ብርሃን የሚሰራ ሲሆን የሚቀየሩ የባትሪ ድንጋዮች አያስፈልጉትም። (ተጨማሪ መመሪያዎችን በዩኒስኬል ማስታወሻ ላይ ያለውን ተመልከት)።

